«የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንት፣ ዛሬና ነገ»
ዐውደ ጥናት፤ የጥናት ጽሑፎች

Proceedings of the Workshop on
«The Ethiopian Church Yesterday, Today and Tomorrow »

ከሚያዝያ 9-10 ቀን 1994 ዓ.ም
አፍሪካ አዳራሽ፣ አዲስ አበባ

April 18-19, 2002
Africa Hall, U.N.E.C.A.- Addis Ababa

አዘጋጅ - በኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ ሰ/ት/ቤቶች ማ.መ. ማኅበረ ቅዱሳን የተዘጋጀ
Organized by EOTC– Mahibere Kidusan

አሳታሚ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
ማኅበረ ትዳሳን
ፖ.ሣ.ቁጥር 80078
ስልክ ቁጥር 114870፣ 556327
Email: eoc-m-kidusan@telecom.net.et
Website: www.telecom.net.et/~mkidusan
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ

አርታእያን ዲያቆን መርሻ አለኸኝ
ታዬ በቀለ
ነጸነት ተስፋዬ

Published by
Ethiopian Orthodox Tewahido Church, Sunday Schools Department
MAHIBERE KIDUSAN
P.O.Box: 80078
Tel. 114870/ 556328
Email: eoc-m-kidusan@telecom.net.et
Website: www.telecom.net.et/~mkidusan
Addis Abeba – Ethiopia

Editors: Deacon Mersha Alehegne
Taye Bekele
Netsanet Tesfaye

Copyright © 2002 by E.O.C. S.S.D. Mahibere Kidusan

የሽፋን ሥዕል - የዘመዱ ርዕዩ አርማ
Cover Picture – Logo of the Exhibition

ማውጫ Table of Contents

ምሥጋና ____ i

የማኅበሩ መልእክት ____ ii

The Role of the Ethiopian Orthodox Tewahido Church in HIV/AIDS Control Programme in Ethiopia
Kesis Kefyalew Merahi ____ 1

በደሬር ሡልጣን ገዳም የኢትዮጵያ ባለቤትነትና የይዞታ መብት ከጎለም አቀፍ ሕግ አንጻር
ደሳለኝ ዓለሙ እና ረታ ዓለሙ ____ 5

ሐሳበ ዘመን በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ዲ/ን ዳንኤል ሠይፈ ሚካኤል ____ 28

The Role of the Ethiopian Orthodox Church in the Development of Tourism
Sisay Ayalew ____ 42

A Glimpse on the Role and Position of the Ethiopian Church in Literature and Performing Arts
Nebiou Baye ____ 60

የድርሳናተ መላእክት ባሕርያት
ሣሙኤል ያለው ____ 79

የመልክአ መልክአ ልዩ ልዩ ባሕርያት
ዝክሸኝ ጌታቸው ____ 90

ግእዝ ትናንትዛሬና ነገ
ዲ/ን መርሻ አለሽኝ ____ 115

Indigenous Knowledge of Medicinal Plants: Perspectives of the Ethiopian Orthodox Church
Taye Bekele ____ 133

በመጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ልዩ ትርጉሞች ላይ የሚታዩ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው
ዲ/ን ዳንኤል ክብረት ____ 146

የአብነት ትምህርት ቤቶች ገነት ከበደ ____ 158

Role of the Ethiopian Orthodox Tewahido Church in Poverty Reduction
Belachew Mekuria and Eleni Tekalign ____ 170

ምሥጋና

በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን ይህ የጥናት ጽሑፎች መድብል እንዲታተም የማተሚያ ወጭዉን ለከፈለው በሕይወታዊ ሀብት ጥበቃና ምርምር ኢንስቲትዩት በዓሰም ባንክ የሚደገፈው የመድኃኒት ዕፅዋት ጥበቃና ዘለቄታዊ አጠቃቀም ፕሮጀክት ልባዊ ምሥጋናውን ያቀርባል። ከዚሀም በተጨማሪ ዐውደ ጥናቱ በተሳካ ሁኔታ እንዲከናወን የአፍሪካ አዳራሽን በመፍቀድ ከፍተኛ ትብብር ያደረገውን የተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ አሕጉሚ ኮሚሽንን ያመሰግናል።

ACKNOWLEDGEMENT

The Ethiopian Orthodox Tewahido Church, Sunday Schools Department, Mahibere Kidusan is deeply indebted to the World Bank-supported Conservation and Sustainable use of Medicinal Plant Project of the Institute of Biodiversity Conservation and Research for its financial assistance without which the production of this Proceedings would not have been possible. And its special thanks are due also to the United Nations Economic Commission for Africa for its cooperation in giving the Africa Hall free of charge for the work shop.

The views and interpretations expressd in this book are entirely those of the authors and should not be attributed in any manner to the E.O.T.C. S.S.D. MAHIBERE KIDUSAN.

የማኅበሩ መልእክት

ትላንትን ዛሬ ለማየት – ጥናት
ነገን ለማመልከት – ጥናት

ኢትዮጵያ ሀገራችን ገናና ታሪክ ካላቸው የዓለም ታላላቅ ሀገሮች መካከል አንዲ ናት። ለዚህ ገናና ታሪኪ ደግሞ ዋነኛው ምንጭ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መሆኗ አያጠራጥርም። ቤተ ክርስቲያናችን የሀገራችንን መንፈላዊ፣ ታሪካዊ፣ ባሕላዊና የሥልጣኔ ገዛ በውስጧ እየዘገበች ጠብቃ ያቆየች ሕያው ቤተ መዝገብ ናት።

በመሆኑም አሁን ያለውም ሆነ የሚመጣው ትውልድ ማንነቱን እንዲያውቅ በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ያሉት መንፈላዊና ቁሳዊ ሀብቶች ሊታወቁ ይገባል። ወደዚህ ስፌ፣ ሩቅና ጥልቅ አዳራሽ ለመግባት እጅግም የተመቻቸ ሁኔታ ተፈጥሯል ማለት ባይቻልም፡ መዛንብቱ በራ ላቸው ግን ኑ እዩኝ፣ ሰወቁኝ የሚል ጥሪ የሚያስሙበት ደዘል አላቸው። ይህንን ጥሪ ሰምቶ ምላሽ መስጠት ደግሞ የእኛ ኃላፊነት ነው።

ጕልቆ መሳፍርት የሌላቸው የሥነ ጽሑፍ፣ የሥነ ሥዕል፣ የሥነ ዜማ፣ የሥነ ሕንፃ፣ የቅኔና፣ የፍልስፍና...ወዘተ ሀብታት መሳኛ ቤተ ክርስቲያን እንደመሆኗ መጠን ይዘታቸው፣ ታሪካቸው፣ ባለቤታቸውና ጥቅማቸው በሚገባ እየተጠና ለልትውልድ ሙተላስፍ ይኖርበታል። የትላንትናውን ትውልድ ከዛሬውና ከነገው ትውልድ ጋር ለማዛኘት የሚያስችል የጥበብ መንገድ ነውና የጥናትና የምርምር ሥራ እጅግ ሊበረታታ ያስፈልጋል።

እግዚአብሔር ቢፈቅድ ቤተ ክርስቲያን የራሷን የጥናትና የምርምር ተቋም መክፈት ይገባታል። ለዚህም ደግሞ አቅሙም፣ ብቃቱም ችሎታውም አላት። ትላንትን ዛሬ ስማየት ጥናት ነገንም ለማመልከት ጥናት እጅግ በጣም ይጠትሃል።

ማኅበራችን ማኅበረ ቅዱሳንም ከተቋቋመበት ዓላማ አንዱ የሆነውን የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ማንነት የማላወቅ ተግባሩን እንደ ስብዙተ ወንጌሉ ሁሉ በጥናቱም ዘርፍ አተኩሮ የበኩሉን አስተዋጽኦ እያበረከተ ነው። ከሚያዚያ 4–13 ቀን 1994 ዓ.ም «የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትላንት ዛሬና ነገ» በሚል ርዕስ ታላቅ ሀመደ ርእይ በአዲስ አበባ ኤግዚአቢሽን ማዕከል አካሂዷል። ከዐውደ ርእዩ በተጓዳኝ ከሚያዝያ 9–10 ቀን 1994 ዓ.ም በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን የአፍሪካ አዳራሽ ዐውደ ጥናትም አዘጋጅቷል።

ማኅበሩ ዐውደ ጥናት በሰፊ መድረክ ሲያቀርብ ይኸ ስሁለተኛ ጊዜ ሲሆን የመጀመሪያው በ1991 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የባሕል ማዕከል 12 የጥናት ወረቀቶች የቀረቡበት ነበር። ሁለተኛው ደግሞ እንዴለፈው ዓመት ሁለ 12 የጥናት ወረቀቶች የቀረበበት ሲሆን በየርእሱ የሚመለከታቸው አካላት በመገኝታቸው ሙጤቱ እጅግ በጣም ወሐመሂ ሆኖ አልፏል። ስለሆነም የበርካታ መንናኛ ብዙኃንን ትኩረት አግኝቷል።

በዚህ አጋጣሚ በጥናቱ ሂደት የተሳተፉትን ሁሉ እግዚአብሔር ይስጥልን እንላለን። ከሁሉ በላይ ደግሞ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ዐውደ ጥናቱን ለማካሄድ ታሪካዊውን የአፍሪካ አዳራሽ በነጂ ሸለፈቀደልን ማንነታችንን ለማያነሳው ታላቅ ሥራ ከጎናችን በመቆሙ ከልብ እናመሰግ ግናለን።

በጥናት ትላንትናን ከዛሬ፣ ዛሬን ከነገ፣ ትላንትንም ከነገ ማያያዝ ይቻላልና ማኅበረ ቅዱሳን ወደፊትም የበለጠ በተጠናከረ ሁኔታ የተለያዩ ዐውደ ጥናቶችን የማዘጋጅቱን ሂደት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ይቀጥልበታል። ሪድኤታ እግዚአብሔር አይለየን።

በዴር ሡልጣን ገዳም የኢትዮጵያ ባለቤትነትና የይዞታ መብት ከዓለም አ ቀፍ ሕግ አንፃር

ደሣለኝ ዓለሙ
Email :desyealex@yahoo.com
እና ረታ ዓለሙ
Email:Fikeresellassie@yahoo.com
ስ.ቁጥር 517345
/ሡሙ ገዳይ ሚኒስቴር/



አቶ ደሣለኝ ዓለሙ እና አቶ ረታ ዓለሙ ጥናታቸውን ሲያቀርቡ

1. መግቢያ

በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ታሪክ ሲነሣ የደብረ - ሥልጣን /ዴር ሡልጣን/ ገዳም ጉዳይ መነሣቱ አይቀሬ ነው። ይህ ጥንታዊ ገዳም የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅርስ፣ ሀብትና ንብረት ብ ቻ ሳይሆን የዓለም ጥቁር ሕዝቦች አለኝታና መኩሪያ ቁምር መሆኑን እያሉ ምሁራን ይስማሙበታል።

የዚህ ጥናት ዓይነተኛ ዓላማም ቀደምት አባቶቻችንና እናቶቻችን በኢየሩሳሌምና አካባቢው በባለቤትነት የያዙትንና ጠብቀው ያቆዩልንን ርስት ለመጭው ትውልድ ከማስተላለፍ አኳያ በዴር -ሡልጣን ገዳም ላይ ሕጋዊ የባለቤትነትና የይዞታ መብታችንን ለማስከበር ከተጠ ቀምንባቸው ባሻገር ያሉትን እስከአሁን የተሞከሩም ሆነ ገና ያልተቃኙ መንገዶች መዳሰስ ሲሆን፣ ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ ሕዝብ ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፍ የኖረውን ይህንኑ ታሪ ኩንና መብቱን ለማስከበር እንዲችል በቡተ ክህነትም ሆነ በመንግሥት በኩል ጉዳዩን እስመልክቶ ሲወሰዱ የቆዩት እርምጃዎች በምን መልኩ ሊጠናከሩ ይችላሉ? ኢትዮጵያ በደብረ-ሥልጣን / በዴር-ሡልጣን/ ገዳም ያላትን የባለቤትነት መብት በዓለም አቀፍ ሕግና በዓለም ዓቀፍ መድረክ ማስከበር ትችላለች ወይ? በሚሉት ነጥቦች ዙሪያ ለውይይትና ሰፋ ላለ የጥናት ምርምር ሥራ

መነሻ የሚሆኑ አንዳንድ ሀሳቦችን ማቅረብ ነው።

በዚህ ጥናት በደብረ ሥልጣን ገዳም ዙሪያ ያለውን የባለቤትነትና የይዞታ ክርክር አመጣጥ ታሪካዊ ሂደት በመቃኘት፣ የችግሩን አሳሳቢነት ሰማስረዳትና የተለያዩ አካላት ችግሩን በመፍታት ረገድ የሚራቸውን ሚና ለማመላከት የተሞከረ ሲሆን፣ በተለይ ገዳዩ በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት ሊፈታ የሚችልበት መንገድ ካለ ወደፊት በዚህ አቅጣጫ ምን ሊደረግ ይገባል? በሚለው ጥያቄ ላይ በማነጣጠር ለመነሻ የሚያገለግሉ አንዳንድ ሀሳቦችን ለመፈንጠቅ ተሞክሯል። የጥናቱ ትኩረት የርእስ ጉዳዩን መሠረታዊ ጭብጦ በመዳሰስ ብቻ የተወሰነ በመሆኑ፣ ከጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ተያይዘው ሊነሱ የሚችሉ ሴሱች ጥያቄዎችን አይመለከትም።

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢዎች ጥናቱን ለማካሄድ የተጠቀምንበት ስልት በርእሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተጻፉ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን፣ መጽሔቶችንና ጋዜጦችን በማንበብ፣ በጉዳዩ ዙሪያ የዓለም አቀፍ ስምምነቶችንና በመንግሥታት የወጡ ድንጋጌዎችን፣ እንዲሁም በዓለም አቀፍ አካላት የተላለፉ ከጉዳዩ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ውሳኔዎች በማገናዘብ በርእሱ ጭብጦች ዙሪያ ውይይት ማድረግ ነው።

በጥናት ጽሑፉ አዘገጃጀት ያጋጠሙ ችግሮችን ከተመለከተ ርዕሱ በሚያተኩርበት ጉዳይ ላይ የተዘጋጁ ቀደምት ጥናቶች ባለመኖራቸው ፣ ተዛማጅ መረጃዎችን በማሰባሰብ ረገድ እጥረት የነበረ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪም ርእሰ-ጉዳዩ ስፊና ውስብስብ በመሆኑ ካሉት መረጃዎችና የማገናዘቢያ መጻሕፍት ውስንነት አኳያ ስጊዜው በዝርዝር ጉዳዮች ላይ ጠለቅ ያለ ምርምር ለማድረግ አዳጋች እንደነበረም ከወዲሁ ማስገንዘቡ ተገቢ ይሆናል።

ጥናቱ በጉዳዩ የወደፊት አያያዝና አካሄድ ላይ ሊያሳድር የሚችለውን እንደምታ በተመለከተም ይህ ጥናት የተለያዩ አካላት እንደየአግባባቸው መጠን በርእሰ-ጉዳዩ ዙሪያ ሲወስዱ የሚችሉትን እርምጃ በመለቆም፣ በጉዳዩ ላይ ያለውን አቋም ይበልጥ ፈር ለማስያዝ ይረዳል የሚል እምነት አለን።

በመጨረሻም ጥናቱ የሚያስተላልፈውን መልእክትና እንዲረው የሚጠበቁውን ጠቀሜታ ጠቅለል ባለ መልኩ ለመግለጽ ያህል፦

- ኢትዮጵያ በደብረ - ሥልጣን / ዴር ሡልጣን / ገዳም ያላትን ሕጋዊ የባለቤትነት መብት በዓለም አቀፍ መድረክ ጭምር ለማስከበር የምትችልበትን መንገድ የሚጥናቱ ተገባር ሊ ታስብበት የሚገባ መሆኑን፣
- ገዳሙ የአትዮጵያ ሕዝብ ታሪካዊ ቅርስ መሆኑንና የንብረቱ ሕጋዊ ባለቤት መሆናችንን በማስረጃ በማረጋገጥ ጉዳዩን በያዘው መንግሥት አካላት ዘንድ የምናደርገው ክርክር በማናቸውም ምክንያት በአድሏዊነት ታይቶ ጥቅማችን የሚጎዳበት ሁኔታ ቢፈጠር በዓለም አቀፍ የሕግ መድረክ እንዲታይ የማድረጉ አማራጭ ሊያስገኝ የሚችለውን ውጤትና ጠቀሜታ ጉዳዩ በቅድ ሚያ በጥናትና ምርምር ላይ ተመርኩዞ ማመዛዘን እንደሚያስፈልግ፣
- በኢትዮጵያ በኩል በገዳሙ የባለቤትነት ክርክር ላይ የሚቀርብ የመብት ጥያቄ ዓለም አቀፍ ሕግጋትን መሠረት ቢያደርግ የሚያዋጣ መሆኑ በጥናት ከተረጋገጠ፣ ይኸው ተቀባይነት እንዲያገኝ ተገቢውን እንቅስቃሴ መጀመርና ከዚህ አንፃር በቦታው ላይ ያለንን መብት ለማስከበር የሚቻልባቸውን ተጓዳኝ ስልቶች ከወዲሁ አጥንቶ መቀየስ እንደሚያሻ ማስገንዘብ ይሆናል።

II. የዴር ሡልጣን ባለቤትነትና ይዞታ ጉዳይ ታሪካዊ ቅኝት

በኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ይዞታ ስር የሚገኘው ደብረ - ሥልጣን / ዴር ሡልጣን / ወይም የንጉሥ ገዳም የተሰኘው ቦታ ከብዙ ዘመናት ጀምሮ ያሰማንም ተቀናቃኝ በኢትዮጵያውያን ብቸኛ ይዞታና ባለቤትነት ሥር ስለመቆየቱ ተጨባጭ ታሪካዊና ሃይማታዊ መረጃ ዎችን ዋቢ ያደረገ ጽሑፎች ያስረዳሉ ::

ይዝው ጥንታዊ ገዳም የተቆረቆረበትን ቦታ በኢየሩሳሌም ቀደምት የነበሩት አ ትዮጵያውያን ሊያገኙ የቻሉበት ሁኔታና መንገድ እነኚሁኑ ዋቢዎች በመመርኮዝ ጠቅሰል ባሰ አኳኋን ሲገለጽ ክክርስቶስ ልደት በፊት በ950 ዓመተ ዓለም ገደማ ዘወቅቱ ኢትዮጵያን እ ልፋ ቀይ ባሕርን ዘመሻገር የዛሬዎቹ የዓረብ አገሮች ያሉበትን አካባቢ ቁምር በከፊል ትገዛ የነበ ረችው አትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳ / ወይም ንግስተ ሳባ / በዘመኑ በተለይ በጥበበኛነቱ ይታወቅ የነበረውን የአሥራኤል ንጉሥ ስሎሞንን የከበሩ ገፀ በረክቶችን ይዛ በጎበኘችበት ወቅት ከቤተ መንግሥቱ አቅራቢያ የሚገኘውን ይህንኑ ቦታ ከብዙ ጓዟ ጋር ዘማረፈያነት እንድትጠቀምበት በመታሰቢያነት እንደሰጣት ይነገራል።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቦታው አሁንም የሚጠራበትን ስያሜ በመያዝ የክብሯ መታሰቢያ ሆ አዘያው ሰቆዩት ተከታዮቿና በስተጓላም አገር አቁርሰው በየዘመናቱ ወደ ኢየሩሳሌም ለተጓዙት ወገናቿ አትዮጵያውያን ሁሉ በቋሚ መቀመጫነት ሲያገለግል እንደረ በተለያዩ ታሪካዊና ሃይማታዊ ድርሳናት ውስጥ በተመሳሳይ አኳኋን ተደጋግሞ የተገለፀ መሆኑን ለመረዳት ይቻ ላል።

የዴር ሡልጣን ገዳም ክርስቶስ እስኩቶወሰደበት ዘመን ድረስ ያሰአንዳች ባላንጣ ለኢ ትዮጵያውያን የኢየሩሳሌም ተጓዦች ማረፊያ፣ መቀመጫና መኖሪያ ሆኖ እንደዘለቀ ሁሉ ከኢ የሱስ ክርስቶስ ልደት በኋላም አካባቢው በሮማውያን በቤዛንታውያን፣ በመስቀሳውያን፣ በእስላማውያን፣ በማምሉኮች በተከታታይ አየተገዛ ሲተዳደር ዘቆየባቸው ዘመናት ቁምር የኢ ትዮጵያ ሕጋዊ ንብረትና ይዞታነቱ ይበልጡኑ ተረጋግጦ መቀጠሉን ታሪክ ይመስክራል። በተ ለይም በ4ኛው ምዕተ-ዓመት ከርስትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት ሆኖ በይፋ መደንገጉ የ ኢትዮጵያውያንን የኢየሩሳሰም ተጓዞች ቁጥር በማዘራከትና የአውሮፓውያንን አትኩሮት በመሳብ ይዞታውን ደብልጥ ለማጠናከርና ለማስፋፋት ቁምር እንደጠቀመ ሰንዳዩ ዋቢ የሆኑት የተለያዩ ድርሣናት ያወሳሉ።

ኢትዮጵያውያን ክክርስቶስ ልደት በኋላ በዴር ሡልጣን ገዳም ላይ የነበራቸው መሉ የባለቤትነትና የይዞታ መብት በይፋ ከተረጋገጠባቸው ዓበይት ታሪካዊና ሃይማታዊ ኩነቶች መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሰው ጉዳይ ኢየሩሳሌም በሮማዊው ንጉሥ ቆስጠንጢስ ሥር ትተዳደር በነበረችበት ወቅት አንደተፈፀመ የሚገለፀው የገዳሙን ይዞታ የማስከበር ክንዋኔ ነው። ይኸውም የንጉስ ቆስጠንጢስ እናት የነበረችው ንግሥት አሌኒ ኢየስስ ክርስቶስ የተ ሰቀለበትን ዕፀ-መስቀል ከተቀበረበት የጐልጐታ ኮረብታ አስቆፍራ ካስወጣች በኋላ በሥፍራው ላይ አስከአሁን በማዘፈ-አነል ቆሞ የሚገኘውን ቅዱሱ መቃብር (The Holy Sepulcher) የተሰኘ ታላቅ ሕንፃ በማስገንባት በጊዜው በአካባቢው ለነበሩት ክርስቲያናዊ ማኅበረሰቦች ቦታ ስታደላድል በአንጥያኮስ ዘመን ተከስቶ የነበረው የአይሁዳውያውን ስደት ባስከተሰው የሁኔታዎች መዘበራረቅ ሳቢያ ከታሪካዊ ይዞታቸው ለመፈናቀል ተቃርበው የነበሩት ኢትዮጵያውያን ወደቀድሞ ቦታቸው እንዲመሰሱ አብርሃ ወአፅብሐ ስሚባሉት በወቅቱ የነበሩት የኢትዮጵያ ነገሥታት የተሳከሳትን ተ ማፅኖ አክብራ ዘመቀበልና ለንጉሡ አቅርባ በማስወሰን ይዞታቸው እንደነበረ ፀንቶ እንዲተዋል

ማድረጓን የተለያዩ ጸሐፍት የገዳሙን ታሪክ ሲያወሱ በዋነኝነት የሚጠቅሱት ፍሬ ነገር ሆኖ ይገኛል።

ከዚህም ቀጥሎ ኢትዮጵያውያኑ በቦታው ላይ መኖሪያና ቤተ-ጸሎት ሠርተው ለሦስት መቶ ዓመታት ያህል በሰላም ይዘታቸውን ጠብቀው ከኖሩ በኋላ የመጀመሪያው ጁኪየሩሳሌም እሥላማዊ ንጉሥ ዑማር ኢብን አል ካታብ መስቀላውያንን ድል አድርጉ ኢየሩሳሌም እንደገባ የ«ዑማር ቃል ኪዳን» በተሰኘው ታዋቂ አዋጁ አማካይነት አትዮጵያውያን በዴር ሡልጣን ላይ ያላቸውን የባለቤትነትና የይዞታ ባለመብትነት በማረጋገጥ የሰጠው የጽሁፍ ድንጋጌና ይፋዊ መግለጫ ሌላው ተደጋግሞ የሚጠቀስ ዐቢይ አስረጂ ነው።

በዴር ሡልጣን ገዳም ላይ በዚህ አኳኋን ለአያሌ ዓመታት ሳያቋርጥ የቀጠለው የኢ ትዮጵያ ቤተክርስቲያን የባለቤትነትና የይዞታ መብት ቱርኮች ኢየሩሳሌምን ሲገዙ በሩባቸው በርካታ ቀጣይ ዓመታትም አመዛኙን ጊዜ እንደፀና ዘልቆ ነበር። ይሁን እንጂ በከተማይቱ ከነበ ሩት ጥንታውያት አብያተ-ክርስትያናት መካከል አንዳንዶቹ ከጊዜ በኋላ ቅዱሳት መካናትን በመቀራመት ሰፊ ቦታ ይዘው በብቸኝነት ለመቆጣጠር በየፈናቸው ስለተነሱ፣ በተለያዩ የክርስቲያን ማኅበረሰቦች መካከል ቀስ በቀስ ተነስቶ አሳሳቢ ደረጃ የደረሰው ይኸው የኃይለኞች የአርስ በርስ ሽኩቻ እና ቡተመሣሣይ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ይካሄድ ስነበረው የመሳፍንት ክፍፍልና ግጭት ሳቢያ በአንፃራዊ አቋማቸው ደካማ የነበሩት ኢትዮጵያውያን ድጋፍ በማጣታቸው የተነሳ በቀላሉ ለጥቃቱ ለለባ ሲሆኑ የቻሉበት አስከፊ የታሪክ አጋጣሚ ሲፈጠር እንደቻለ ተደጋግሞ የሚወሳ ጉዳይ ነው።

በዚህ አኳኋን ከ12ኛው ክፍለ-ዘመን ገደማ ጀምሮ ውስጥ ውስጡን ሲብላላ ቆይቶ አስከ 19ኛው ክፍለ-ዘመን ድረስ የዘለቀው የአብያተ-ክርስቲያናት የይዞታ ሽኩቻ ዋና ከመነሻው አንሥቶ በኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱሱ መቃብር ውስጥ የነበሩትን የኢትዮጵያ ገዳም ይዞታዎች ከአ ትዮጵያውያን ቀምቶ ለመቆጣጠር የግሪክና የአርመን አብያተ ክርስቲያናት አርስ በእርስላቸው ሲፋለሙ የቆዩበት ሂደት ሲሆን፣ በዚህም የተነሣ አቅመ-ደካማና ደጋፊ ያልነበራቸው ኢ ትዮጵያውያን ከይዞታቸው ቀስ በቀስ ሲገፉ ቆይተው በመጨረሻ በቅዱሱ መቃብር ከነበራቸው ይዞታ ጭራሹኑ ተፈናቅለው በአሳዛኝ ሁኔታ ሊነቀሉ እንደቻሉ የገዳሙ ታሪክ ያስረዳል።

እንደሚታወቀው አስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን በበላይነት ሲመሩ የነበሩት የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት በኢየሩ ሳሌም የነበሩት ኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ወገኖቻቸው ደጋፊ አጥተው በተጻሕሙባት በአሥራ ሰምንተኛው ምዕተ ዓመት ይህንኑ ምቹ ሁኔታ ተጠቅመው የኢትዮጵያውያን ተጠሪና ወኪል ነን ብለው በመቅረብ ጥንታዊውን የኢትዮጵያውያን የዴር ሡልጣን ገዳም ይዞታ በረቀቀ ዘዴ ስመጋራት ብዙ ያልተሳኩ መከራዎችን ሲያደርጉ የቻሉበት አጋጣሚ እንደተፈጠረ ስለቦታው ታሪክ የጻፉ ሊቃውንት ያወሣሉ። ሁኔታዎች በዚህ አኳኋን ቀጥለው ሳለ፣ በግብጾች ይገዛኛል ባይነት በዴር ሡልጣን ላይ ሉተጫረውና እስከአሁንም ድረስ ሁነኛ ዕልባት ላላገኘው የባለቤ ትነትና የይዞታ ውዝግብና ክርክር አርሾና መነሾ የሆነው መዘዘኛ ክስተት እንደሞላ መድረሱ ከዚ ሁ ጋር ተያይዞ የሚገለጽ ነው።

ይኸውም ኢብራሒም ሞዓልም ዝዘሪ የተባለ የግብጽ ቤተክርስቲያን ምእመን በ1766 ዓ. ም. ከግብጽ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ በዴር ሡልጣን ገዳም ለነበሩት ኢትዮጵያውያን መነኮሳት ማደሪያ እንደሌሰው በመግለጽ የአምነት ወንድማቸው መሆኑን አይተው በእንግድነት ገዳሙ

ውስጥ እንዲያስርፋት ላቀረበላቸው ልመና የሰጡት ቀና ምላሽ ግብጾች ገዳሙን እጃቸው ሰማስ ገባት ሲያውጠነጥኑ የሩትን መስሪ ዕቅድ እውን ሰማድረግ በመንደርደሪያነት የተጠቀሙበትን ምቹ መንገድ ባልተገመተ ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረጉ ነበር። ይህም አጋጣሚ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በገዳሙ ላይ ያላት ታሪካዊና ሕጋዊ የባለቤትነት መብት ጥያቄ ላይ እንዲወድቅ ያደረገውን መርዘኛ ጋሬጣ ተከሉ ሲያልፍ መቻሉ በምሬት ሲታወሰ የሚኖር ነው።

በልቡ መሠረ ተልዕኮ ይዞ በአስጠጊነ ልመና ሰብብ ወደ ገዳሙ በእንግድነት የገባው መስሪ ግብጻዊ /ኮፕት/ በቅድሚያ ራሱን በሚገባ እስኪያደላድልና ከአካባቢው አስተዳዳሪ ባለሥልጣናት ጋር በደንብ እስኪግባባ ድረስ ከኢትዮጵያውያኑ መነኮሳት ጋር ለተወሰነ ጊዜ ተመሳስሎ ከቆየ በኋላ የገዳሙና የመነኮሣቱ ተጠሪ እኔ ነኝ በማለትና አስተዳዳሪዎቹ ቱርኮች የሚናገሩትን ሀ ረብኛ ቋንቋና ባሕል በማያውቁት ኢትዮጵያውያን እንደተወከለ አድርጉ ራሱን በማቅረብ ሰውር ዓላማውን ለማስፈጸም ከተጠበሩት ባዕዳን ወገኖች ጋር በሰውር በመመሣጠር ከግብጽ ተሳልኮ ያስመጣውን ቀሲስ ጊዮርጊስ የተባለ የኮፕት ካህን በገዳሙ ውስጥ ለማስተመጥና አልፎ ተርፎም የራሱን ሰዎች በዙሪያው ለማሰባሰብ የበቃበት ሁኔታ ሊፈጠር እንደቻለ ታሪክ በተጨባጭ ይመሰክራል።

ኢትዮጵያውያኑ መነኮሳት በዚህ ተራ የሚታለል እድሪኑት የተጀመረው የግብጾች የተንኮል አንቅስቃሴ ከሕጋዊ የገዳሙ ይዞታቸው በዘዴ ለማፈናቀል የተወጠነ አደገኛ ሴራ መሆኑን ዘግይተው ከተገነዘቡ በኋላ የተፈፀመባቸውን ማጭበርበርና ደባ በአስተዳዳሪዎቹ የቱርክ ባለሥልጣናት ዘንድ አምርረው ቢቃወሙም አንደ ግብጾቹ ገዳያቸውን እንደ ልብ የሚገልጸብት በቂ የበረብኛ ቋንቋ ችሎታ ስላልነበራቸው፣ ይልቁንም ደግሞ ግብፃውያን በወቅቱ ቅኝ ገዥያቸው ቡቱርክ መንግሥት ዘንድ አንደዜጋ ይቆጠሩ ስለነበር በባይተዋርነት አቤቱታቸው በሚ አጥዩ ተገቢውን ፍርድ ሊያገኙ ካለመቻላቸው ሌላ፣ በገዳሙ የነበራቸው ሙብትና ንብረት ቀሰ በቀስ እየተቆረሰ ጭርሱን ሲወሰድ በቁጭት መመልከት ግዴታ እንደሆነባቸው የተለያዩ ዋቢዎች የሚገልጹት አውነታ ነው። ቀሲስ ጊዮርጊስ ከዚህም ይባስ ብለው ለውንብድና ተግባር ከግብፅ መልምሎ ባሰመጣቸው ቅጥረኞች እየተደበደቡ ብዙ ሥቃይና መከራ የደረሰባቸው ከመሆኑም ሌላ፣ ይኸው አድራጊና ፈጣሪ ሆኖ በሳያቸው ላይ የተቀመጠው የኮፕት ቄስ በመጨረሻው በምሥራቅ በኩል የነበረውን የዴር ሡልጣን ገዳም ከፍል ቆርጦ ለመስኮቦች /ለፍሲ ያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን/ አንደሸጠባቸው የገዳሙ ታሪክ ሲያወሳው የሚኖረው አሳዛኝ ክስተት ነው።

ይህን የመሠለው የግብፆች አስከፊ ጥቃት በነገሠባት ሁኔታ የዋሆኑ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መነኮሳት በእንግድነት ካስጠጓቸው ግብፆች ጋር ለአርባ ሰባት ዓመታት ያህል ሳይወጹ በግድ አብረው ከቆዩ በኋላ፣ በመጨረሻው ከእብዛኛው የይዞታቸው ክፍል አስከመፈናቀል ሰደረሱብትና ኢትዮጵያ በገዳሙ ላይ ባላት ታሪካዊና ሕጋዊ መብት ላይ የ ማይሽር ጠባሳ ሳሳረፈው ረቂቅ ደባ ዳግም ሰለባ ሲሆኑ በመቻላቸው፣ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳምና በግብፅ ኮፕት ቤተ ክርስቲያን መካከል በገዳሙ የባለቤትነትና የይዞታ መብት ዙሪያ አንደዋዛ የተጫረው ውዝግብ ወደ መደበኛ ክርክርነት ተሸጋግሮ አሰካለንበት ዘመን ድረስ ሲ ዘልቅ አንደቻለ የሚታወቅ ነው። ለዚህ ጥናት መሠረታዊው የመነሻ ነጥብ ይህንን ለዘመናት ሲ ንከባለል የመጣውን ውስብስብ ችግር ለመፍታት ዓለም አቀፍ ሕግን በመጠቀም ምን ማድረግ ይቻላል? ቅሚል በመሆኑ ለመግቢያ ያህል ይህን ካልን ወደ ዋናው ርዕሴ-ጉዳይ አናልፋለን።

3. የደር ሡልጣን ገዳም የባለቤትነት ክርክር በሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሕግጋት ሥር ያለው ገጽታ

1. <u>መንደርደርያ</u>

የዚህ ጥናታዊ ቅኝት መሠረታዊ ትኩረት ኢትዮጵያ በደብረ-ሥልጣን ገዳም ላይ ያላትን የባለቤትነት መብት ከዓለም አቀፍ ሕግ አንፃር መቃኘት ቢሆንም፣ በቅድሚያ ጉዳዩ ከሥር ጀምሮ ሲታይባቸው የቆዩትን ሀገራዊ ሕግጋት፣ ቀጥሎም ዓለም አቀፍ ሕግ በጉዳዩ ላይ ያሰውን አገባብ በቅደም ተከተል ማየቱ የጭብጡን ሕጋዊ ማዕዘናት በግልጽ ለመረዳት ይጠቅማል።

«ሀገራዊ ሕግ» /ወይም የሀገር ውሰጥ ሕግ/ የሚለው ሐረግ በእንግሊዝኛ አጠራር «Domestic or Municipal law» በመባል የሚታወቀው ፅንሰ-ሐሳብ ሲሆን፣ በዚሁ አገባቡም በደር ሡልጣን ገዳም ላይ የባለቤትነት ውዝግብና ክርክር ከተጀመረበት ዋዜማ አንስቶ እስካሰንበት ዘመን ድረስ አካባቢውን በበላይነት ሲያስተዳድሩ የነበሩት የተሰያዩ መንግሥታት በኢየሩሳሌም ቅዱሳት መካናት ቀደምት ባለይዞታዎች መካከል በየወቅቱ የተነሱትን የይገባኛል ጥያቄዎችና ይዞታን ሰላማዊ ባልሆኑ መንገዶች ለማስፋፋት ከሙከር ጋር የተያያዙ ግጭታዊ ክስተቶችን ከመፍታትና ወጥነት ያለው ሥርዓት ከማስያዝ አኳያ በየጊዜው ያወጧቸውን፣ በሥራ ላይ ያዋሏቸውንና በሂደት ተፈጻሚነታቸው ያበቃውንም ሆነ አንደበና የሚገኘውን ልዩ ልዩ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሕግጋትና ደንቦች የሚያጠቃልል መሆኑን በቅድሚያ መግለፁ ተገቢ ይሆናል።

እንዲሁም በኮመሞሃይ ሁኔታ ከላይ በርዕሱ እንደተጠቀሰው ችግሩ ከ«ዓለም አቀፍ ሕግ» እንፃር የሚታይ በመሆኑ፣ International law በሚል የእንግሊዝኛ ፍቺ የሚገለፀው ፅንሰ-ሐሳብ በዚህ ጥናታዊ ቅኝት ውሰጥ ያለው መሠረታዊ አገባብ ዴግሞ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ያገባናል የሚሉ የተሰያዩ ወገኖችን ትኩረትና ተሳትፎ በሚጋብዝ ድንበር ተሻጋሪ ጠባዩ ምክንያት ከረዥም ጊዜያት አንስቶ ዓለም አቀፋዊ ገጽታ በመላበስ ለዘመናት ከዘለቀው የዴር ሡልጣን ገዳም የባለቤትነት ክርክር አኳሳስ፣ ይዘትና ዓይነተኛ ባህርይ ጋር በሞነኝነት የተሣሰረ ሆኖ፣ በሚከተሉት መሠረታዊ ፍሬ ሐሳቦች እማካይነት ሊገለጽ የሚችል ነው።

በቅድሚያ ገዳሙ የሚገኝበት አካባቢ ዙሪያ መለስ የሦስቱ የዓለም አብይት ኃይማኖቶች /አይሁድ፣ ክርስትና እሥልምና/ መፍለቂያና የጋራ መናኸሪያ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ መልኩ ከጥንት ጀምሮ ከሚታወቅበት እሰከዛሬም ድረስ ገና ያልሰከኑ የእርስ በርስ ግጭቶችና ሽኩቻዎች ታሪካዊ ሂደትና ዘርፈ ብዙ ወቅታዊ ገጽታ ተገንዝቦ የማይታየው የገዳሙ የባለቤትነት ውዝግብ ከዚህ አጠቃላይ ሁኔታ ጋር ተገናዝቦ ሲጤን የጉዳዩን ዓለም አቀፋዊ ገጽታ እጉልቶ ያሳያል።

በሌላ በኩል የገዳሙ የባለቤትነት ክርክር በተሰያዩ የአካባቢው አስተዳዳሪ ሰዓላዊ መንግሥታት ሥልጣን ሥር በየዘመናቱ መታየቱ በራሱ የጉዳዩ አያያዝና አመራር ድንበር እጅ ራጭ ማዕዘናት እንዳሉት የሚያመላክት ሲሆን፣ በተራዘመው የክርክሩ ሂደት በይገባኛል ባይነት ግንባር ቀደም ሆነው ሲሚገቱ ከኖሩት የሁለቱ ሀገሮች /የኢትዮጵያና የግብጽ/ አብያተ - ክርሰቲያናት ባሻገር መጠንና ይዙቱ የተሰያየ ይሁን እንጂ ከተራ ወገናዊነት ያለፈ ፖለቲካዊ አቋም ይዘው ከበለተጀርባቸው በመሰሰፍ በክርክሩ እካሄድ፣ እቅጣጫና እወሰን ላይ በየፊናቸው ተፅዕኖ የሚያደርጉት መንግሥቶቻቸው በጉዳዩ ላይ ያላቸውን የተሰያየ ዓላማ፣ ፍላጐትና ጥቅም በእጅ እዙር የሚያንፀባርቁበት ከመሆኑ አኳያ ሲታይ የጉዳዩን ዓለም አቀፋዊ እድማሰ በተጨባጭ ያመላክታል።

ከዚህ በተጨማሪም እሥራኤል ከአረቦች፡ በተለይም ክፍልስጤማውያን ጋር ባላለፈችው ረዥም ዘመናትን ያስቆጠረ ግጭት· ሳቢያ እ.አ.አ. 1947ዓ.ም በተ.መ.ድ. ውሣኔ ዓሰም አቀፋዊ ቀጠና ሆና የተፈረጀችው የኢየሩሳሌም ከተማ የወደፊት ዕጣ ፈንታ እስከአሁንም ድረስ ገና አልባት ያላገኘ ጉዳይ መሆኑ፣ የዴር ሡልጣን ገዳምን ጨምሮ ልዩ ልዩ ጥንታዊ ቅዱሳት መካናት የሚገኙበት የኢየሩሳሌም ክፍለ ከተማ ዓለም አቀፍ ጥበቃና ከለላ እንደሚያሻው በተለይ በጥንታዊ ቅዱሳት መካናት ባሰይዞታዎቹ ወገኖች ዘንድ በተጠናከረ ሁኔታ እየታመነበት መምጣቱና ብዙ ሺህ ዓመታትን ያስቆጠሩት እነኚሁ ቅዱሳት መካናት በዓለም አቀፍ ቅርስነት የሚታዩ መሆናቸው ተዳምሮ ከፍ ሲል የተገለፀውን የባለቤትነት ክርክር ዓለም አቀፋዊ ገጽታ በ ማጉላት አግባብነት ያላቸውን ዓለም አቀፍ ሕግጋትና ከዚህም ጐን ሰጐን በንተው የቆዩ ተቀባይነት ያላቸው ዓለም አቀፍ ልማዳዊ አሠራሮች አግባብ በጥንቃቄ እንዲፈተሽ የሚጋብዝ ሆኖ ይገኛል።

ከላይ በቅደም ተከተል የተገለፁትን የጥናታዊ ቅኝቱ ቁልፍ ጽንሰ - ሐሳቦች ከዴር ሡልጣን ገዳም የባለቤትነት ክርክር በተዛመደ መልኩ እንደሚከተለው ዘርዘር ባሰ ሁኔታ ለመግለጽ ተሞክሯል።

2. ሀገራዊ ሕግጋት

2.1. የአቶማን ቱርክ መንግሥት

በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና በግብጽ ኮፕቶች መካከል በዴር ሡልጣን ገዳም የባለቤትነት ጉዳይ ላይ ውዝግብ ሊነሳ የቻለው መጀመሪያ ክላይ በተጠቀሰው አኳኋን ዴር ሡልጣን ገዳም ውስጥ በዘዴ የገቡት ኮፕቶች እ.ኤ.አ. በ1820 ዓ.ም. ገዳሙን እናሳድስ በሚል ምክንያት· አሳበው እነሱ ከነበሩበት የነዳሙ· ክፍል ኢትዮጵያውያኑን አግባብተው ካስወጡ በኋላ ከአርመኖችና ከአስተዳዳሪዎቹ ቱርኮች ጋር በመመሳጠር ኢ ትዮጵያውያኑ ወደቦታቸው ተመልሰው እንዳይገቡ በማድረጋቸው ላቢያ ቢሆንም፣ ኮፕቶቹ ሁለት የነዳሙን ቁልፎች በእጃቸው አስገብተው በገዳሙ ባለቤትነት ላይ በይፋ የይገባኛል ጥያቄ ለማንሣት የቻሉት እ.ኤ.አ. በ1838 ዓ.ም. በኢየሩሳሌምና አካባቢው ተከስቶ የነበረውንና ኢ ትዮጵያውያኑ መነኮሣት በገፍ ያለቁበትን መጠነሰፊ የወረርሽኝ በሽታ መላቻ ተከትሎ እንደነበር ታሪክ ደጋግሞ አውስቶታል።

ይኸውም ከተጠቀሰው ወቅት ቀደም ባሉት ዓመታት ቀስ በቀስ በረቀቀ የማሞቸርበር ዘዴ እግራቸውን ገዳሙ ውስጥ አስገብተው የተጠናከሩት የግብጽ መነኮሳት የተነሣውን በሽታ ለመግታት ገዳሙን ማጽዳት ያስፈልጋል በሚል ሰበብ በእልቂቱ ቁጥራቸው የተመናመነውን ጥቂት ኢትዮጵያውያን መነኮሣት ምንም ዓይነት የመከላከል አቅም እንደሌላቸው በማየት ሁኔታውን ተጠቅመው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በገዳሙ ላይ ያላትን ብቸኛ ባለቤትነት የሚያረጋግጡ ፀርካታ ዋና አርጅናል የማስረጃ ሠነዶችን በቆሻሻ ስም በማቃጠል ማውደማቸው ነው። ከዚህ በኋላ በሙሉ ልብ ገዳሙ የኛ ነው ከማለታቸውም ባሻገር፣ አጋሮቻቸው በነበሩት አርመኖች እየተረዱ የኢትዮጵያውያኑን መነኮሣት ንብረት ዘርፈው ወደተቆጣጠሩት አብዛኛው የገዳሙ ·ክፍል ኢትዮጵያውያኑ ተመልሰው እንዳይገቡ በመከልከላቸው የተነሣ ውዝግቡ ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ እንደተቀሰቀሰ የታሪክ ዋቢዎች ያስረዳሉ።

በወቅቱ አካባቢውን ያስተዳድር የነበረው የቱርክ መንግሥት ግን በኢትዮጵያኑ ላይ የደረሰውን ግፍና በደል ተመልክቶ ለችግሩ የሚበጅ መፍትሔ ከመስጠት ይልቅ ቀደም ሲል በግሪክና በአርመን አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናት፣ እንዲሁም በሌሎች የቅዱሳን ቦታ

ባለይዞታዎች መካከል በየወቅቱ እየተነሱ አስተዳደሩን ያውኩ የነበሩትን የይገባኛል ጥያቄዎችና ይዞታን የማስፋፋት ግፊያዎች አስከመጨረሻው ለመግታት አልሞ እ.አ.አ. በ1835 ዓ.ም. ያወጣውን ማናቸውም የቅዱሳት መካናት ባለይዞታ ባለበት ረግቶ እንዲዐና የሚያስገድድ ድንጋጌ /Firman of Zilcade/ ወይም አስከለሁን ድረስ «ስታተስ ኮ» የሚሰኘውን ይሕግ መርህ ጠቅሶ ተበዳዮቹ ኢትዮጵያውያን መነኩሳትና ያፈናቀሏቸው ኮፕቶች በነበሩበት ተቻችለው እንዲቆዩ ማዘዙ የሚታወቅ ነው።

ይህ ኢትዮጵያውያኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ፍትህ የተነፈጉበት የ«ስታተስ ኮ» ወይም የባለሀበት እርጋ ሥርዓተ ዕግድ ማፅኛ ውሳኔ በአህበቢው በነበሩ ተወዛጋቢ ወገኖች ላይ በሙሉ ወጥነት ባለው መልኩ ይሠራ የነበረ ቢሆንም፣ አንዳቸውም ቢሆኑ እንደ ኢትዮጵያውያኑ ያለ አግባብ በሕገ-ወጥ መንገድ ከይዞታቸው እንደተፈናቀሉ ለመቅረት እልተዳረጉበትም። በዚህም የተነሣ በወቅቱ በቱርክ መንግሥት ሹመኞች ዘንድ ተሰሚነትና ከእትዮ አኳያም በኢ ትዮጵያውያኑ ላይ የበላይነት የነበራቸው ኮፕቶች ከሕጉ ዓላማና መንፈስ ውጭ ኢ ትዮጵያውያኑን ከሕጋዊ ይዞታቸው በማፈናቀል የተቆጣጠሩትን የደር ሡልጣን ገዳም ያለምንም ተጨማሪ የማስረጃ ድጋፍ የኛ ነው ብለው በድፍረት ለመከራከር ያበቃቸውን ዕውቅናና መብት በዚህ ሕግ ከለላ ስጭነት ሊያገኙ ቻሉ ማለት ነው።

ከዚህ አኳያ በቱርክ የተደነገገው የ«ስታተስ ኮ» ሕግ በደር ሡልጣን ገዳም የባለቤትነት ክርክር ላይ ግዙፍ ተጽዕኖ በማሳደር የመጀመሪያውን ምዕራፍ የያዘ ሲሆን፣ ከዚያም ወዲህ የአካባቢው አስተዳዳሪ መንግሥታት እየተለዋወጡ ቢሄዱም ሳይሻርና ሳይተካ እስከዘሬም ድረስ ፀንቶ እንደቀጠለና በኢየሩሳሌም የሚገኘውን የቅዱሳን ቦታዎች ይዞታ አስመልክተው ለተነሳፉት የመንግሥታት ቀጣይ ድንጋጌዎችና ውሳኔዎች ዋነኛ ግብር መሠረት ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል።

የባለሀበት አርጋ ሥርዓተ-ዕግድ በጥንታዊ የቅዱሳት መካናት ይዞታ ላይ ፀንቶ እንዲኖር በተደነገገበት የኦቶማን ቱርክ ሕግ /ፊርማን/ ከላይ በተጠቀሰው አኳኋን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በገዳሙ ላይ ያላትን ሐቅን የተመረከዘ የባለቤትነት የይዞታ መብት ለማስከበር ተገቢው ፍትህ የተነፈጋት ቢሆንም፣ ኢትዮጵያውያኑ መነኮሳት በዚህ ተስፋ ሳይቆርጡ አትክልት ይተክሉበት በነበረው የገዳሙ ትጥር ሡስዋ በከፊል በቅድስት ዕሌኒ ቤተ ክርስቲያን እናት ሁሪያ እንዲኖም ወጣ ባሉ ቦታዎች ላይ ደሳሳ የጭቃ ጉጅዎችን በመሥራት መንፈሳዊ ተልዕኮአቸውን እየተወጡ በቱሳዮቹ ረዥም ዓመታት ትክክለኛ ፍርድና ፍትሕ ለማግኘትና ሕ ጋዊ ይዞታቸውን ለማስመለስ ከብዙ ሥቃይና መከራ ጋር እልህ አስጨራሽ ተጋድሎ ማድረጋቸውን ታሪክ ይዘክራል።

በዚያ ዘመን በኢየሩሳሌም በነበሩና ወደ ኢየሩሳሌም በተነዙ ኢትዮጵያውያን ያልተቋረጠ ጥረትና በኢትዮጵያ ነገሥታት ድጋፍ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያውያንን እውነተኛ ባለቤትነት አውቀው የበኩላቸውን ቀና እገዛ ባደረጉ የተለያዩ አውሮፓውያን በተለይም እሠቅ እንግሊዛውያን የሃይማኖትና የታሪክ ሰዎች በኩ አስተዋጽኦ በማበጸኞ የተነጠቀውን የደር ሡልጣን ገዳም ይዞታ ለማስመለስ ባለበት እርጋ በሚለው የሕግ መርህ ጫና ሥር በየጊዜው ከተደረጉት በርካታ ያልተሳኩ ሙከራዎች መካከል የሚከተሉት በምሳሌነት ይጠቀሳሉ።

- አ.አ.አ. ከ1849-1850 ዓ.ም ድረስ በኢየሩሳሌም የነበሩ ኢትዮጵያውያን የደረሰባቸውን ግፍና በደል ሰምተው ከኢትዮጵያ የመጡ በቁጥር 100 ገደማ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ግብጸኞቹ በሕገ-ወጥ መንገድ የያዙትን ቦታን ለማስለቀቅ ያደረጉት ጥረት ሙሉ በሙሉ ባይሳካም፣ በመረርሺኝ በሽታው የሞቱት ኢትዮጵያውያን በሠጅቸውና ግብጸኞ

በስታቲስቲክው ሕግ ምክንያት ለማፍረስ ሳይችሉ ቀርተው ባቀዩአቸው የጭቃ ጉጆዎች ውስጥ ገብተው ለመቀመጥና ከከፕቶቹ የተረፈውን የዳርቻ ይዞታ በመቆናጠጥ የባለቤትነት መብት የማስከበሩን እንቅስቃሴ ነፍስ ዘርተውበታል።

- እነዚህ በዴር ሡልጣን ገዳም ደጣጣ የጭቃ ጉጆዎች ውስጥ ይኖሩ የነበሩት ኢትዮጵያውያን መነኮሳት እ.ኤ.አ በ1863 ዓ.ም ጊዜ ጠብቀው ኃይል ጭምር በመጠቀም ገዳሙንም ሆነ የበር ቁልፎቹን በእጃቸው ለማስገባት ቢችሉም፣ ግብጾቹ በወቅቱ እንደዜጋ በሚቆጥራቸው ገዢያቸው የቱርክ መንግሥትና አርመኖች ይደገፉ ስለነበረ ቦታው የኢትዮጵያውያን ታሪካዊና ሕጋዊ ንብረት እንደሆነ ቢታወቅም እንኳ፣ ቦታውን ያስተዳድር በነበረው የቱርክ መንግሥት ሹም ትእዛዝ አዲስ የበር ቁልፎች ተሰውጠው ለግብጾቹ ተሰጥቷቸዋል። በዚህ ወቅት ኢትዮጵያውያኑ ብአብዛኛው የተጉዱት ከመንግሥት በኩል ድጋፍ በማጣት ሲሆን፣ ይህውም በቅድሚያ በመሣፍንት መከፋፈልና የሥልጣን ሽኩቻ የተነሣ በኢትዮጵያ የነበረው ማዕከላዊ መንግሥት መዳከሙና በኋላም የአጤ ቴዎድሮስ ከታላቋ ብሪታንያ ጋር መጣላት እንደነበረ የታሪክ ጸሐፍቶች ይገልፃሉ። በዚህ አጋጣሚ አጤ ቴዎድሮስ ወደ ኢየሩሳሌም ዘምተው የኢትዮጵያን ይዞታ ለማስከበር ሐሳብ እንደነበራቸው በተለያዩ የታሪክ ምሁራን እንደተወሳ የሚታወቅ ሲሆን፣ የዘመኑ በገና ደርዳሪዎችም «ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሣ ብሎ ስም፡ አርብ አርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም» በማለት አዚመው እንደነበር አይዘነጋም።

- ግብጾች ዴር-ሡልጣን ገዳም ውስጥ በሕገ ወጥ ሁኔታ የያዙትን ቦታ በማስፋፋት በገዳሙ ባለቤትነት ላይ ያነሱትን የይገባኛል ጥያቄ ይበልጥ ለማጠናከር እንዲረዳቸው እ.ኤ.አ በ1893 ዓ.ም በስተሰሜን በኩል የነበረውን የገዳሙን አነስተኛ በር ዛሬ በሚታየው ዓይነት አስፋፍተው ለመሥራት ማፍረስ ሲጀምሩ፣ በገዳሙና በአካባቢው የነበሩት ኢትዮጵያውያን አድራጉቱን በኃይል በመቃወማቸው በሰው ላይ ጉዳት ያደረሰና የተወሰኑ ኢትዮጵያውያን ለእሥር የተዳረጉበት ከፍተኛ ረብሻ ተፈጥሮ ነበር። በዚህ ወቅት የነበረው የኮንቶቹ ዓለ ማኅ ዕቅድ ብሩን አስፋፍቶ በማሠራት የተገደበ ብቻ ሳይሆን በገዳሙ ዙሪያ የሚገኘውን ታላቅ ግንብ አፍርሶ ጠቅላላ ቦታውን ብይዞታቸው ሥር ለማጠቃለል እንደነበረ የገዳሙ ታሪክ ያስረዳል።

- ይህ ሁከት ያስከተለው የግብጾች ሕገ-ወጥ የመስፋፋት ሙከራ እንደተከሰተ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ በዚያኑ ዓመት ራስ መኮንን ወደ ቱርክ ኢስታምቡል ማመልከቻ በማስያዝ ልከው ከኮፕቶች የሚፈፅሙት በደል እንዲቆምና ገዳሙም ለሕጋዊ ባለይዞታዋ ለኢትዮጵያ እንዲ መለስ ጥረት ቢያደርጉም፣ ከፍ ሲል በተጠቀሱት የወገናዊነትና የአድሎአዊነት ምክንያቶች ተልለስዋቸው ውጤታማ ሊሆን አልቻለም።

- ከዚህም በኋላ ዳግማዊ አጤ ምኒልክ በሁኔታው ተስፋ ሳይቆርጡ ደጃዝማች መሸሻ ወርቁ የተባሉ ባለሥልጣናቸውን እንደራሴ አድርገው በጉዳዩ ላይ ከአቶማን ቱርክ ባለሥልጣናት ጋር እንዲነጋገሩ እ.ኤ.አ በ1905 ዓ.ም ወደ ቁስጥንጥንያና ኢየሩሳሌም እንደላኩ ሰለጋዳሙ የተጻፉት የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፣

በ[illegible]ረሻ የተጠቀሰውን ከንዋኔ ዘርዘር ባለ መልኩ ለመግለጽ ያህል፣ ደጃዝማች መሸሻ ወርቁ ይህንኑ ተልዕኮ ለማሳካት ባደረጉት ጥረት የኢትዮጵያ ሕጋዊ ንብረትና ይዞታ የሆነው የዴር ሡልጣን ገዳም ለባለቤቱ እንዲመለስ ለቱርክ ባለሥልጣናት አቤቱታ ሲያቀርቡም፣ አብዛኞቹ የኢትዮጵያን የገዳሙ ባለቤትነት የሚመሰክሩ ዋና ለነዶች ቀደም ሲል በኮፕቶቹ ተቃጥለው እንዲጠፉ ተደርገው ስለነበረ፣ አቤቱታቸው ተቀባይነት ሊያገኝ አልቻለም።

ሆኖም እኒህ መልዕክተኛ የሚሰረጃዎቹ ትጂ የሚገኙበትን የቱርክ መንግሥት ቤተ መዛግብት በመፈተሽ መረጃ ለማሰባሰብ እንዲችሉ አስከተለው ለቱርክ ባለሥልጣናት ያቀረቡት ጥያቄ አምንታዊ ምላሽ በማግኘቱ አስከዛሬም ድረስ በዋቢነት የሚጠቀሱትንና ኢትዮጲያ ገዳሙ ላይ ያላትን የሚያመላክቱ የባለቤትነት መብት የሚያረጋግጡትን ቁልፍ የሚሰረጃ ሠነዶች ለ ማሰባሰብ ችለዋል።

ተልዕኮአቸውን በመቀጠል ጉዞአቸውን ወደ ኢየሩሳሌም ያቀኑት ደጃዝማች መሸሻ ወርቁ በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያውያኑ መነኮሳት የያዩር ሡልጣን ገዳም ሰሜናዊ በር በግብጾች ቁጥጥር ሥር ወድቆባቸው መሠዊያ መገቢያ አጥተው በሚጨነቁበት ቀውጢ ወቅት ላይ በመድረሳቸው ፡ ችግሩን ለመፍታት ባደረጉት ብርቱ ጥረት ቦታውን ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ ገዳም ይዞታ ሥር አድርገው መነኮሳቱ እስከ አሁን ድረስ ያለችግር የሚጠቀሙበትን የገዳሙን ምሥራቃዊ /ዮሞኒሲክ/ በር ለማስከፈት የቻሉ ሲሆን፣ ይህም በወቅቱ ለተፈጠረው ችግር ሁነኛ መፍትሔ ከማስገኘት አልፎ የኢትዮጵያን ገዳም የይዞታና የባለቤትነት መብት በማጠናከር ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ ሊያበረክት የቻለ ተጠቃሽ እርምጃ ነው።

በሊላ በዙል የደር ሡልጣን ገዳም ከሥረ-መሠረቱ የኢትዮጵያ መሆኑን፣ በሕገ-ሞገድ በግብጾች ይዞታ ሥር ሊወድቅ መቻሉንና በዚህም የተነሣ በአካባቢው የነበሩት ኢ ትዮጵያውያን አውነተኛ ሰሚ ዳኛ፣ ትክክለኛ ፍርድና ፍትሕ አጥተው በገዛ ንብረታቸው ከፍተኛ ግፍና በደል እንደደረሰባቸው ተረድተው ጉዳታቸውንና ተቀርቋሪነታቸውን በየጊዜው በተለያዩ መንገዶች ከስተጋብትና ይህንኑም በጽሑፍ አስፍረው የታሪክ መዘክር ካስቀሩት በርካታ አሙር፣ተሙያን ተንገሮች፡ የሃይማኖትና የታሪክ ሰዎች መካከል ሁለት አውቅ እንግሊ ንዙያን አካዘቢው በአቶማን ቱርክ ሥር ይተዳደር በነበረበት ወቅት የፈፀሙት ተና የምስክርነት ተግባር ከዚህ ረገድ ጉልቆ የሚጠቀስ ሆኖ ይገኛል።

አንደኛው አባ ሳሙኤል ጉባት የሚባሉ የአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ሲሆኑ፣ እነርሱም በዚያን ዘመን ረዘም ሳሰ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ በመንፈሳዊ ተልዕኮ የተቀመጡ፣ የተመላለሱና አማርኛ ቋንቋ ፅሁፍ የተማሩ የኢትዮጵያ ወዳጅ የነበሩ ሰው ናቸው። እኚሁ ዕ ውቅ እንግሊዛዊ ጳጳስ በዴር ሡልጣን ገዳም የነበሩት ኢትየጵያውያን መነኮሳት አ.አ.አ በ1838 ዓ.ም በተከሠተው መረርሽኝ በሽታ ተፈጅተው አብዛኛው የገዳሙ ይዞታ በግብጾች ቀ ጥጥር ሥር ከመውደቁ አስቀድሞ በ1820ዎቹ ውስጥ ኢየሩሳሌም በተቀመጡበት ወቅት ግብጾች እንዴት አድርገው በተጭበረበረ ዘዴ ወደ ገዳሙ እንደገቡ፣ በዚህ መሰረ የተቀናበሩ ትን ይዞታም እንዴት ቀስ በቀስ እንዳስፋፉ፣ በተለይም ከአርመኖችና ከዙታው አስተዳዳሪ ቱ ርክች ጋር በመመሳጠር እ.አ.አ በ1820 ኢትዮጵያውያኑን ከገዳሙ ከፊል ይዞታ እንዴት እንዳስወጧቸውና በመጨረሻም በኢትዮጵያውያኑ አጅ የነበሩትን የባለቤትነት ማስረጃዎች እ.ኤ. አ. በ1838 ዓ.ም በተከሰተው የመረርሽኝ በሽታ አሳብበው በማቃጠልና የገዳሙን ቁልፎች እጃቸው በማስገባት ሁኔታዎችን ካመቻቹ በኋላ በገዳሙ ባለቤትነት ላይ በግን አለብኝነት ይፋ ያደረጉትን የይገባኛል ጥያቄ እንዴት ሊያነሱ እንደቻሉ ጠንቅቀው ያውቁ ስለነበር፣ በወቅቱ የከተማይቱ አስተዳዳሪዎች ከነበሩት የኦቶማን ቱርክ ባለሥልጣናት ፊት በመቆም ስለተበዳየቹ ኢትዮጵያውያን መብት በሙሉ ልብ ተቆርቋሪ ሆነው ከመሟገታቸው ባሻገር፡ በወቅቱ ሰሚ ባያገኙም ጉዳዩ በፍርድ አደባባይ እንዲታይ ሰፊ ቅስቀሳ አድርገው እንደነበር የገዳሙን ታሪክ የሚዘክሩ የተለያዩ ጽሑፎች ያሰረዳሉ።

በመሆኑም ይኸው የአባ ጉባት ጥረት በአንድ በኩል በኢትዮጵያውያን ላይ የደረሰው በሕገ ወጥ መንገድ ከይዞታ የመፈናቀል አስከፊ በደል በቱርክ ባለሥልጣናት ታፍኖ ላይቀር በመላው ኢየሩሳሌምና ከዚያም አልፎ እስከ ታላቋ ብሪታንያ ድረስ ሰሚና ተመልካች እንዲያገኝ

የበኩሉን እገዛ ሲያደርግ፣ በሌላ በኩል ኢትዮጵያ በዴር ሡልጣን ላይ ስላላት ሕጋዊ የባለቤትነት መብት ታጠቃሽ ጽሑፋዊ ምስክርነት ለማቆየት አስችሏል።

ሌላኛው እንግሊዛዊ የኢትዮጵያ ወዳጅ ኢየሩሳሌም በኦቶማን ቱርክ መንግሥት ሥር ትተዳደር በነበረበት ወቅት የእንግሊዝ ቆንስል ጀኔራል የነበሩት ሰር ጆምስ ፊን ናቸው። እኚሁ የእንግሊዝ ቆንስል ግብጻችና አርመኖች በመተባበር በዚያን ወቅት በዴር ሡልጣን ገዳም የነበሩትን ኢትዮጵያውያን መነኰሳት ከይዞታቸው አፈናቅለው ለማባረር ሲሉ ይፈጽሙባቸው የነበሩትን አደሌ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች ዘርዝረው በመግለጽ በተለይ በ1860ዎቹ ውስጥ ለእንግሊዝ መንግሥት በየጊዜው በርካታ ደብዳቤዎችን እንዳስተላለፉ በተለያዩ የገዳሙ የታሪክ ድርሣናት ተጠቅሷል። ምንም እንኳን እኚሁ የሰር ጆምስ ፊን ጥረቶች በወቅቱ ያሰቡትን ተጨባጭ ሩይዳ ለጊዜው ባይታወቅም፣ የኢትዮጵያውያኑን መሪር ጥቃት በማስተጋባትና በተለይም ደግሞ ኢትዮጵያ በዴር ሡልጣን ገዳም ላይ ስላላት የባለቤትነት መብት በተጥያቄ ሆነ በተዘዋዋሪ ቋሚ የጽሑፍ ምሥክርነት በመስጠት የበኩላቸውን ገንቢ አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ ይታመናል።

2.2. የእንግሊዝ መንግሥት

እ.አ.አ. ከ1914–1918 ዓ.ም በተካሄደው የአንደኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የኦቶማን ቱርክ የተሰለፈበት ጉራ በመሸነፉ ከጦርነቱ ፍጻሜ በኋላ በሊግ አፍ ኔሽንስ ውሳኔ ኢየሩሳሌምን በ ማንዴትነት የማስተዳደር ኃላፊነት የተረከበው ቦታላዊ ብሪታንያ መንግሥት እንደነበር ይታወቃል። ይኖን እንጂ የኢየሩሳሌም ቡኤታ እንደሌሎቹ በዚያኑ ወቅት በተመሣሣይ አኳኋን በማንዴት ሥር እንዲተዳደሩ እንደተደረጉት ቅኝ ግዛቶች ሳይሆን ከተማይቱ ከጥንት ጀምሮ የሦስቱ የዓለም ዘበይት ኃይማኖቶች መናኸሪያ በመሆኗ፣ ከዚህም ጋር ተያይዞ በውስጧ በሚገኙት ጥንታዊ ቅዱሳት መካናት ምክንያት በወቅቱ በነበረው የመንግሥታቱ ሀብረት /ሊግ አፍ ኔሽንስ/ ዘንድ ዓለም አቀፋዊ ግዕታና ባሕርይ ይዛ በተሰየ አኳኋን እንድትተዳደር ስለተረገች፣ የእንግሊዝ መንግሥት በዚሁ የአትዙሮት ከዐባ ጫና ሥር ሆኖ በማንዴት የሥልጣን ዘመኑ የፈፀመው ጉልህ ነዝር አልነበረም ለማለት ይቻላል።

ያም ሆኖ ግን ከኦቶማን ቱርክ ዘመን እንስቶ በተለያዩ ወገኖች መካከል ሲካሄዱ የነበሩትንና ዕልባት ሳያገኙ በእንግሊዝ የማንዴት አስተዳደር የተወረሱትን የኢየሩሳሌም ከተማ ጥንታዊ ቅዱሣት መካናት አወዛጋቢ የይዛባኛል ጥያቄዎች ከነመፍትሔዎቻቸው አጥንቶ ሐሳብ በማቅረብ የመፍታት ሥልጣን የተሰጠው ኮሚሽን በእንግሊዝ መንግሥት የማንዴት አስተዳደር ሥር ተቋቁሞ እ.አ.አ. ከ1921–22 ዓ.ም ድረስ አንዳንድ ጥረቶችን አድርጎ እንደነበር ታሪክ ያስታውሳል።

በዚሁ መሠረት በዴር ሡልጣን ገዳም የባለቤትነት ውዝግብ በተነሣበት ሂደት የኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን ያለአግባብ ቀደም ሲል ተነጥቆ የተወሰደባት ንብረት ስታተስኮ በሚባለው ሕግ ሽፋን ተድበስብሶ መቅረቱን ለማየት በዚሚሽኑ በኩል ጥረት ቢደረግም፣ ይኸው በኦቶማን ቱርክ መንግሥት የተደነገገውና በተፈጻሚነት ፀንቶ ለዘመናት የቆየው የባለሀበት ዕርኃ ሥርዓተ-ሰግድ ሳይሻር በነበረበት እንዲቀጥል ከጥቅማቸው አኳያ በየፊናቸው ፍላጎት የነበራቸው የሲኀ አፍ ኔሽንስ አባል መንግሥታት፣ በተለይም ፈረንሣይና ግሪክ ብርቱ አቋም ይዘው ባደረጉት ተደጋጋፊ እንቅስቃሴ ምክንያት የእንግሊዝ መንግሥት በዚህ አቅጣጫ የጀመረው ጥረት በእንጭጩ ሊከሽፍ ችሏል።

ከዚህ በኋላ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት በኢየሩሳሌም የነበሩትን ጥንታዊ ቅዱሳት መካናት ባለቤትነትና ይዞታ በማስመልከት በተለያዩ ወገኖች መካከል ሲካሄዱ የቆዩትን

የይገባኛል ክርክሮች ሥርዓት አስይዞ ለመምራት በሚል ዓላማ በ1924 ምክር ቤት የንጉሡ ትእዛዝ /The Kings Order in the 1924 Council/ የተሰኘውን ድንጋጌ አውጥቶ ሥራ ላይ እንዳዋለ አግባብነት ካላቸው የተለያዩ ዋቢ ጽሑፎች ለመረዳት ይቻላል። ይሽሙ የአንግሊዝ መንግሥት ድንጋጌ ከዝርዝር ይዘት አኳያ የተለያዩ ድንጋጌዎች ያሉት ቢሆንም፣ መሠረታዊ ቃሻማና ውጤቱ በአቶማን ቱርክ መንግሥት የወጣውን የባለሀበት ዕርጋ ሥርዓተ ዕገድ በእዲስ መልክ እንደገና ከማጽናት ያለፈ ስላልነበር፣ አሥራኤል እ.አ.አ በ1948 ዓ.ም በሀገርና በመንግሥትነት እስከ ተቋቋመችበትና በወቅቱ አብዛኛው ምሥራቃዊው የኢየሩሳሌም ክፍለ - ከተማ በሐሻ ማዊው የዮርዳኖስ ንጉሠ-ነገሥት መንግሥት ሥር እንዲተዳደር እስከተላለፈበት ጊዜ ድረስ በኢትዮጵያውያንና በግብጾች መካከል ያለውን ጨምሮ ሌሎችም አወዛጋቢ የጥንታዊ ቅዱሳት መካናት የባለቤትነትና የይዞታ መብት ይገባኛል ጥያቄዎች ሁኔታ በእንግሊዝ ማንዴት ሥር በተናጠልም ሆነ አንዳች እልባት አግኝቶ ሳይለወጥ የማድ በነበረበት ሲቀጥል ችሏል።

2.3. ሀሺማዊው የዮርዳኖስ ንጉሠ ነገሥት (The Hashimite Jordanian Kingdom)

እንደሚታወቀው ሁሉ፣ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጀምሮ ከጥንት ዘመን ጀምሮ ተያይዘው በመጡ ሃይማኖታዊና ታሪካዊ ምክንያቶች የተነሣ እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ በኢትዮጵያ ቤተ ክህነትና በሀገሪቱ ነገሥታት ዘንድ ሙሉ ተቀባይነት ከነበረው የግብጽ አሌክሳንድሪያ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ በቀጥታ ተቀብተው በሚላኩላት ግብፃዊ ጳጳሳት /የኃይማኖት መሪዎች/ ሥር ስትተዳደር መቆየቷ ከያዝነው ርዕሰ - ጉዳይ ጋር ተገናዝቦ በአንክሮ ሲጤን በጉዳዩ ላይ ራሱን የቻለ ተፅዕኖ እንደነበረው ሰመግንዘብ ይቻላል።

በቅድሚያ ግብጾች ያላ አግባብ የበላይነት እንዲሰማቸው ያደረገውና በተለይም ወደ ዴር ሡልጣን ገዳም አንገታቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያስገቡ ማግባቢያና መደለያ ሞምር አድርገው እንደተጠቀመ-በት የሚገመተው ይኸው የተጣባ ግኃኙነት የኮኖቶች መሠሪ ተልዕኮና ባላንጣነት ከ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መባቻ አንስቶ ሙ-ሉ በሙ-ሉ ለይቶለት ከታወቀም በኋላ ሳይሰወር እንደነበረ መቀጠሉ ኢትዮጵያ በዴር ሡልጣን ገዳም ላይ ያላትን የባለቤትነት መብት ለ ማስከበር በእነዚሁ ዘመናት ውስጥ ያደረገችውን ትግል በማዳከምና በማምከን ረገድ ቀላል ግምት የማይሰጠው አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ አጠያያቂ አይሆንም።

ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በመንበረ ፓትርያርክ ሙሉ አቋምና ሥልጣን ራሷን ችላ ከግብጽ ቤተ ክርስቲያን መንበረ-ጵጵስና ሰትሰይ ባቋቋመችው ቅዱስ ሲኖዶስ አማካይነት ጳጳሳቷን ለመሾም በመቻሏ፣ ቀድሞ በመምህር ደረጃ ይመራ ለነበረውም በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳም የመጀመሪያው ጳጳስ /ብፁዕ አቡነ ፊሊጶስ/ እ.አ.አ በ1951 ዓ.ም ከነገር ቤት ተመድበው መላካቸው ይታወቃል።

ይህም ወሳኝ ታሪካዊ ምዕራፍ በበኩሉ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ይዞታና አስተዳደር፣ በተለይም ሰአያሌ ዘመናት ከግብጾች ጋር የማያቋርጥ ውዝግብ ሲካሄድበት በቆየው የዴር ሡልጣን ገዳም ጉዳይ ይዘትና አካሄድ ላይ ተጨባጭና ጉልህ የሚጠቀስ ገንቢ ተጽዕኖ አሳድሯል።

ይኸውም እኝሁ የገዳሙ የመጀመሪያው ሲቄ-ጳጳስ ለዘመናት ሲንከባለል ሰቆየው የገዳሙ የባለቤትነትና የይዞታ ውዝግብ አልባት የመሻቱ ጉዳይ የተልዕኮአቸው ተቀዳሚና አንገብጋቢ ተግባር ሆኖ የይገባኛል ጥያቄው በሕጋዊ መንገድ እንዲፈታ ከፍተኛ ትግል ማድረጋቸው ሲ ሆን፣ በዚሁ አቅጣጫ በፅናት ያካሄዱት ያላሰለሰ ጥረትም ለአጭር ጊዜ ያህል ይሁን እንጂ

የታለመውን ውጤት ሙሉ በሙሉ አስገኝቶ እንደነበር በገዳሙ የታሪክ ድርሣናት ተደጋግሞ ተመስክሏል። በዚሁ መሠረት ብዙዕ አቡነ ፊልጶስ በገዳሙ እጅ ከነበሩት ማስረጃዎች ሌላ ከተለያዩ ምንጮች ያሰባሰቧቸውን ደጋፊ መረጃዎች ጭምር በመመርኮዝ ከእንግሊዝ መንግሥት ማንዴት ማብቃት በኋላ አብዛኞቹ ቅዱሳት መካናት የሚገኙበትን የምሥራቃዊ ኢየሩሳሌም ከፍለ-ከተማ አስተዳደር በቀጥታ ለተረከበው ሃሺማዊው የዮርዳኖስ ንጉሠ ነገሥት እ.አ.አ በ1953 ዓ.ም ባቀረቡት ዝርዝር አቤቱታ መነሻነት የደ፟ር ሡልጣን ገዳም የባለቤትነት ሙዝግብ ለመጀመሪያ ጊዜ በሕጋዊ መድረክ በአግባቡ ሲታይ የቻለበት ዕድል ሊፈጠር ችሏል። በመሆኑም አቤቱታው የቀረበለት የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት በዚያኑ ዓመት በዘገራቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የሚመራና የኢየሩሳሌም ዘገረ-ገዥ የሚገኙበት የሚኒስትሮች ኮሚቴ ጉዳዩን አጥንቶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲያሳልፍ ሙሉ ሥልጣን ሰጥቶ መሠየሙ፣ ኮሚቴውም ለሰምንት ዓመታት ያህል ሁሰቱም ወገኖች በየፊናቸው አለኝ የሚሉትን ክርክርና ማስረጃ ሁሉ በአግባቡ ከመረመረ በኋላ ፍትሐዊ ውሳኔ በመስጠት በተራዘመ ሂደት የተወሳሰበውን የገዳሙ የይዞታና የባለቤትነት ሙዝግብ ሕጋዊ እልባት ማስያዙ በጉዳዩ ቀጣይ አካሄድና አቅጣጫ ሳይ ጉልህ ተፅዕኖ ያሳረፈ ፀ ቢይ ክንዋኔ ሆኖ ምንጊዜም እንዲጠቀስ አድርጎታል።

ከመሠረታዊ ይዘት አኳያ ይኸው እ.አ.አ በ1961 የተሳለፈው የዮርዳኖስ የሚኒስትሮች ኮሚቴ ውሳኔ በደ፟ር ሡልጣን ገዳምና በሙሰጡ የሚገኙት ሁለት አብያተ ክርስቲያናት /የቅዱስ ሚካኤልና በርባዕቱ አንስሳት/ ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያ ገዳም ሕጋዊ ንብረቶች መሆናቸውን በ ማያሻማ ቋንቋ ሲመሰክር፣ ኮንቶቹ ያለአግባብ በእጃቸው ያሰገቧቸውን የገዳሙን ቁልፎች ለኢ ትዮጵያውያኑ አስረክበው ከሕገ-ወጥ የገዳሙ ይዞታቸው እንዲለቁ የታዘዙበት ስለነበር፣ ኢ ትዮጵያ በገዳሙ ላይ ያሳትን ሕጋዊ የባለቤትነት መብት ለመጀመሪያ ጊዜ በማያሻማ ሁኔታ በዚህ የፍትሕ መድረክ መረጋገጡ አዘዘ ላይ በአጽንኦት ሊገለጽ የሚገባው ሕጋዊና ታሪካዊ ክንዋኔ ነው።

ይሁን እንጂ በአንድ በኩል በመቅቱ የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥት ይዘንኑ ፍትሐዊ ውሳኔና ገንቢ ሕጋዊ አርምጃ እንደ መልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ ጉዳዩን በሐቀኛ ሚዛን ለተመለከተው በሽማግሌው የዮርዳኖስ ንጉሠ ነገሥት ቢያንስ አፈሴላዊ ምሥጋና እንኳ በማቅረብ የጉዳዩ አደያደዝ በዘሥ እንዲሰምር መጠየቅን ችላ በማለቱ፣ በሌላ በኩል የክርክሩን አካሄድ በዓ ይነ ቁራኛ ሲከታተል የነበረውና በውሳኔው እጅጉን ቅር የተሰኘው የግብጽ መንግሥት በፕሮቲ ጳጳት ጋግል አብዱል ናስር አማካይነት በመስደው ፈጣን አርምጃ ውሳኔው እንዲቀለበስ አልያም አፈጻጸሙ እንዲታገድ ለዮርዳኖስ መሪ ተዳማጊ ንጉሥ አብደላ ያቀረበው ልመናና ምልጃ ተቀባይነት በማግኘቱ የተነሣ ለዘመናት በገዳሙ ጉዳይ ፍትሕ አጥተው የተሰቃዩት ኢ ትየጵያውያን በውሳኔው ተጠቃሚ ሆነው የባለቤትነትና የይዞታ መብታቸውን ሙሉ በሙሉ በ ማስከበር ሊቆዩ የቻሉት ለአርባ ቀናት ያህል ብቻ እንደነበር የገዳሙ ታሪክ ያስረዳል።

በሌላ በኩል ተፈጻሚነቱ ከፋ ሲል በተጠቀሰው አኳኋን ያለአግባብ እንዲታገድ የተደረገው ይኸው የሃሺማዊው የዮርዳኖስ ንጉሠ ነገሥት ታሪካዊ ውሳኔ ሥርወ-መንግሥቱ ይተዳደርበት በነበረው ሕግ መሠረት የተሰጠ፣ ቅጂው ለሁሉም ተከራካሪ ወገኖች የደረሰና በአፈሴላዊ የመንግሥት ሠነድነትም ታውቆ በመዘክርነት የተቀመጠ በመሆኑ፣ ኢትየጵያ በደ፟ር ሡልጣን ገዳም ላይ፟ ያሳት ሕጋዊ የባለቤትነት መብት በማያወላዳ መልኩ የተረጋገጠበት በቢይ ማስረጃ ሆኖ ምን ግዜም ቢሆን እንደአግባቡ ሊጠቀስ የሚችል ነው።

2.4. የእሥራኤል መንግሥት

የእንግሊዝ መንግሥት በፍልስጤም የነበረው የግንዴት ሥልጣን እብቅቶ እሥራ

አል እ.አ.አ በ1948 ዓ.ም እንደሀገር ከተመሠረተች በኋላ አብዛኛው የኢየሩሳሌም ክፍል ከሳይ እንደተገለጸው በዘሺማዊው የዮርዳኖስ ንጉሥ ነገሥት ሥር ይተዳደር ስለነበር፣ እ.አ.አ እስከ 1967 ዓ.ም ድረስ የከተማይቱን አስተዳደርና በውስጧ የነበሩትን ማናቸውም ይዞታዎች አስመልክቶ በእሥራኤል መንግሥት በኩል የተደረገ ነገር አልነበረም።

በዚህ ረገድ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣው ክስተት እ.አ.አ በ1967 ዓ.ም በእሥራኤልና በአረቦች መካከል የተነሣው ጦርነት ሲሆን፣ በዚህም ወቅት የእሥራኤል መንግሥት ግብጽ፣ ሶሪያንና ዮርዳኖስን ዘጠር ኃይል በማሸነፉ በዘሺማዊው የዮርዳኖስ መንግሥት ሥር የነበረውን አብዛኛውን ምሥራቃዊ የኢየሩሳሌም ክፍል ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሮ በራሱ አስተዳደር ሥር ከነበረው ምዕራባዊው የኢየሩሳሌም ክፍል ጋር አንድ አድርጉ ለማዋሀድ እንደቻለ ይታመቃል።

ከዚህ በኋላ መሰ ኢየሩሳሌምን በበላይነት ማስተዳደር የጀመረው የእሥራኤል መንግሥት እ.አ.አ በ1969 ዓ.ም በትንሣኤ በዓል አከባበር ወቅት በኮፕቶችና በኢትዮጵያውያን መካከል ከዴር ሡልጣን ገዳም የይገባኛል ጥያቄ ጋር በተያያዘ የተነሣውን ኃይል የተቀላቀለበት እምባንሮ የፖሊስ ኃይሉን በሥፍራው አሰማርቶ በማብረድና ነገሮችን ሥርዓት በማስያዝ በሁሰቱ ወገኖች መካከል ለአያሌ ዘመናት የቀየውን ውስብስብ ችግር ለማስተናገድና ለመፍታት ያለበትን መንግሥታዊ ኃላፊነት የመወጣቱን ተግባር የጀመረበት ምዕራፍ እንደቀጠለ የገዳሙ የቅርብ ጊዜ ታሪክ ያስረዳል። በዚህ አኳኋን ጉዳዩ ሙሉ በሙሉ በእሥራኤል መንግሥት እጅ ተይዞ መታየት በቀጠለበት ማግሥትም በገዳሙ የተራዘመ የውዝግብ ሂደት ላይ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣ ዓቢይ ክስተት አስከትሎ መፈጸሙን የተለያዩ ጸሐፍት በዋቢነት ይገልጻሉ።

ይኸውም ኢትዮጵያውያኑ መነኮሳት በኮፕቶች ረቂቅ የማጭበርበር ዘዴ ተታልለው ከፊል የዴር ሡልጣን ገዳም ይዞታቸውን የለቀቁበት፣ እ.አ.አ 1820-1838 ዓ.ም በእድሳት ሰበብ ኮፕቶች ከነበሩበት የዴር ሡልጣን ከፊል ይዞታ ኢትዮጵያውያኑን አስወጥተው ያስቀሩበትና በኋላም በአካባቢው በተነሣው የወረርሺኝ በሽታ ምክንያት ኢትዮጵያውያኑ በሞት ሲያልቁ ኮፕቶቹ ተክለካይ በሌለበት ከአባሪ ተባባሪዎቻቸው ጋር ተመሣጥረው የኢትዮጵያውያኑን የባለቤትነት ማሥረጃዎች አቃጥለው ሁለቱን የገዳሙ ቁልፎች እጃቸው ያስገቡበት፣ በመጨረሻም እ.አ.አ እስከ ከ1890 ዓ.ም ድረስ ከሕጋዊ ይዞታቸው በግፍ የተነቀሉት ኢትዮጵያውያኑ መነኮሳት እንደምንም ተቆናጥጠው ባቆዩት አነስተኛ የገዳሙ ይዞታ እንኳን እንዳይጠቀሙ በማድረግ ገዳሙን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥረው የቆዩበት ረዥም የሥቃይና የግፍ ዘመን ያከተመበት ምዕራፍ በወላኝ መልኩ ሊከፈት መቻሉ ነው።

ይህም የሆነው እ.አ.አ. በ1970 ዓ.ም የትንሣኤ በዓል አከባበር ወቅት ሲሆን፣ በዚሁ ወቅት ኢትዮጵያውያኑ መነኮሳት ሁለቱን የገዳሙን ቁልፎች ጊዜ ጠብቀው በማሰቀየር መልሰው እጃቸው ለማስገባትና የገዳሙን መውጫና መግቢያ በሮች ሙሉ በሙሉ ሰመቆጣጠር በመቻላቸው፣ ከዚሁ ጊዜ እንሥቶ በገዛ ንብረታቸው ሰእያሌ ዘመናት ትክክለኛ ፍርድና ፍትሕ አጥተው የተንገላቱበት የዴር ሡልጣን ገዳም ጉዳይ መልኩን ቀይሮ ከክሳሽነት ወደ ተከሳሽነት የተሸጋገሩበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህንኑ በማስመልከት ዶ/ር ሳሙኤል ቦርከቪች የተባሉ እሥራኤላዊ የታሪክ ጸሐፊ «የቅዱሳን ቦታዎች ጦርነት» በተሰኘው መጽሐፋቸው ውስጥ ሁኔታውን እንደሚከተለው ገልጸውታል።

«ኮፕቶቹ ሁኔታው ወደነበረበት እንዲመለስ ለፖሊስ ቢያመለክቱም፣ ተቀባይነት ስላላገኙ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት አመለከቱ። ፍርድ ቤቱ በበኩሉ በጉዳዩ ላይ ለመወሰን ሥልጣን እንደሌለው ጠቅሶ አቤቱታውን ሲመለከት እንደማይችል ሲገልጽ፣ የፖሊስን እድራጉት አጥብቆ በመንቀፍ ኮፕቶቹ የባለሀበት እርጋ መብታቸውን ለማስከበር እንዲችሉ አስፈላጊውን ድጋፍ

እንዲሰጣቸው /ቁልፎቹን ከኢትየጵያውያኑ ነጥቆ ኮፕቶቹ በመተሳሰፊያው ላይ ወደነበራቸው ይዞታ እንዲመልሳቸውና እሷል። ነገር ግን የቅዱሳት ቦታዎችን እሰተዳደር አስመልክቶ ቀደም ሲ ል በእንግሊዝ የግንዴት አሰተዳደር ዘመን ወቅት በወጣው የንጉሡ ትእዛዝና አሥራኤል ከተመ ሠረተችም በኋላ ስለመንግሥት ሥልጣን በተደነገገው የ1968 ዓ.ም መሠረታዊ ሕግ አንቀጽ 29 መሠረት የእሥራኤል መንግሥት ያሰውን ልዩ መብት ተጠቅሞ ጉዳዩን በማንቀሳቀስ በኮፕቶችና በኢትዮጵያውያን መካከል የተነሣውን ውዝግብ ለማሰተናገድ የሚችልበት በቂ ጊዜ እንዲያገኝ ወሰነ።

ግብጸቹም በሚያዝያ ወር 1976 ዓ.ም ለእሥራኤል ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ብለው ባቀረቡት የተቃውሞ አቤቱታ «ቀደም ሲል ለእሥራኤል የፖሊስ ሚኒሰቴር የተሳሰፈው ውሳኔና ትእዛዝ እንዲፈጸም ይደረግልን» ሲሉ ቢጠይቁም፣ ፍርድ ቤቱ በበኩሉ በ30.12.1976 ዓ.ም በሰጠው ብይን አሰቀድሞ ትእዛዝ በተላለፈበት ጉዳይ ላይ የቀረበው ጥያቄ ከጭብጡ አኳያ የሚያስኬድ አይደለም፣ የሚል ምክንያት በመስጠት ይግባኙን ላይቀበለው ቀርቷል። በሌላ በኩል የእሥራኤል መንግሥት ውዝግቡን ለማስተናገድ ያለበትን ኃላፊነት ለመወጣት በተነሳበት ወቅት ቀደም ሲል ጉዳዩን አስመልክቶ የተላለፈው ውሳኔና ትእዛዝ የማስፈጸሚያ ጊዜ በመተላለፉ፣ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩ የሚመራበት ተጣዩ ትክክለኛ አካሄድ ምን እንደሆነ የራሱን እሰተያየት ከመግለጽ ተቆጠበ።

ከዚያም በኋላ በሚያዝያ ወር 1977 ዓ.ም ኮፕቶቹ ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በድጋሚ ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ የእሥራኤል መንግሥት የገዳሙን የመተሳሰፊያ ቦታ ይዞታ ለኮፕቶቹ እንዲያስመልሰ፣ አልያም ውዝግቡን የማሰተናገዱን ጉዳይ ፍርድ ቤቱ በሚሰጠው የተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ጀምሮ እንድያሰፈጽም ትእዛዝ እንዲሰጥሳቸው ቢጠይቁም፣ የጉዳዩ ጠባይ ለማልቃ ገብነት በር የሚከፍት እይደለም፣ በሚል ምክንያት ፍርድ ቤቱ በበዙኃን ድምፅ ይግባኙን ላይቀበለው የቀረ ሲሆን፣ ከዚህ ባሻገር መንግሥት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ለማላለፍ ወቅቱም ሆነ የሚሰጠው የጊዜ ገደብ አሳመቸኝም ብሎ የመወሰን ሥልጣን ሙምር አንዳሰው ፍርድ ቤቱ በይኗል።

በ1977 ዓ.ም የሊኩድ ጋርቲ ሥልጣን ላይ በወጣበት ወቅት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ሚና'ሽ ም ቤጊን የውዝግቡን ጉዳይ እንዲከታተል የተዋቋመውን የሚኒስትሮች ኮሚቴ አፍርሰው በምትኩ ድጋፍ ሰጪ ንዑስ ኮሚቴ በሥሩ እዋቁሞ በጉዳዩ ላይ ቀጣዩን ክትትል ያደርግ ዘንድ ወደ አየሩሳሌም ጉዳዮች አጥኝ ኮሚቴ እጅ የሥልጣን ውክልናው እንዲተላለፍ አደረጉ። በእሥ ራኤልና በግብጽ መካከል የካምፕ ዴቪዳ የሰላም ሰምምነት /በ26/3/79 ዓ.ም/ ከተፈረመ በኋላ፣ ኮፕቶች የሰምነታቸውና የዘገራቸው ልጅ በሆኑት የግብፁ ምክትል የውሥ ጉዳይ ሚኒስትር ቡትሮስ ጋሊ አማካይነት በገዳሙ የባለቤትነትና የይዞታ ጉዳይ ላይ የመጨረሻውን መፍትሔ የሚያገኙበት ቀን የደረሰ መስሎ ታያቸው። በእርግጥም ቡትሮስ ጋሊ ወኖያቸው ኮፕቶች ከቅዱሱ መቃብር አጠገብ ወደሚገኙት ሁለቱ ቤተ-መቅደሶች ይዞታ እንዲመለሱ የማድረጉን ጉዳይ ከእሥራኤል ጋር /በ1980 እና 1982 ዓ.ም/ በተካሄዱት ግንኙነትን መልሰ የማሻሻል ውይይቶች ላይ አጋማሚውን በመጠቀም አንስተውታል። ያም ሆኖ ግብጽ ከእሥራኤል ጋር ግንኙነቷን ለማሻሻል ባካሄደችው ድርድር ላይ እንደቅድመ-ሁኔታ ካሰቀመጠቻቸው ጉዳዮች መካከል በገዳሙ የይገባኛል ጥያቄ ዙሪያ ከኢትዮጵያውያን ጋር የሚካሄደው ውዝግብ ሁነኛ ፅ ልባት እንዲደረሰበት የሚለውን ነጥብ እንደ አንድ ጉዳይ እድርጋ ብታንፀባርቅም፣ የኮፕቶቹ የይገባኛል ጥያቄ በዚህ የድርድር ሂደት ምንም ዓይነት ውጤት ላይገኝበት ቀርቷል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ ኮፕቶች እንደመጨረሻ የመፍትሔ አማራጭ በማሰብ በሁለቱ ቤተ-መቅደሰች ላይ አለን የሚሉት የይዞታ መብት ጉዳይ እንዲታይላቸው በሰኔ ወር 1980 ዓ.

ም ለሦስተኛ ጊዜ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ቢያቀርቡም፣ ፍርድ ቤቱ በ30/7/1981 ዓ.ም በሰጠው ብይን ሁለተኛውን የይግባኝ አቤቱታ ውድቅ ያደረገባቸውን ምክንያቶች ጠቅሶ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል።»

ከዚህ አኳኋን እ.አ.አ በ1960ዎቹ መጨረሻ ገደማ አንስቶ እስካሁን ድረስ ከሠላሳ ዓመታት በላይ የዲር ሡልጣን ገዳምን የባለቤትነት ክርክር ጉዳይ በቅድሚያ በፍርድ ቤትና በኋላም በመንግሥታዊ ልዩ ሥልጣን ሲያስተናግድና ሲመራ የቆየው የእሥራኤል መንግሥት ከኢትዮጵያና ከግብጽ ጋር ያለውን የሚንኙነት ሁኔታ በዋነኛ ታሳቢነት እያመዛዘነ ጉዳዩን በከፍተኛ ጥንቃቄ ይዞ ቁርጥ ያለ ውሳኔ ከመሰጠት ይልቅ ከጉመት ወደ ዓመት እያንከባለለ መቀጠሉን እንደመረጠ በዚህ ሂደት የታዩት ሁኔታዎች ያስገነዝባሉ።

ጉዳዩን እንዲያጠና በተለያዩ ጊዜያት የተሰየመው የእሥራኤል መንግሥት የሚኒስትሮች ኮሚቴም ቢሆን በጣት የሚቆጠሩ ስብሰባዎችን እመቺ ወቅት ጠብቆ ከሚካሄዱና ከፍሬ ነገር ይልቅ በአመዛኙ ሥነ ሥርዓታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ማተኮሩ በአንድ በኩል የእሥራኤል መንግሥት ሁኔታዎችን አረጋግቶ ለመምራት ሲጠቀሙው በሌላ በኩል ግን ሁለቱ ወገኖች ያለ ማቋረጥ እርስ በርስ የሳሪዋ በባላንጣነት አየተያዩ እንዲቀጥሉና አልፎ አልፎም በገሃድ እንዳ ፋጠጡ የሚዳርግ አካሄድ እንደሆነ ዚታወቅም፡ ከጉዳዩ ውስብስብነት አኳያ ከዚህ የተለየ አማራ ጭ እንደሌለው በተጨባጭ የታዩትና እዮንም የሚታዩት ሁኔታዎች ያመለክታሉ።

እንደ እውነቱ ከሆነም የኮፕቶቹ መሠረታዊ የመከራከሪያ አቋም እ.አ.አ በ1970 ዓ.ም ቢኒይል የተተየሩት የገዳሙ ቋልፎች እንዲመለሱላቸውና ይኸው ቁልፎቹን የመቀየሩ እድራጐት ከመፈጸሙ እስተድሞ የነበረው ሁኔታ /Status Quo Ante/ ተከብሮላቸው የገዳሙን ይዞታ ለመቆጣጠር እንዲችሉ እንዲወሰንላቸው ሲሆን፡ በኢትዮጵያ ገዳም በኩል ያለው ሁኔታ ደግሞ ሁለቱም ወገኖች ያላቸው ማስረጃና ክርክር ከሥር ጀምሮ ታይቶ በገዳሙ የባለቤትነትና የይዞታ ጭብጥ ላይ ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥበት በመሻት ላይ ያነጣጠረ በመሆኑ ሰአሥራኤል መንግሥት የትኛውንም ቢሆን መቀበሉ እጅግ አስቸጋሪ ፈተና ከመሆኑ አኳያ ጉዳዩ ሳይነካካ ባለበት እየተንከባለለ እንዲቀዋል ማድረጉ እማራጭ የሌለው ብቸኛው አካሄድ መስሎ ይታያል። የጉዳዩ ሳይነካካ መቀጠል ደግሞ ካለፉት መራር የታሪክ ተመክሮዎችና ከጉዳዩ ውስብስብነት አኳያ ለኢትዮጵያ ገዳም ከጉዳቱ ጥቅሙ የሚያመዝን መስሎ ስለሚታይ፣ ውጤቱ ሊገመት ከ ማይችልና ከፖለቲካዊ ጫናና ተዕዕኖ ነፃ ከማይሆን የእደባባይ ፀሐፃት ይልቅ መብትን በተለያዩ ስልቶች ለማስከበር የመጣሩ አካሄድ የተለየ አቅጣጫ ለመከተል የሚያስገድድ የከፋ ሁኔታ ካልተከሰተ በስተቀር የተሻለ እማራጭ ይሆናል።

በሌላ በኩል የገዳሙን ቁልፍና በግፍ የያዙትን የገዳሙን ይዞታ ያጡት ኮፕቶቹ እንደጥያቄያቸው እንዲፈጸም ምንጊዜም ቢሆን ከመጠየቃት ወደኃላ የማይሉ ሲሆን፣ መንግሥታቸውም ቢሆን ይህንኑ አቋም በፖለቲካውና ዲፕሎማሲው መድረክ እንዳመቺነቱ እያንጸባረቀ በእሥራኤል መንግሥት ላይ የበኩሉን ጫናና ሲያደርግ ቆይቷል፤ በማድረግም ላይ ነው። ለዚህም በርካታ እብነቶች ሊጠቀሱ የሚችሉ ሲሆን፣ ከዚህ በተጓዳኝ በርካታ የግብጽ መገናኛ ብዙኃን፣ ምሁራንና የፖለቲካ ሰዎች ጉዳዩን እስመልክተው በሚካሄዱ ሲምፖዚየሞችና በኮገኘው እመቺ እጋጣሚ ሁሉ የኮፕቶቹን የይገባኛል ጥያቄ በእጽንኦት ሲያስተጋቡ ይገኛሉ። በተለይም ደግሞ ተቀማጭነታቸው በአሌክሳንድርያ የሆነው የኮፕት ታትሪያርክ እቡነ ሺኖዳ የዲር ሡልጣን ገዳም ለኮፕቶች እስኪመለስ ድረስ የቤተ ክርስቲያናቸው ምእመናን ኢየሩ ሳሌምን እንዳይሳለሙ በይፋ መገዘታቸውና ይህም እስካሁን ድረስ ለበርካታ ዓመታት እንደጸና የሚገኝ መሆኑ ሲታይ በሐቅና በተጨባጭ ማስረጃ ላይ ያልተመሠረተው የኮፕቶቹ የተስፈኝነት እቋም የቱን ያህል የከረረ እንደሆነ ያስገነዝባል።

በሌላ በኩል ከጉቶቹ በጉዳዩ ላይ ምንም ዓይነት የፍሬ ነገር ክርክር ሳይካሄድ የተለመጡት የገዳሙ ቁልፎች እንዲመለሱላቸው በፍርድ ቤት የተላለፈውን ውሳኔ የእሥራኤል መንግሥት የማያስፈጽምላቸው ከሆነ በዓለም አቀፍ የግልግል ፍርድ ቤት ጉዳዩ እንዲታይላቸው የሚሹ መሆኑን በተሰያዩ ጊዜያት ቢገልጹም፣ ለዚህ ጥያቄያቸው ቁርጥ ያለ አዎንታዊ ምላሽ ያልሰጠው የእሥራኤል መንግሥት በበኩሉ ሁለቱ ወገኖች ጉዳዩን በስምምነት /በመግባባት/ ለመጨረስ ባልቻሉ በዓለም አቀፍ የግልገል ጸንነት እንዲታይ የሚያደርግ መሆኑን አልፎ አልፎ በገለጸባቸው አጋጣሚዎች ደግሞ ከጉቶቹ በዚሁ ሃሣብ እንደማይስማሙ መግለጻቸው ይህንን አቋም ከማስፈራሪያነት ባለፈ አምርረው የሚያራምዱት እንዳልሆነ ያመላክታል።

በኢትዮጵያ ገዳም በኩል በዚህ ነጥብ ላይ እስከአሁን ድረስ በውል ተለይቶ የሚታወቅ አቋም መኖሩ ባይታወቅም፣ ይህ ሐሳብ ተግባራዊ ይደረግ ቢባል በአንድ በኩል ዝርዝር ጉዳዩ ከሥር ጀምሮ በተሞና ቢታይ የኢትዮጵያን የባለቤትነት መብት የሚያረጋግጥ የመጨረሻ ውሳኔ የማግኘቱ ዕድል እንደሚኖር የተወሰነ ግምት ለመውሰድ የሚቻለውን ያህል፣ ጉዳዩ በዚህ መንገድ በሚታይበት ሂደት አንደገና ወደኋላ ተመልሶ ጥሬ ከሚሆንበት ሁኔታ ጋር ተዳምሮ በአካሄዱ ላይ ሊደረጉ በሚችሉ ማናቸውም ፖለቲካዊ መድልኦዎችና ዲፕሎማሲያዊ ተጽዕኖዎች ላቢያ በእሥራኤል መንግሥት እጅ ካለው የጉዳዩ አያያዝ ባፈነገጠ መልኩ የኢትዮጵያን ጥቅም ሊጐዳ የሚችል ውጤት ሊመጣ የሚችልበት አደጋ በሌላ በኩል የሚያሰጋ ሆኖ ይታያል።

3. <u>የዓለም አቀፍ ሕግ</u>

ዓለም አቀፍ ሕግ በዲር ሡልጣን ገዳም የባለቤትነት ክርክር ውስጥ ሊኖረው የሚችለው ዓይነተኛ አገባብ ቀደም ሲል በአጭሩ እንደተጠቆመው ሲሆን፣ ዐበይት ገጽታዎቹን እንደሚከተለው ዘርዘር ባለ መልኩ ለማየት ተሞክሯል።

ሀ/ <u>ቀደምት ዓለም አቀፍ ስምምነቶች</u>

እ.አ.አ ከ1835 ዓ.ም በፊት በፍልስጤም የነበሩ የቅዱሳት መካናት የይዞታ መብቶች ሳይለወጡ ረግተው እንዲቀጥሉ የተመሰከበት የኦቶማን ቱርክ መንግሥት መሠረታዊ ድንጋጌ ያጸደቀባቸውና ኢትዮጵያ በዲር ሡልጣን ገዳም ላይ ያላት የባለቤትነት መብት ጭምር የተረጋገጠባቸው ቀዳሚ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እ.አ.አ በ1856 በበርሊን፣ እና አ.አ.አ በ1878 ዓ.ም ደግሞ በፓሪስ በወቅቱ የአውሮፓ ሃገሮች መካከል የተደረጉት ሲሆኑ፣ በዚህ ረገድ በህቢይነት የሚጠቀሱ መሠረታዊ ሰነዶች ናቸው።

በእነዚህ ስምምነቶች ከተጠቀሰው መሠረታዊ መርህና ከሰፊረው ድንጋጌ አኳያ ኢትዮጵያውያን በኢየሩሳሌም እንደሚገኙት ሌሎች የክርስቲያን ማኅበረሰቦች በቀደምት ይዞታቸው በዲር ሡልጣን ገዳም ያላቸው ሙበት መከበር እንዳለበት የተረጋገጠ ሲሆን፣ በዚሁ መሠረት ከሕግ ትርጉምና ግምት አኳያ ግብጾች በማታለልና በተንኮልም ሆነ በጉልበት የነጠቁት የኢትዮጵያ ገዳም ይዞታ እንደሌሎቹ በሕጉ-ወጥ መንገድ የተወሰዱ የቅዱሳን ቦታ ይዞታዎች ሁሉ ለሕጋዊ ባለቤቱ ሊመለስ እንደሚገባው መንግሥታት ከእነዚህ ስምምነቶች አማካይነት ተመሣሣይ አቋም ወስደው ነበር ለማሰት ይቻላል።

ለ/ <u>አግባብነት ያለው ወቅታዊ ዓለም አቀፍ ሕግ</u>

በዚህ ረገድ ቅድሚያ ተጠቃሽ የሆነው ዐቢይ ዓለም አቀፍ ውሳኔ (resolution) በእንግሊዝ ማንዴት ሥር ሲተዳደር የቆየው ፓለስታይን ግዛት የአረብና የአሥራኤል መንግሥታት ጉን ለጉን የመሠረቱበት ሆኖ ለሁለት እንዲከፈል እ.አ.አ በኅዳር ወር 1947 ዓ.ም የተላለፈውና

partition plan አየተሰኘ በአሜሩ የሚጠራው የተባበሩት መንግሥታት ውሳኔ ቁጥር 181 ሲሆን፣ ከዚሁ በማስከተል በመንግሥታቱ ድርጅት የወጡት ሌሎች ሁለት ውሳኔዎች /ማለትም የመንግሥታቱ ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ቁጥር 194 እ.አ.አ ታኅሣሥ 1948 እና የጠቅላ ጉባኤው ውሳኔ ቁጥር 303 እ.አ.አ ጎዳር 1949/ ከያዝነው ርዕሰ ጉዳይ አንፃሩ ሊታዩ የዘሁሁ ቀዳሚ ውሳኔ ማጠናከሪያ ስለሆኑ፣ አስካሁን በሥራ ላይ ያሉት መርሆዎች ለመጀመሪያ ጊዜ የተንጸባረቀበትን የተ.መ.ድ ቀዳሚ የውሳኔ ሠነድ ይዘት በአብነት መመልከቱ በቂ ይሆናል።

ይኸው ውሳኔ በእንግሊዝ የማንዴት አስተዳደር ሥር የቆዩትና አርስ በአርስ በግዛት ይገባኛል ጥያቄ ሲጋፉ የነበሩት አይሁዳውያንና ፍልስጤማውያን ይገባኛል የሚሉትን የግዛት ክልል ይዘው የየራሳቸውን ሀገርና መንግሥት እንዲያቋቁሙ ሲደነግግ፣ በአንድ ጎኗ የግጭታቸው ዋነኛ እምብርት፣ በሌላ ጎኗ የተለያዩ የዓለም ሀበይት ሃይማኖቶችና የመንፈሳዊና ታሪካዊ ተቋማቶቻቸው መናኸሪያ የሆነችው የኢየሩሳሌም ከተማ ግን ልዩ ዓለም አቀፍ ቀጠና ሆና በተ.መ.ድ. የበላይ ጠባቂነት ሥር በሕግ ተለይታ የምትተዳደር አካል (corpus separatum) እንድትሆን የተመለነበት ነው። በዚህም ምክንያት ታዋቂ የዓለም አቀፍ ሕግ ምሁራን በሚ ጽፏቸው መጻሕፍት ከተማይቱ በሌሎች የዓለም አካባቢዎች እንደሚገኙትና በተለያዩ ምክንያቶች አመዛጋቢ አስተዳደራዊ ጠባይ እንዳሳቸው የተመሰኑ ግዛታዊ ክልሎች ሁሉ Sui Generis Territorial Entity በመሰኘት ትገለጻለች።

ከዝርዝር ይዘት አኳያ ከላይ በተጠቀሰው ዓለም አቀፍ ውሳኔ በተለይ በምዕራፍ I ሥር ከአንቀጽ 1–5 የሰፈሩት ድንጋጌዎች ከያዝነዉ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ቀጥተኛ አግባብነት ያላቸው ሲ ሆን፣ በዋነኛነትም፡– ስምምነቱ ከመውጣቱ አስቀድሞ በከተማይቱ ቦሚገኙ ቅዱሳት መካናት ላይ የነበሩ ማናቸውም በሕግ የታወቁ መብቶች ሁሉ እንደማይገፈፉ ተጠቅሷል። በተጨማሪም ከነዚሁ መብቶች ጋር ተጓዳኝ በሆነ ሁኔታ ቅዱሳት መካናቱን የማደስ፣ የመጠበቅንና የመመለስን፣ እንዲሁም ሃይማኖታዊ የአምልኮ ሥርዓቶችን አንደልብ የመፈጸም ነጻነቶች ያለአንዳች ገደብ መከበራቸው ተረጋግጧል።

ለቅዱሳት መካናቱና ለኃይማኖታዊ ተቋማትና ቦታዎች ተገቢው እንክብካቤና ጥበቃ እንደሚደረግ፣ የቅድስና ቦታዎቻውን የሚጉዳ ማናቸውም ተግባር መፈጸም እንደማይፈቀድ፣ በእርጅናም ሆነ በማናቸውም ምክንያት አካላዊ ጉዳት ሲደርስባቸው በመንግሥት አስተባባሪነትና አስፈጻሚነት የሚመለከታቸው ሃይማኖታዊ ማኅበረሰቦች ጥገናና ዕድሳት እንዲያደርጉ፣ ይህ በጠቅላ ሲሆን ካልታሰበ መንግሥት በሚመለከታቸው ኃይማኖታዊ ማኅበረሰቦች ወጪ ጥገናና አድሳቱን የሚስፈጸም ኃላፊነት እንዳለበት ተደንግጓል።

በሌላ በኩል ፍልስጤምን በሚንዴትነት ሲያስተዳድር የነበረው የእንግሊዝ መንግሥትም ሆነ በተ.መ.ድ. ውሳኔ መሠረት እንዲቋቋሙ የተባሉት የአረብና የእሥራኤል መንግሥታት፣ እንዲሁም የኢየሩሳሌምን ከተማ ዓለም አቀፍ ልዩ ቀጠና አስተዳደር የገቡባቸው የዓለም አቀፍ ውሎች፣ ስምምነቶችና ግዴታዎች በሙሉ እንደሚከበሩ በውሳኔዉ አንቀጽ 2 የተደነገገ ሲሆን፣ ይኸው ግዴታም ይዘንኑ ዘቢደ የተ.መ.ድ. ውሳኔ ስምምነት ማክበርን ቁምር የሚያጠቃልል ነው። ከዚህም በተያያዘ ሁኔታ በዓለም አቀፍ ውሎችና ስምምነቶች ተፈጻሚነትና ቀጣይ ሕጋዊ ዋጋ ላይ የሚነሱ አለመግባባቶች በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ሥልጣን ሥር የሚዳኙ መሆናቸውን ይኸው የውሳኔው አንቀጽ በተጨማሪ ይገልጻል።

ከዚህ ባሻገር ይኸው የፍልስጤም የግዛት ክልል ለአረብና ለአይሁድ መንግሥታት መመስረቻ ሆኖ ለሁለት እንዲከፈል የተወሰነበት ዓለም አቀፍ ውሳኔ በልዩ ቀጠናነት ስለተፈረጀችው የኢየሩሳሌም ከተማ የአስተዳደር ሁኔታ፣ ውጫዊ ወሰኖች፣ አንዲሁም የከተ

ማይቱን የአበተዳደር አካል ማቋቋሚያና መመሪያ ደንቦች (Status of the City) ዝርዝር ድንጋጌዎችን በክፍል 3 ውስጥ አካትቷል።

በዚሁ መሠረት ከተማይቱ በተመድ የባለአደራ ምክር ቤት (Trusteeship Council) ጸድቆ በሚወጣ ዝርዝር የመተዳደሪያ ደንብና ዓለም አቀፋዊ የመስተዳድር አካል እንደምትመራ የተወሰነ ሲሆን፣ ይኸው ዓለም አቀፋዊ መስተዳድር ከሚኖሩት በርካታ ተግባራትና ኃላፊነቶች መካከል ከላይ የተጠቀሱትን የቅዱሳት መካናትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች አፈጻጸም በባለቤትነት መከታተል ዋነኛ ትኩረቱና ግዴታው እንደሚሆን ተገልጿል። ከዚህ በተጨማሪ የተለየ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ የመስተዳድሩ ልዩ ሥልጣን ከቅዱሳት መካኖቱ ጋር በተያያዘ በተለያዩ ሃይማኖታዊ ማኅበረሰቦች መካከል የሚነሱ ግናኙነቱም ከይዞታና ከባለቤትነት መብት ይገባኛል ጥያቄዎች የሚመነጩ አለመግባባቶችን ተመልክቶ ውሳኔ ሊሰጥ እንደሚችል መደንገጉ ነው። ይህ ደግሞ በኢትዮጵያና በግብጽ ቤተ ክርስቲያናት መካከል በዲር ሡልጣን የባለቤትነት መብት ይገባኛል ጥያቄ ዙሪያ የተንጣውን የመሠለ ውዝግብ በሣይነተኛነት እንደሚመለከት ግልጽ ነው።

ምንም እንኳን ይህ ዓለም አቀፍ ውሳኔ በተለያዩ ችግሮች፣ በተለይም ከአይሁዳውያንና ከፍልስጤማውያን አልፎ ተርፎም ከእሥራኤልና ከአረቦች ግጭት መነሪር ጋር በተያያዘ ምክንያት ገና ከጅምሩም ቢሆን በአመነች ተፈጻሚ ሊሆን አንዳልቻለ የሚታወቅ ቢሆንም፣ በኢየሩሳሌም የሚገኙትን ቅዱሳት መካናት አያያዝና አስተዳደር በተመለከተ ያስቀመጠው መሠረታዊ የሆነ ዓለም አቀፍ መርሆ ግን ምን ጊዜም ቢሆን ሊጠቀስ የሚችል ነው። ይኸው በውሳኔው ልሙቅና አግኝቶ የተቀመጠው መርሆ ቀድሞውኑም ቢሆን በአካባቢው አስተዳዳሪ መንግሥታት ዘንድ ተከብሮ ሲፈፀም የቆየውን የወና ልማድ (state practice) መነሻ ያደረገ ሲ ሆን፣ ከዚህ አኳያ ለዘመናት ሲሰራበት የቆየው ይኸው የወና ልማድ የመደበኛው የዓለም አቀፍ ሕግ አካል ሆኖ በዚህ ዓለም አቀፍ ሰነድ ውስጥ መንበረቀቁ ተቀባይነቱ ከፍ እንዲል አስችሎታል።

ሐ/ <u>የመንግሥታት ልማዳዊ አሠራር (Customary State Practice) እና የጸና አመለካከት (Opinio Juris)</u>

የዓለም አቀፍ ሕግ መሠረቶች ሆነው ከሚጠቀሱት ዋነኛ ምንጮች መካከል አንዱ የሆነው ዓለም አቀፍ ልማዳዊ አሠራር በኢየሩሳሌም ቅዱሳን መካናት ይዞታና አስተዳደር ላይ በኑልህ የሚንጸባረቅ ሲሆን፣ ይህም ከተማይቱ በተለያዩ መንግሥታት ሥር ስትተዳደር በቆየችበት ሂደት የልዩ ልዩ ሃይማኖታዊ ማኅበረሰቦች መገልገያ የሆኑትን ቅዱሳት መካናት አያያዝና አስተዳደር አስመልከተው አስተዳዳሪ መንግሥታቱ ሲከተሏቸው በቆዩትና አሁንም ጸንተው በሚገኙት ተቀባይነት ያላቸው በርካታ ልማዶች የሚገለጽ ነው።

በተለይም በክርስቲያን ማኅበረሰቦች መካከል ከጥንት ጀምሮ ሲካሄዱ የቆዩትን የባለቤትነትና የይዞታ ውዝግቦች ለዘለቄታው ለመፍታት ታስቦ እ.አ.አ በ1835 ዓ.ም በኦቶማን ቱርክ መንግሥት የወጣውን የስታተስ ሕግ በመከተል ከዚያ ወዲህ አካባቢውን ባስተዳደሩት የተለያዩ ቋንግሥታት ዘንድ በሰፋት ሲሠራበት የቆየው ልምድ ከዚህ ረገድ በሞንኝነት ሊጠቀስ የሚችል ነው።

ከዚህም በተጓዳኝ እያንዳንዱ አካባቢውን ያስተዳድር የነበረ መንግሥት የቅዱሳት መካናቱን አያያዝና አስተዳደር አንዲሁም የስታተስ ኮዙን አክብሮ ሁኔታ አልመልከቶ በራሱ መንገድ፣ በልማድነት ያዳበረውና የግዴታ ያህል አምኖበት የተከተለው ተጠቃሽ አመለካከትና ድርጊት

ጭምር በዴር ሡልጣን ገዳም የባለቤትነት ክርክር ጉዳይ አግባብነት ያለው ሆኖ ይታያል። ይህም ማለት የቱርክ፣ የእንግሊዝ፣ የዮርዳኖስና የእሥራኤል መንግሥታት የገዳሙን የባለቤትነት ውዝግብም ሆነ ሌሎች መሰል በኩተግይቱ ውስጥ ያሉ የጥንታዊ ቅዱሳት መካናት ጉዳዮችን የራሳቸውን አቋም ወስደው በአስተዳደር ዘመናቸው ሂደት ውስጥ ያሏቸውንና ይዘው የአመለካከት ዘይቤ የአስተዳደራቸው ተግባራዊ መገለጫ ሆኖ ሊወሰድ እንደሚችል የሚያመለክት ነው።

ሠ/ <u>የሃለም አቀፍ ሕግ ምሁራን አስተያየት</u>

የኅለም አቀፍ ሕግ ክፍተት ባለባቸው ቦታዎች እንደ አንድ የማሟያ ምንጭ ሆኖ እንደሚያገለግል የሚታወቀው የዕውቅ ዓለም አቀፍ የሕግ ምሁራን አስተያየት በዴር ሡልጣን ገዳም የባለቤትነት ክርክር ላይ አግባብነት ያለው ሆኖ ሊጠቀስ የሚችልበትን አንድ ዘዚይ ከንሞኔ በዚህ ርዕስ ሥር ለማየት ይቻላል።

ይኸውም ፕሮፌሰር ባርን ቦሪስ ኖልድ የተባሉ ሩሲያዊ የኅለም አቀፍ ሕግ ምሁር፣ በሊግ አፍ አሽንስ ሥር ተቋቁሞ የነበረው ዓለም አቀፍ የግልግል ፍርድ ቤት ዳኛና የዓለም አቀፍ ሕግ ኢንስቲትዩት አባል ከአቶማን ቱርክ ቤተ-መዛግብት የተሰባሰቡትን ስለ ዴር ሡልጣን ገዳም ሕጋዊ የባለቤትነት አቋም የሚያስረዱ በርካታ የሠነድ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም ጥንታውያን ኢየሩሳሌም ተሳላሚዎች፣ ዘገር ጉብኝዎች፣ የታሪክ ሰዎች፣ የሃይማኖት መሪዎችና ማኅበረሰቦች በየጊዜው የሰጧቸውን ምስክርነቶችና የባለሀብት ዕርጋን /የስታቲስ ኮውን/ መርህ አጠቃላይ ሁኔታ በሥነተኑተን እ.አ.አ በ1914 ዓ.ም የሰጡትና ቅጂው ለሩሲያ፣ ለእንግሊዝና በኋላም ለኢትዮጵያ መንግሥት ፅፁር የደረሰውን የሕግ አስተያየት የሚመለከት ነው።

ፕሮፌሰሩ በዚሁ ተጠቃሽ የሕግ አስተያየታቸው የዴር ሡልጣን ገዳምም ሆነ በውስጡ ተያይዘው የሚገኙት የቅዱስ ሚካኤልና የዘርባሉቱ እንስሳት አብያተ ክርስቲያናት ክርስቲያናት የኢትዮጵያ ንብረቶች እንደሆኑና በክፕቶች በኃፍ የተወሰዱ መሆናቸውን በማረጋገጥ ለሕጋዊ ባለቤታቸው ሊመለሱ እንደሚገባቸው አስገንዝበዋል።

፭. <u>ኢትዮጵያ በዴር ሡልጣን ገዳም ያላት የባለቤትነት መብት ከዓለም አቀፍ ሕግ አንጻር ያለው ገጽታ</u>፡

ከላይ ለመግለጽ ከተሞከረው አኳያ በዴር ሡልጣን ገዳም የባለቤትነት ክርክር የዓለም አቀፍ ሕግ ያለው አግባብ በጎልጽ ሊታይ የሚችል እንደሆነ ይታመናል።

ይኖን አንጂ በጉዳዩ ላይ ለዘመናት ሲካሄድ የቆየው ውዝግብና ክርክር አካባቢውን ሲ ያስተዳድሩ የቆዩት መንግሥታት ካወጧቸው ሕግጋትና ከፍርድ ቤቶቻቸው እንዲሁም በተለያዩ የሥልጣን እርከን ላይ ካሉ አስተዳደራዊ አካላቶቻቸው አልፎ ጉዳዩ በዓለም አቀፍ ሕግጋትና መድረኮች የታየበት አጋጣሚ አስካሁን ድረስ አልተፈጠረም። እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ጥያቄ ጉዳዩ በማናቸውም ምክንያት በዓለም አፋፍ ሕገና በዓለም አቀፍ የግልግል አካል ይዳኝ የሚባልበት ሁኔታ ቢከሰት ኢትዮጵያ የሚኖራት አቋም ምን ዓይነት ሊሆን ይገባዋል? ይህን በመሰለ መድረክ መከራከሩስ ያዋጣታል ወይ? የሚለው ይሆናል።

አንደሚታወቀው እ.አ.አ ከ1970 ዓ.ም አንስቶ እስካሁን ድረስ የነዳሙ ቁልፎችና አመዛኝ ይዞታ በኢትዮጵያ ሥር ያሉ ሲሆን፣ ምንም እንኳን የባለቤትነቱ ጉዳይ እስካሁን የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበት ቢሆንም የኢትዮጵያ ገዳም በኮፕቶች ተከሣሽ ሆኖ ከቀድሞው በተሻሸ ሁኔታ ላይ የሚገኝ በመሆኑ፣ በዓለም አቀፍ ብቻ ላይሆን በየትኛውም የሕግ መድረክም ቢሆን

ከሣሽ ሆኖ ከመቅረብ ይልቅ በተከሳይነት ይዞታን እያጠናከሩ ባሉት የማያወላዱ ማስረጃዎች ላይ ተመሥርቶ የባለቤትነት መብትን የማስከበሩ አካሄድ ተመራጩነት እንዳለው ይታመናል።

ያም ሆኖ ግን በዓለም አቀፍ የግልግል መድረክ ወይም መሰል የፍርድ አካል ጉዳዩ ቀርቦ በአግባቡ ቢታይ ሊኖር የሚችለው የክርክር ሂደት በአቶማን ቱርክ መንግሥት ለመጀመሪያ ጊዜ ተደንግጉ አካባቢውን በተከታታይ ሲያስተዳድሩ የነበሩት መንግሥታት ጭምር ሲከተሉት የቆዩትንና በፓሪስና በበርሊን ስምምነቶች ጭምር የጸደቀውን የባለሀብት እርጋ ሕግ በዋነኝነት መነሻ ያደረገ እንደሚሆን አያጠያይቅም። ከዚህም ባሻገር የተመድ ከተመሠረተ በኋላ አካባቢውን በሚመለከት የተሳለፉት ልዩ ልዩ ውሳኔዎች ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ ከነሱም መውጣት በፊት በኢየሩሳሌም የነበሩትን የቅዱሳት መካናት ይዞታዎች አስመልክተው በከተማይቱ አስተዳዳሪ መንግሥታት የተደነገጉትን ሕግጋት የማጽናት ጠባይ ጭምር ያላቸው በመሆኑ፣ የክርክሩ ጭብጥ በገዳሙ ቁልፍ መመለስ ላይ ብቻ ሳይወሰን ከሥር ጀምሮ የነበረውን የባለቤትነትና የይዞታ ሁኔታ ባጠቃላይ መልኩ የሚታይ እንደሚሆን የሚጠበቅ ነው።

ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ በገዳሙ ባለቤትነት ላይ ያላት ክርክርና ማስረጃ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከዓለም አቀፍ ሕግጋት አንጻር ድጋፍ ያለው ሆኖ ስለሚታይ፣ በክፕቶቹ ጠያቂነት ጉዳዩ በማናቸውም መንግሥት ሥር ይሁን በዓለም አቀፍ የግልግል አካል የሚታይበት ሁኔታ ቢፈጠር እውነተኛ ዳኝነትና ፍትህ እስካለ ድረስ በእሸናፊነት መወጣት እንደምትችል መተንበይ ይቻላል።

ይሁን እንጂ በታሪክ የታየው የጉዳዩ ዓይነተኛ ጠባይ እጅግ የተወሳሰበና ከሕግና ከፍትሕ ይልቅ ፖለቲካዊ ባሕርዩ ያመዘነ በመሆኑ፣ በየትኛውም መድረክ ቢሆን በሕግ ብቻ ተማምኖ መቀመጡ ሳያዋጣ ስለሚችል፣ በተለያዩ እቅጣጫዎችም የነቃ ትግል ማካሄዱ የግድ ይላል። በተለይም የከተማይቱን የወደፊት ዕጣ ፈንታ አወሳሰን አስመልክተው ተስሚነት ያላቸው ሌሎች ዐብይ ከርስቲያኖች /እንደ ግሪክ ኦርቶዶክስ፣ ፍራንሲስካን ቤተ ክርስቲያን፣ አርመን ቤተ ክርስቲያን የመሣሠሉት የክርስቲያን ቅዱሳት መካናት ያሉበት የከተማይቱ ክልል ነጻ ዓለም አቀፋዊ ቀጠና አንዲሆን ድምጻቸውን በጋራ በግለግት የሚያደርጉት የተቀናጀ እንቅስቃሴና ግፊት በዚሁ ክልል ውስጥ በሚገኘው የዴር ሡልጣን ገዳም የባለቤትነት ክርክር ላይ ሊኖረው የሚችለውን እንድምታና ተጨባጭ ትርጉም በቅርብና በጥልቀት ማጤኑ በጉዳዩ የወደፊት ሂደት ላይ የሰከነ አቋም ለመያዝ ስለሚረዳ በእጅጉ አስፈላጊ ሆኖ ይታያል።

በሌላ በኩል ፀንተው የኖሩትንና በዓለም አቀፍ ሕግ ዘንድ ተቀባይነት አግኝተው የጸደቁትን ሀገራዊ ሕግጋት፣ ደንቦችና ልምዶች ሳያገናዝብ በፖለቲካ ተጽዕኖ እስገዳጅነት በጉዳዩ ላይ የሚተላለፍ ማናቸውም ውሳኔ ከዓለም አቀፍ ሕግ እንፃር ፈጽሞ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ገዳም የዚህ ዓይነቱ ውሳኔ ሰለባ የሚሆንበት ሁኔታ የሚከሰት ቢሆን በዓለም አቀፍ ሕግ አማራጭ የመጠቀሙ ዕድል አንጻለ ከወዲሁ ማሰቡ ተገቢ እንደሆነ ማስተዋል ይጠቅማል።

እንዲሁም በሌላ በኩል በኢየሩሳሌምና አካባቢው የሚገኙትን ቅዱሳት መካናት ይዞታ፣ ባለቤትነቱንና አስተዳደር አስመልክተው በአቶማን ቱርክ መንግሥት ዘመን ጀምሮ እስከ እለንበት ጊዜ ድረስ እየተላለፉ መጥተው በአሁኑ ወቅት በእሥራኤል መንግሥት የሚሠራባቸው ሕግጋት፣ ደንቦችና የደረጁ ልምዶች ከዓለም አቀፍ ሕግ አንፃር ከፍተኛ ግምት የሚሰጣቸው ስለሆነ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት አግኝተው ፀንተው እንዲቀጥሉ የተደረጉበትን የተባበሩት መንግሥት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች ሕጋዊ ባሕርይ አዚህ ላይ ማንሳቱ ተገቢ ይሆናል።

በአጠቃላይ አነጋገር የመንግሥታቱ ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ ሕግ አውጪ አካል ባለመሆኑ የሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች አባል ሀገሮችን በቀጥታ የማስገደድ ባሕርይ አላቸው ማለት ባይቻልም፣ በይዘትና መልክ የሚተላለፉት የድርጅቱ ውሳኔዎች ተፈጻሚነታቸው የሚደገፍ ከመሆኑም በላይ፣ አባል መንግሥታት ለአፈጻፀማቸው ድጋፍ እንዲያደርጉ የሚጠበቅባቸው መሆኑ ይታወቃል። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በቅሳላ ጉባኤ ሲቋቋም አባል ሀገሮች በመካከላቸው ያለውን ልዩነት በማጥበብ ለሰላምና ሰደሀንነት በጋራ ለመሥራት እንዲችሉ የሐሳብ መለዋወጫ፣ መከራከሪያና መለሚሚያ መድረክ እንዲሆን ታስቦ መሆኑ እውን ነው።

ያዙን እንጂ ከጊዜ በኋላ የድርጅቱ ልዕልና እየተጠናከረ መምጣቱና የኃላፊነት አድ ማሱም እየሰፋ መሄዱ በተሰያዩ ጉዳዮች ላይ የሚያላልፋቸውን ውሳኔዎች ሕጋዊ ፋይዳ ከፍ እንዲል ያደረገው ሲሆን፣ ከዚህም አልፎ የውሳኔዎቹ ተቀባይነትና ተፈፃሚነት በፖለቲካም ረገድ ያላቸው አንድምታ አስገዳጅ እንዲሆን አስችሎታል። ከዚህ አንፃር የኅለም አቀፍ ሕግ ምሁራን አንዳሚሉት በአባል መንግሥታት ውሳኔዎች ዓለም አቀፍ የአስገዳጅነት ባሕርይ ያላቸው ድንጋጌዎች (JUS COGENS) ናቸው። ስለሆነም በኢየሩሳሌምና አካባቢው ያሉትን ቅዱሳት መካናት በሚመለከት ቀደም ሲል የወጡትን የህገር ውስጥ ሕግጋትና የመንግሥታት የቆዩ አሠራር ልምዶች በማጽደቅ የተላለፉትና ከሕግ ትርጉም አኳያ ሀገራችን በዴር ሡልጣን ገዳም ላይ ያላትን የባለቤትነት መብት የሚደግፉት የተመድ ውሳኔዎች በግልጽ እስካልተሻሩ ድረስ አሁንም ቢሆን የአስገዳጅነት ባሕርይ ያላቸው ናቸው ለማለት ይቻላል።

ይህ እንዳለ ሆኖ፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሳይንስ፣ የትምህርትና የባሕል ድርጅት (UNESCO) የተቋቋመበትን ዓላማ ከግለፅም አኳያ ተገቢውን ዕውቅና ሰጥቶ በዓለም የባሕል ቅርስነት እስከአሁን ከመዘገባቸውና በተሰያዩ የዓለም ክፍሎች ከሚገኙት 721 ታሪካዊ ሕንፃዎችና ቦታዎች ውስጥ የዴር ሡልጣን ገዳም በስም ተሰይቶ አይጠቀስ እንጂ ድርጅቱ በጥቅሱ የኢየሩሳሌም አሮጌው ከተማ (The Old City of Jerusalem) በሚል በመዘገበው የወል ለያሜ ውስጥ የሚጠቃለል እንደሆነ ግልጽ ነው። ከዝርዝር አመዘጋገብ አኳያም ገዳሙ በማን ይዞታ ሥር እንደሚገኝና ከዚሁ ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች ዐቢይ ፍሬ ነገሮችን የሚጠቅስ መረጃ በድርጅቱ ሰነዶች ውስጥ ሰፍሮ እንደተያዘ ስለሚታመን፣ ሀገራችን በገዳሙ ላይ ያላት የይዞታና የባለቤትነት መብት በድርጅቱም ዘንድ ዕውቅና እንደሚኖረው ይገመታል። ይህ ሁኔታም በራሱ የኢትዮጵያን የባለቤትነት መብት በማረጋገጥ ረገድ ገንቢ አስተዋጽኦ ሲያበረክት እንደሚችል ስለሚታመን ሰወደፊቱ በዚህ አቅጣጫ ተገቢ ው ጥናትና ክትትል ቢደረግ ጠቀሜታው የጐላ ይሆናል።

ማጠቃለያ

ከላይ በዚህ ጽሁፍ መግቢያ እንደተገለፀው በርእሰ ጉዳዩ ላይ ሰማተኮር የተፈለገበት ዋነኛ ዓላማና ምክንያት ኢትዮጵያ ለዘመናት ስትወዛገብ በቆየችበት የዴር ሡልጣን ገዳም ከርክር መብቷን በማስከበር ረገድ እንደአስፈላጊነቱ አግባብነት ባለው የኅለምአቀፍ ሕግ ለመጠቀም የምትችልበት አማራጭ እንዳለ ለማመላከት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ከፍሲያዊው ፕሮፌሰር ባሮን በረስ ኖልድ በኋላ በዚህ አቅጣጫ አ ስከአሁን ድረስ በውጭ ሀገርም ሆነ በሀገር ውስጥ ባለሙያዎች በኩል ጥልቅት ያለው ጥናት ያልተካሄደበት በመሆኑ ይኸው ከፍተት መኖሩን በመገንዘብ ወደፊት በመስኩ ሰፋ ባለ ሁኔታ ሊደ ረጉ ለሚችሉ ጥናቶች እንዳንድ የመነሻ ሃሳቦች ለመፈንጠቅ በመሻት የተሞከረ ጅምር ነው ለማለት ይቻላል ።

በሌላ በኩል ይኸው በጎዳዩ ላይ የተሞከረው ጥናታዊ ቅኝት በተጠናከረ ዝርዝር ጥናትና ምርምር ታግዞ ከዳበረ ሀገራችን በዲር ሠልጣን ገዳም ክርክር የባሰቤትነት መብቷን ስማስከበር በምታደርገው ትግል ዓለም አቀፍ ሕግን አሰፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ እንደአንድ አማራጭ ስመጠቀም የሚያስችላትን የአቋምና የፖሊሲ ወሳኔ በአግባቡ ለመቅረጽ እንደሚረዳ ይታመናል ::

ከዚህ ባሻገር ኮሚቶች በሀገራቸው ውስጥ በዜተ- ክህነትም ሆነ በመንግስት ደረጃ እንዲሁም ታዋቂ ምሁራንና የሚዲያ ሰዎቻቸውን ጭምር በስፋት በማሳተፍ በተሰይ በፖሰቲካ ውና በዲኘ ሎማሲው መስክ ለአያሌ ዓመታት ያልተጀረጠ እንቅስቃሴ እያካሄዱ በገዳሙ የባሰቤትነት ክርክር ያነሱትን የይገባኘ ጥያቄ በተደጋጋሚ የማስተጋባት ራሳቸውን ሐቀኛ ባሰመብቶች አድርገው እንደሚያቀርቡ የሚታወቅ ነው:: ከዚሁ እንቅስቃሴያቸው ዓይነተኛ መገለጫዎችም መካከል በጎዳዩ ዙርያ ያለማለስለስ መጻፍ ፣ አልፎ ተርፎም በአንዳንድ አጋጣሚዎች የፕሮፖጋንዳ ዘመቻ ማካሄድ፣ ሲምፖዚየሞችን በተዘታታይ ማዘጋጀት ምሁራኖቻቸውን በተለያዩ ሀገራዊና ዓለማቀፋዊ መድረኮችን እያሳተፉ በጎዳዩ ላይ ጥናትና አስተያየት እንዲያቀርቡ ማድረግ በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው::

ስለሆነም ከዚሁ የግብጾች የለስ እንቅስቃሴ አንጻር በሀገራችን በኩል በገዳሙ ጉዳይ ላይ ከሳይ በተጠቀሱት ዘርፎች በተለይ በሀገር በቀል ባለሙያዎች አማካይነት ሊሠሩ የሚገባቸው በርካታ ቁም ነገሮች እንዳሉ ከማስገንዘብ፣ ዜጎች ሐቅና ፍሬ ነገሩን በማገባ ተረድተው የራሳቸውን ገንዘ አስተዋጽኦ እንደያደርጉ ከማነሳሳትና በጎዳዩ ዙሪያ በሀገራችን የሚካሄደው መብትን የማስጠበቅ እንቅስቃሴ ይበልጥ ተቀናጅቶ እንዲጠናከር ከማገዝ አኳያ ይህ ጥናታዊ ቅኝት የበኩሉን መጠነኛ ድርሻ እንደሚያበረክት ተሥፋ ይደረጋል::

በመጨረሻም የዚህ ዓይነት ጥናታዊ ቅኝቶች ቀደምት አባቶቻችን ለአያሌ ወራት ያህል ረዥም ርቀት በእግራቸው ተጉዘው ኢየሩሳሌም ድረስ በመዝለቅ መብታቸውን አስከበረው ሆኖ ፍ መሆናቸውን በመዘከር፣ የዘመኑ ትውልድ በሀገረ ኢየሩሳሌም ከአበው ከአባቶቹ የተረከበውን ታሪካዊ ቅርስ የማስጠበቅ ኃላፊነቱን ለመወጣት መነሳሳት እንዳስበት በማስገንዘብ ረገድ የሚደናቅ አ ስተዋጽኦ ሊያደርጉ እንደሚችሉ ይታመናል::

ዋቢ መጻሕፍት References

- Malcolm N. Shaw, 1997. International Law, 4th Edition. A Grotius Publication, Cam bridge University Press.
- Martinus,Nijhoff, 1991.International Law in Theory and Practice, Puhlishers, Oscar Schachter,
- መክንን ዘወዲ፡ 1992 ዓ.ም፣ ኢትዮጵያ እና ኢየሩሳሌም፣ አዲስ አበባ
- አማኑል ገበየሁ፡ 1992 ዓ.ም፡ ቅድስት ሀገር፣ ፣ ኢየሩሳሌም
- ብውዕ አቡነ ማቴዎስ፡ 1989 ዓ.ም፡ ያብረ ሥልጣን በኢየሩሳሌም፣ ፣ ኢየሩሳሌም
- ብውዕ አቡነ ፊሊጶስ፡ 1962 ዓ.ም፡ ኢየሩሳሌምን ዕወቁ፡ አዲስ አበባ
- ዶ/ር ሽመ-ኤል ቦርከቪች፡ ኢ.አ.አ 2010፡ የትዳስን በታዎች ቦኒንት፣ (በእብራይስጥ ቋንቋ ተጽፎ ከገጽ 278-80 ድረስ በእንግሊዘኛና በአማርኛ የተተረጐመ)፣ እሥራኤል

ሐሳበ ዘመን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

ዲ/ን ዳንኤል ሰይፈሚካኤል
ቅድስት ሥላሴ ምሥረሳዊ ኮሌጅ



ዲ/ን ዳንኤል ሰይፈሚካኤል ጥናታቸውን ሲያቀርቡ

መግቢያ

ሃሌ ሉያ በዘንዘለር ሐሳባተ ሕጉ ወትእዛዙ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዘ ሃሎነ በዘመነ ቅዱስ ማርቆስ ቡሩክ ያብጽሐነ እስከ ዘመነ ቅዱስ ሉቃስ በሰላመ እግዚአብሔር አሜን።

እሥሩ ወተስኡ ምዕት ተስአ ወአርባዕቱ ኮነ ዓመተ ምሕረት 1994

ሃምላ ወሃምስቱ ምዕተ ዓመት ኮነ ዓመተ ፍዳ

ሰብአ ወአርባዕቱ ምዕት ተስኡ ወረቡኡ ኮነ ዓመተ ዓለም 1994

ዮም ሠረቀ ስነ ወርኃ ሚያዚያ ቡሩክ ያብጽሐነ እስከ ወርኃ ግንቦት

በሰላመ እግዚአብሔር አሜን

አሚሩ – 0 ሠረቀ ሌሊት

ሃመ-ሱ – 5 – ሠርቀ ወርኀ

ኖ-ሱ – 9– ሠላሮቀ መዓልት

ሰኑዩ – 2 – _ጥንተ ዮን

ኢትዮጵያ በዓለም ረዥም ታሪክ አላቸው ከሚባሉት ታላላቅ አገሮች የምትመደብ ራ ሳችውን የቻሉ በርካታ ባሕሎች እና ዘዳቶች ያሏት ጥንታዊት ሀገር ናት። በሃይማኖትም ሪገድ አስቀድሞ በሕገ ልቡና ከዚያም በሕገ ኦሪት ስትተዳደር የነበረች በመጨረሻም ከእምልኮተ እግዚአብሔር ሳትለይ ክርስትናን በመቀበል ቀደምት ከሚባሉት መንግሥታት አንጿ ነች። ይህችን ሀገር እጅግ በጣም ረዥም ለሆነ ዓመትም ስትመራ የኖረችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ለዘሀች ሀገር ከአበረከተቻቸው ቋሚ እና ልዩ አስተዋጽኦዎች አንዱ በሀገሩቱ የራ ሷ እና፣ ከመላው ዓለም ልዩ የሆነ የዘመን አቆጣጠሯ ነው።

ምንም እንኳ በርካታ ታሪክን እና የሰውን ልጅ የትውልድ ሂደት የሚያጠኑ ምሁራን ኢ ትዮጵያ በክርስቲያኑ ዓለም እና በግብጻውያን ተጽዕኖ አዙን ከምትጠቀምባት የዘመን አቆጣጠር ዘዴ ወይም ሐሳብ ዘመን በፊት የራሷ የሆነ ልዩ እና ከሥነ ፍጥረት ጋር እጅግ በጣም ቁርኝት ያለው የዘመን አቆጣጠር ዘዴ እንደነበራት ቢናገሩም ዛሬ የምንገለገልበት ሐሳብ ዘመን ሥሩን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን አድርጉ ለሀገራቱ እና ለሕዝቧ አገልግሎት መስጠቱን አላቋረጠም።

ስያሜ

ሐሳብ ዘመን ወይም አቡሻክር በርካታ ስያሜዎች አሉት። ከእነዚህም ባሕረ ሐሳብ፣ ዘመነ ዓለም፣ መርሐ ለሙር የቁጥር ትምህርት... እየተባለ ይጠራል። ትምህርቱ እጅግ በጣም ጥንታዊ እና ከፍተኛ አገልግሎት ከነበራቸው የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች አንዱ እንደመሆኑ መጠን እነዚህን ሁሉ ስያሜዎች እንዲሁ አላግኛቸውም።

ሐሳብ ማለት ቁጥር ማለት ነው፣ ዘመን ደግሞ በቁሙ ሆኖ ዘመናትን ዓመታትን ወራ ትን ሳምንታትን እና ቀናትን እስከ ሰዓታት እና የደቂቃን ጊዜያት ሳይቀር የሚሰፍር ስለሆነ ሐሳበ ዘመን ተባለ። አቡሻክር የሚለውን ስያሜ ደግሞ ያገኘው የኖረበት ዘመን በውል ባይታወቅም የሐሳበ ዘመንን ትምህርት ካዘጋጇና ካስፋፉ ሊቃውንት አንዱ በኢትዮጵያ ሊቃውንት ዘንድ እጅግ ከመወደዱ የተነሳ መጽሐፉን በስሙ አቡሻክር ብለው በሰየሙለት በዮሐ ንስ አቡሻክር ስም ነው። ይህንንም ከመጽሐፉ አቡሻክር /ለቅላይ ቤተ ክህነት ብራና/ መግቢያ ላይ እንዲህ ብሎት ይገኛል።

> «ዝንቱ መጽሐፍ ቡሩክ ዘደረሰ እግዚእ ትሩፈ ምግባር ማዕምረ መጻሕፍት አቡሻክር ወልደ አብአልከሪም ጴጥሮስ መነኮሰ ዕብን ልመሐደብ በበትርጓሜ ዙ ወልደ ግሡጽ ወእመ አኮ ወልደ ምኑር ዘእሙር በረሺ ዘተሰይመ ዲ ያቆነ በቤተክርስቲያን ዘመዓልቃ እንዘ ይነግር በእንተ ሐሳበ ዓለም አምፍጥረተ አዳም»

> «ይህን የተመሰገነ መጽሐፍ የደረሰ ምግባሩ የቀና መጻሕፍትን የመረመረ የሚያውቅ መነኮሰ የአብአልከሪም ጴጥሮስ ልጅ ሲሉ አበሻክር ነው። ዕብን ልመሐደብም ይሉታል የተረመ ምኑር ልጅ ማለት ነው። በረሺ የታወቀ

በመሠልቅ ዘምትገኘው ቤተክርስቲያን ዲያቆን ሆኖ የተሾመ ሲሆን በመጽሐፉም አዳም ከተፈጠረ ጀምሮ ስለ ሐሳብ ዓለም ይናገራል።» /አቡሻክር ገጽ 7/

«ባሕረ ሐሳብም» ይባላል ባሕረ ዘመን ነው ሐሳብ እንደበፊቱ ቁጥር ነው ያው ሐሳበ ዘመን ካለው ጋር አንድ ይሆናል ልዩነቱ እዚህ ላይ ባሕር ማለቱ የትምህርቱን ስፋት እና ጥልቀት የሚያመለክት መሆኑ ነው። የዘመን አቆጣጠርን ፈሊጥ ስለሚናገር ዘመንን በፋጥር እየሰፈረ ከዚህ ይህን አለፈ ለዚህ ይህን ያህል ቀረ እያለ ያልተሟላውን የተረፈውን የሚነግር በመሆኑ «የቁጥር ትምህርት» ተባለ ስለ የሰው ልጅ ማለትም አዳምን በሚመለከት ታሪክ ሥሚቀምረውን የዘመን አቆጣጠር ሲያመለክት ደግሞ «ዘመነ ዓለም» ይላል። ሌላው ትልቁ ስያሜው ደግሞ መርሐ ዕውር መባሉ ነው። ይህ ግን ከስያሜው አልፎ መጽሐፍ ወይም የትምህርት መርጃ መሣሪያ ሆኖ ከልዩ ልዩ መጻሕፍት ተውጣጥቶ በኢትዮጵያዊያን ሊቃውንት የተቀመረ ነው። ማንም ቢሆን ለው ሆኖ ዕድሜውን የማያሰላ ማንኛው ዘመን ላይ እንዳለ ለ ማወቅ የማይጓጓ የለምና አዋቂውም አላወቂውም ስለሚጠቀምበት በተለይ ለአላዋቂው ለመንገር ለማስተማር ሲባል ይህን መርሐ ዕውር የተሰኘውን ሰያሜ አግኝቷል። ለምንገለገልበት የዘመናት እና የበዐላት፣ የአጽዋማት እና የዕለታት ቀመር እንደ መነሻ የሚቆጠረው አቡሻክር ነውና በዚህ አጭርና ባህርን በማንዚያ በሆነ ጽሑፌ ውስጥ ይዘቱን እና አገልግሎቱን የምናየው የዚህኑ ጽሐ ፍ ነው። እርግጥ ከጥንታዊቷ የአንደኛው ከፍለ ዘመን ቤተክርስቲያን መምህራን ሊቃውንትን እና ካህናትን ጨምሮ የጻፏቸው በርካታ የቁጥር መጻሕፍት አሉ። እንደብዛታቸው ግን ከትዴሳት መጻሕፍት ገብተው የተቆጠሩ የሉም።

በፍትሐ ነገሥት እንቅጽ 2 «በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሊቀበሏቸው የታዘዙ ቁጥራቸው 81 የሆነ አምላካውያኑ መጻሕፍት ዝርዝር አቡሻክር ወይም ሌላ የቁጥር መጽሐፍ የለም ይህም የሆነው እንዲህ ነው። ሐዋርያት መጻሕፍትን ቆጥረው ለቀሌሜንጦስ ዘርም ሲያስረክቡት ሂኖክን እና የቁጥር መጻሕፍትን አሳካተቱም ምክንያቱም።» ከአዳም ሰባተኛ የሆነ የያሬድ ልጅ /ይሁዳ.1÷14፣ ዘፍጥ.5:18/ሂኖክ/ አካሔዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጉ የሰማይ የምድሩ ምስጢር ተገልጸለት የሥነ ፍጥረትንም ነገር መርምሮ የጻፈው መጽሐፍ መጽሐፈ ሂኖክ ነው። ሂኖክ እግዚአብሔርን ዳሰ ያለኝ እንደሆነ ሐዋርያው መስክሯል /ዕብ.11÷15/ በዚህም እግዚአብሔር ሞትን ሊያሳየው ስላልፈለገ ከዚህ ዓለም ሳይሞት ለይቶታል ወደ ራሱም ወስዶታል /ዘፍ.5÷24/ ታዲያ ይህ ቅዱስ በሰማይ ተሰውሮ ሳለ ስለ መላእክት ስለ ሥሲሕ ስለፀሐይ እና ጨረቃ አመላለስ /ሁደት/ የጻፈው መጽሐፍ ለአንድ ቦጥንታዊት ቤተክርስቲያን ላይ ለነበረ ችግር መንስኤ እና ድጋፍ እየሆነ አስቸገረ። ይህም ክርስትናን የተቀበሉ ግሪካውያን የቀድሞ ልምዳቸው ከከብ ቆጠራና አምልኮ የሥነ ፈለክ ምርምር በክርስትናም ተጽፎ ሲያገኙት ይህን ካለ የኛም የቀድሞ መጽሐፍ ይግባ በማለታቸው ሂኖክ እና ሌሎች በርካታ የቁጥር መጻሕፍት ደግነታቸው እየታወቀ ከቁጥር ሳይገቡ ቀሩ።

ከዚህ በኋላ ግን እየቆየ በመጣው የበዓላት አዋዋል እና የአጽዋማት እጀግመር የክፍለ ዘመናት አቆጣጠር ክርክር በተለይ የክርስትናው ተከታይ እየበዛ ሲሄድ የራሱ የሆነ ሐሳበ ዘመን መከተል በመጀመሩ የቁጥር ትምህርት እና አገልግሎት ወሳኝ እየሆነ ሄደ። ሊቃውንትም ከሌላው ትምህርት ጋር የዘመን አቆጣጠሩን ትምህርት እየደረቡ መስጠት ጀመሩ። ለዚህም የእስክንድርያው ትምህርት ቤት አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚገመት አልነበረም። በኋላ ዘመን ተነሥተው አቡን እኛ እና ግብጻውያን አርቶዶክሶች /ኮፕትስ/ የሚጠቀሙበትን ባሕረ ሐሳብ የቀመሩትን ታላላቅ አባቶች እንደ ድሜጥሮስ የመሳሰሉትን ያፈራ ነው።

ለዚህ አጭር ጽሑፍም ቅድመ ክርስትና የነበሩት እና በክርስቲያኖች የዘመን አቆጣጠር

ላይ ቀዋሚዎች ሆነ ተዘዋዋሪ ተጽዕኖ እና ድጋፍ ያደረጉ የአረማውያን አንዲሁም የአይሁድ ዘመን አቆጣጠር በክፍል አንድ በአጭሩ ተመልክተን በክፍል ሁለት ስለ ክርስትና ዘመን አቆጣጠር ዕድገት ከአይሁድ ጋር የነበረውን ተዛምዶ እና ልዩነት በመጠኑ በመዳሰስ በክፍል ሦስት ወደ ኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የአቡኻክር አጠቃቀም እንገመግማለን። በመጨረሻም አንዳንድ በባሕረ ሐሳብ ያሉ ተቃራኒ ሐሳቦችን ወይም ተቃውሞዎችን በመጠኑ ከነ መረጃቸው እናያለን

ክፍል አንድ

ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበሩ ልዩ ልዩ የዘመን አቆጣጠሮች

አግዚአብሔር አምላክ አዳምን ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ ከሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ ፈጥሮ በልጅነት አክብሮ ከአንዲት ዕፀ በለስ በቀር ከሰማይ በታች ከምድር በላይ ያለውን ሁሉ ብሳ፡ ጠጣ፡ ግብ፡ ንዳ፡ ብሉ በነኔት እኖረው። አዳምም ሰባት ዓመት ትዕዛዙን ጠብቆ በሕጉ ጸንቶ ከቆየ በኋላ ምክረ ከይሲ ሰምቶ አምላክነትን ሽቶ ከፈጣሪው ጋር ተባልቶ በሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስ በር.ደተ መቃብር ርደተ ሲኦል ተፈረደበት። በፈተሂነቱ አንጻር መሐሪነቱ እንዳለ አውቆ ንሴሐ ቢገባ በሐሙስ ዕለት ወበመንፈቃ ዕለት እትወለድ እምወለተ መለትከ ወእድህክ ውስተ መርህብከ ወእትቤዘከኪ በመስቀልየ ወበሞትየ ብሎ ተስፋውን ነገረው አዳምም ለልጅቹ ነገራቸው። ልጆቹም እኩሌቹ በጨረቃ እኩሌቹ በከዋክብት እንዲሁም በዐሐይ ሲቆጥሩ ኑረዋል። ቁጥር የተጀመረው በዚህ ምክንያት ነው። ነቢያትም ትንቢት ሲናገሩ ሱባዔ ሲቆጥሩ ኖረዋል።

ጌታም አዳምን እና ሐዋንን ፈጥሮ ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት ዘፍ.1፡28/ ብሎ የተናገረው እየተፈጸመ ሲሄድ የሰው ልጅ በምድር ላይ ተበተነ ቋንቋውም በናምሩድ ዘመን በሰናኦር ተከፈለ። በዚህም የተነሳ ከመኖሪያው ሀገር ከቋንቋው ልዩነት ጋር የተለያየ ባህል እና ልማድ ተከታይም ሆነ። ከአምልኮተ እግዚአብሔርም በተለየ ጊዜ የተሰጠውን የተስፋ ቃል በንጉቶ የማያውቃቸውን ግን በአጄ የሠራቸውን ጣዖታት እያከበረ በአል እየሠራ በተለያየ ሀገ በተለያየ ዓይነት በዓል እና የሃይማኖት ልምድን አስፋፋ። ተስፋውን ካልዘነጋው እና አምላኩን ፈልጉ ከአገኘው ልዩ ሕገብ በቀረም የቀጠርቀሱን ቀን የሚያስብ ከ5500 ዘመን ጀምሮ ያለውን ቁጥር ወደ ታች የሚቆጥር የነቢያትን ሱባዔ የሚመረምር ሕዝብ ጠፋ። በዚህም ረገድ የዘመን አቆጣጠር ከአምልኮተ እግዚአብሔር ወይም ከአምልኮተ ባሰድ ሳይላቀቅ ኖረ ጨረቃን የሚያመልከው በጨረቃ ሲቆጥር ከዋክብት የሚያመልከው በከዋክብት ሲቆጥር ለዘመን መቁጠሪያ የተሰጡት መጋብያን ሰሊታት ፀሐይን ጨረቃን እና ከዋክብትን አማልክት አደረጋቸው።

ፈላስፎች እና የሥነ ፈለክ ተመራማሪዎች ደግሞ ለዚህ ድርጊት ዋንኞች ነበሩ። የሰውን ዕድል እና የወደፊት ዕጣ ከዐደተ ከዋክብት እና ባሕርየ ፍጡራን ጋር እያዛመዱ የጥንቆላ ሥራውን አሰፋፍተዋል። ለዚህም ከኛው ባሕረ ሐሳብ /አቡኻክር/ ጋር የተጠረዘው ዐ ውደ ነገሥት እና ዛሬ በዘመናችን በየግል ጋዜጣው «አስትሮሎጂ» እየተባሉ የሚጠሩት ዓ ይነ.ኖ ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ሁሉ የሆነው የሰውን ደካማ ጉን ተገን በማድረግ ሲሆን ቀደም ሲል በመግቢያው ላይ የተገለጹት መጽሐፈ ሄኖክ እና አቡኻክር ከቅዱሳት መጻሕፍት እንጻይቆጠሩ ያደረጋቸው ዘዚህ ክርስትና በ1ኛው ክፍለ ዘመን ወገቢን ይዛ ስትቃዠመው ለነበረው የግሪክሙያን እና የምሥራቅሙያን «ምዋርት» የተጋለጡ በመሆናቸው ነበር።

የሆነ ሆኖ ዋናው ጉዳይ አሁን የዘመን አቆጣጠሩ ልዩነት በመሆኑ ከዘርካታዎቹ የዘመን አቆጣጠሮች በክርስትና ላይ ተጽእኖም ሆነ ድጋፍ ያደረጉትን የዘመን አቆጣጠሮች በመጠኑ

የ19 ዓመት ቀኖች ብዛት (19 X 365) =	6935.00
የ4 ዓመት ሠግር /1 ቀን/ (19 ÷ 4) =	+ 4.75
የቀኖቹ ድምር	6939.75
የጨረቃ ቀን አማካኝ /Average/ 29 + 30 = 29.50 / 2	
ከዚህ በኋላ አጠቃላዩን የጨረቃ ወር ለማግኘት 6939.75 = 29.5	235.24
235.24 የጨረቃ ወር ያለው ይህ ነው	
የዓበት·ቴ ጉዳይም	
የዐሐይ ዓመት /30 X 12/ + 5	365
አማካኝ የጨረቃ ወር ዓመት /29.5 X 12/	- 354
	11 እበት·ቴ

እንመለከታለን::

ከዚህ በፊት ግን አንዳንድ ጊዜ ዘሐይን እና ጨረቃን እንዲሁም ከዋክብትን ከዘመን መቁጠሪያነታቸው ባሻገር ለጥንቆላና ለምዋርት የሚያውሉ በመኖራቸው ከባሕረ ሐሳብ ጋር ያለውን ልዩነት ለመግለጽ ያህል ትንሽ ወደ እነሱ እንመለስ:: ስለ እነዚህ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ «ኖኅተ ብርሃን» በተባለ መጽሐፉ «ረዓይተ ኮከብ ወእለ ይትአመኑ በሐሳበ ፀሐይ ወወርኅ ወከዋከብት ወበትእምርት... እመሂ ሰብአ ሰገል መእመኒ መስግል እያለ ይገልጻቸዋል:: /አርጋኖን 279/

መስግላን ወይም መጥኅሙያን /ጠንቋዮች/ /ከከብ ቆጣሪዎች/

እነዚህ በጨረቃ እና በመንበቶ ከዋክብት /ፕላኔቶች/ ሲካሄድ የሚታየው የጊዜ መለዋወጥና መመላለስ ከመቅታዊ ጊዜ እልፎ በሰው ኑሮና ሕይወት በእንስሳና በባሕር ዓሣዎች እንቅስቃሴ በዕፅዋት ትርኒም አለው» ብለው የተራቀቁ ናቸው:: እነዚህ ሰዎች ምንም እንኳ ለሐሳብ ዘመን ያበረከቱት እስተዋጽኦ ቢኖርም የተነቀፉ ናቸው:: መልካሙን ጥበብ ለክፉት አውለዋልና:: ዮሐንስ አቡሻክርም በእንቀጽ 4 ገጽ 8 ላይ ከአቡሻኸር ጋር ያሳቸውን ልዩነት ገልጸዋል::[9]

መስግላንን ስናነሳ ሰብአ ሰገል ትዝ ይሉናል:: እነዚህም ከከዋከብት ጋር ስላለሳቸው ግንኙነት /ዘማቴ.2÷1–2/ ላይ «እስመ ርኢነ ኮከበ ዚአሁ» በማለታቸው ታውቋል::

ፋሌካውያን ፈለክ ከሚለው የመጣ /Universe/ /Astronomer/ እነዚህ ከነሥጋት ጋር ባደረጉት ተከምዶ መስግላንን እና መጥኅሙያንን በሥራቸው በማድረግ ምርምራቸውን ሰ ማስፋፋት እና ተጽዕኖ ለማድረግ ዕድል አግኝተዋል:: እነርሱም የዕለታትን የወራትን የክፍለ ዘመናትን የዓመታትን የዜንትሮሳትንና የደቂቁ ዜከሮስን ውሳኔ የሚጠቀ ብርሃናት /በብርሃናት መመላለስ/ መሠረት ከሥርዓታዊ ሕገ ተፈጥሮ ጋር ይዛመዳሳቸው ዘንድ ከነዋብ እስከ ነጥብ የሚወሰኑባቸውን እርስጠላሶች /መመዘኛዎች/ እያበጁ በእስተሳሰብ የጉደለውን እየተቆጣጠሩ በክርክር እያስነውቀ እየሚሉ ውሳኔዎችን ገልጸዋል:: ዮሐንስ አቡሻክር ስለ እነዚህ ሰዎች አብርክስና አረማድረስ የተባሉ ፋሌካውያን በመጥቀስ በአሌክሳንደር ጊዜ መኖራቸውን ይገልጻል::[10] /አንቀጽ 37 ገጽ 65–66/በሌላም መልኩ ስለፋሌካውያን ሐሳበ ፈለክን የሚቆጥሩ የምርምር ክፍል ወገኖች /Astronomers/ የእንድ ዕለት ማለት /24/ ሰዓት መነሻን ከእኩለ ቀን

ከቀትር ይጀምራሉ በሌላውም ቀን እንዲሁ ያደርጋሉ። ይኸውም የጨለማና የብርሃን ጊዜ የሚተካከልበት የፀሐይ ምልክት በሚያርፍበት ጊዜ ነው። እርሱም የፈለክ ምልክት ነው ይላሉ።

«ይህም ኢክርስቲያናዊ እና የተባባው የአውሮፓውያን አቆጣጠር ነው ምክንያቱም :-

1. ሥነ ፍጥረትን አይከተልም

2. ጌታ በመቃብር ያሳለፈውን ጊዜ መረጃ በማድረግና

3. ሰመራት እስቸጋሪ የሆነ /ilogical/መሆኑ ነው

ስለዚህ በዚህ አቆጣጠር ሰዓታችንን የሞላን ካለን ፈለካውያን ነን እንጂ ክርስቲያናዊ አቆጣጠር አልተከተልንም።

ሠራዕያን ሕግ እነዚህ ደግሞ ሰው በዚህ ዓለም የሚኖረው ለ7000 ዓመታት ብቻ ነው የሚሉ የአህዛብ ፈላስፎች ናቸው። የዘመኑንም ቁጥር ከዚሁ ጋር ነው የሚሄደው ይላሉ። አሁን ዓለም ከተፈጠረ 7494 ዓመተ ዓለም ሆኖታል። እንደ ሠራዕያን ሕግ ከሆነ አሁን ያለነው ወይ በተሳሳተ ቁጥር ላይ ነው ወይ ደግሞ ያኛው ትውልድ ከ494 ዓመት በፊት ጠፍቶ በሌላ ትውልድ ላይ ነው ማለት ነው።

መገንዘብ የሚገባን ዓቢይ ጉዳይ በነዚህ ሁሉ የፍልስፍና ስምች ዘመን ኢ ትየጵያውያን ለ ቃውንት እንደነበሩ ሲሆን ልዩነቱ ኢትዮጵያውያን ሐሳበ ዘመናቸው ፍጹም ሥነ ፍጥረትን የተከተለ በመሆኑ እና ተጽዕኖ ያልደረሰበት መሆኑ ነው። ነገር ግን አባቶቻችን ለኛ አስበውልን ለኛ የሚሆኑ መዛግብትንም ትተውልን አልፈዋል እኛ ግን ስለ አባቶቻችን እናስብም ስለ እነሱም አንጽፍም። እነሱ አርቀው ያዩትን እኛ ዞረን ማየት አልቻልንም ወይም ከፊታችን ማየት አልቻልንም እና አልጻፍነውም። ስለ ውሽቱ ጊዜ የሚያጋልጠውና የሰው ልጅ ሞራል ስለማይቀበለው ትምህርት እጅግ ብዙ ተጽፎለታል እውነቱ እና ጠቃሚው ግን የሚያየውም አጥቶ በየዕቃ ቤቱ እና ቤተ መጻሕፍቱ ባለ ቤት አጥቶ ተቀምጧል።

ወደ ጥንታዊያቹ ዘመን አቆጣጠሮች ስንመለስ ቀደም ብሎ እንጋተጠቀስው ቀን መቁጠር እና ሐሳብ ማስላት የተጀመረው አዳም ከገነት ከወጣ እና ተስፋውን ከሰማ ጊዜ ጀምሮ ነው ብለናል ከላይ ያየናቸው ከክብ ቆጣሪዎች፣ ፈለካውያን እና ሠራዕያን ሕግ የራሳቸው የሆነ አቆጣጠር አላቸው። ከእነሱ በተጨማሪ የጥንታዊ አይሁድ ሐሳበ ዘመን፣ የግብጻውያን፣ የዮልዩስ ቄሣር /Julian calander/ እና የሩቅ ምሥራቁን /ሒንዱ/ ሐሳበ ዘመን አጠር አጠር አድርገን እንመለከታለን።

የአይሁድ አቆጣጠር

ይህ አቆጣጠር የፀሐይን እና ጨረቃን አቆጣጠር የቀከተለ ሲሆን ሁለቱንም ለማጣጣም ይሞክራል። በክርስትናም የዘመን አቆጣጠር ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል። ዓመቱን በአራት የአየር ጸባይ ወራት ከፍሎ በጨረቃ አንጻንዴ 30 አንጻንዴ 29 ቀን የሆኑ 12 ወሮች አሉት። ይህ አቆጣጠር 30 ቀናት ካሉት ከዐለ 12ቱ ወር የፀሐይ ወር በ11 ቀኖች ያንሳል። ሁኔታውን ለማመጣጠን በ19 ዓመት ስባት ጊዜ ያኸል ሠገር ዓመቶች እንዲኖሩት ተደርጓል ይህም ሮሜ ቶን ዑደት /Methon cycle/ነው። አነዚህ ወሮቹ የጨረቃ ዓመቶቹ የፀሐይ የሆኑ የዕብራውያን ሐ ሳበ ዘመን ሠገሮች ወደ ፊት ከምናያቸው የዓመተ ምሕረት ሠገሮች የተለዩ ናቸው። የዕብራ ውያን ዓመት የሚጀምረው ከጌታ ልደት በፊት 3761 ዓመት ነው ይህም ራሳቸው ቀምረው ክርስቶስ አልመጣም በማለት ዓለምን ያምታቱበት ቁጥር ነው። የዘመን መለወጫቸው ደግሞ

በመስከረም ወር ሌሊቱና ቀኑ እኩል በሚሆኑበት ዕለት ሲሆን ይህም ቀን አሁንም በእነሱ ቀመር ከጌታ ልደት በፊት በ3761 ዓለም የተፈጠረበት ብለው የሚያምኑበት ቀን ነው። እዚህ ላይ ከእኛ ጋር አንድ የሚያደርጋቸው ነገር በዓመት መቀየሪያቸው የነሱ /ቲሸሪ/ እና በእኛ መስከረም /መዝከረ አሞ/ ነው። በርካታ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ፌተክርስቲያን ሊቃውንት ዓለም የተፈጠረበት መስከረም 1 ነው ብለው ያስተምራሉ መጋቢት 29 ነው በሚለውም የሚስማሙ እጅግ በርካታ ናቸው ። ይህንንም እኛ የእኛን ባህረ ሐሳብ በሚነቅፈው በንዑረ ዕድ ኢርምያስ ከበደ ሠልደሚካኤል «ኢትዮጵያ የዓለሙ መፈራረጃ» አስተያየት በመጨረሻ ላይ እናየዋለን።

ከክርስቶስ ልደት በፊት 432 ዓመት ላይ ሜቶን የተባለው ግሪካዊ አንድ አዲስ ጨረቃ በየ19 ዓመቱ መጀመሪያ /ቢታየበት/ በወሳበት ዕለት እንደገና ይወሳል። በ19 ዓመት ውስጥ 235 የጨረቃ ወሮች አሉ። አለ። የጨረቃን እና የፀሐይን ዓመት የ11 ቀን ልዩነትም ተረዱ ይህም እኛ «አበቅቴ» በግሪኩ /አፖክቱ/ የሚለው ነው። ተራፊ ተረፍ ማለት ነው። 235ቱ የጨረቃ ዓይቶች የተመሠረቱት በዚህ ላይ ነው። ከዚህም ጋር የጨረቃ ወርነዊ ዕድሜ በ29 እና በ30 የፀሐይ ቀኖች መካከል መሆኑን አረጋገጠ የዚህ ሁሉ ስሌት እንዲህ ነው።

በዚህ ሜቶን ትክክል ነበር በኋላ ዘመንም በእክስንድርያው የአርጊንስ /Origin/ ት/ቤት ይሠጥ ስለነበረ ለክርስትና ሐሳብ ዘመን ትልቅ መሠረት ሆኖ አገልግሏል።

- **የግብጻውያን የዘመን ስሌት**

አሌክሳንደርያ /Alex anderia/ ጥንቱንም ቢሆን ቢታላላቆቹ የሒሳብ ቡቲሊይ ጂኦሜትሪ /Geometry/ የታወቀች ናት። ትልቁ እስክንድር /Alexander the Great/ ከግሪክ እስከ ፋርስ ሲ ገዛ ይህችው ኩቲማ የመኮንኑ የበጥሊሞስ ማዕከል ነበረች። በዚህም ከፍተኛ የሥነ ፈለክ /Astronomy/ እና ኮከብ ቆጠራ /Astrology/ ማዕከል ሆነች። የዚህ ሁሉ ጥርቅም ታዲያ ግብጻውያንን ቀደም ብሎ በጨረቃ በኋላ ደኅሞ በፀሐይ እንዲቆጥሩ አድርጓቸዋል። በአጠ ታላይም 30 ቀኖት ያላቸው 12 ወራት ለአንድ ዓመት መቁጠሪያ ይጠቀማሉ። 5 ቀን ትርፏን ጨምረው በአጠቃላይ 365 ቀናትን አንድ ዓመት ይላሉ። በኋላ በBC 239 በጠሊሞስ መኮንን ውሳኔም አንድ አራተኛ ቀን ጨምረው 365 1/4 ቀንን አንድ ዓመት ማለት ጀመሩ። ይህ አቆጣጠር አሁን እኛ የምንጠቀምበት የኢትዮጵያ የጥንት እና የአሁን ሐሳብ ዘመን ነው። ግብጻውንም በመንግሥት ደረጃ እስከ 46 ዓመተ ፍዳ የጁሊዮስ ቄሣር ዘመን ድረስ ይጠቀሙበት ነበር። አሁን ግን የግብጽ አርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ብቻ ዓመቱን ት ሠፋርበት።

- **የዮልዩስ ቄሣር ሐሳብ ዘመን**

ዛሬ በምዕራቡ ዓለም ባለው የሥልጣኔ እና የህብት የበላይነት የሁሉንም ዘመን አቆጣጠሮች እየጐተተ ወደ ራሱ ያስጠጋበት ለነሱ የሚገብሩት ሁሉ የዘመን አቆጣጠራ ቸውንም ሐሳብ ዘመናቸውን ከነሱ ለማውራት እንዲመች የራሳቸውን ለታሪክ ገብረው የሚከተሉት ሐሳብ ዘመን መነሻው ይህ የዮልዩስ ቄሣር ዘመን አቆጣጠር ነው /Julious leasar/ ታሪኩ እንዲህ ነው። በመጀመሪያ አንድ ዓመት 304 ቀናትን በያዘ 10 ወሮች ባሉት ተወሰነ ከዚያ ሮምን ከመሠረተው ከንጉሥ ሮሞሉስ ቀጥሎ የነገሠው ሁለት ወር በመጨመር የዓ መቱን ቀኖች ወደ 355 ከፍ እንዲል አደረገ ይህም አሠራር ማንንም የማያረካ ሆኖ በመግኘቱ ለለሠጥ የተጋለጠ ነበር። አልቀረለትም Julios Clasai /ጁሊዮስ ቄሣር/ በሮም ሲ ነግሥ /46 BC/ ከሶሲጀንስ /Sosigenes/ 46 BC /አሌክስአንደራዊ/ ጋር በመሆን 365 ቀናት

ያሉትን የአሌክሳንደርያ ዘመን አቆጣጠር አብነት በሚድረግ የጳጉሜን 5 ቀናት እየበተኑ 30 ቀን የሆነውን የካቲት /Feb/28 አድርጉ መስከረም፣ ኅዳር፣ ሚያዚያ፣ ሰኔ 30 ቀናት እንዲ ኖራቸው ሌሎቹ ጥቅምት፣ ታኅሣሥ፣ ጥር፣ መጋቢት፣ ግንቦት ሐምሌ እና ነሐሴ 31 ቀናት ሆኖ የካቲት በ4 ዓመት አንድ ጊዜ በእኛ በዘመን /leap year/29 እየሆነች በሌሎች ደግሞ 28 ቀናት ይዛ እንድትኖር ሆኑ። በዚህም ሮማውያኑ 12ቱን ወር በ365 ቀን ወይም በ366 ቀን ሲያጠናቅቁ 1 ዓመት ይሳሉ እኛ እና ግብጻውያን ግን 12ቱ ወር ላይ አንድ ባለ 5 ወይም 6 ቀን ያለው ትንሽ ወር በመጨመር በአሉል ቀን ብዛት መሆናቸው ግን በሚለያይ ወሮች አንድ ዓመት እንላለን።

እንግዲህ ከዚህ በላይ ያየናቸው የአረማውያን እና ሌሎች ሐሳበ ዘመኖች ቀናቱንም ዓ መታቱንም ወራቱንም ስያሜያቸውን ስናያቸው ከአምልኮተ እግዚአብሔር የራቁ ሆነው እናገኛቸዋለን። ለምሳሌ ቀናቶቹ ን እሁድ ሰንደይ የፀሐይ ቀን /Sun - day/

ሰኞ መንደይ የጨረቃ ቀን Mon - day moon day ቅዳሜ ሳተርደይ ሳተርን የምትባል የፈስክ አካል ቀን /Sater - day Saturn day/ በግልጽ አብነት ማየት እንችላለን

ይህ ሐሳበ ዘመን ከ1582 – 1924 መካከል ባሉት ዓመታት በተደረገበት ለውጥ እና ማሻሻያ የምዕራቡን ዓለም ሲያገለግል ቆይቷል። እሱን የተካውም አሁን ግሪጎሪያን ሐሳበ ዘመን /Gregorian Calender/ ነው። በኬልቀዶናውያን አብያተ ክርስቲያናት ስፋሲካ እና ተንቀሳቃሽ በዓላት ማማሸም ይውሳል።

የሩቅ ምሥራቅ ሐሳበ ዘመን

በእርግጥ በሩቅ ምሥራቅ ያለው የአምልኮ እና የዘመን አቆጣጠር በመካከለኛው ምሥራ ቅ፣ በአፍሪካ እና በምዕራብ አውሮፓ ሀገሮች ባህል ላይ ያለው ተጽዕኖ በሙል ይህን ያህል ነው ባይባልም አልፎ አልፎ አንዳንዴ በጠቅላላው ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ሆኖ ይገኛል። አቆጣጠሩ ይለይ እንጂ ዓመቱ በ30 ቀን የተከፈሉ 12 ወሮች አሉ ለክርስትናው ባህል እስተዋጽኦ አድርጓል የሚባለው ባህል ግን የበዓል እከባበራቸው ነው። እንደ /ሂንዱይዝም/ የመሰሉትን አ ማልክት ብዙኅ የሆነ አምልኮ ብናይ Ramah /ሀማሽ/ ቪሽኑ (Vishnu) እና ሻቫ (shiva) ለመሳሰሉት ታላላቅ አማልክቶቻው ልደታቸውን ትልቅ ሥራ የሠሩበትን እና ለሰው የተ ገለጹበትን በርካታ ዕለታት ያከብራሉ እንደ ቀን መቁጠሪያ ማንባቢያም ይቆጠራሉ። ወሮቻቸው ግን በእርሻ ወይም ግብርና ወቅቶች ላይ የተመሠረተ ነው።

ክፍል ሁለት

የክርስቲያኖች ዘመን አቆጣጠር

ክርስትና በመጀመሪያ የነበረችበት ዘመን በሁሉም አንፃር ሲታይ እጅግ ሁሣም አሰቸጋሪ እና መከራ የመላበት ነበር። አረማውያን ቅጥ አጥቶ በነበረው ምዋርት፣ ጥንቆላ፣ ጣዖት አምልኮ ክርክር የእውቀት አምልኮ እና የመሣሠሉት በሽታዎቻቸው እጅግ የባሰበት አይሁድም ጌታቄ ከሠቀሉ በኋላ እራሳቸውን ከተጠያቂነት ነፃ ለማውጣት ለመጀመሪያ የወሰዱት እርምጃ ለጌታ የተነገረውን ትንቢት ማዘበራረቅ የተቆጠረውን ሱባዔ እና የዘመን ልክ ማዛባት ነበር። ይህንንም ለማድረግ የተጠቀሙት ዘዴ መጻሕፍትን መቆንጸል ቁጥሮችን መቀነስ ነበር። ይህንን ያደረጉበት ዋና ዋና ምክንያቶች

1ኛ. የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያን አማኞች አይሁድ በመሆናቸው /ዕብራውያን/ እኩሉን ለ

ማደናገር

2ኛ. ክርስቶስን /ስጊድ ስስሙ/ አምላክ አይደለም ለማለት እና ስመሣሠሉት ነው።

ታዲያ ስዚህ አደጋ የተጋለጠው እና በሁሉም መሥክ የጌታን መገለጽ በአንደኛነት ስ ማረጋገጥ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ የሆነው ባህረ ሐሳብ በክርስትና የነበረው አስተዋጽኦ ቀላል አልነበረም። ስስዚህ ከጌታ ጀምሮ የአይሁድንም የአረማውያንንም ልማድ መንቀፉ በመጀመሪያ የሐዋርያት ከዚያ የነሱ ተከታዮች የሊቃውንት የመጀመሪያ ሥራ ነበር።

በሃቱ 16÷4 ላይ ጌታ እራሱ የአይሁድን በተሰይ የሰዱቃውያንን የጊዜ ግንዛቤ ነቅፎቸዋል። «የዘመኑንስ ምልክት መለየት አትችለምን» በማለት የሚመጣበትን እንደስዘበ ተናግሯል ከዚያም ሐዋርያት ይህንን በመከተል በመጀመሪያ ዮሐንስ መጥምቅ «ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ይሰብክ ነበረ» /ማር.2÷15/ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «የዘመኑ ፍጻሜ በደረስ ጊዜ እግዚአብሔር ከድንግል» መወለዱን ይናገራል /ገላ.4÷4 ከዚያም ከአዲስ ሐሳብ ባህር ይናገራል /4÷9/ቅዱስ ጴጥሮስ ሊቀ ሐዋርያትም በመጨረሻው ዘመን ይነስጥ ዘንድ ስተዘጋጀ መጸን እያለ /በ1ኛ ጴጥ.1÷5/ ያስተምር ነበር። ይህ እንግዲህ ከአይሁድ ጋር ስነበረው ነው። የትውልድ ሐረጉንም ስስአዛቡት እና ትውልዱን ስለተጠራጠሩም ነበር ወንጌላዊው ማቴዎስ በወንጌሉ መጀመሪያ የዘር ሐረጉን የጻፈው። ከአረ ማውያንም ጋር ይኸው ክርክር አላቋረጠም በመጀመሪያ ደረጃ ክርስትና ክከክብ ቆጣሪ እና ሥነ ፈለክ /Astronomy and Astrology/ ጋር ሆድና ጀርባ ነበር። ይህንንም ለማየት የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን መልዕክት መጥቀስ ይቻላል። /በገላ.4÷9/ ላይ እግዚአብሔርን ሰታውቁ ይልቀ .ንም በእግዚአብሔር ስትታወቁ እንደገና ወደ ደካማ ወደ ማያልቅ ወደ መጀመሪያ ትምህርት እንዴት ትመለሳላችሁ? እንደገና ባሪያዎች ሆናችሁ ስዚያ ልትገዙ ትወዳላችሁን? ቀንና ወራትን ዘመንንም ዓመትንም በጥንቃቄ ትጠብቃላችሁ? ምናልባት በከንቱ ለእናንተ ደክሜያለሁ ብየ እፈራላችኋለሁ» በማለት በጻፈው ሥነ ፈለክ እና ኮክብ ቆጠራን ነቅፎ በአዲሱ የዘመን አቆጣጠ ር እንደሚጠቀሙ ይናገራል። ምንም እንኳ ቅ/ጳውሎስ ደክሜያለሁ የሚለው ለገላትያ ሰዎች ዘመን መቁጠሪያ እየሰጋ መሆኑን የሚገልጽ መረጃ ባይኖርም ወደ ኋላ እንመለስና ወደ ክርስትናው ሐሳበ ዘመን ከመግባታችን በፊት የዕብራውያን /እይሁድ/ ሐሳበ ዘመን ከሁሉም ይልቅ በክርስትና ዘመን አቆጣጠር መሠረት ነበር።

ዓመቶቹ የሚቆጠሩት በፀሐይ ነው ዕድሜ ደግሞ በዓመት ነው የሚሠፈረው ይህንን አዳም ይህን ያህል ዓመት ኖረ እያለ ከሚለው አባባል ማወቅ ይቻላል። የአዳምን ዕድሜ መነሻ በማድረግ ከአዳም እስከ ክርስቶስ ያለው ዘመን ሲቆጠር 5500 ዓመት ነው።

ዝርዝሩም:

ዘመነ እበው	3842
ዘመነ መሳፍንት	589
ዘመነ ነገሥት	543
ሠመነ ካህናት	526
ድምር	5500

ዓመት ነው አይሁድ ያዛቡት እና እነሱ 3761 ዓመት ነው የሚሉት ይህን ነው

5500

3761

1759

በአጠቃላይ 1759 ዓመት ቀንሰዋል። ሐዋርያው የዘመኑ ፍጻሜ ሲደርስ ያለው ግን 5500 ዓመት ማለቁን ሲያይ ነው።

ሱባዔያት የተባሉት ደግሞ

ይህ ነቢያት የጌታን መመለድ በምሳሌ በትንቢት ያሳወቁበት እነሱ በኛ ዘመን ይሁን እያሉ ነበር ግን የሁሉም ነቢያት አቆጣጠር ሰልት ልዩነት አስው ዓላማው አንድ ቢሆንም ይህ የጌታ ጥበብ እና ጌታ እንደየችሎታቸው እንዲናገሩ ለሰዎች በሰጠው ነፃ ፈቃድ የተነሣ ነው።

ሀ. የመጀመሪያው ሱባዔ ሱባዔ አዳም ነው አዳም በ1ነት 7 ዓመት ከ1 ወር ከ17 ቀን በደስታ ኖሮ ከሠላ በኋላ /35/ ሱባዔ ገብቷል። በመጨረሻው ተሰፋውን ኪዳኑን ተቀብሏል።

በ2ኛው ኢዮቤልዩ በ3ኛው ሱባዔ ቀደሰ ተወሰደ

ከአዳም – ኖኅ 25 ኢዮቤልዩ

ከኖኅ – አብርሃም 19 ኢዮቤልዩ

አብርሃም ሙሴ – 5 ኢዮቤልዩ + 1 ሱባዔ + 2 ዓመት

በአጠቃላይ ከአዳም – ሙሴ 49 ኢዮቤልዩ ነው

<u>ከአዳም እስከ ክርስቶስ ደግሞ ከሔድን</u> ማለት ከፍጥረት ዓለም ጀምሮ

ዘመኑ 5500 ዓመት ነው

በሱባዔ 787 ሱባዔ ከ2 ዓመት

በኢዮቤልዩ 112 ኢዮቤልዩ

ኢዮቤልዩ ቀንደ መለከት ማለት ነው። ከ49 /ቅጾች/ ዓመት በኋላ 50ኛው ዓመት በዚህ ይታወጃል ለባሪያዎቹ ነፃነት የሚሠጠው በዚህ ዕለት ነው /ዘሌ.25/

ለ. <u>ሐሳቤ ሄኖክ</u>፡– የአዳም ለባተኛ የያሬድ ልጅ ነው እሱም ትንቢት ተናግሯል ሱባዔ ቆጥሯል። ሐሳበ ሄኖክ ይህ 35 ዓመትን እንደ አንድ መሥፈርት እየቆጠረ የተናገረው የሄኖክ ሐሳብ ሴሳም አቆጣጠር ነበረው ትንቢተ ሄኖክ ይባላል። ይኸውም 700 ዓመትን 1 ሰንበት ማድረግ ነው።

ሐ. <u>ኢዮቤልዩ ዘሙሴ</u>

ሙሴ ስለጌታ በሚናገርበት ትንቢት በሚመስለው ምሳሌ የሚቆጥረው በኢዮቤልዩ ነበር ይኸውም 3 ኢዮቤልዩ ነው።

መ. <u>ቁመረ አብርሃም</u>

አብርሃም ትንቢቱን ሲያይ በእኔ ዘመን ነው የምትመጣው ብሎ ተመኝቶ ነበር ግን ትንቢት በማየቱ ተደሰተ ዕሰቱን በማሠቡ ረክቷል /ዮሐ.8÷57/ የአብርሃም ቁመር ግን አልተገኘም

ሠ. <u>ቁመረ ዳዊት፡-</u>

ዳዊት ልበ እምላክ የተባለ ነው ስለጌታ ያልተናገረው ነገር የለም ሰብዔም ቆጥሯል በመዝሙሩ ላይ ይገኛል። «140» ሆኖ ተገኝቷል «አንዱን ሽህ ዓመት በፊት እንደትናንት ያልፋል» ያሰውን ነው ይህም 1 ዓመት ብሏታል።

ሦስቦክ /35 X 19/ X 12 = 7980

የሙሴ /57 X 140/ = 7980

የዳዊት /1140 X 7 / = 7980

ሁሉም ምጽአቱን ይናገራሉ።

ረ. ሰብዔ ኤርምያስ እም ዐበይተ ነቢያት

ከእናቱ ማኅፀን የተመረጠ ኤርምያስ ስለ ጌታ ብቻ ሳይሆን ለለ ሐዋርያትም መመረጥ ተናግሯል። /ኤር.1÷5/ የኤርምስ ሰባኤ 7ቱን ቀን አንድ በማለት ነው 7 ጊዜ ይቆጥረዋል 7 X 7 – 49 በአሰር ሲሆን ግን 7 X 70 = 490 ነው ይህንን ቁጥር እስከ 333 ሰባዔ በሚወለድ 333 X 490 = 163170 ዕሰት ይወጣል ይህን ወደ ወር ቢቆጠር

163170 = 5439 ወር ይሆናል።

30

በዓመት ቢቆጠር 446 ዓመት ነው እንዲህ እያሉ ሲወርዱ ጌታ የተወሰደበት ዕለት ያገኛሉ።

ሰባኤ ዳንኤል

በዳንኤልም እቆጣጠር አንድ ሰባኤ 7 ቀን ነው ይህም ትክክል ነው። ሰባዔ ዕዝራም አሰ የሆኖ ሆኖ ሰማመልከት የተፈለገው የጌታ ምጽአት እንዲሁ እንደ ውሃ ደራሽ ሆኖ ሳይሆን ትንቢት ተነግሮለት ሰባዔ ተቆጥሮለት መሆኑ ሐሰበ ዘመኑ ሳይዛባ ስመሆኑ ጭምር ስማረጋገጥ ነው።

ይህም ስለሆነ ነው ሐዋርያው በገላትያ መልዕክቱ የዘመኑ ቀጠሮ ሲደርስ መጣ ያለው ታዲያ እንዲህ ሆኖ የተመሠረተችው ቤተክርስቲያን እየቆየች በዚሁ ሐሳበ ዘመን የተነሳ ክርክር እና ውዝግብ አላጣችም አይሁድ ከልደተ ክርስቶስ በፊት። የሚያከብሯቸው የሚወዷቸው በጣም በጥንቃቄ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሥርዓታቸው እና ደንባቸው ሳይዛባ ያስተላልፏቸው የነበሩ በርካታ በዓላት እና እጽዋግት ነበሯቸው አነሱም በክርስትና ተተክተዋል።

እነዚህ በዓላት እና አጽዋማት ከመሥዋዕት ጋር የተገናኙም ነበሩ። በክርስትና የተተኩት ስለ ሦስት ነገር ነው።

1. እነሱ ምሳሌ እንጂ እማናዊ አልነበሩም ጥላ እንጂ ዋና አልነበሩም

2. በመጀመሪያ ሲሠሩ ለዘለዓለም ጠብቂቸው እየተባሉ ነው የተሠሩት ስለዚህ በአማናዊው መተካት እንጅ መተው የለባቸውም ነበር። ጌታም ልሽር አልመጣሁም ብሏልና።

3. ክርስትናም የተቀበሉት አይሁድ በዓል ስለለመዱ በዚህኛውም የሐዲስ ኪዳን እምነታቸው ወደ ቀደመው እንዳይመለሱ በዓል ያስፈልጋቸዋል። ደም ያስፈልጋቸዋል።

ታዲያ እነዚህ /1ኛ/በዓለ መጥቅዕ ከጳጉሜን 15 መስከረም የሚውል በዓል የዘመን መለወጫ የተባው /2/ ጾመ አይሁድ /3/ በዓለ መጸለት የቂጣ በዓል በሕማማት የተተካ /4/ በዓለ ፍሥሕ ከግብጽ ባርነት ነፃ የወጡበት በፋሲካ የተተካው /5/ ልበ ምድር – በማዕዶት የተተካው ባህረ ኤርትራን ያለፉበት /6/ በዓለ ሠሊት – የእዝመራ በዓል /7/ ጾመ አስቴር ራሷ የጾመችው /6/ ጾመ ዮዲት ራሷ የጾመችው በኋላ የተጨመሩት እነ ሐኖካ /የመቃብያን/ በዓል ሁሉም ከአብርሃም እስከ መቃብያን ድረስ የተቀበሏቸው በዓላት ክርስቲያን ከሆኑ በኋላ እንደ አይሁድ ሆነው ማክበር አልነበረባቸውም በተለይ የፋሲካውን ዘግ በተመለከተ እና የቤተ መቅደሱን የመስዋዕት ሥርዓት ተክትሎ የመጣው ችግር ቀላል አልነበረም። በአሪት ይፈጸሙ የነበሩት ሁሉም መሥዋዕቶች በክርስቶስ ተፈጽመዋል በዓመት አንድ ጊዜ ሊቀ ካህኑ ከቤተ መቅደስ ገብቶ የርሱን እና የሀዝቡን ኃጢአት በበጉ ላይ በማሣረፍ ሰራሱ እና ለሀዝቡ በልዑል እግዚ አብሔር እና በሕዝበ እስራኤል መካከል ገብቶ የሚያቀርበው የምልጃ መሥዋዕት /የድኅነት መሥዋዕት/ በጌታችን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ለስሙ ክብር ምስጋና ይግባውና ራሱ መሥዋዕት ሪሱ አቅራቢ ራሱ ተቀባይ ሆኖ ተፈጽሟል። የፋሲካው በግ /በዘፀ.12/ ላይ ያለው ያለ አንድ እንክን እጅግ በሚያስገርም ተምሳሌት የተሠራው ሥርዓት ተፈጽሟል። ታዲያ ከአይሁድ ክርስቲያኖች እነዚህን ደግሞ መሥራት ክርስቶስ አልሞተልኝም እንደማለት ስለሆነ በሙሉ መተካት ነበረባቸው።

በአረማውያን ክርስቲያኖችም እንዲሁ ነበር ለምሳሌ. የምንመስደው የገና በዓል አሁን በሚከበርበት እኛም በተቀበልነው በታኅሣሥ 25 ለነሱ የሆነው እነሱ በዚህ ቀን የሚያከብሩት የፀሐይ በዓል ነበር። ክርስቲያን ከሆኑም በኋላ ይህን ቀን ማክበር አልተው አሉ ስለዚህ ሐ ዋርያት /በሚልክያስ 4÷2/ ላይ «ነገር ግን ስሜን ለምትፈሩ ለእናንተ የጽድቅ ፀሐይ ትወጣላችኋለች» የሚለውን በመውሰድ የፀሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ልደት እንደ ሥርቀተ ፀሐይ አማናዊ እንደሚያከብሩት ሆነ። ከእኛ ጋር ግንኙነት የሌለው የጥድ ዛፍ ቆረጣም እኛ ጾሮ እያሰን የማንሠማ በአሮጌ እራፊ አዲስ ጨርቅ የምንጥፍ በአሮጌ እቁማዳ አዲስ የወይን ጠ ጅ የምንይዝ ሆኖ ነው እንጅ የዚሁ የአረማውያን የጥንት አምልኮ ርዝራዥ ነው። ታዲያ እንዲ ህ እያለ ሲመጣ ክርስቲያኖችም የጌታችን በዓላት በተሰይ ትንሣኤን እንደፈለጉ ባሰኛቸው ዕለት ማክበር ጀመሩ ማለት ሰኞም ማክሰኞም ማለት ነው። የጌታ በዓላት /ብሥራቱ፣ ልደቱ፣ ጥምቀቱ፣ ሆሣዕና፣ ትንሣኤው፣ ዕርገቱ ሆነው እራትሊጦስ የመንፈስ ቅዱስ በዓል ከጌታ በዓል ገብቶ 7 ሣብዕው ይከበራሉ/ ግዝረቱን ካስገቡ ግን የሱ የብቻው 7 ይሆናል ንዑሳን የማይባሉ ቃና ዘገሊላ፣ በዓለ ስምዖን /የካ.8/ የእሎተ ለሙስ በአሰ ቆማስ ስደቱ ደብረታቦር ይከበራሉ።/

ይህ ሁሉ ሆኖ ክርስትና እንደተሥፋፋች በአህዛብ ዘገሮች ሁሉ ተሰማ እዙን ሌላ ችግር መጣ በየሀገታው ያሉ ክርስቲያኖች በዓላትን እና አጽዋማትን እኩል መጀመር እና መጨረስ አልቻሉም። በዚህም ረገድ የዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ ደቀ መዝሙር የነበረው ቅዱስ ፖሊካርፖስ

ከአግናጥዮስ ምጥው ሰአንበሳ ጋር ሰሚርና /Smirna/ እስክ ሮም እና ቆሮንቶስ ድረስ እየተጓዙ ብዙ ምክክር እና አነስተኛ ሲኖዶሶችን አድርገዋል። በተሰይ በጣም አሰቸጋሪ የነበረው ክርስቲያኖች አንድ ሆነው የአንድ የክርስቶስ አካል ተብለው እንደ ዘመን አቆጣጠር በመሠሉ አስቸጋሪ ፍልስፍናዎች አንድነታቸው መለያየቱ ነበር። በተለያየ ቦታ ያሉ ክርስቲያኖች የተለያየ ዓይነት የዘመን አቆጣጠር ተከታዮች ናቸውና። እዚህ ላይ የጌታ ልደት በዓል አልነበረም ችግሩ በተሰይ በፋሲካ በዓል እና አጽዋማት ሳይ ነበር። የጌታን በዓል በተመለከተ የተወሠነው በሮማ ነገሥታት ሲሆን እሱም ዘግይቶ በ6ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ በዲዮናሲዩስ ዘሮም አማካኒነት ዘመን መለወጫ በጌታ ልደት እንጅ በሮም ምሥረታ አይሁን በማለቱ ክርስቲያኖችም ነፃነት ያገኙበት ዘመን በመሆኑ ተቀባይነት ሰሳገኘ ነው። ይህም አሁን ላለው የዘመን መለወጫ አከባበር እና የጌታ ልደት በዓል /የጌታ ልደት ቀን/ ውዝግብ ዓይነተኛ አስተዋጽአ ሲኖረው አሁን አሁን የጌታ ልደት ቀን አይታወቅም ወደ ማለት እንዲደርስ ያደረገ ነው።

በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ግን ሁሉንም መግፋት ባለመቻሉ ቀድሞ እንደተገሰጸው በተሰይ የፋሲካ ጉዳይ በ325 ለተደረገው ጉባኤ ኒቂያ በራሱ አንደኛ ምክንያት ነበር ማለት የእርዮስ ከሀደት እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህም ጉባዔ ነው የመጨረሻውን ውሳኔ ያገኘው ውሳኔውም ከአንቀጾቹ አንዱን የያዘ ነበር።

1. የፋሲካ በዓል አሁድን እንዳይለቅ
2. የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን የፋሲካን በዓል ቀን ሰዓስም እንድታሳውቅ የሚል ይገኝበታል። /ማብራሪያ/

ሆኖም ሰምን የእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ይህን ኃላፊነት ትቀበሳለች የሚለውን ለመመስስ ወደኋላ መመሰስ አስብን ግን እውነታው የእስክንድርያ ት/ቤት ችሎትን ተገነ በ ማድረግ ነው ከእነ ዮሐንስ አቡሻህር በፊት በእስክንድርያ እና በት/ቤቱ በ2ኛው–3ኛው ክፍስ ዘመን የኖሩ እንደ እነ ጲሜኖሮስ የመሠሉ አርጌንስ /origen/ /በኋላ የተወገዘ/ታላሳቅ አባቶች የሐሳብ ሊቅውንት /Astronomy/የተማሩ ነበሩ እርግጥ በኋላ ዘመን ቅ/ዮሐንስ አፈወርቅ ኤጲ ፋንዮስ ዘቆጵሮስ ማር ዮሐንስ ዘደማስቆስ፣ ስዲድ ወልደ በጥሪቅ ማንበብ ዘመባንረ፣ ጊዮርጊስ ወልደ ዓማድ፣ ሳዊሮስ ዘእስሙናይን፣ በርካታ ስማቸውን መግስጽ በሥራቸው /ጸሎቶሙ ወበረከቶሙ/ እያልን የምናውቃቸው ኢትዮጵያዊያን ሊቃውንት ነበሩ /ምሳሌ መርሐ ዕውር/ /ር-ቱዕ ጎይማኖት፣ መዝሙር ክርስቶስ/ /Getachew Haile/

ኑሐ ዘመን

(የሙሴጌታ ትርፌ የዘላለማዊ የኪስ መቁጠሪያ)

ከአራት ዓመት በፊት ከአንድ የ4 ኪሎ ዩኒቨርስቲ ሒሳብ ድህረ ምረቃ ተማሪ ጋር ስስ ባሕረ ሃሳብ እና አቡሻህር ስንነጋገር እንድ ጥያቄ ተነሳ። ጥያቄው ይህ ቀመር በጣም ስፌ እና ጥንታዊ ነው፤ አሁን ደግሞ ትውልዱ በጣም ዘመናዊ አሞርና ቀላል ነገር ይወዳል፣ ታዲያ ትውፊቱን ሳንለቅ ዘመናዊ መቁጠሪያ ቢዘጋጅ ተቀባይነት ይኖረዋል ወይ ? የሚል ነበር ። እንደነገሩ በጉዳዩ ተወያየንና ተለያየን።። ከጥቂት ቀናት በፊት ስዚህ ጽሑፍ ዋቢ የዚህን ጽሑ ፍ የሚረዱ መጻሕፍት በመፈለግ ላይ ሳለሁ አንዲት አነስተኛ ከኪስ ቦርሳ በማትበልጥ መጠን የተዘጋጀች ባለ 31 ገጽ መጽሐፍ አገኘሁ። ርስሷ «የዘላዓለም የኪስ ቀን መቁጠሪያ» ይላል። በውስጧም በርካታ ነገሮችን ይዛለች። መጽሐፏ የተዘጋጀችው በዓመት ውስጥ በተመሣሣይ ዕለት

የመጀመሪያ ዓመታት መሠረት በማድረግ ጥልቅ ምርምር ታክሎበት ነው።

ይህም በዚህ ጽሑፍ ተካትተው አልፎ አልፎ የሚኑ ሐሳበ ዘመን ለማሳደግ የሚደረጉ ጥረቶችን ስመጠቆም ነው። ቤተክርስቲያን ለእንደዚህ ያሉ ለውጠች ልዩ ዓይን ቢኖራት ይጣልና።

ማጠቃለያ

ባሕረ ሐሳብ እንደ ስሙ ባሕር ነው። በቀላሉ የሚዘለቅ አይደለም። ሆኖም ግን ዐንብረተሰቡ በቤተክርስቲያንም ሊቃውንት አሁን አሁን የሚሠጠው ትኩረት እየተሸረሸረ መጥቶአል። ባሕ ረ ሐሳብ የእኛነታችን መገለጫ ቤተ ክርስቲያን ካሷት በርካታ ሀብቶች አንዱ ነው። ስለዚህ ይህ ሀብት በቤተ ክርስቲያንም ሆነ በሁሉም ኃላፊነት ለሚሠማው ኢትዮጵያዊ ውሰጥ ልዩ ቦታ ተስጥቶት ሊስፋፋ ሊታወቅ እና ሊዳብር የሚችልበት መንገድ መታሰብ አለበት።

በዚህ ጽሑፍ ዝግጅት ወቅት አንድ መምህር እንዲህ የሚል አስተያየት ሰጥተው ነበር። «ባሕረ ሐሳብን ሲያስጠላ ሲያሰነቅፍ ሲያሰተች የኖረ ለማዕረጉም ዕንቅፋት ሆኖ የኖረ ከባሕ ረ ሐሳብ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ርዓውደ ነገሥትÈ የተንቆላ መጽሐፍ በቅርቡ ታትሟል። ከአሁን በፊትም በልዩ ልዩ ዓይነት መንገድ ሲቀርብ ነበር። ይህ የሚያሳየው የሰው ልጅ የሚጠቅመውን ትቶ ወደሚጐዳው መሮጡን ነው። ለዚህ የወጣውን ለባሕረ ሐሳብ ቢያደርጉት ምንኛ ሰው በተማረበት» ብለዋል። ስለዚህ አግዚአብሔር ለሰው ልጅ በመጀመሪያ የሰጠው ሀብቱ ጊዜ ነው። ጊዜውን ደግሞ በደንብ ተጠቅሞ ለፍሬ የሚያበቃ ሥራ የሚሠራው የጊዜውን ስሌት ከማወቅ ጋር ሲሆን ነው። በማንኛው ጊዜ ምን መሥራት እንዳሰበት ስሰማይነገዘብ ሰሰዚ ህ ይህን የቤተ ክርስቲያ ሀብት በማወቅ እንጠቀምበት። ለዚህም የጊዜ ባለቤት የዘመናት ጌታ ልሁል እግዚአብሔር ጋልና ጥበቡን ይሰጠን፤ የአናቱ የቅድስት ድንግል ማርያም ረድኤት የቅዱሳን ጥበቃና ጸሎት አይለየን። መስብሐት ለእግዚአብሔር።

የድርሳናተ መላእክት ባሕርያት

ሳሙኤል ያለው

Syalew4aku@hotmail.com

Tel. 09/238364



ጸዶ ሳሙኤል ያለው ጥናታቸውን ሲያቀርቡ

መግቢያ

የመላእክት ድርሳናት ከበርካታዎቹ ጥንታዊ የግእዝ የሥነ ጽሑፍ ቅርሶቻችን መካከል የሚመደቡ መጻሕፍት ሲሆኑ የመላእክትን ማንነትና ምንነት፣ በፈጣሪያቸው ፊትና በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች የሚሰጣቸውንና ሊሰጣቸው የሚገባውን ክብርና ያደረጓቸውንና ሊያደርጓቸው የሚችሉትን ተአምራት ያብራሩ ናቸው። እነዚህ መጻሕፍት በእምነቱና በምእመናኑ ዘንድ የሚከበሩና ለጸሎት የሚውሉ ናቸው። መጻሕፍቱን በማንበብ በሚደርስ ጸሎት ምክንያት የአማላጅነት አገልግሎትና ከተሰያዩ ደዌያት ፈውስ እንደሚያስገኙ ይታመንባቸዋል።

ከዚህ ቀደም ስነዚህ መጻሕፍት ውስጥ ዘሁሉ ሳይ በግርማ ዘነበ (1991) እና በእንግዳው መሉዓለም (1982) የተደረጉ ጥናቶች ቢኖሩም የትኩረት አቅጣጫችን በፍጹም የተለያየ ነው። እንግዳው በዲግሪ ማሟያ ጽሑፉ ድርሳነ ሚካኤልን እንደ አንድ ወጥ ትረካ ዘመቱበረ በ20ኛው ክፍለ ዘመን የሥነ ጽሑፍ መሥፈርት እየስፈረ ሲገመግመው፣ ግርማ ዘነበም በድርሳነ ዑራኤል ውስጥ ያሉትን ስነጽሑፋዊ (በተለይ ሥነ ቃላዊ) ባሕርያት ለማሳየት ሞክሯል። የዚህች ጠ ረቀት ዓላማ ግን የመጻሕፍቱን አጠቃላይ ባሕርያት መግለጥ ነው። በውስጣቸው ምን እንደያዙና የይዘታቸው ባሕርያት ምን እንደሚመስሉ ማሳየት።

የዚህ ጽሑፍ አትራቢ የግእዝን ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታው ውሰን በመሆኑ መዝገበ ቃላትና በቋንቋው የላቀ ችሎታ ያላቸው ሊቃውንት ሊሰው የሚችሉትን አገልግሎት ሁሉ ተ ወቅሟል። የትርጉም ስሕተት እንዳይኖር በቅዎ የፊቀደውን ያክል ጥረት አድርጓል።

ድርሳናተ መላእክት ምንድን ናቸው?

እንደ አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሉ አፈታት (1948:363) ድርሳን

> በቁሙ የተደረሰ፣ የተጣፈ፣ ቃለ ነገር፣ ስፉ ንባብ፣ረዥ ም ስብከት፣ ትርጓሜ አፈታት፣ ጉሥዐተ ልብ (ጻዝዙር)፣ መዝሙር፣ ምሥጢሩ የሚያጠግብ፣ ቃለ የተሳካ፣ ጣዕመ ቃሉና ኃይለ ቃሉ ደስ የሚያሰኝ ልብ የሚነካ። ... ድርሳነ ማርያም፣ ድርሳነ ሚካኤል ቢል ጠግ፣ ታሪክ፣ ዜና ማለት ነው። ሥሥጢሩ ነገር ከማለት ይገባል።

ድርሳን ስለመላእክት፣ ስለቅድስት ማርያም፣ ስለተቀደሰች ቀን እና ስለኢየሱስ ክርስቶስ የሚያትቱ መጻሕፍትን የሚጠቅስ ሲሆን ይችላል፣ በቅደም ተከተላቸው ድርሳነ ሚካኤል፣ ድርሳነ ማርያም፣ ድርሳነ ሰንበት፣ ድርሳነ ማኅያዊ እንዲል። በሊቃውንት የተደረሱ መጻሕፍትም በድርሳን ገለጣነት የሚጠሩበት ጊዜ አለ፣ ደርሳነ ቦሐንስ አፈወርቅ እንዲል።

ሊቀ ጠበብት አክሊለ ብርሃን ወልደቂርቆስ (1945:67-72) በተሰያዩ እድባራትና ገዳማት ውስጥ 138 በድርሳን ገለጭነት የሚጠሩ መጻሕፍት መኖራቸውን መርሐ ልቡና በተባለው መጽሐፋቸው ይገልጻሉ። ከነዚህ ውስጥ 11ዱ የመላእክት ድርሳናት ሲሆኑ መሰእክቱም ቅዱስ ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ሩፋኤል፣ ራጉኤል፣ ዑራኤል፣ እፍኒን፣ ፋኑኤል፣ ሳቁኤል፣ ሱርያል፣ ስራፊኤልና ሕሩቤል በመባል ይታወቃሉ። ከነዚህም መካከል በሌሎቹ ውስጥ ተጠቃሎ የሚገኝ ውን ድርሳነ ሩፋኤልን ሳይጨምር አራቱ ድርሳናት ለምእመናንና ስተመራማሪዎች ጥቅም እንዲውሉ ወደ አማርኛ ተመልሰው ታትመዋል።የታተሙት መጻሕፍት ድርሳነ ሚካኤል፣ ድርሳነ ገብርኤል፣ ድርሳነ ዑራኤልና ድርሳነ ራጉኤል ናቸው።ድርሳነ ሩፋኤል ራሱን ችሎ ከለመታተሙም ባሻገር በአብዛኛው በደርሳነ ሚካኤልና በደርሳነ ገብርኤል ውስጥ አንድ ክፍል ሆኖ ይቀርባል።

ድርሳናቱ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ ልዩነት ቢራቸውም በአብዛኛው ተመሳሳይ ባሕርያት አ ሏቸው። በዙሪያም ደርሳናት ውስጥ የሚገኙትና የድርሳናትን ዓይነተኛ ባሕርያት የሚያንጸባርቁት አሳባዎች መቅድም፣ ድርሳን፣ ዕአምር፣ እርኩና መልክአ ናቸው። እነዚህ አሳባ ዎች በባሕርያቸው ራሳቸውን የቻሉና ከመጻሕፍቱ ውስጥ ወጥተው ለየብቻቸው ቢነበቡ በራሳቸው ትርጉም የሚሰጡና ምሉዕ ናቸው። እነዚህ አሳባዎች ከተሰያዩ መጻሕፍት ወይም ድርሳናት ተሰብስበው የተጠቃለሙና ድርሳንን ድርሳን ያደረጉ ድርሳናት ሊባሉ ይችላሉ። አሳባዎ ቹ ምን እንደሚመስሉ ደግሞ ከዚህ ቀጥሎ አንድ በአንድ እንመልከት።

1. መቅድም

መቅድም በደርሳነ ሚካኤል ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ የሚሰጠው ዘፍል ነው። ይህ ክፍል የሚገኘው በዚሁ ድርሳን ብቻ ነው። መቅድሙ ስለመላእክት ተፈጥሮ፣ ነበር፣ ስላደረጉት ተአ ምራትና ድርሳኑን የጸፉት፣ ያጸፉት፣ ያነበቡትና የፈጣሪን ትእዛዝ የጠበቁት የሚያገኙትን ዋጋ ያስነብባል። ከዚህም ሌላ ስሰ ነገረ መለኮትና ስሰሌሎች ከነይማቱ ጋር ስለሚገኙ ጉዳዮች እያወሳ ያስተምራል።

የመቅድሙ ጸሐፊ መጻፍ ሲጀምር የፈጣሪን ስም ጠርቶ በማስፈቀድ የመልአኩን ምልጃና ጸሎት ይለምናል። ሲጨርስም በሰላም ያስጨረሰውን አምላክ አመስግ በመልአኩ በኩል ጸሎቱ እንዲደርስለት ይማጸናል።

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ
ንቀድም በረድኤተ እግዚአብሔር ልዑል ጸሐፊ ዜና
ዕበዩ ወክብሩ ወልዕልናሁ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ
መላእክት ክመ ይሰአል ለነ ወአለቱ ወትንብልናሁሰ
ወአስተብቁዖቱ ለቅዱስ ሚካኤል ሊቀ ሰማያውያን ይዕቀበነ
ወያድኅነነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ
ስም አምነን በልዑል እግዚአብሔር ረዳትነት የመላእክት
አለቃ የሆነ የቅዱስ ሚካኤል የልዕልናውን የገናንነቱን
ነገር መጻፍ እንጀምራለን። ይቅር ባይ ከሆነ ከፈጣሪው
ከእግዚአብሔር ምሕረትን ይቅርታን ይለምንልን ዘንድ
የሰማያውያን መላእክት አለቃ በሆነ በሚካኤል ምልጃና
ፍጹም ልመናው ከመክረው ይጠብቀን ያድነን።(ድርሳነ
ሚካኤል፣ ገፅ ፩)

ይህ መቅድም የሚገኘው በቅዱስ ሚካኤል ድርሳን ውስጥ ብቻ ይሁን እንጅ በውስጡ የያዛቸው መልእክቶች ሁሉንም መላእክት የሚጨምሩ በመሆናቸውና ይህም መልአክ ሊቀ መላእክት ስለሆነ ለክብሩ እንዲሆን ወይም ደግሞ በሌሎቹ ላይ መጻፍ ቢያስፈልግ ተመሳሳይ የሆነን ጉዳይ መደጋገም ስለሚሆን በአንዱ ላይ ብቻ እንዲወጣ ተደርጎ ሊሆን ይችላል የሚል ክርክር የሚያስነሳ ቀዳዳ አለ። ይሄ ሐሳብ ተቀባይነት ካገኘ ደግሞ መቅድመ ስሁሉም ድርሳናት የሚያገለግል የሁሉም ድርሳናት መቅድም ነው የሚል ሌላ ክርክር ሊያስነሳ ይችላል። ከዚህ ወ ረቀት ውስጥ መቅድም እንደ አንድ አላባ መነሳቱም በዚሁ ምክንያት ነው።

2. ድርሳን

በዚህኛው ሀውድ ድርሳን የሚለው ቃል ጠቅላላውን መጽሐፍ የሚመለክት ሳይሆን በመጽሐፉ ውስጥ የባለድርሳኑን መልእክ ግብር፣ በፈጣሪው ዘንድ ያለውን ሞገስ፣ የሰራቸውን ተአምራት እየዘረዘረና ከመጽሐፍ ቅዱስና ከሌሎች መጻሐፍት እያጣቀሰ የሚያስተ ምር ክፍል ነው። ትምህርቱን ሲሰጥ አንባብያን/አድማጮች ባለመሰልቸትና በተመሰጠ እንዲከታተሉ የተለያዩ ዘዴዎችን የሚጠቀም ሲሆን ከነዚህም መካከል ራሱ በማብራራት የሚመልሳቸውን ጥያቄዎች መጠየቅ አንዱ ነው። በድርሳነ ሚካኤል ውስጥ ስለ መልአኩ ተ ራዳኢነት ሲሰብክ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቃል፡-

መኑ እምኩሉሙ ቅዱሳን ዘአሠሉ ምስሌሁ
ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክተ ወዘኢያጽንዖ
በትእዛዘ እግዚአብሔር ከመ ይንሣእ አክሊለ
ክብር።

ከቅዱሳን ወገን የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል
ከጎኑ ያልቆመለት ማን ነው? በእግዚአብሔር

እየታዘዘ የነዘር አክሊል ይቀዳጅ ዘንድ ያላጽናናው

ማን ነው?(ድርሳነ ሚካኤል፣ ገፅ ሃሮ፰)

ይህ አላባ በአምስቱም መላእክት ድርሳናት ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ስድርሳነ ሩፋኤል በስተ ቀር በሌሎቹ ውስጥ በአሥራ ሁለቱ ወራት ተከፋፍሎ ይገኛል። ነገር ግን ሁሉም በአባሪችን አ ቆጣጠር የወሮች መጀመሪያ በሆነው በመስከረም ወር አይጀምሩም። ሁሉም የሚጀምሩት የመላእክቱ የዓመት ነበረ በዓል የሚከበርበት ቀን በሚውልበት ወር ነው። ለምሳሌ የቅዱስ ሚካኤል ዓመታዊ በዓል የሚከበረው በየዓመቱ ጎንደር 12 ቀን ስለሆነ ድርሳኑም የሚጀምረው በጎንደር ወር ነው። ስለዚህ ድርሳነ ገብርኤል በታኅሳስ፣ ድርሳነ ሁራኤል በጎንደር፣ ድርሳነ ራጉኤ ል ደግሞ በመስከረም ይጀምራሉ። በአብዛኛው በድርሳነ ሚካኤልና በድርሳነ ገብርኤል ውስጥ የ13ኛው ወር ድርሳን በድርሳነ ሩፋኤል ተሸፍኗል፣ የቅዱስ ሩፋኤል በዓል የሚከበረው ጳጉሜ 3 ቀን ስለሆነ።

የየወሩ ድርሳን በመልአኩ የወር በዓል አስት በምእመናን ፊት ይነበባል። ለዚህም ይመስላል የሁሉም ወር ድርሳን ሲጀምር በዚያው ወርና በዚያው አስት እንደሚነበብ የሚናገ ረው።

> በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ዱ አምላክ አሜን።
> ድርሳን በቅዱስ ዑራኤል ሊቀ መላእክት ዘይትነበብ አመ
> ፳ወ፪ኛ ለወርኃ ሚያዚያ ጸሎቱ ወበረከቱ የሃሉ ምስለ ኵበሩ
> ለዓለመ ዓለም አሜን።
>
> አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ
> ስም እናምናለን አሜን። ልመናው በረከቱ ለዘላለሙ
> ከአገልጋዩ ጋር ይሁንና በሚያዝያ 22 ቀን የሚነበብ የሚ
> ጸለይ የመላእክት አለቃ የቅዱስ ሁራኤል ድርሳን ይህ
> ነው። (ድርሳነ ሁራኤል፣ ገፅ ፳፮፭፱)

ከዚህ በኋላ የተለያዩ ጉዳዮችን እያነሱ ማስተማር ይቀጥላሉ። እነዚህ ድርሳናት ስለነዘርስቲያናዊ ሥነ ምግባር፣ ስለኢየሱስ ነዘንስቶስ፣ ስለ ቅድስት ማርያም (ድርሳነ ሚካኤል፣ ድርሳነ ገብርኤልና ድርሳነ ሁራኤል)፣ ስለነዘርስትና እመጣጥና መስፋፋት በኢትዮጵያ(ድርሳነ ሁ ራኤል)፣ ስለኢትዮጵያ ቅዱሳን ነገሥታት(ድርሳነ ራጉኤልና ድርሳነ ሁራኤል)፣ ወዘተ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የተገናዘበ በርዘር ያለ ማብራሪያ የሚሰጡ ሲሆን የድርሳኑን ባለቤት መልአክ ከብር በጥቅል በቀረቡ ተአምራቶቹ በማስደገፍ ያቀርባሉ።

የየወሩ ድርሳናት የሚያስተላልፉትን መልእክት ሲጨርሱ ሲጀምሩ አንዳደረጉት የመልአ ኩን ወይም መልአክ የተራዳውን ቅዱስ ምልጃ በመማፀን ይፈጽማሉ።

> ጸሎቶመ· ወበረከቶሙ ስእስ· ቅዱሳን መስአለተ
> ወስቶመ· እመ ብርሃን ወትንብልናሁ ስቅዱስ
> ገብርኤል ሊቅ ትኩን የሃሉ ምስለ ፍቁሩ
> ለዓስም ዓስም አሜን።
>
> የኒህ የቅዱሳን ጸሎታቸውና በረከታቸው የብርሃን
> አናት ልጃቸውም ልመናና የትጉሃን አለቃ የቅዱስ

ገብርኤልም ልመና ከወዳቹ ጋር ይሁን ለዘላለሙ
አሜን።(ድርሳነ ገብርኤል፣ ገፅ ፱፻፴)

3. ተአምር

አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ (1948:228) ተአምር የሚለውን ቃል እንደሚከተለው ይፈቱታል፡-

ተአምር /ራት/ ... ድንቅ ምልክት፣ እንደ ነቢያት
እንደ ሐዋርያት በእግዚአብሔር ኃይል በክርስቶስ
ስም ካልኾነ በቀር ማንም ሰው ሊሠራው የማይችል
ልዩ ድንቅ ጉድ ብርቅ የኾነ አምላካዊ ሥራ።

ተአምር ማድረግ የሚችለው ፈጣሪ ብቻ ቢሆንም በእርሱ ፊት ሞገስን ያገኙ ቅዱሳን መላእክትና ቅዱሳን ሰዎች በስሙ ተአምራትን የማድረግ ዘኃ ስለተሰጣቸው ተአምራት ያደርጋሉ። እነዚህም ተአምራት በየስማቸው ይጠራሉ፣ ተአምረ ገብርኤል፣ተአምረ ጊዮርጊስ፣ ወዘተ እየተባሉ።

ተአምራት የእግዚአብሔር ኃይል መገለጫ ምልክቶች ናቸው። እነዚህ ምልክቶች በኃይል፣ በሕልም ወይም በድምጽ ይገለጻሉ። መላእክት የአማንያንን ጠላቶች ሲያጠፉ፣ የተናወጠውን ባሕር ሲያረጋጉ፣ የተቸገሩ ምእመናን ከችግራቸው መላቀቃቸውን ሲያበስሯቸውና የታመሙትን ሰዎች በሕልማቸው ፈውሰዋቸው ሲነጋ ጤነኞች እንዲሆኑ ሲያደርጓቸው ይታያሉ።የተአምራትን አጠቃላይ ባሕርይ ዘርቁቱም ቢሆን ስመገንዘብ በአባሪነት የተያያዘውን ተአምር ለአብነት ያክል መመልከት ይቻላል።

ተአምራቱ በድርሳነ ሚካኤል፣ ድርሳነ ገብርኤልና ድርሳነ ውራኤል ውስጥ ከእያንዳንዱ ወር ድርሳን ቀጥሎ ይመጣሉ። ከየወሩ ድርሳን ቀጥለው የሚመጡት ተአምራት ብዛት በአብዛኛው ሦስት ሲሆን አልፎ አልፎ አንድ ወይም አሪት የሚሆንበት ጊዜ አለ። በድርሳነ ራጉኤል ውስጥ ግን ከመጀመሩ መጨረሻ ገፆች ከመልኩ አስቀድሞ ይገኛሉ። የቅዱስ ሩፋኤል ተአምራት አቀማመጥ ደግሞ ከሌሎቹ ለየት ያለ ነው። ድርሳኑ በሚገኝበት መጽሐፍ ውስጥ እንደ አንድ ወር የገባ ከመሆኑም ሌላ በተአምር ይጀምርና ቀጥሎ ድርሳኑን ያስነብባል።

በድርሳነ ሚካኤልና በድርሳነ ገብርኤል ውስጥ ከሚገኙት ተአምራት መካከል የየወሩ የመጨረሻ ተአምራት ከሚነበቡበት ወርና ቀን ጋር ቀጥተኛ ትሥሥር አላቸው። ተአምራቱ የተፈፀሙት በዚያው ቀን ከመሆኑም ባሻገር በመጽሐፈ ስንክሳር ዘዕለቱ ከሚነበቡት ተአምራት ጋር አንድ ዓይነት ናቸው። ከመጽሐፈ ስንክሳር የተወሰዱት ተአምራት ምእመናን በምንም ዓይነት ሥራ ሳይጠመዱ ዕለቱን እንዲያከብሩት ያዛሉ።

ወበእንተዝ አዘዙነ መምህራነ ቤተክርስቲያን
ከመ ንግብር ተዝካረ በዓሉ ለመላእከ ክቡር ሚካኤል
ሊቀ መላእክት አመ ፀሥሩ ወለኑዩ ለለኩሱ
እውራኅ ትጉበልናሁ የሃሉ ምስሌነ ለዓለም ዓለም።

ስለዚህ ዐየወሩ በአስራ ሁለት ቀን የመላእክት
አለቃ የቅዱስ ሚካኤልን በዓለ መታሰቢያ እናደርግ
ዘንድ የቤተክርስቲያን መምህራን አዘውናል።
(ድርሳነ ሚካኤል፣ ገፅ ፪፷፩)

ከነዚህኞቹ በቀር የሌሎቹ ተአምራት በየወሩ መከፋፈል ለንባብ ምቹ ሁኔታ ከመፍጠር ባሻገር ሌላ አላማ ያለው አይመስልም።

የብዙዎቹን ተአምራት መቼት ለማወቅ አስቸጋሪ ቢሆንም በርካታዎቹ ስለክርስቶስ ዐቂሳ መፈፀማቸውን መገመት አያዳግትም። ነገር ግን ድርሳነ ራጉኤል ከብሉይና ከሀዲስ ኪዳን የተወሰዱ አምስት ተአምራትን ብቻ ይዟል። ሌሎችም ድርሳናት ከብሉይና ከሀዲስ ኪዳናትና ከቀኖና መጻሕፍት የተወሰዱ ተአምራትን አካተዋል።

ስመጽሐፍ ቅዱሱ የተወሰዱ ጥቂት ተአምራት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በየትኛው መልኩ ከ አንደተፈበሙ በግልጽ ስለማይናገሩ በድርሳናቱ ውስጥ አንድ ተአምር በሁለት መላእክት እንደተደረገ የሚገልጹ ተአምራት አናያለን። ለምሳሌ ሦስቱ ሕፃናት በመነደል የሚታወቁትን አናንያን፣ አዛርያንና ሚሳዔልን ከናቡከደነፆር እቶን እሳት ያዳናቸው በድርሳነ ሚካኤል ውስጥ ቅዱስ ሚካኤል ሲሆን በድርሳነ ገብርኤል ውስጥ ደግሞ ቅዱስ ገብርኤል ነው። ይህ የሚሆነው ሊቃውንት መጻሕፍትን ከመጻሕፍት አያዋሀዱና አያመሳከሩ በአንድምታ ሊተረጉሙ ሁለት መላእክት የተአምሩ አድራጊ ሆነው ይገኙና የድርሳናቱ ጸሐፊዎች የወደዱትን መልእክ ተአምሩን እንዳደረገ አድርገው ስለሚጽፉ ሊሆን ይችላል። አንደ አለቃ አየሌው ታምሩ (1992)* ትንታኔ ከሆነ አንዳንድ ሰዎች የመጽሐፍ እውቀት ሳይራቸው የቁም ጽሕፈት ስለሚችሉ ብቻ መጻሕፍትን ይጽፋሉ። በዚህም ምክንያት ከግል አመለካከታቸው በመነሳት የአንዱን መልእክ ተአምር ስሌላው ሊሰጠ ይችላሉ። ለምሳሌ አግባብ ባለው ትንተና መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአሪት ዘዳግም ምዕራፍ 22 የሚገኘው ተአምር በቅዱስ ሚካኤል ተደረጎ እያለ በድርሳነ ራጉኤል ውስጥ የቅዱስ ራጉኤል ተአምር ተደርጎ ተመዝግቧል።

ሁሉም ተአምራት ሲጀምሩ አንደሌሎቹ የቤተክርስቲያን መጻሕፍት ስአንባቢው/ለአድማጩ የመልእክቱን ምልጃ ይስምናሉ።

ተአምር ዘገብረ ቅዱስ ዑራኤል ሊቀ መላእክት ጸሎቱ
ወበረከተ፡ የሃሉ ምስለ ገበሩ ሰዓሰም ዓለም።

ልመናው በረከቱ ከአገልጋዩ ጋር ይሁንና የመላዕክት
አለቃ የሚሆን የቅዱስ ዑራኤል ተአምር ይህ ነው።
(ድርሳነ ዑራኤል፣ ገፅ ፱፩፫)

ተአምሩ ተነቦ ሲያበቃም በተመሳሳይ ሁኔታ ለምእመናን ምህረትን በመለመን ያጠቃልላል።

ትንብልናሁ ወሀብተ ረድኤቱ ስቅዱስ ዑራኤል
የሃሉ ምስለ ገብሩ ለዓለም ዓስም።

የቅዱስ ዑራኤል ሀብተ ረድኤት ከአገልጋዩ
ጋር ይሁን ለዘላለሙ አሜን።(ድርሳነ ዑራኤል፣
ገፅ ፱፩፭)

4. አርኪ

አርኪ ባለአምስት መስመር በአንድ ዓይነት ቤት መሃከል ፊደል የሚጨርስ ግጥም ነው። ይህ ግጥም በየወሩ መጨረሻ ባሉት በመላእክቱ ተአምራት ዙሪያ እያጠነጠነና የመልእክቱን ግብር እያሞገስ ለምእመናን ምህረትን ያስምናል። እነዚህ ግጥሞች በድርሳነ ሚካኤል፣ በድርሳነ ገብርኤልና በድርሳነ ሩፋኤል በሁሉም ወሮች ውስጥ ሲገኙ በድርሳነ ዑራኤል ውስጥ ደግሞ በጥቂት ወራት ውስጥ ይገኛሉ።

አርኪዎቹ ከላይ ከመጀመሪያ ስንነሳነር የተጠቀሱ ናቸው ካልናቸው ተአምራት ጋር አብረው የመጡ ሲሆን በድርሳነ ገብርኤል ውስጥ ያሉት በሌሎቹ ውስጥ ካሉት መጠነኛ ልዩነት ይታይባቸዋል። ለምሳሌ ከዚህ በታች እንደምንመለከተው በድርሳነ ገብርኤል ውስጥ የሚገኘው አርኪ ቀኖሱ እንደሚመሰጠው በሌሎቹ ውስጥ እንደሚገኘው ሰላም ዘማለፀ ቃል አ ይጀምርም ወይም ይህንኑ ቃል አይጠቀምም።

ለጢሞቴሥስ ሰማለት አክሊለ ስምዕ ዘነሥአ
ዘበከንፍከ ከለልኮ አመ ውስተ አለት ዘአ
ረዳኤ ማፋጣ ገብርኤል እንበለ ትነሥሥ መርድአ
ያስትአፅብ መንክራቲከ ወጎሩተከ ስመዐ
እምነ ገፋዒ ትባልሕ ኪያየ ማፋዐ።

የሰማዕትነት አክሊል የተቀበለ ሰማዕት ጢሞቴዎስን
ከአለት ውስጥ በገባ ጊዜ በከንፍህ ያዳንክው
ረዳት ላትሻ የተበደሉትን የምትረዳ ገብርኤል ሆይ
ተአምራትህና የታወቀ ቸርነትህ ያስደንቃልና በሚገፉ
የተገፋሁ እኔን ታድናለህ።(ድርሳነ ገብርኤል፣ ፱፻፴፫)

ነገር ግን በሚቀጥለው አርኬ 'ሰላም' የሚለው ቃል ጥቅም ላይ ከመዋሉም ሌላ አርዝሙው ራሱ 'ሰላም' በመባል ይታወቃል።

ሰላም አብል ኪያከ መልእክ፣
ርኁሩኀ ልብ ለኩሉ እንተ ኢኮንክ ድሩክ፣
ሚካኤል ሊቅየ ለለ ዕቤለከ፣
ኀብአኒ በጽላሎትከ ነግሀ ወሰርክ፣
አስመ እምንአስየ አፈርሀ ዘከከ።

የመላእክት አለቃ እንተን ሰላም እላለሁ።
ጨካኝ ያይደለህ ለሁሉ የምትራራ፣
ሚካኤል አለቃዬ ባልሁህ ቁጥር፣
ጥዋት ማታ በረድኤትህ ጥላ ስሥረኝ፣
ከሕዋንኑቴ ጀምሮ ጭቅጭት አፈራለሁና።
(ድርሳነ ሚካኤል፣ ገፅ ፹፰)

አንድ አንድ ጊዜ በቅዱስ ሚካኤል፣ ገብርኤልና ሩፋኤል ድርሰናት ውስጥ ከአንድ በላይ አርኬዎች ይገኛሉ። ይህ የሚሆነው በአንደ ወር ድርሳን ውስጥ ከአንድ በላይ ከመጻሕፈ ሰንዝሰር የተወሰዱ ተአምራት ሲኖሩ ነው። ለምሳሌ ለኒ 12 ቀን ቅዱስ ሚካኤል ለቅዱስ ላሊበላና ለቅዱስ ቁርስዓ ተአምራት አደርጓል። ሁለቱም ተአምራት በዚሁ አለት አንዲነበሩና የቅዱሳኑም በዓላት አንዲከበሩ ታህ ሁለቱንም ተአምራት ተከትለው የመጡት አርኬዎች በቅደም ተራ ቀርበዋል።
በተለይ በቅዱስ ሚካኤል ድርሳን ውስጥ፣ አልፎ አልፎ ደግሞ በቅዱስ ገብርኤል ድርሳን ከየወራቱ ድርሳን መጨረሻ ላይ ከላይ ካነሳነቸው ለየት ያለ አርኬ እናገኛለን። ይህ አርኬ በቅርጹ ሌሎቹን ቢመስልም በይዘቱ የተለየ ነው። አርኬው ደራሲው/አንባቢው ጸሎት እንዲያቀርብ ስለተፈቀደለት አያመሰገነ ይሽው ጸሎት ተቀባይነት እንዲያገኝ ፈጣሪን የሚማጸንበት ነው።

ዘአቅረብኩ ማኅሌተ አዘዚርየ አእላፈ፣
አምአሰ ተዐምዱከ በልፈ፣
ለለ አነብብ ተወከፍ፡ በንዴትየ መጽሐፈ፣
እንተ ረሰይክ እግዚኦ ጸዲቀ መበለተ ውኩፈ፣
አምአሰ አብኡ ብዑሳን ዘተርፈ።

ባለዐጎች ከተረፋቸው ካቀረቡት ወርቅና ብር
ይልቅ የምስኪንዋን መበለት ስጦታ /ቂጣ/
የተቀበልህ ሆይ አቤቱ ባመሰገንኩ ቁጥር የኔን

የምስክሩን ፀሎት ተቀብል።(ድረሳነ ሚካኤል፣ገፅ ፪፻፫)

ይህ አርኬ በድረሳነ ሚካኤል ውስጥ ከጎዳር ወር በስተቀር በሌሎቹ ወራት ውስጥ ከላይ እንደተመለከትነው በዝርዝር ተሰድሮ አናገኘውም፣ ነገር ግን የድርሳኑን አንብቢዎች ወይም አ ድማጮች ይዛንኑ ጸሎት በቃላቸው እንዲደግሙት (እንዲያደርሱት) አስታውሶ ወይም አዞ ያልፋል፣ "ዘአቅረብኩ ግኅሌተ በል" በሚሰት። ይኸው ትእዛዝ በድርሳነ ገብርኤል ውስጥ በመጨረሻው (ጎዳር) ወር መጨረሻ ላይ ይገኛል።

5. መልክአ

ከድርሳነ ገብርኤል በስተቀር ከሁሉም ድርሳናት መጨረሻ ላይ የመልአኩን የተሰያየ የአካል ክፋሎች፣ ጎልተው የሚታወቁ ግብሮችና ሌሎች ነገሮች እየጠራና በምሳሌ እያጣቀሰ የሚያወድስና ምልጃን የሚማጸን ግጥም አለ። ይህ ግጥም መልክአ በመባል ይታወቃል። መልክአ በሚያወድሰው የአካል ክፍል፣ ግብርና ሌላ ነገር ቁጥር ልክ በአንድ ዓይነት ቤት መም ቻ ፊደል የሚጨርሰ አምስት ስንኞች ያሉዋቸው አርኬዎችን የያዘ ግጥም ነው። እነዚህ አርኬ ዎች ሰባሰመልክ የተደረሱ ከመሆናቸው ባሻገር እርስ በርሳቸው ምንም አይነት ግንኙነት ያላቸው አደለመስሉም፣ እርግዮ ከስም ጀምረው በራስ ሀገር ቀጥለው እስከ እግር ጥፍር ድረስና ከዚያም አልፎ በሌሎች ነገሮች የሚቀጥሉ ናቸው። ለአብነት ያክል እንዲሆን የሚከተለውን እንመልከት።

ሰላም ለቀራንብቲክ ዘኢፈቀዳ ንዋመ።
ወለአዕይንቲክ አብያዘ አስ ይሜግባ ዓለመ።
ገብርኤል ጸሐቅ ትጸግወኒ ሰላመ።
ሚካኤልሰ አመ ላዕለ ሙሴ ተሰይመ።
ከፈለ ሰቱ ማየ ባሕር ግሩመ።

ገብርኤል ሆይ ዕንቅልፍ ለማይፈታቱናቸው
የዓይኖችህ ሽፋሽፍትና ዓለምን በብርሃነቸው
ለሚያገለግሉ ከዋክብት ዓይኖችህ ሰላም አላለሁ።
ገብርኤል ሆይ ሚካኤል ለሙሴ ጠባቂ
ሆኖ በተሾመ ጊዜ ታላቁን የኤርትራ ባሕር
ከፋሱ አንዳሻገረው እንተም ሰላም ትሰጠኝ
ዘንድ ትጋ። (ድርሳነ ገብርኤል፣ ገፅ ፲)

መልክአ በአብዛኛው በንባብ፣ በቃል በመድገምና በዜማ ለጸሎት አገልግሎት ይውላል። በተ ጨማሪም በባሰመልክ መልአክ የወር በዓል አስት በቃል የሚደረሰ ሲሆን በዓመት ክብሩ ደግሞ በክራል በቃል በክራል ደግሞ በዜማ ይባላል። ይህ የግዕዝ ግጥም ዓይነት ከእግዚአብሔር አብ ጀምሮ ለቅዱሳን ሁሉ የተደረሰ ነው፣ ከሁሉት በላይ መልክአመልክአ የተደረሰላቸውም አሉ።

ማጠቃለያ

ከላይ እንደተመለከትነው ድርሳናተ መላዕክት የሀይማኖታዊ ትምህርቶች፣ መነሻና መድረሻ ያላቸው ትረካዎችና ግጥሞች መድበል ናቸው። እነዚህም ሆኑ ሌሎች ጥንታዊ ጽሑፎች በአፀፋትና በዝርዝር ቢጠኑ ለዘመናዊው ሰነጽሑፍ ያበረክቱት ወይም የሚያበረክቱት አስተ ዋጽኦ ሊታወቅ ይችላል።

የስነጽሑፍ ተማሪዎችም ሚዛናዊ (objective) በሆነ ዘዴ የመጻሕፍቱን ባህርያት ከአ ውዳቸው ሳይነጥሉ የማጥናት ባህል አዳብረው የስነጽሑፍ ታሪካችን ትክክለኛ ገጽታ እንዲፈጠር ለማድረግና ባልተዛባ መሰረት ጽፎ ለማሰቀረት ይህ መስክ ገና ያልተነካ የጥናትና ምርምር አ ቅጣጫ መሆኑን ሊገነዘቡ ይገባል።

ዋቢ መጻሕፍት

አያሌው፡ ታምሩ (አለቃ)፣(1992)፣ *ቃለመጠይቅ*፣ አዲስ አበባ ::

አክሊለብርሃን ወልደቂርቁስ (ሊቀጠበብት)፣ (1945)፣ *መርሐ ልሳን*፣ አዲስ አበባ ::

እንግዳው መሰናዓለም፣(1982)፣ "*የድርሳነ ሚካኤል* በአንጽሑፍ *መመዘኛ* መስፈርቶች ሲለካ"፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ስኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ት/ክፍል የቀረበ ዲማጽ::

ግርማ ዘነበ፣ "ስነጥበባዊ ሁኔታዎች በ*ድርሳነ ዑራኤል* ውስጥ"፣ ለ9ኛው የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም ጉባኤ የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (1991) ::

ድርሳነ ራጉኤል፣(1982)፣ አዲስ አስባ፣ ተስፋ ማተሚያ ቤት::

ድርሳነ ሚካኤል፣ (1969)፣ አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ማተሚያ ቤት

ድረሳነ ገብርኤል፣(1969)፣ አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ማተሚያ ቤት *ድርሳነ ዑራኤል*፣ አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ማተሚያ ቤት

ኪዳነወልድ ክፍሌ (አለቃ)፣ (1948)፣ *መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሀዲስ*፣ አዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት ::

መጽሐፍ ቅዱስ፣ (1980)፣ *የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት*፣ አዲስ አበባ፣ ብዙሃንና ስላም ማተሚያ ቤት ::

አባሪ

የቅዱስ ዑራኤል ተአምር

(ድርሳነ ዑራኤል፣ ገፅ 158)

ተአምር ዘገብረ ቅዱስ ዑራኤል ሊቀ መላእክት ጸሎቱ ወበረከቱ የሃሉ ምስሶ ንብሩ ለዓለመ ዓለም አሜን።

ጸሎቱና በረከቱ ከአንልጋዩ ጋር ለዘላላሙ ይሁንና የመላእክት አለቃ ቅዱስ ዑራኤል ያደረገው ተአምር ይህ ነው።

ወሀሎ ፩ዱ ብእሲ እዴሁ ወያወድቆ ጋኔን ዘልፈ በበክሉ ዕሰት።

እጁ ሽባ የሆነና በየእለቱ ጋኔል የሚጥለው አንድ ሰው ነበር።

መበእሀተ ዕለት ቦአ ውስተ ቤተክርስቲያና ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ በዕለተ በእሱ ለቅዱስ ዑራኤል ሊቀ መላእክት ወሀሎ ኅልለ በዓል ምስሌሁ ዘአብዓለ ደቅስዮስ ኤጲስቆጶስ ዐየ ሰገደ ወአስተብረከ ታሕተ ሥዕሉ ለቅዱስ ዑራኤል ወውስቱ ድውይ እንዘ ይበኪ ወይላሁ ብኪየ መሪረ በእንተ ጻማሁ ወሕማሙ።

ከዕለታት በአንድ ቀን ኤጲስቆጶሱ ደቅስዮስ በተ ጩማረ ያከበረው ሱላ በዓል ስለነበር በሽተኛው በመላእክት አለቃ በቅዱስ ዑራኤል በዓል ቀን አ ምላክን ወደ ወለደች ወደ እመቤታችን ድንግል ማርያም ቤተክርስቲያን ሄዶ ለቅዱስ ዑራኤል ሥዕ ል በታች በጉልበቱ እየሰገደ ስለበሽታውና ስለድካሙ አምርሮ ያለቅስ ጀመር።

ወውእቱ ጊዜ መጽአ ቅዱስ ዑራኤል በዓቢይ ግርማ እኂዞ ሰይፈ በእዴሁ።

ያን ጊዜ ቅዱስ ዑራኤል ሰይፉን እንደያዘ በታላቅ ግርማ መጣ።

ወሶበ ርእዮ ጋኔኑ ደንገፀ መፈርሐ ወወድቀ ውስተ ምድር ወአጋዞ ቅዱስ ዑራኤል ለውእቱ ጋኔን ቀሠፎ ወዘለጦ ገሃደ።

ጋኔሉም ባየው ጊዜ ፈርቶ ደነገጠና በምድር ላይ ወደቀ። ቅዱስ ዑራኤልም ያንን ጋኔል ይዞ በግልጽ ገረፈው። ደስደበው።

ወጸኒሖ ንስቲተ ይቤሎ ለውእቱ ጋኔን እንከሰ ትበውእኑ ኀቤሁ ከመ ትግቅዮ ለዝንቱ ብእሲ።

ትንሽ ቆይቶም ጋኔሉን ከእንግዲህ ወዲያ ይህን ሰው ታሰቃየው ዘንድ ሁሉተኛ ትመለስበታለህን? አለው።

ወይቤሎ ውእቱ ጋኔን እንክሰ እይትመየጥ ያም ጋኔል ከእንግዲህ ወዲህ ወደዚህ ሰው ብመለስ

ኅቡሀ መቅሠፍትክ ወመቅሠፍተ አምላክክ ይኩን ዘልፈ በላዕሌየ ሰዓለም። የእምላክህና ያንተ ቅጣትና መቅሰፍት ለዘላለሙ በኔ ላይ ይፈጸምብኝ አለው።

ወእምድኅረ ዝንቱ ይቤሎ ቅዱስ ዑራኤል ለውእቱ ብእሲ ንግር አርኢክ ተአምረ ዘከመ እድኃነክ እግዚአብሔር ወዘንብረ ሰክ። ከዚህ በኋላ ቅዱስ ዑራኤል ያን ሰው ያየኸውን ተአምርና እግዚአብሔር ያደረገልህንም ሰህሱም ሰው ተናገር አለው።

ወወፂአ እምውስተ ቤተክርስቲያን ሖረ ወነገረ ለኩሉ ሰብእ ለአዝማዲሁኒ ወለአርኅኒሁ ዘንብረ ሎቱ ቅዱስ ዑራኤል ሊቀ መላእክት። ሰውየውም ከቤተክርስትያኑ ወጥቶ ለወዳጆቹ ሰዘመዶቹና ለሰው ሁሉ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ዑራኤል ያደረገለትን ተአምር ተናገረ።

ወበእንተ ዝንቱ ስብኤም ወአዕኮም ለእግዚአብሔር። ይሄንን ነገር የሰሙ ሁሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

ወእምድኅረዝ ነበረ ውእቱ ብእሲ በፍሥሐ እንዘ ይትለአክ ለቤተ ክርስትያኑ ሰቅዱስ ዑራኤል ሊቀ መላእክት በኩሉ መዋዕለ ሕይወቱ። ስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ማርያም ለዓለመ ዓለም አሜን። ከዚህም በኋላ ያ ሰው ህይወቱን ሙሉ የመላእክት አለቃ የቅዱስ ዑራኤልን ቤተ ክርስቲያን በደስታ ሲያገለግል ረ። ለእግዚአ ብሔርና ለእናቱ ለድንግል ማርያም ምስጋና ይሁን ለዘላለሙ አሜን።

ጸሎቱ ወረድኤቱ ሰቅዱስ ዑራኤል የኅሰ ምስለ ንብሩ ለዓለም ዓለም አሜን። የቅዱስ ዑራኤል ጸሎቱና በረከቱ ከእነልጋዩ ጋር ይሁን ለዘላለሙ አሜን።

የመልክአ መልክአ ልዩ ልዩ ባሕርያት

ገዛኸኝ ጌታቸው
P.O.Box 170285
Addis Ababa, Ethiopia
Email– gczageta@yahoo.com
Tel. 09/219998



አቶ ገዛኸኝ ጌታቸው ቀናታቸውን ሲያቀርቡ

1. አጠቃላይ ባሕርያት

1.1 መልክአ ምንድን ነው?

«መልክአ» የግእዝ ቃል ሲሆን ለክአ ከሚለው ግስ የወጣ ነው። አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ «ለክአ» ማለት «ጣፈ፣ ዐተመ፣ ሣለ፣ መሰለ፣ መልክ አወጣ፣ በቀለመ በቅርጽ» /1948፣ 565/ ነው በማለት «መልክአ»ን «በቁሙ ፣ መልክ፣ ገጽ፣ የፊት ቅርጽ፣ ሥዕል፣ ምስል፣ ልክ ያለው፣ በልክ የተሠራ» /1948፡566/ ሲሉ ይፈቱታል። ስለዚህ መልክአ ለግዙፍ ነገር ማለት ለለምኞች ወይም ለእንስሳት የሚነገር ይሆናል፡ ብዙ ቁጥሩም መልክአት ነው።

ሌላውና ለዚህ ጽሑፍ ተስማሚው የቃሉ ፍቺ ለግእዝ የሥነ ግጥም ዓይነት የተሰጠ ስም መሆኑ ነው። በቤተ ክርስተያን ሊቃውንትም ሆነ በዘመናዊ ምሁራን የተሰጡት ፍቺዎች አሚልተው ያልያዙት ነገር ያለ ይመስለኛል። ከሁለቱም ከፍሎች ሁለት ሁለት ፍቺዎች እንመልከት።

ኪዳነወልድ ክፍሌ /1948፣566/ መልክአ «የድርሰት ሰም ፣ የመልክ ሙሳኤና መዝሙር፣ ከራስ ጠጉር እስከ እግር ጥፍር የሚቆጥር» ይሉታል። ይህ ፍቺ በብዙ የቤተ ክርስቲያን ሆነ ዘመናዊ ሊቃውንት ተቀባይነት ያገኘ ነው። አለቃ አያሌው እነዚህን ግሮሞች «የባለመ ልክኡን መልክ ከስሙ በመጀመር ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ድረስ በቅደም ተከተል በስንኝ የሚያመሰግኑ ናቸው» /1992/ ይላሉ። እንደ አለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ የአለቃ አያሌውም ፍቺ የመልክእን ዋና ዋና ባሕርያት ግለት ገላጭ መሆኑን፣ የሰውነት አካላትን መዘርዘሩን፣ ምስጋና መሆኑንና በስንኝ መጻፉን ይጠቅሳሉ። በነዚህ ሁለት ፍቺዎች መካከል ያለው ልዩነት የመልክእን የምስጋና መጀመሪያ ክፍል በመጥቀስና ባለመጥቀስ ነው።

ፖላንዳዊው ምሁር እሌክሳንደር ፈሬንክ /1985፣283/ መልክእን ሲፈታው «የባለመልክኡን የተለየዩ የሰውነት አካላት በአብዛኛው ከራስ ጀምሮ እስከ እግር ድረስ የሚያመሰግን ገላጭ ግጥም ነው» ይላል። ይህ የፈሬንክ ፍቺም ከላይ ከጠቀስናቸው የቤተ ክህነት ሊቃውንት ፍቺዎች ጋር የተመሳሰለ ነው፤ ከጥቂት ልዩነቶች በቀር። ፈሬንክ መልክእ የሚጀምረው ከራስ ነው በማለት ስምንና ፀጉርን ሳይጠቅስ ያልፋቸዋል። ሌላው ሀርደን /1926፣29/ የተባለ ምሁር «መልክእ የእያንዳንዱን ቅዱስ የሰውነት አካል እየዘረዘረ በእንዳንድ አርኬ የሚመሰገንበት መዝሙር ነው» ይላል። ይህ ፍቺ የሰውነት አካላት በቅደም ተከተል ስለመመሰገናቸው እይናገረም። እርግጥ ብዙ አርኬዎች ያሉት መሆኑን ይጠቅሳል፤ አንድ አርኬ ለአንድ የሰውነት ክፍል በማስት ከመሳሳቱ በተጨማሪም መልክእ የሚጸፍላቸው ቅዱሳን ብቻ እንደሆኑ ያስመስላል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የመልክእ ፍቺዎች በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ባለመልክእቹ የተለያየ ብልቶች ያሰው ግዙፍ አካል ያላቸው እንደሆኑ ይጠቅሳሉ። ግዙፍ አካላት የሌላቸው መልክእ የተጸፈላቸውም እሱ። ከእነዚህ ግዙፍ አካል ሳይኖራቸው መልክእ ከተጸፈላቸው ውስጥ ንዋያተ ቅድሳት፣ የጸሎት መጻሕፍት እና ልዑል እግዚአብሔር ይገኙበታል። ሰምሳሰ. ያህል ጠቢበ ጠቢባንን፣ መልክእ መስቀልን፣ መልክእ ሰንበትን፣ መልክእ አንቀጸ ብርሃንን መጥቀስ ይቻላል።

ስለዚህ መልክእ ማለት የባለመልኩን የሰውነት አካላት እና/ወይም ሌሎች ነገሮችን በ ማመስገን ምሕረትን የሚለምን ባሰፋዙ አርኬዎች የምስጋና ግጥም ነው። መልክእ የሚጸፍላቸውም መለኮት፣ ሰዎች፣ መላእክት እና ግዑዝ ነገሮች ወይም ረቂቅ ሀሳቦች ሊሆኑ ይችላሉ። መለኮት ሲሆን ሥላሴ እና ሦስቱ አካላት፣ ሀያዋን ሲሆኑ መላእክትና ጻድቃን፣ ግዑዝ ነገሮች ሲሆኑ የጸሎት መጻሕፍት፣ ንዋያተ ቅድሳት፣ በዓላትና የመሳሰሉት፣ ረቂቅ ሀሳቦች ሲ ሆኑ ፍቅር፣ ባህርይ፣ ጠባይና የመሳሰሉት ሆነው እናገኛቸዋለን።

በመልክኡ የሚጸልየው ሰው በእንደኛ መደብ እኔ እያለ ሲሆን በትሕትና ምሕረትንና ሌሎች እርዳታዎችን በኩለተኛ መደብ ከተጠቀሰው ከዘለመልክኡ ይሰምናል። በቤተ ክርሰቲያን መልክእ ድርሰት ተብሎ የሚጠቀስ ሲሆን ፀሐፊውም ይራሲ ይባላል። በተጨማሪም የመልክእ ጸሐፊዎች ለመልክእ የተሰያየ ስም ሰጥተውት ይገኛል- በመልክኡ ውስጥ። ለምሳሌ. በመልክእ እስጢፋኖስ ስላመ መልክእ /አርኬ] ፣ በመልክእ ሰንበት ድርሰት /አርኬ 16/ ፣ በመልክእ ሰንበት ዝግራ /አርኬ 10፣ በመልክእ ዮሐንስ መጥምቅ ማኅሌት ሥም አርኬ 27 በመልክእ ኡራኤል ቀዳሚት ሙዳሴ አርኬ] ፣ በመልክእ ኢያቄም ወሐና ደግሞ መዝሙር /አርኬ 11/ ተብሎ ተጠቅሷል። መልክእ የተባሰው ግጥም ብዙ ቁጥሩ መልክእ መልክእ ነው። መልክእት የሚለው ብዙ ቁጥር ሰሰሙነት አካላት የሚያገለግል እንጂ ለግጥሞቹ

አይደለም።

በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ክርስቲያኖች ዘንድ መልክአ መልክአ ከባለመልክኡና ከእግዚአብሔር ጋ ጋር የሚያገናኝና ጸሎት እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል። በመልክአ መልክአ ውስጥ የሚነሡት ነገሮች ምስጋና፣ ንስሐና ልመና በሚሉ ዘርፎች የሚከፈሉ ናቸው። እነዚህ ግጥሞች የያዙዋቸው ሥነ ሥነ ጉዳዮች ባለመልክኡን ማመስገንና ምሕረትን መለመን ናቸው። ደራሲዎቹ አካላትን በሚገልጹበት ወቃ የባለመልክኡን ሕይወትና ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከአዋልድ መጻሕፍት ታሪክን፣ ሁኔታንና ባለታሪኮችን ይጠቀማሉ።

ስላሙ መልክኡ ለቂርቆስ ወለኢየሉጣ እባሉ
ናሁ ጸሐፍኩ እንዘ አስተዋድኦ አምነ ገድሉ
ባርኪ ሊተ ማርያም እግዘእቲ ኩሉ
ወረሲ በዲበ ምድር ብሩክ ውእቱ በላዕሉ
ወዘቀደሰኪ ለዓለም ይሄሉ

/መልክአ ቂርቆስ፣ አርኪ 47/

በሁለተኛው ስንኝ በግልፅ አንደተጠቀሰው ገጣሚው ከቅዱስ ቂርቆስ ገድል አያወጣጣ እንደጻፈ ይገልፁል።

መልክአ መልክአ በትኩረት ቢነበቡ ሃይማኖታዊ ዕሙቀትንም የሚያስፉ ናቸው። እነኩን ለመረዳትም መጽሐፍ ቅዱስንና የባለመልክኡን ታሪክ ማወቅ ያስፈልጋል። የቤተ ክርስቲያንንም ዋና ዋና መመረያዎች ሰመረዳት ይጠቅማሉ። ከመልክአ አማኑኤል ምሳሌ ልጥቀስ፡

በሠሊዳ ዝንቱ ልብየ አምጣነ ለመንክር ተጽሕፈ
ፈደሰ አሐዱ ፍቅርከ እንተ ኢኮነ ግዱፈ
አማኑኤል ክናኒ ግዕስክላተ ሠጽንፈ
ከመእንብብ ቅድመ ጉባኤ ነገረ ሥጋዌከ ዘልፈ
እግዚአብሔር ዘበኒ ጥበበ ወአፈ
/አርኪ 1/

ይህ አርኪ በግልፅ እንደሚያሳየው የገጣሚው ዓላማ ምሥጢረ ሥጋዌን በጉባኤ ፊት መናገር ነው፡ ምሥጢረ ሥጋዌ ከዚኑ ክርስቲያን አዕማደ ምሥጢራት አንዱ ነው።

መልክአ መልክአ አእምሮን በሃይማኖታዊ ዕሙቀት ከመገንባት ይልቅ በባለመልክኡ ተአምራትና በማመለድ ኃይሉ የአንባቢው ልቡና ወደ እግዚአብሔር እንዲመሰጥ ያደርጋል። የደከመ /ያዘነ/ መንፈስን በማበረታታትና ጸሎተኛው ባለመልክኡን በቀጥታ አንተ እያለ ከባለመልክኡ ጋር በአካል ተገናኝቶ የሚነጋገር ያህል እንዲሰማው ያደርጋል። መልክአ መልክአ ጸሎት ሲሆን ምስጋና፣ የንጠሰትን ኑዛዜና ምሕረት እና ልመናን የያዘ ግጥም ነው።

1.2 መልክአ መልክአ የተጀመረበትና የቆመበት ዘመን

መልክአ መልክአ የተጻፉበትን ዘመን መናገር አይቻልም። መልክአ መጻፍ

የተጀመረበትንም ጊዜ በእርግጠኛነት ሥናገር አይቻልም። እኔ እስከማውቀው ድረስም መልክአ የተጀመረበትን አርግጠኛ ጊዜ የተናገረ ተመራማሪ የለም።

መልክአ መልክአ መደረስ የጀመሩበትን ሳይሆን በስፋት የተጻፉበትን ዘመን 17ኛው ምእተአመት የሚያደርጉ አሉ /ፈሬንክ፣ 1985፣285/፣ ዓለማየሁ ሞገስ /1952:4/ ወደ 14ኛ ምእተ አመት ይወስዱታል። እንደ ፒደርሰን /1989:557/ ያሉት ደግሞ መልክአ እስከ 17ኛ ምእተ አመት ድረስ አንጻልተጀመረ ይናገራሉ። የዚህ ሁሉ ልዩነት መነሻው ድርሰቶቹ በተጻፉበት ብራና ላይ ጊዜን የሚጠቁም ምንም ነገር አለመገኘቱ ነው።

እግዚአብሔር መልክ አለው ወይስ የለውም የሚለው ጉዳይ በአዲ ዘርዐያዕቆብ ጊዜ ያወዛገበ ነገር ነበር /ሩንግሬን፣ 1982፣59/። ደቀ እስጢፋ የተባሉ የድንግል ማርያምን፣ የመላእክትን፣ የቅዱሳንንና የጻድቃንን ከእግዚአብሔር የማማለድ ጉዳይን የልተቀበሉት በዚያው ዘመን የተነሡ ነበሩ። እነዚሁ ሰዎች ለቅዱሳንና ለሥዕል አድነኖ ክብር የሚሰጠውን ስግደትም ይቃወሙ ነበር። ይህ የደቀ እስጢፋ እንቅስቃሴ በቤተ ክርስቲያን ኑፋቄ ነው ተብሎ በንጉሡ ፍርድ የከፋ ቅጣት ተፈጽሞባቸዋል።

ይህ ውዝግብ በኔ ግምት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትን የምልጃን ኃይልና ለቅዱሳንና ለሥእሉ፦ቻቸው መሰገድ የሚያረጋግጡበትን አዳስ የግእዝ ግጥም ስልት እንዲያሰገኙ ግፊት ሆቸዋል። ይህ መሳምት እውነት የሚመስለው በዚያ ዘመን ይህን ኑፋቄ የሚቃወሙ ብዙ ሃይ ማኖታዊ ጽሑፎች በመውጣታቸውም ነው። የሚከተለው አርኬ የዚህን ኑፋቄ ችግር ያነሳል።

ሰላም ሰላም ለመልክአ ሥዕልኪ ኩሉ
እምን በሐይ መወርጎ ዘያበርህ ሥነ በጻሉ
ጠበእንተዝ ማርያም ሰብእ ቤትኪ ይብሉ
ሰብሐት መክብር መሰጊድ ለመንግሥትኪ ይደሉ
ማርያም በረከትኪ ምስሌነ የሀሉ።

መልክአ ሥዕል፣ አርኬ 23/

ይህ አርኬ ለቅድስት ድንግል ማርያም መስገድ ተገቢ መሆኑን ይናገራል። የሚከተለውም ሰንኝ ይህንኑ ኑፋቄ በቀጥታ ያወግዛል።

ሰላም ለማርያም ዘጽፈ ወልድ ዋሕድ
ወ መንበረ ሕያው ነድ
ለድንግልናሃ ይደሉ ሰጊድ
ለማርያም ዘይቤ ኢይሰግድ
ሞጸፈ መብረቅ በሊኅ በርእሱ ለይረድ

/መልክአ ሥዕል ጻግሚት፣ አርኬ 1/

በተጨመሪም፦

እሰግድ ቅድመ ማርያም ለዝክረ ስምኪ ብጽዋኤ
ወእሰግድ ካዕበ ለድንግልናኪ ክልኤ

ወእሰግድ ሥልሰ ለሥዕልኪ እሥሪጸ ምግዒ

በሥጋሁ ወበነፍሱ ኢይርከብ ትንሣኤ
/መልክአ ሥዕል ዘበዓለ ሃምሳ፡ አርኪ 20/

ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸው ሦስት አርኪዎች የስግደትን ተገቢነትና ስግደትን መቃወም ኑፋቄ እንደሆነ ብሎም አለመስገድ ትንሣኤን እንደማያስገኝ ሚያስረዱ ናቸው።

ሴላው ይህን መላምት የሚደግፈው በየገድላቱ መጨረሻ ወይም መጀመሪያ መልክእን መጨመር ልማድ መሆኑ ነው። ገድላት በአፄ ዘርዐያዕቆብ ዘመነ መንግሥት መጻፍ እንደተጀመሩ ይነገራል /አምሳሉ፣ 1976:54/። ስለዚህ መልክእም በዚያው ጊዜ መገጠም ጀመሮ ሊሆን ይችላል።

መልክእ መጻፍ ያቆመበት ዘመንም እንደዚሁ በግልፅ አይታወቅም። መልክእ መጻፍ ያቆመበትን ዘመን በመመርመር ጉዳይ ላይ ሁለት ነጥቦች መነሣት አለባቸው። አንደኛ ባለመልክእ /መልክእ የሚጻፍላቸው ቅዱሳን/ መጥፋት የጀመረው መቼ ነው? /አሁን መልክእ ያልተጻፈለት ጻድቅ አይኖኝምና/ ሁለተኛው ደግሞ ስቀደሙ ቅዱሳን መልክእ መጻፍ ያቆመው መቼ ነው? ሁለቱንም ጥያቄዎች ለመመለስ ከባድ ነው።

በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እንደ ጻድቅ ተቆጥሮ መልክእ እንዲጻፍ ቅድሳኑ በአጸደ ሕይወትም በአጸደ ነፍስም እያሉ ተአምራት ማድረግ አለባቸው። አለቃ አያሌው ታምሩ /1992/ እንደሚሉት **ዛሬ በአጸደ ሥጋም** በአጸደ ነፍስም ሆነው ተአምራትን የሚያደርጉ ቅዱሳን የሉም። ይህ ማለት መልክአ መልክእ የሚጻፍላቸው ቅዱሳን የሉም ማለት ነው። ለቀደሙት ቅዱሳን ደግሞ መልክእ መልክእ መጻፍም የሚያበረታታ አይደለም። በተለያየ መንገድ ቀድመው የተጻፉት በአሉበትነት ተቀባይነት አግኝተዋልና። እኔ ያገኘሁዋቸው በቅርብ የተጻፉ መልክአ መልክእ ምድራውያን ስሆኑት ለቀድሞው ንጉሠ ነገሥት ለአፄ ኃይለሥላሴና ለባለቤታቸው ለእቴጌ መነን የተጻፉት ሲሆኑ በቅርቡ ፓትርያርኩን ፊሴምሮ ስሌሎች አንዳንድ ጳጳሳት የተጣፉ ጥቂት መልክአ መልክእም ይኖሱ። በዚህ ዘመን ከነዚህ ሴላ የተጻፈ መልክአ ሳይኖር ይችላል።

መልክአ መልክእ መጻፍ የጀመሩበትንና ያቆሙበት ዘመን የብራናዎቹን ጥልቅ ጥናት የሚሻና የመልክአቹን ታሪክ ማጥናትን የሚጠይቅ የምርምር መስክ ነው። የለም አዞንም መልክአ መልክእ እየተደረሱ ናቸው በማለትም ሴላ ተቃራኒ አቋም ይህ ለመመረመርም ክፍት ይመስለኛል።

1.3. ደራሲ

የሁሉም መልክአ መልክእ ደራሲዎች /በአብዛኛው/ አይታወቁም። እያንዳንዱ የመልክእ ደራሲ በድርሰቱ ውስጥ የራሱን የተለየ የአጻጻፍ ስልት ስለማይጠቀም ይህ ጉዳይ ብዙም ችግር አይሆንም። ሥነቃል ደራሲው አይታወቅም፣ ደራሲያቸውን ስመለየት ያስቸገሩ ብዙ ድርሰቶችም በዓለማችን ይገኛሉ፣ ነገር ግን መልክአን ልዩ የሚያደርገው ደራሲያቸው የራሳቸውን ልዩ ስልት ሳይጠቀሙ ራሳቸውን ሆን ብለው ያልጠፉት በመሆናቸውና ነው። በመልክአ መልክእ ደራሲዎቹ ሆን ብለው ራሳቸውን ያልገለፁ በመሆናቸውና እንደጸለዩት የሚያገለግሉ

በመሆናቸው ዋጋ የሚሰጣቸው በግጥሙ ጥራትና በደራሲው ማንነት ሳይሆን በባለመልክኡ ክብር ነው።

የመልክአ መልክእ ደራሲያን እንደ ባለቅኔዎች አካባቢን በመከታተልና በምናብ ምጥቀት አይታወቁም /አያሌው ፣1992/ እንደ ተማሪና ጥሩ መናገር/መጻፍ እንደሚችል ሰው እንጂ። የመልክኡ ክብር በደራሲው ታላቅነት ሳይሆን በባለመልክኡ ታላቅነት ነው። በመልክአ መልክእ ውስጥ የሠፈሩት የአንድን ሰው ስሜት የያዙ ሳይሆኑ ለሁሉም ሰው የሚሆኑ ምስጋና፣ ኑዛዜና ምሕረት እና ልመናን የያዙ ናቸው።

የመልክአ መልክእ ደራሲያን የአጻጻፍ ልማድን ተከትለው የሚጽፉ ናቸው። ደራሲያኑ የሚጽፉበት ርእሰ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የአጻጻፍ ስልቱም፣ የሚይዙት ስሜትም ተወስኖ የተሰጣቸው ነው። እንድ ጊዜ የአጻጻፍ ስልቱ ካደገ በኋላ የመልክአ ቅርፅ እንደ ሕግ ተይዞ ተከታዮቹ እንዲከተሉት ሆል። ስለዚህም ግላዊ የሆነው ስሜታቸው በሚጽፉት መልክአ ውስጥ ሊገለጽ አይችልም። ዋና ጉዳያቸው ያጻጻፍ ሥርዓቱን ተከትለው መጻፍ ነው። በአጠቃላይ መልክአ መልክእ ግልጽ የአጻጻፍ ስልት ያለው የአካላት ገለጻ ነው። ስለዚህም ሊነበቡ የሚገባቸው በ ማስተዋል ነው።

መልክአ መልክእ ለጸሎትነት የሚያገለግሉ ግጥሞች ናቸው። ምሕረትን የሚሰምኑትም ደ ራሲዎቹ ብቻ ሳይሆኑ ጸሎተኛው ራሱን በደራሲው ቦታ ተክቶ እኔ እያለ በመናገሩ ነው። ይህ ራስን በደራሲው ቦታ ማስቀመጥ ደራሲውን ከአንባቢው አእምሮ ያርቀዋል። ይህም ጸሎተኛው የሚያቀርበው የምስጋናና የልመና ጸሎት የራሱ አድርጎ እንዲቆጥር ያደርገዋል። ይህን የሚያስረዳ ምሳሌ ልስጥ።

ማኅበረ ምእመናን ወምእመናት እለኪያክ ተእመኑ
ለኃጢአ ሥጋክ ወትረ ኀበ ተዐየኑ
ወልደ እብ ክርስቶስ ዘኢትትፈለጥ እም ሕፅኑ
እስብክ ለሙ ሕማመክ ወመስቀልክ እዜኑ
ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ሰ,ተ እመሰማይ ፈኑ።

/መልክአ ቁርባን፣ እርኬ 1/

ይህ ግጥም የሚደገመው በካህናት ሲሆን ካህኑ ሁሉ ራሱን በደራሲው ቦታ እንዲተካ የሚያደርግ ነው።

1.3 ባለመልክኡ

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ባለመልክእ ማለት መልክኡ የተጻፈለት ቅዱስ ወይም ሌላ ነገር ማለት ነው። የተለያዩ ባለመልክእ መልክእ ያሉ ሲሆን በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ኡፊት ቦታ ተከፍለዋል።

ሀ. እግዚአብሔር

ለእግዚአብሔር /ሥላሴ/ የተጻፉ መልክእ መልክእ አሉ። ለምሳሌ **መልክኡ እግዚአብሔር**

እብ፣ ጠቢበ ጠቢባን፣ መልክአ ጸራቅሊጦስና መልክአ ሥላሴ ይጠቀሳሉ።

ለ. መላእክት

ለመላእክት የተጻፉ ብዙ መልክአ መልክአ አሉ። እነዚህን ለሁለት መክፈል እንችላለን፤ በወል ስም የተጻፉና ለእኔ ብይ የተጻፉ። የወል ስም ለተሰጣቸው መላእክት የተጻፉ እንደ መልክአ ኩቅቤ መልአክ እና መልክአ መላእክት ያሉ፣ እኔ ብይ ለሆኑ የተጸውኦ ስም ላላቸው መላእክትም በስማቸው መልክአ መልክአ የተደረሰላቸው ሲሆን ለምሳሌም መልክአ ሚካኤልንና መልክአ ጉብርኤልን መጥቀስ ይቻላል።

ሐ. የሰው ልጅ

ለቅዱሳን ለሰማለታትና ለጻድቃን የተጻፉ ብዙ መልክአ መልክአ አሉ። እነዚህም ባለመልክአ መልክአን እንደላይኛው ለሁለት መክፈል እንችላለን። የወል ስም ያላቸው እንደ መልክአ ሰማለታት፣ መልክአ ነቢያት፣ መልክአ ጻድቃን፣ መልክአ ሠለስቱ ምእትና የመሳሰሉት ናቸው። እኔ ብይ የተጸውኦ ስም ለተሰጣቸው የተጻፉ መልክአ ጊዮርጊስ፣ መልክአ እጸም፣ ... ከዚህም በተመጨማሪ በዜተክርስቲያን ጻድቅ ናቸው ተብለው ላልተከበሩ ነገሥታትም መልክአ ተደርሰላቸዋል። መልክአ አፄ ቴዎድሮስ፣ መልክአ አፄ ዮሐንስ፣ መልክአ ምኒልክና የመሳሰሉት።

መ. ረቂቅና ሕይው ያልሆኑ

ለረቀቁ ሀሳቦችና ሕይው ላልሆኑ ግዑዝ ነገሮች መልክአ መልክአ ተጽፎ እናገኛለን። ረቂቅ ሀሳቦች ማለት እንደ ፍቅር፣ ብሥርይና ጠባይ ሲሆኑ ለነዚህ መልክአ ፍቅር፣ መልክአ ብሥርይ፣ መልክአ ጠባይ፣ መልክአ ስንክት የሚሉ መልክአ መልክአ ተጽፈውላቸዋል። ሕይው ያልሆኑ ነገሮች ያልኪቸውም ንዋየ ቅድሳት፣ የጸሎት መጻሕፍትና የመሳሰሉት ሲሆኑ በዚህ ክፍል መልክአ አንቀጸ ብርሃን፣ መልክአ ሥዕልና መልክአ ቤተ ክርስቲያንን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል።

እንዳንድ ባለመልክአ ግዙፍ አካልና ስብእዊ መልክአ ባይኖራቸውም እንዳላቸው ተደርጎ በሰውኛ ተጽፎላቸዋል። ለምሳሌ መልክአ ቤተ ክርስቲያን፣ መልክአ ፍቅር እና መልክአ ሰንበት የሰው አካል እንዳላቸው ተደርጎ ነው የተጻፈላቸው።

በቤተ ክርስቲያን በልዩ ክብር የሚታዩ እንዳንድ ባለመልክአ መልክአ በስማቸው የተለያዩ ብዙ መልክአ መልክአ ተደርሰላቸዋል። ለምሳሌ የባለመልክአን ልዩ በዓላት፣ እንዳንድ ሁኔታዎችና ሌሎች ነገሮችን ከግምት መልክአ መልክአ ይጻፋል። ለምሳሌ ለኢየሱስ ክርስቶስና ለድንግል ማርያም የተደረሱትን እንመልከት።

ለኢየሱስ ክርስቶስ	ለድንግል ማርያም
1. መልክአ ኢየሱስ	1. መልክአ ማርያም
2. መልክአ አማኑኤል	2. መልክአ አዶም
3. መልክአ መድኃኒዓለም	3. መልክአ ፋሲለ ለማርያም

4. መልክአ መድኃኔዓለም አሰግድ
5. መልክአ ቁርባን
6. መልክአ መስቀል
7. ልሳነ ሰብአ
8. መልክአ ቅንዋት
9. መልክአ ሚካኤል

4. መልክአ ቁስቋም
5. መልክአ ስእል
6. መልክአ ኪዳነ ምሕረት
7. መልክአ ልደታ ለማርያም
8. መልክአ ልደታ ለማርያም ዳግሚት
9. መልክአ ማርያም ካልእ
10. መልክአ ማርያም ሣልሲት
11. መልክአ ድንግል
12. መልክአ ጳልጣ
13. መልክአ በአታ

ከዚህም ሌላ ጥንድና ከዚያ በላይ ለሆኑ ባለመልክአ መልክአ አንድ መልክአ ተደርሰላቸው ይገኛል።

አራት የመልክአ መልክአ ደራሲያን በስም ይታወቃሉ። እነሱም መልክአ ሥላሴን ጽፈዋል የሚባለት አባ ስብሐት ለአብ /መልክአ ሥላሴ፣ 1972/ ፣ መልክአ ኢየሱስን ጽፈዋል የሚባሉት ገብረ ናዝራዊ ዘሳንደር /አያሌው፣ 1992/፣ መልክአ ቁርባንን ጽፈዋል የሚባሉት አባ ጊዮርጊስ /አያሌው፣ 1992/ እና መልክአ ማርያምን ጽፈዋል የሚባለት አፄናኦድ /ሀርደን፣ 1926፣59፣ ሀያት፣ 1928፣249/ ናቸው። እነዚህ ይታመቁ እንጂ የአብዛኞቹ ደራሲያን አይታመቁም።

1.5 መልክአ መልክአና ቅዳሴ

ቅዳሴ መሥዋዕት፣ ጸሎትና የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት የሚከናወኑበት ሥርዓተ አምልኮት ነው። ሥጋ ወደሙን ካዘዘት ለምእመናን ከማቀበላቸው በፊትና በኋላ መልክአ ቁርባንን ይዘምሩ ታል። መልክአ ቁርባን የክርስቶስን ሥጋና ደም የሚያከብር መልክአ ነው።

ከቅዳሴ በኋላ በየዕለቱ ከሚደገሙ ጸሎቶች ውስጥ ከውዳሴ ማርያም ጋር የሚጸለዩት መልክአ ማርያምና መልክአ ኢየሱስ ይገኙበታል፤ እነዚህ መልክአ መልክአ በካህናቱ ይደገማሉ። ይዘ ጸሎት የሚካሄደው መልክአ አስኪፈጸም ድረስ በቅዳም ተከተሉ ለካህናቱና ሰሲቃውንቱ አንዳንድ አርኬ በማደል ነው። ማደሉ የሚካሄደው በዲያቆናት ወይም በሌሎች የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሲሆን የሚጠቅሱት አያንዳንዱ አርኬ የሚያመሰግኑትን የመጀመሪያውን የሰውነት አካል ወይም ሌላ ቃል ነው።

ከዚህ በተጨማሪም ዕለቱ መታሰቢያው የሆነ ጻድቅ፣ ሰማዕት፣ መልአክ ወይም ሌላ በእለቱ ከተጠቀሱት መልክአ መልክአ በተጨማሪ የሱ መልክአእም ይደገማል። ቤተ ክርስቲያኑ የሚታሰብበትን ስም የያዘው መልክአ ወይም ጻድቅ ስምም በዚያ ቤተ ክርስቲያን መልክአ በየዕለቱ ይደገማል። ለምሳሌ በላሊበላ መልክአ ላሊበላ እና በሳማ ሰንበት ደግሞ መልክአ ሰንበት በየቀኑ ይደገማሉ።

መልክአ መልክአ በዜማ ሊዘመሩ ይችላሉ። የሚዘመሩትም ከመልክአ ውስጥ ተመርጠው የወጡ ጥቂት ስንኞች ናቸው። የሚከበረው ዕለት የሚታሰብበት መልአክ ወይም ጻድቅ ... በዓ ሠታዊ ከብሩ ዕለት ከመልክአ ውስጥ ጥቂት ስንኞች ተመርጠው በጸናጽል፣ በከበሮ ይዘመራሉ። ለምሳሌ ለልደት በዓል ከመልክአ ኢየሱስ ሁለት አርኬዎች ይዘመራሉ፤ አርኬ ፤ እና አርኬ 28።

መልክአ መልክአ በአጠቃላይ ለሃይማኖቱ ተከታዮች እንደግል የጸሎት መጻሕፍት የሚቆጠሩ ናቸው።

መልክአ እንደጸሎት መጽሐፍ ከማገልገሉ በተጨማሪ የማስተማር ተግባርንም ያከናውናል። የባለመልክአኑን ሕይወትና ተአምራት ከጸሎተኛው ጋር ያስተዋውቃል። ይህን የሚያደርገውም መልክአ የተመሠረተው በባለመልክአ ታሪክ ላይ በመሆኑ ነው። ስለዚህም መልክአ መልክአን ለመረዳት የባለመልክአኑን ታሪክና ትምህርተ ሃይማኖት ማወቅ አስፈላጊ ነው።

ሰላም ለዝክረ ስምከ ስመ መሐላ ዘኢይሔሱ
ዘእንበረ ቅድመ እግዚአብሔር በአትሮንሱ
ኢየሱስ ክርስቶስ ለዳዊት ባሕርየ ዘርሁ
አክሲለ ስምከ እንዘ ይተቄጸል በርእሱ
አሀጉረ ጸር መረስ ኢያሱ

/መልክአ ኢየሱስ፣ አርኬ 1/

ይህን አርኬ ለመረዳት የኢያሱን ታሪክ፣ የኢየሱስን ትውልድና ምሥጢረ ሥጋዌ ማወቅ ያሻል። የኢየሱስና የኢያሱን የስም አንድነት ማወቅም አስፈላጊ ነው። ኢየሱ የተሰፋይቱን ምድር የመውረሱ ታሪክና የኢየሱስ ከዳዊት ዘር መወለድንም ማወቅ አስፈላጊ ነው። እያንዳንዱ እንደየመሥፈርቱ መጠን የዚህን አርኬ ትርጓሜ እያሰፋና ተልቀት እየሰጠ መቀጠል ይችላል።

ለላሙ የመልክአ የአስተማሪነት ባህርይ በተጥታ የሚጠቀሰው የመልክአ ቀርባን የመጀመሪያው አርኬ ነው።

ማኅበረ ምእመናን ወምእመናት እለኪየከ ተአመኑ
ሰንሚአ ሥጋከ ወጥረ ኅዘ ተበየኑ
ወልደ አብ ክርስቶስ ዘ ኢትትፈለዮ እምሕፅኑ
አስብከ ሎሙ ሕማመከ ወመስቀልከ እዜኑ
ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ሊተ እምስማይ ፈኑ።

አራተኛው ስንኝ ዐግልፅ የነበሚው /የጸሎተኛው/ ግብ የክርስቶስን መከራ መስቀል መስከክ መሆኑን ይገልጻል። እኔ አስከየውት ድረስ አንባቢ /ካህን ካልሆነ በቀር/ ራሱን በደራሲው ቦታ ተክቶ የመጸለይ አተሙን የሚያሳበት መልክአ ይህ ብቻ ነው።

2. አሰነኛንት /Prosody

አሰነኛንት ያልኩት የግጥሙን ሙዓዛዊ ገጽታ የሚያሳዩትን ቤት ምትና አርኬን ነው።

2.1 ቤት

በመልክአ መልክአ የስንኞቹ የመጨረሻ ቤት፣ መምጅ ሁልጊዜ አንድ ዓይነት ሆሄ ነው። መልክአ መልክአ ሁልጊዜም በአንድ ዓይነት ሆሄ ቤት የሚመቱ ባለአምስት ስንኝ አርኬዎች

ያሏቸው ናቸው።

ሰላም ለአዕይንቲከ ከመ ምሁሪ ምዕቃሰግይ
እሰ ይትረአይ ወትረ በመንበረ መጽሔት ርሱይ
ኢየሱስ ክርስቶስ መስተሥርየ ኩሉ ጌጋይ
ንዝኃኒ እግዚኦ በአዛብክ ሥናይ
ወእጻዕድወኒ እም በረድ ጽፉይ
/መልክአ ኢየሱስ፣ አርኬ 6/

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው አርኬ ውስጥ ያሉት 5 ስንኞች ቤት የሚመሠረቱ «ይ» በተባለው ሆሄ ነው።

ቤት የሚመታው ሁል ጊዜ በተናባቢ ድምጽ ሲሆን አናባቢዎች ቤት የሚመቱት እንደተነባቢ ሲያገለግሉ ብቻ ነው። ለምሳሌ፦

ሰላም ለእመትከ ዘይሜጥን ተራድኦ
አኮ ሰንዱን ወአልባሰ ረፍዖ
ሚካኤል ኀቤከ እወፍ በአስተብቁዖ
ከመ ታድኅነኒ ሥመር እግዚኦ
እስመ ኩሉ ይተግህ ከመ ያድኅን ስብኦ
/ መልክአ ሚካኤል፣ አርኬ 28/

የዚህ አርኬ ስንኞች ቤት የሚመቱት በ «አ» ሲሆን እሱም ከአናባቢነት ይልቅ በተነባቢነት እያገለገለ ስለገባ ነው።

አንዳንድ ጊዜ ደራሲዎቹ የገጣሚነት መብታቸውን በመጠቀም አንዳንድ ቃላትን በቤት መምቻው ሆሄ እንዲጨርሱ ያስገድዷቸዋል። የሚከተሉት ምሳሌዎች ይህን ያስረዳሉ።

ሰላም ለኩልያቲከ ውስተ ልበ አምላከ ዘተሣዋኒ
ወሰንሲናከ ሰላም እንዘ ኢይቤኒ
ዮሐንስ ንጹሕ ፍትወተ ዓለም ኀጻኒ
እምግበረ ሕማም ጽፉቀ ያስተብቁዓከ ዮኀኒ
መከብበ ሰማዕታት ተርቢናስ እጕስ ጊዮርጊ
/መልክአ ዮሐንስ መጥምቅ፣ አርኬ 19 /

የመጨረሻው ሰንኝ የመጨረሻ ቃል ጊዮርጊስ መሆን ሲገባው በእንድ ዓይነት ሆሄ ቤት እንዲመታ ሲባል ጊዮርጊ ሆል።

ሰላም ለአስትንፋስከ አስትንፋስ ሕይወት ወተሚና
ወለጉርኤከ ዓዲ ኖኅተ ሰሆሳስ ወዴዴ ገዘና
እግዚአብሔር አብ መድሎመ ልዕልና
ዘታበድር ጽድቀ ወይዋሃ ወግብረ ኩሉ ትሕትና
ትሰቢትስ አመደቆ ሰሳጥና።

/መልክአ እግዚአብሔር አብ፡ አርኪ 12/

በዚህ አርኪም በመጨረሻው ስንኝ ላይ ያለው የመጨረሻ ቃል ሳጥናኤል መሆን ሲ ገባው ሳጥና የሆነው በተመሳሳይ ሆሄ ቤት እንዲመታ ነው።

በአጠቃላይ በአንድ አርኪ ውስጥ የሚገኙ ስንኞች ሁሉ በአንድ ዓይነት ሆሄ ቤት መምታት አለባቸው። መልክአ መልክአ ሲዘመሩ የሚችሉ ስለሆነም ይህ ቤት መምታት ለዜ ማው ይጠቅማል።

2.2 ምት /ቀለም/

ዓለማየሁ ሞገስ /1969/ የግእዝን ሥነ ግጥም አስነኛኘት ሲያብራሩ የግዕዝን ሥነ ግጥም ዜ ማ የሚወስኑት የሚቆጠሩ ድምፆች /ሆሂያት/ እና የአነባብ ሥርዓት /ተነሽ፣ ወዳቂ፣ ሰያፍ/ ናቸው። እንደ አቶ ዓለማየሁ ሞገስ ጥናት በአንድ አርኪ ውስጥ የሚገኙ ስንኞች የተለያየ መጠ ን /የቀለም/ ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህም በአንድ አርኪ ውስጥ ያሉ ስንኞች የቀለም መጠ ናቸው የተለያየ ነው። የሚከተለት አራት አርኪዎች ቀለም አንደሚያሳየው መልክአ መልክአ አንድ ዓይነት የቀለም መጠን የላቸውም። ከዚህም ሌላ የመጀመሪያው አርኪ ስንኞች ቀለም ከተከታዩ አርኪ ስንኞች እኩል ሆነው የሚጣመዱ አይደሉም። ይህም አሰልቺነትን ያስወግዳል።

ሰላም ለመልክአኪ ዘተሠርገዉ አሚረ	16	ሀ
ዘያበርህ ወትረ	7	ለ
ፍቅርትየ አንቲ እንተ ታበድሪ ፍቅረ	14	ሐ
አርእይኒ ገጸ ዚአኪ ማርያም ምስረ	16	ሀ
ዘኢይሰምየ ካልዕ እንግርኪ ነገረ	14	ሐ

/መልክአ ማርያም፣ አርኪ 51/

ሰላም ለገጽከ እምሥነ አርያሬስ ስቡሕ	15	ሀ
ወፍሡሕ ክመወርኅ ዘአሜ ገሃሀ	12	ለ
ኢየሱስ ክርስቶስ ታቦተ ሕይወቱ ለኖኅ	12	ለ
ኅብአኒ አግዚኦ በውሳጤከ ስፉሕ	12	ለ
ማየ ኩነኔ አመ ዘንመ አይኅ	12	ለ

/መልክአ ኢየሱስ፣ አርኪ 4 /

ሰላም ለአእናፊከ አለ በሰማያት ያንበለብሉ	18	ሀ
ከመሠርቀ ፀሐይ ሥነ ጸዳሉ	11	ለ
አ መልአከ ጊዜ ተፈናከ ዘእምሳዕሉ	14	ሐ
ይትፈሥሑ በምጽአትከ ነፍሳተ ኃጥአን ኩሉ	16	መ
መጻእከኑ መጻእከኑ ሚካኤል ይብሉ	15	ሠ

/መልክአ ሚካኤል፣ አርኪ 20/

ሰላም ለእራኀ መሀቤ ጲጋ ብሩክ	12	ሀ
ወለአጻብኢከ የውጣ አጻብአ ክቡር መልአክ	16	ለ
እማንፅኒ ገብርኤል ኀበ አማናዊ አምላክ	16	ለ
በዓለምሰ ኢይትረከብ ዐርክ	11	ሐ
አስመ በጽባሕ ዘተናገረ ኢይደግም በሠርክ	16	ለ

/መልክአ ገብርኤል፣ አርኪ 16/

በመልክአ መልክእ አንድ ዓይነት የማይቀያየር ወጥ ዜማ የሌለው በባለ አምስት ስንኝ አርኪ ውስጥ አንድ አይነት ወጥ ምት ባለመኖሩ ነው። በአጠቃላይ መልክኡ ቁርጥ ያለ የምት ቀመር የለለው ሲሆን ዜማዊ ነው።

2.3 አርኪ

መልክአ መልክእ በአርኪዎች የተከፋፈሉ ግጥሞች ናቸው። አያንዳንዱ አርኪ አምስት አምስት ስንኞች አሉት። ባለአምስት ስንኝ አርኪዎች በሌሉችም የግእዝ የግጥም ዓይነቶች ውስጥ የተለመደ ነው። ባለአምስት ስንኝ አርኪ ከሚጠቀሙት ውስጥ የስንክሳር አርኪዎች፣ ቅኔ፣ ስዓታት፣ ማኅሌተ ጽጌና ሰቆቃወ ድንግል ሲጠቀሱ ይችላሉ። ሰቆቃወ ድንግል አንዳንድ ጊዜ ባለስድስት ስንኝ አርኪም ይጠቀማል።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሱት አርኪዎች በሙሉ ይሆንን የሚያስረዱ ናቸው። ለምሳሌ ግን የሚከተለውን አርኪ አንመልከት።

ሰላም ለፍልሰተ ሥጋከ ለዘርዐ ያዕቆብ ዘተከስተ /1/
ወሊቀ ካህናት ገብርኤል ዘሐዘለከ መሳልተ /2/
ዜና ማርቆስ ያዕቆብ ፈውሶተ ድውይ ሐውልተ /3/
አቅሞ በቅድሜየ እንዘ ታስተበቁዕ አንተ /4/
ኀበ አምላክከ ሰማያዊ ለቤዛ ዘሞተ። /5/

/መልክአ ዜና ማርቆስ፣ አርኪ 48/

በጣም ሕገ ወጥ ከሆኑትና በጥቂት መልክአ መልክእ ውስጥ ከሚገኙት ጥቂት አርኪዎች በቀር የመልክአ መልክእ አርኪዎች ባለአምስት ስንኞች ናቸው።

የመልክአ መልክእ አርኪዎች ሌላም ባሕርይ አላቸው። እያንዳንዱ አርኪ የራሱ መነሻ ቃል አለው። ከዚህ ቀጥሉ የመልክአ መልክእ አርኪዎች የመጀመሪያ ስንኞች የመጀመሪያ ቃል መነሻ ቃል እየተባለ ይጠራል። የአንድ መልክእ አርኪዎች /አልፎ አልፎ ከሚለዩት የመጨረሻዎቹ አንድ ወይም ሁለት በስተቀር/ መነሻ ቃላቸው አንድ ዓይነት ነው። በብዙ መልክአ መልክእ አርኪዎች የመጀመሪያ ስንኝ ላይ የሚገኘው መነሻ ቃል ሰላም ነው። ታትመው ካገኘኋቸው 50 መልክአ መልክእ ውስጥ የአርባ ሁለቱ መልክአ መልክእ አርኪዎች የመነሻ ቃል ሰላም ነው። /ተማኅፀንኩ/ የሁለት መልክእ መልክእ፣ /እ/፣ /ንእ/ እና /ነእ/ የአንዳንድ መልክአ መልክእ አርኪዎች መነሻ ቃላት ሲሆኑ የሦስት መልክአ መልክእ ደግሞ አርኪዎች መነሻ ቃል የላቸውም። በአጠቃላይ ሲታይ ሰላም የመልክአ መልክእ አርኪዎች መነሻ ቃል ነው።

በመልክአ መልክአ አርኬዎች ውስጥ ክመነሻ ቃሉ ቀጥሎ የሚመሰገነው የባለመልክኡ የአካል ስም ወይም ሌላ ነገር ይከተላል። ከየኋቸው 50 መልክአ መልክአ ውስጥ አርባ አንዱ የየባለመልክኡን የሰውነት ክፍሎች እየዘረዘሩ የሚያመሰግኑ ናቸው። አራቱ የየባለመልክኡን ተግባራትና እንዳንድ ሁነቶችን፣ ሦስቱ ደግሞ ምንም የተለየ የሚዘረዝሩት ነገር የለም። የቀሩት ሁለቱ መልክአ መልክአ ግን የተጻፉት ለጸሎት መጻሕፍት ነው፣ ለውዳሴ ማርያምና ለእንቀጸ ብርሃን። የነዚህ ሁለት መልክአ መልክአ አርኬዎች መነሻ ቃል የጸሎት መጻሕፍቱ እንቀጾች መነሻ ቃል ነው። ለምሳሌ የመልክአ አንቀጸ ብርሃን የመጀመሪያዎቹ ሦስት አርኬዎችና የእንቀጸ ብርሃን የመጀመሪያዎቹ ሦስት አንቀጾች መነሻ ቃላት ቅድስት፣ አሠርቱ እና ቀዲሙ ናቸው።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መልክአ መልክአ አርኬዎች በሙሉ መነሻ ቃላቸው ሰላም ነው። ከዚህ ቀጥሎ እሰግድ ለሚለው መነሻ ቃል አንድ ምሳሌ አጠቅሳለሁ።

እሰግድ ለእእዳዊከ በቀኖተ ኀጢን እለተሰቅራ
ወለመዛርኢክ ወሐብል እለ ድኀሪት ተአሥራ

/መልክአ መድኃኔ ዓለም እሰግድ፣ አርኬ 20፣ ሰንኝ 1ና2/

የየባለመልክኡን የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች የማይዘረዝሩና የማያመሰግኑ ነገር ግን የባለመልክኡን መለያ ሁነት የሚናገሩ አንዳንድ መልክአ መልክአ እስ። ስምሳሌ በብራና ላይ ተጽፎ በጀመዳ ማርያም ገዳም ያገኘሁት መልክአ ልደታ ከየአርኬዎች ሁሉ በመነሻ ሀረግነት የተጠቀመው ሰላም ለልደትኪ ... የሚለውን ነው። የታተመው መልክአ ልደታ ለማርያም የድንግል ማርያምን የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች እየዘረዘረ የሚያመሰግን ቢሆንም ልደቷን ካሉት 31 አርኬዎች ውስጥ በሃያ ዘጠኙ ይጠቅሰዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ በመልክአ ፍልሰታ ለ ማርያም ውስጥ ትንሣኤዋንና የበድነ ሥጋዋን ዕርገት ክሚያመሰግኑት የመጨረሻዎቹ ሁለት አርኬዎች በስተቀር የሁሉም አርኬዎች መነሻ ሀረግ ሰላም ለፍልሰተ ሥጋኪ ነው።

መልክኡ የተደረሰለት ግዑዝ ነገር ወይሥ የተቀደሱ ዕለታት ሰዋዊ ባሕርይ ተሰጥቷቸው ልዩ ልዩ የሰውነት ክፍሎች እንዳላቸው ተደርገዋል። ለምሳሌ ሰንሰትን ብንወስድ በመልክአ ሰንበት ውስጥ የሰውነት ክፍሎች ተዘርዝረው ሲመሰገኑ እናያለን።

ሰላም ለከናፍርኪ ዘኅበ በሡባሬ
አንበለ ድማሬ
ሰንበተ ክርስቲያን ቅድስት ሙዳየ ምጽዋት ዘቤተ ጎሬ
አስሶለኪ አግዝእትየ አስሙ አቅረብኩ ዝሞሬ
ጸጋ ሥነፈስ ቅዱስ ሊተ ጸግውኒ ፍሬ

/መልክአ ሰንበት፣ አርኬ 10/

ከላይ በተጠቀሰው አርኬ የተመሰገነው የሰውነት ክፍል ከንፈር ነው፣ ነገር ግን ሰዋዊ ባሕርይ ካልተሰጠው በቀር ዕለት ከንፈር የለውም። ግዑዝና ረቂቅ ሀሳቦችን ሰዋዊ ባሕርይ ስጥቶ ማመስገን አንደ እንድ ባሕርይ የሚቆጠር ነው።

መልከአ መልክአ በአንደኛ መደብ የተጻፉ ሲሆን ባለመልክአ መልክኡ ደግሞ በሁለተኛ መደብ የሚጠሩበት ግጥም ነው። በተጨማሪም ደራሲው ወይም መልክኡን ደጋሚው በአንደኛ መደብ ባለመልክኡ ደግሞ በሁለተኛ መደብ ሆነው በተጥታ አንደሚነጋገሩ ሆኖ በመጻፍ የልመናና ምልጃ ማቅረቢያም ነው።

በዞመልክአ መልክኡ ውስጥ በቋሚነት የሚገኘው «እኔ» የሚለው ተውላጠ ስም በደራሲው ወይም በደጋሚውና በባለመልክኡ መካከል መንፈሳዊ መቀራረብን መፍጠሪያ መንገድ ነው። እኔ የሚለው ተውላጠ ስም ጸሎተኛውን ወይም ልመና አቅራቢውን በመልክኡ ደራሲ ቦታ ራሱን አንዲያስቀምጥ አድርጎ በአሱ /አሷ/ እና በባለመልክኡ መካከል ግላዊና ቀጥተኛ ግንኙነት ፈጥሮ ለባለመልክኡ ልመናውን አንዲያቀርብና ኃጢአቱን አንዲናገር አስችሏል። ይህ ራስን በመልክኡ ደራሲ ቦታ መተካት አንድ ቦታ ችግር ሲገጥመው እናያለን። «ልሳነስብአ» /መልክአ ልሳን ሊባል ይችላል/ ውስጥ ያለው አኔ ባይ በአንደበቱ 50 ዓመታት አንደተገዛ/ አንደተመራ/ ይናገራል። ይህ ግላዊ የሆነ የአንድ ሰው /ምናልባት የመልክኡ ደራሲ/ አድሜ ቁጥር ከ50 ዓመት በታች የሆኑትን የመልክኡ ደጋሚዎች ዘደራሲው ቦታ ራሳቸውን አንዲያስቀምጡ ያደርጋቸዋል።

ሰድርሰቱ /መልክኡ/ መሰካት ልመና በሚቀርብበት አርኪ /ብዙ ጊዜ የመጀመሪያው ነው/ ውስጥ ያለው «አኔ» የመልክኡን ደራሲ የሚመለከት ነው። የመልክኡ ደጋሚ ራሱን በደራሲው ቦታ አድርጎ ደካማነቱን በመግለጽ የባለመልክኡን ህዘኔታና ተራድኦ የሚጠይቅበት ነው። ደካማነቱም መልክኡን መደገም ሰቻሉት ሁሉ ሲሆን በውስጣቸውም የትሕትናን ስሜት ያሳድራል።

አርኪዎቹ የራሳቸው የሆነ ክፍል ክፍል አላቸው። የአርኪዎቹን ይዘት አንደመሥፈርት ይዘን ስንመረምራቸው አያንዳንዱ አርኪ ለሦስት የተከፈለ ሆኖ አናገኘዋለን።

1. ገለጻ :- በአብዛኛው ይህ ክፍል የአርኪውን የመጀመሪያ ሁለት ስንኞች የሚይዝ ሲሆን የባለመልክኡን የሰውነት አካላት ወይም ሌሎች ነገሮች በዘይቤ የሚገልጽ ነው፣
2. ጽዋኄ /ጥሪ/:- ጥሪ በአብዛኛው የአርኪዎቹ ሦስተኛ ሰንኝ ባለመልክኡን በተጸውኦ ስሙ የሚጠራበት ነው /አንደ አንድ ግለሰብም የሚገልጸበት/።
3. ሰዕለት /ልመና/:- ይህ ክፍል በአብዛኛው የመጨረሻዎቹን ሁለት ስንኞች የሚይዝ ነው። ተናጋሪው /አኔ ባዩ/ በትሕትና ከባለመልክኡ ረድኤትንና አማላጅነትን የሚለምንበት ነው። ይህ ልመናው ሁለት ዓይነት መልክ አለው፣ አንድ ኃጢአትን በሙናዘዝ ሥርዓት ይቅርታ የሚጠየቅበት ሲሆን ሁለተኛው ግን በጠላት ላይ በቀልና አሸናፊነት ለማግኘት የሚቀርብ ነው።

የመልክአ ማርያምን ሁለተኛ አርኪ በምሳሌነት እንመልክት።

ገለጻ:- ሰላም ለሥእርተ ርእሰኪ ዙተንአደ ጽፍሮሁ
ለአቡኪ በከናፍሪሁ

ጽዋኄ /ጥሪ/:- ማርያም ድንግል ለእግዚአብሔር ጽርሑ

ሰአለት /ልመና/:- ሰገብርኪ እግዚእትየ ኢትጎድግኒ አላሁ
ከመ ኢይበሉኒ ፀር አይቴኑመ ምኩሑ

/መልክአ ማርያም፣ አርኪ 2/

በዚህ አርኪ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ስንኞች የቅድስት ማርያም ጸጉርና አሠራሩ ከመጎልየ መጎልዩ በተወሰደ ጥቆምታ ይገለጻል። ሦስተኛው ስንኝ /በገለጻውና በስእለቱ መካከል አማካኝ ነው/ ድንግል ማርያምን በቀጥታ በመጥራት የእግዚአብሔር አዳራሽ /አልፍኝ/ ነሽ ይላታል፤ ያለዘር ፀንሳ የእግዚአብሔርን ልጅ ወልዳስችና። የመጨረሻዎቹ ሁለት ስንኞች ደጋሚው ለድንግል ማርያም የሚያቀርበው ልመና ነው፤ ጠላቶቼ መሰኪያው ወጄት አለች እንዳይሉኝ አትተይኝ በማለት።

ሦስተኛውን ስንኝ በሚመለከት የተለየ ባሕርያት ያላቸውን ሁለት መልክአ መልክአ አይቻለሁ። የመጀመሪያው መልክአ ማርያም ካልእ ሲሆን የሁሉም አርኪዎች ሦስተኛ ስንኞች በሙሉ አንድ ዓይነት ናቸው። አንድነታቸው በፍቺ እና አልፎ አልፎ በቅርፅም ነው። ሁሉም አመቤታችን በሕፃንነቷ ቤተመቅደስ መግባቷን ይገልጻሉ። ሁለተኛው «መልከአ መጥልሲ» የሚባለው /ለማርያም የተደረሰ/ ሲሆን ሦስተኛው ስንኝ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱን የሚጠቅስ ነው። መልክኡ 12 አርኪዎች ያሉት ሲሆን በሦስተኛዎቹ ስንኞች ውስጥ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት በየተራ በምሳሌነት ተጠቅሰዋል፤ ድንግል ማርያምን ለመግለጽ።

ይህ የአርኪዎች ቅርጽ በሁሉም ወይም በአብዛኞቹ መልክአ መልክአ አርኪዎች ውስጥ የታየ ነው። ነገር ግን የሦስተኛውን ስንኝ ተግባር በሁለተኛው ስንኝ የተኩ ወይም ስእለቱን /ልመናውን/ በገለጻ የተኩ ጥቂት አርኪዎች ተገኝተዋል። ይህም የተገኘው በመልክአ ሥላሲ ውስጥ ነው። መልክአ ሥላሴ 47 አርኪዎች ሲኖሩት በሠላሳ ስምንቱ ውስጥ ጽዋዔ /ጥሪ/ የሚገኘው በሁለተኛው ስንኝ ውስጥ ነው። ጽዋዔ/ጥሪ/ እና ስእለት/ልመናም/ በአንድነት በዚሁ በሁለተኛው ስንኝ ውስጥ ይገኛል።

ሰላም አብል ለዘዚአክሙ ክናፍር
·ኮክሉኒ ሥላሴ በኅሊ ቤትክሙ ፍቅር
እስመ ሃይማኖትየ ሞተት እምነ ሕይወት ምግባር
እንዘ ብየ ተስፋ ጽሙአ ጽዋዐ ማይ ቆሪር
ወሐዋጺ ብእሲ ድውይ እንዘ ብየ አግር
/መልክአ ሥላሴ፣ አርኪ 11/

የመጀመሪያው ስንኝ ለባለመልክኡ ከንፈሮች የቀረበ ሰላምታ ነው፤ ያለምንም ዘይቤ። ሁለተኛው ስንኝ በለመልክኡን /ሥላሴን/ በስም በመጥራት ልመናና ጥሪ በአንድነት የቀረበበት ነው። የመጨረሻዎቹ ሦስት ስንኞች የልመናውና የኑዛዜው ምክንያቶች የቀረቡበት ነው። የመልክአ አጠቃላይ ቀርጽ ልዩ ስርአት ያለው አይደለም፤ ነገር ግን በአብዛኞቹ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ጥቂት አርኪዎች ስመልክኡ መሳካት የቀረቡ ልመናዎች ናቸው። የመልክኡ ደራሲ ባለመልክኡን በቀጥታ በመጥራት በመልክአ እጻጻፍ ላይ ርዳታቸውን እንዲሰማሱት የሚያቀርበው ልመና ነው። መልክኡን ለመድረስ እንደቀረበው ልመና ሁሉ መልክኡ ስለተደረሰ ምስጋናንም የያዙ አርኪዎች አሉ። የዚህ ዓይነት አርኪ ካላቸው መልክአ መልክአ ውስጥ የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል።

መልክአ ኦራቅሊጦስ	መልክአ ኪዳነ ምሕረት
መልክአ ቁርባን	መልክአ እስጢፋኖስ
መልክአ አማኑኤል	መልክአ ሰንበት
መልክአ ኢያቄም ወሐና	መልክአ አረጋዊ

የዚህ ዓይነቱ ልመና ሁለት ዓይነት ነው። አንደኛው ደራሲው ባለመልክኡ በቀጥታ ባለው ኃይል ወይም ባማላጅነቱ በድርሰቱ ሳይ እንዲረዳው የሚለምንበት ሲሆን ሁለተኛው እግዚአብሔርን በእንደኛ መደብ በቀጥታ ወይም ድንግል ማርያምን በሦስተኛ መደብ በመጥራት እንዲረዱት ልመና የሚቀርብበት ነው።

የመልክአ አስጢፋኖስ የመጀመሪያው አርኬ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ይሆናል።

በስመ ሥሉስ ቅዱስ እግዚአብሔር አሐዱ
ናሁ ወጠንኩ ወአቤ ሰላመ መልክአከ ዘበፍቅዱ
ለፈጽሞቱ ርድአኒ አስጢፋኖስ ጽጌ ናርዱ
ክመ ዘይረድኦ አብ ለወልዱ
ወመንፈሀርነ, ለጽኑሰ ተልሚዱ።

/መልክአ አስጢፋኖስ፣ አርኬ 1/

በዚህ አርኬ ደራሲው የባሰመልክኡን ተራድኦ በቀጥታ የጠየቀበት ነው።

ሰላመ ገብርኤል መልአክ በሳዕሰ ማርያም ዘአዕረፈ
ክመ አዜኑ ጎዳጠ ወአኮ ትሩፈ
እግዚአብሔር ሀበነ, ሲሳየ ልቡና መጽሐፈ
ወአፉየ ሙሴ ለአመ ኮነ ጸያፈ
ጸራቅሊጦስ አሮን ይኩነነ, አፈ።

/መልክአ ገብርኤል፣ አርኬ 1/

ከዚህ በላይ በተጠቀሰው አርኬ ደግሞ ደራሲው ተራድኦ የጠየቀው ከባመልክኡ ሳይሆን በቀጥታ ከእግዚአብሔር ነው።

ሰላም ለዝክረ ስምከ ዘጥንተ ፈደሱ መስቀል
ስም ከቡር ወስም ልዑል
ተክለሃይማኖት ማቴዎስ በዓለ ቀዳማይ ወንጌል
ክመ አወድስክ መጠነ አሙሥአተ አክል
ማእሠረ ልሳንየ ትፍታሕ ማርያም ድንግል።

/መልክአ ተክለሃይማኖት፣ አርኬ 2/

በዚህ አርኬ ደግሞ ተራድኦ የተጠየቀው በሦስተኛ መደብ ከድንግል ማርያም ነው።

በአንድ አርኬ ውስጥ የሚገለፀውን የሰውነት ክፍሎች ብዛት የሚወስነው የመልክኡ ርዝመት ነው። መልክኡ አብዛኞቹን የሰውነት ክፍሎች ለመግለፅ የሚበቃ ርዝመት ካለው አንድ አርኬ አንድ የሰውነት ክፍልን ብቻ ይገልፃል። መልክኡ በጣም አጭር ከሆነ ግን አንድ አርኬ እስከ 5 የሰውነት ክፍሎችን ይዘረዝራል።

ሰላም ለቃልከ ወለአለትንፋስከ ርጢን
ለጉርዔከ ወሳክሳድከ ወለሙትክፍትከ ሁጽፍተ ብርሃን
መልአከ ሁቃቢ ዘለሊት ከመ ስምከ አማን
አሰሰል አምላለዩ ምክረ ንዋማዊ ሰይጣን
ዘበኃይለ መንፈሰ ብከ ሠልጣን

/መልክአ ሁቃቤ መልአክ፣ አርኬ 5/

ይህ መልክአ 14 አርኬዎችን ብቻ የያዘ በመሆኑ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው አርኬ እንኳ 5 የሰውነት ክፍሎችን ያመሰግናል።

የመልክአ መልክእን ርዝመት በሚመለከት ከታተሙት ውስጥ ረዥሙ ጠቢበ ጠቢባን ሲ ሆን 102 አርኬዎች ይዟል። በጣም አጭሩ ደግሞ መልክአ ሁቃቤ መልአክ ሲሆን ባለ 14 አርኬዎች ነው። መልክአ ፍልሰታ ለማርያም 16 አርኬዎች ያሉት ሲሆን ፍሰሰቷ የሚከበረውም ነሐሴ 16 ቀን መሆኑ የእርኬዎቹ ቁጥር ፍቺ ያለው መሆኑንም ይጠቁማል። አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ መልክአ መልክአ ስንት አርኬዎች እንደያዙ በመጨረሻ አርኬአቸው አንዱ ስንኝ ውስጥ ይጠቅሱታል። ለምሳሌ ፦

አምኃ ሰብሐት አቅረብኩ ለመልክአከ በጽሞ
እንዘ አሰተዋድድ ቃለ መጠነ ራብአ ሱባኤ
ተመከፈኒ ዮሐንስ ምስለ በርተሎሜዎስ ቀርነ ጉባኤ
ከመ ተመከፈ እግዚአከ ቅድመ ወንጌላዊት ትንሣኤ
እምነ አሐቲ ብእሲት ጸራይቀ ከልኡ

/መልክአ ዮሐንስ መጥምቅ፣ አርኬ 28/

የዚህ አርኬ ሁለተኛው ስንኝ መልክኡ 28 /4 x 7/ አርኬዎች እንዳሉት ይናገራል።

አንዳንድ ጊዜ የአርኬው ስንኞች እምስት መሆን ሰላሰባቸው ብቻ የሚገቡ ስንኞች አሉ።
ሰላም ለአጻብዒከ እንተ በዲቤሆን አጽፋር
ዘኑላቄሆን በሥር
በማኑኤል አንተ ንጉሠ ሰማያት ወምድር
ተራወጹ በኃይልከ ሐንካሳነ እግር
ወብርሃነ አዕይንት አጽምዐ ሰሙር

/መልክአ በማኑኤል ፡ አርኬ 28/

የሚከተለውም ሌላ ምሳሌ ነው።

ሰላም፣ ሰላም ወሰላም እብሎን
ለአጻብኢከ አሥር ምስለ አጽፋሪሆን
ጎድፈኒ ቂርቆስ ኖትያ መንገለ መቦስ ወዛንን
ናሁ አስጠሙ ጎሲናየ በዝ ዘመን
ሰቆቃወ ጤግሮስ ወግዮን ነዘን

/መልክአ ቂርቆስ፣ አርኬ 26/

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ሁለት አርኬዎች ውስጥ የመጀመሪያውና ሁለተኛው ስንኞች ለቋንቋው ውበትም ሆነ ለይዘቱ የሚስሙት ጥቅም የለም። ያላቸው ጠቀሜታ አንድ ብቻ ነው፤ የአርኬውን ስንኞች አምስት ማድረግ። የዚህ ዓይነት ተግባር ያላቸው ስንኞች አንዳንድ መልክአ መልክአ ውስጥ ይገኛሉ።

3. ዘይቤ /ምሳሌ/

ዘይቤ የሥነ ግጥም ዋነኛ መሣሪያ ነው። ለቅኔያዊ ፍች፣ ለሥነ ግጥማዊ ቅርጽና ለውበተ ም ዋነኛ ጠቃሚ ነው። ዘይቤን እዚህ የምንጠቀምበት በመልክአ መልክአ ውስጥ የገቡ ምስሎችን /ዘይቤያዊ አነጋገሮችን/ ወክሎ ነው።

መልክአ የብለመልክኡን አካላዊ ክፍሎች የሚገልፅ ነው። የመልክአ መልክአን ዘይቤ መ ጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነና ያልሆነ ብለን ለሁለት መክፈል እንችላለን። ሁለቱንም የዘይቤ ዓይነቶች ጥቂት ምሳሌዎች በመጥቀስ ስማስረዳት እሞክራለሁ።

3.1 መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘይቤ

ጥቅምታ ማለት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ግለሰብን ወይም ሁኔትን ወይም ሌላ ሥነ ጽሑ ፋዊ ሥራን በመጥቀስ ሌላ ነገርን ለመግለፅ ወይም ለማብራራት የሚያስችል ነው። የጥቅምታ ግብ አንድን ጽሑፍ /ነገር/ አጉልቶ ማሳየት ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅምታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰ ሰውን፣ ድርጊትን ወይም ሁኔትን የሚጠቁም ነው። የሚጠቆመው ነገር ተግባሩ ሌላን ነገር አጉልቶ ማሳየት ነው።

በመልክአ መልክአ ውስጥ ካሉት ዘይቤዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱት በቁጥር ከሌሎቹ የዘይቤ ዓይነቶች በጣም ይበልጣሉ። ከብሉይና ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተወሰዱ ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ለተራው አንባቢ የማይታወቁ ነገሮችም ተጠቅመው ይገኛሉ።

ለምሳሌ፡-

ማርያም ኅትምት መጽሐፈ ዮሐንስ ዝቢየ ፍጥሞ /3/
ልክኒ ባስዕሌየ ለፊደልኪ ማኅተሞ /4/
ከመ ኢይርአየኒ ዓይነ ሞት ዘሰሙ መጽአሞ /5/

/መልክአ ማ፡ያም መጥልሊ፣ አርኬ 3፣ ስንኝ 3-5/

ሦስተኛው ስንኝ ድንግል ማርያምን ከዮሐንስ ራእይ በተወሰደ ጥቅምታ ይገልጻታል። በዮሐንስ ራእይ እንደተጻፈው ቅዱስ ዮሐንስ በ7 ማኅተም የተዘጋ መጽሐፍ ያያል። ይህ መጽሐ ፍ የክርስቶስ ምሳሌ በሆነው በበጉ ካልሆነ በቀር የሚከፈት አይደለም /ራዕይ 5:1/። በዚህ ስንኝ ውስጥ በማኅተም የተዘጋው መጽሐፍ ድንግል ማርያምን የሚገልጽ ሲሆን /መጻሕፍተ ሐዲሳት ሠለስቱ፣ 1989:382/ ማኅተሙ ደግሞ ድንግልናዋን ይገልጻል። በዮሐንስ ራእይ ውስጥ ያለው በግ መጥምቁ ዮሐንስ አነሆ የእግዚአብሔር በግ /ዮሐ. 1:29/ ሲል እንደመሰከረ የኢየሱስ

ክርስቶስ ምሳሌ ነው። በዮሐንስ ራእይ መጽሐፉን የሚከፍተው በጉ እንደሆነ ከድንግል ማርያምም በድንግልና የተወለደው ኢየሱስ መሆኑን ያስረዳል።

ሌላ ምሳሌ ልየቀስ፡-

እግዚአብሔር ሀበኒ ሲሳየ ልቡና መጽሐፈ
ወአፉየ ሙሴ ለእመ ኮነ ጸያፈ
ጸራቅሊጦስ አሮን ይኩነኒ አፈ።

/መልክአ ገብርኤል፣ አርኬ1፣ ስንኝ 3-5/

በአራተኛውና በአምስተኛው ስንኞች ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱሶቹ ሙሴና አሮን ተጠ ቅሰዋል። በአሪት ዘጸአት እንደተጠቀሰው ሙሴ እንደበቱ ኮልታፋ ነበር /ዘጸ 4፤10/፤ ስለዚህም እግዚአብሔር አሮንን የሙሴ እንደበት አደረገለት /ዘጸ. 4፤ 14-15/። ይሆን ታሪክ በመጠቆም ደራሲው እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን «ጸራቅሊጦስ»ን እንደበት አድርጎ እንዲልክለት ይለምናል። ሙሴ የደራሲውን አሳምሮ መናገር አለመቻል አሮን ደግሞ የመንፈስ ቅዱስን ለሰዎች እንደበት መሆን ይገልጻል። ዘይቤው ትይዩ ነው፤ ሙሴና አሮን ስለእንደበተ ኮልታፋነትና ለጸራቅሊጦስ ቆመዋልና።

አንድ ምሳሌ መጨመር ነገሩን የበለጠ ሊያብራራው ይችላል፡-

ልብስ ስማዕትና ይኩነኒ ምሕረትክሙ ከዳን
ላዕሌየ እስመ ኢሀሎ ልብስ አስጢፋኖስ እብን
ወሥርጋዌሁ አሳት ሰቂርቆስ ሕፃን

/መልክአ ሥላሴ፣ አርኬ 37፣ ስንኝ 3-5/

ከ4ኛውና ከ5ኛው ስንኝ ውስጥ «የአስጢፋኖስ ልብስ ድንጋይ » እና «የቂርቆስ ጌጥ እሳት» ጥቆምታ ሆነው ገብተዋል። እነዚህ ጥቆምታዎች የተገኙት ከመጽሐፍ ቅዱስ የሐዋርያት ሥራ እና ከድርሳነ ሚካኤልና ከገድለ ቂርቆስ ወኢየሉጣ ነው። አስጢፋኖስ በአይሁድ በድንጋይ ተወግሮ የተገደለ የመጀመሪያው ሰማዕት ነው /የሐዋ. 7፡54-60/። ደራሲው ድንጋይን ለሰማዕትነት ተለዋጭ አድርጎ ተጠቅሞበታል። እነዚህ ሁለት ስንኞች በዘይቤ የታሠሩ ናቸው። ደራሲው የሚያነሣው ልብስ በቁሙ ልብስ ሳይሆን የሥላሴ ምሕረት ሲሆን ራሱ ደግሞ በተራው አስጢፋኖስ በተወገረበት ድንጋይ ይገለጻል። ያው ልብስ በእሳትም ይገለጻል፤ እሳት በተራው ደግሞ በጌጥ እንደሚገለጽ። በእነዚህ ሁለት ስንኞች ውስጥ ዘይቤ በዘይቤ ላይ ተደራርቦ ይገኛል። ቅዱስ አስጢፋኖስ የተወገረበት ድንጋይና ቅዱስ ቂርቆስ የተጣሰበት እሳት በልብስና በጌጥ ተገልጸዋል፤ ሁለቱም ግን ስማዕትነትን የሚገልጹ ራሳቸው ገላጭ ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቆምታን በብዛት በዘይቤነት መጠቀም የመልክአ መልክእ አንዱ ባሕ ርይ ነው። ለምሳሌ በመልክአ ማርያም አርኬዎች 3ኛ ስንኞች ውስጥ ብቻ 20 መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቆምታዎች ሲኖሩ በመልክአ ኢየሱስ ውስጥ ደግሞ 12 አሉ። በመልክአ ማርያም ውስጥ በአጠ ቃላይ ከ50 በላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቆምታዎች ይገኛሉ። መልክአ መጥልሊ 12 አርኬዎች ያሉት ሲሆን በ12ቱ አርኬዎች 3ኛ ስንኞች ውስጥ 12 መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቆምታዎች አሉ።

የተጠቆሙት የመጽሐፍ ቅዱስ ባለታሪኮች 12ቱ ሐዋርያት ናቸው። የ12ቱን ሐዋርያት ተጋድሎና ድል በመጠቀም ድንግል ማርያምን ይገልጻል።

መልክአ ተክለሃይማኖት በተመሳሳይ ሁኔታ አንደ መልክአ መዮልሲ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቆምታን ተገልግሎብታል። ካሉት 57 አርኬዎች ውስጥ የ28ቱ አርኬዎች ሦስተኛ ስንኞች 24 የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችንና 4 የጓሳ ዘመን የቤተ ክርስቲያንን ቅዱሳን በተስዋጭነት በመጠቀም ባለመልክኡን ይገልፃል። በመልክአ መዮልሲ ከመጀመሪያው ቀጥሎ ያሉት አራት አርኬዎች ሦስተኛ ስንኞች አራቱን ወንጌላውያን በወንጌላቸው አፋጣመጥ ተራ በጥቆምታነት ይጠቀማል፡ ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፡ ዮሐንስ።

አንድ ምሳሌ ከመልክአ ተክለሃይማኖት እንጥቀስ ፦

ተክለሃይማኖት ለ.ቃስ ዓቃቢ ሥራይ
/መልክአ ተክለሃይማኖት፣ አርኬ 4፣ ስንኝ 3/

ይህ ስንኝ የወንጌላዊውን የለ.ቃስን ሐኪምነት በጥቆምታነት ይጠቀማል። ይህ ጥቆምታ የተክለሃይማኖትን በአማላጅነት በሽተኛውን የመፈወስ ኃይል ይገልጻል። የቅዱስ ለ.ቃስ ሐኪምነት የተገኘው ከቅዱስ ጳውሉስ መልእክት ነው /ቆላ. 4፡14/።

የዚህ ዓይነቱ ተሰዋጭ ዘይቤ በመልክአ መልክአ ውስጥ በብዛት የሚገኝ ነው። ይህም በቅዳሴ ማርያም ምዕራፍ 3 እና 4 ውስጥ በብዛት ያገለገለ ሲሆን ትርጓሜውን ማየት ብዙ ነገር ግልጽ ያደርጋል።

ሌላው የመልክአ መልክአ ዘይቤ ባሕርይ ተመሳሳይ ገላጮችን በብዙ መልክአ መልክአ ውስጥ መጠቀም ነው። ለምሳሌ ከዋክብት፣ ጨረቃና በሐይ የባለመልክቹን ፊት መግለጫ ሆነው በብዙ መልክአ መልክአ ውስጥ አገልግለዋል። ጥቂት ምሳሌዎችን እንመልከት ፦

መልክአ ማርያም የድንግል ማርያምን ፊት /ገፅ/ እንደሚከተለው ይገልፀዋል።

ሰላም ስገጽኪ ዘጥቀ ይልሂ
እምሥነ ከዋክብት መወርጎ ወእምሥነ ፀሐይ መላዘርሂ።
/መልክአ ማርያም፡ አርኬ 4፣ ስንኝ 1 እና 2/

ይህ ምስል ምናልባት ከመኃልየ መኃልይ የተወሰደ ሊሆን ይችላል።
መኑ ይእቲ እንተ ትሔውጽ ከመሳነ፡ ሠናይት ከመወርኀ ወብርህት
ከመ ፀሐይ /መኃ 6፡10/ ይሳልና። እንደመልክአ ማርያም ሁሉ የተክለሃይማኖት ፊት /ገፅ/ ፦

ዘይኤድም እምፀሐይ መወርጎ
/አርኬ 5፣ ስንኝ 2/

በመልክአ ስንበትም ፊት /ገፅ/ ሲገለጽ፦

ሰላም ለገጽኪ ጽዱል በራሕይ
አምሳሰ ፀሐይ
/አርኬ4፣ ስንኝ 1 እና 2/

በመልክአ ኪዳነ ምሕረት፡-

ዘይኤድም ሥኑ እምጸዳሰ ፀሐይ ወወርኀ
/አርኬ 5፣ ስንኝ 2/

በመልክአ ቁስቋም፡-

ሰላም ለርእስኪ ወለገጽኪ ሥነ ከከብ
/አርኬ 2፣ ስንኝ 1/

በመልክአ ኢየሱስ፡-

ሰላም ሰገጽክ እምሥነ አርያፌስ ስዙሕ
ወፍሡሕ ከመ ወርኀ ዘአሚ ገሃሀ
/አርኬ 4፣ ስንኝ 1 እና 2/

በመልክአ ገብረ መንፈስ ቅዱስ

ሰላም ሰገጽክ ዘያበርህ ምስብዒተ
እምብርሃነ ፀሐይ ዘይኮንን ወዘይመስል መዓልተ
/አርኬ 5፣ ስንኝ 1 እና 2/

ስለዚህ በመልክአ መልክአ ውስጥ የሚያገለግሉት አንዳንድ ዘይቤዎች /በተለይ መጻሐፍ ቅዱሳዊዎቹ/ በተለያዩ መልክአ መልክአ ውስጥ በተደጋጋሚ ይገኛሉ።

3.2 መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ዘይቤዎች

በመልክአ መልክአ ውስጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ያልተወሰዱ ዘይቤዎች አሉ። ዘይቤዎቹን ደራሲዎቹ ባላቸው ምናባዊ ምጥቀት ከአካባቢያቸው ያገኟቸው ናቸው።
አበባ በዘይቤነት ገብቶ እናገኛለን።

አስተጋብእ ውስተ ልብየ አቅማሃተ ኩሉ ጥበብ
ከመጽጌያት ዘገዳም ያስተጋብእ ጌሕብ
/መልክአ ኢየሱስ፣አርኬ5፣ ስንኝ 4 እና 5/

ይህ ተነፃፃሪ ዘይቤ የገባው የደራሲው/ደጋሚው የጥበብን ሁሉ ፍሬዎች **በልቤ** ውስጥ ሰብስብልኝ፣ የዱር አበቦች ንቦችን ወደራሳቸው እንደሚሰበስቡ ብሉ ልመናውን ስመግስጽ ነው። እዚህ ላይ ገላጩ አበባው ሳይሆን የአበባው ንብን የመሰብሰብ ኃይል ነው።

ሰላም ለከናፍሪከ ሙሐላተ ከርቤ ሐዋዝ

እምጽጌ ገጸማት ኩሉን ዘጺናሆን ምዑዝ
/መልክአ ኢየሱስ፣አርኪ 8፣ ስንኝ 1 እና 2/

ማርያም ምዕዝት አምነ ጽጌያት
/መልክአ ፍልሰታ ለማርያም፣አርኪ 8፣ ስንኝ 3/

ማርያም ድንግል ምዕዝት ዘአም ጽጌረዳ
/መልክአ ማርያም፣ አርኪ 58፣ ስንኝ 3/

ወለመላትሕከ ልሑያት አምሳላተ ጽጌ ዘበድው
/መልክአ ገብርኤል፣ አርኪ7፣ ስንኝ 2/

ሌላው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የልሆኑትና በተደጋጋሚ የሚገኙት ዘይቤዎች /ምስሎች/ በርካ መስከት ናቸው። በነዚህ ምስሎች የሚገለጹት የሰውነት ክፍሎች አፍንጫ፣ ጆሮዎችና ከንፈሮች ናቸው። አፍንጫ በመስከትም በዘርም ወይም ባንዱ ተገልጾ ይገኛል፤ በመልክአ ኢየሱስ /አርኪ 9/ ፣ በመልክአ ኪዳነ ምሕረት /አርኪ 10/፣ በመልክአ ማርያም /አርኪ 9/ እና በመልክአ ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ /አርኪ 9/።

ለምሳሌ የሚከተለውን እንመልከት፡-

ሰላም ለአእናፊከ ሌሥጋከ መዓዛዊ
አጣነ አርያም ምዑዝ እለ አዜንዋ
/መልክአ ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ፣ አርኪ 9፣ ስንኝ 1 እና 2/

ወለአእናፊከ ሰላም አናቅጸ ስኒን ወከረቤ
/መልክአ ፋኑኤል፣ አርኪ 7፣ ስንኝ 2/

ጆሮዎች በበሮች በመልክአ አማኑኤል /አርኪ 14/ እና በመልክአ ሥላሴ /አርኪ 8/ ውስጥም ተገልጸው ይገኛሉ።

ለአእዛኒከ ሰላም አናቅጸ ኩሉ ጸሎት
/መልክአ አማኑኤል፣ አርኪ 14፣ ስንኝ 2/

ከንፈሮች በበሮች ተገልጸዋል፡-

ሰላም ለአእናፊከ መዓዛከ ጺና ርጉው
ወለከናፍሪከ ዓዲ አናቅጸ ንባብ ፍትው
/መልክአ እግዚአብሔር አብ፣ አርኪ9፣ ስንኝ 1እና2/

ሌላው መነሣት ያለበት ምስል ለንቁ ነው። የተከበሩ ማዕድናት የባለመልክአ መልክኡን ጥርስ መግለጫ ሆነው አገልግለዋል። ስዎላሴ መልክአ ኢየሱስ /አርኪ 12/፣ መልክአ ቁስቋም /አርኪ 4/ ና መልክአ ገብርኤል /አርኪ 9/ ውስጥ የተከበሩ ማእድናት የባለመልክአ መልክኡን /ኢየሱስ፣ማርያምና ገብርኤል/ ጥርስ መግለጫ ሆነው ገብተዋል።

ወለአስናኒክ አዕናቁ ንዋያተ ሐX+ት ሠ አንፈርዕየ
/መልክአ ገብርኤል፣ አርኬ 9፣ ስንኝ 2/

በመልክአ መልክኡ ውስጥ አገልግሉት የሰጡ የባሕር አካላት፣ ሰማያዊ አካላት /ከከብ፣ ጨረቃ፣ፀሐይ/ አና ሌሉች ምሰሉች አሉ። ሰማያዊ አካላትን በሚመለክት ክዋክብት፣ ጨረቃና ፀሐይ የአንዳንድ ባለመልክአ መልክአን ዓይኖች ለመግለጽ አገልግለዋል። መልክአ ገብርኤል /አርኬ 6/፣ መልክአ ተክለሃይማኖት /አርኬ 7/፣ መልክአ ገብረ ክርስቶስ /አርኬ 2/፣ መልክአ አረጋዊ /አርኬ 5/ አና መልክአ ማርያም /አርኬ 6/ ክዋክብትን ለአይን መግለጫ ካደረጉት መልክአ መልክአ ውሰጥ ናቸው፣ መልክአ አረጋዊ ግን ፀሐይና ጨረቃን ነው የተጠቀመው።

ሰላም ለአዕይንትኪ ዘተመሰላ አብያዝ
/መልክአ ማርያም፣ አርኬ 6፣ ስንኝ 1/

3.3 የምሰሉቹ አገልግሉት

በመልክአ መልክአ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የምሰሉቹ አገልግለቶች ሁለት ናቸው። ሃይ ማኖታዊ እውነትን ማስተላለፍና መልክአ መልክኡን ውብ አድርጎ መግለጽ።

አንዱ የምሰሉቹ አገልግሉት ሃይማኖታዊ አውነትን ለልብ /ለምናብ/ ሳይሆን ለአእምሮ ማስተላለፍ ነው። የአንባቢውን ስሜት ለመያዝ አይደለም። ስዚህ ተገቢ የሚሆኑን ምሳሌዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰዱት ምሰሉች ናቸው። አነዚህ ምሰሉች በአብዛኛው በወኪልነት የሚገቡ ናቸው። በመልክአ ማርያም ውስጥ ድንግል ማርያም እንደሚከተለው ተገልጻለች።

ማርያም ድንግል ዘገጸመ ሲና ጳጦስ
/አርኬ 37፣ስንኝ 3/

የሲና ቁጥቋጦ /ዘጸ 1:1-4/ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የትርጓሜ መምህራን አተረጓጎም የድንግል ማርያምና የአግዚአብሔርን ልጅ የመጸነሲ ተምሳሌት ነው /ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም፣ ንባቡና ትርጓሜው፣ 1983: 51/:: ቁጥቋጦው የድንግል ማርያም ምሳሌ፣ እሳቱ ቁጥቋጦውን አለማቃጠሉ ድንግል ማርያም መለኮትን በማጎጸሳት ቃጠ ል የመሸከሚ ምሳለ. ነው:: ከዚህ ሌላም አንዱ አንዱን ሳያጠፋው የትስብአትና የመለኮት ተዋሕ ዶ ምሳለ. ነው፣ ምሥጢረ ሥጋዌ:: ሰለዚህ ገላፊዬ /የሲና ቁጥቋጦ/ አና ተገላፊዬ /ድንግል ማርያም/ ምክንያታዊ ዝምድና አላቸው።

ሁለተኛው የምሰሉቹ አገልግሉት ባለመልክአ መልክኡን በመጠቀ ቋንቋ መግለጽ ነው፣ ከይዘቱ ይልቅ ወደ ቋንቋ ውበት ያደላል። ይኼ በአብዛኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ ምሰሉች አገልግሉት ነው። አንዲህ ያሉት ምሰሉች ባለመልክአ መልክኡንና አንዳንድ ተጨማሪ ነገሮቹን የሚገልጡ ናቸው።

ትበእየከሙ አሰስ ይእዜ ቤተ ክርስቲያን ደብተራ
ከሙ ብእሲት ጎዝንት ዘቀበረት በኩራ
/መልክአ ጳጥርስ ወጳውሎስ፣ አርኬ 3፣ ስንኝ 3 እና 4 /

እዚህ ላይ የበኩር ልጇን የቀበረች ሴት ልቅሶ /ጎዘን/ ባስመልከስ መልክኡ /ጴጥሮስና ጳውሎስ/ መሥዋዕትነትን በተቀበሉ ጊዜ ቤተክርስቲያን ያዘነችውን ኀዘን የሚገልጽ ነው። ስለዚ ህም አገልግሎቱ የጀንጀውን አጠቃቀም የመጠቀ በማድረግ ስሜቱን ማስተላለፍ ነው።

በአጠቃላይ ምስሎቹ የተለመዱ ሲሆኑ አገልግሎታቸውም ማስተማርና የሚገለጸውን ነገር/ሀሳብ ባማሪ ቋንቋ መግለጽ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምስሎቹ ባላቸው የይዘት ተገቢነት የሚመረጡ ሲሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑት ደግሞ አንድን ነገር አጉልቶ አግዝፎ ለማሳየት በመቻላቸው ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምስሎቹ በአብዛኛው የተወሰዱት ከብሉይ ኪዳን መጻሕ ፍት ነው።

<u>የቢ መጻሕፍት</u>

መልክአ ጉባኤ፣ 1959 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት።

<u>መልክአ ጉባኤ</u>፣ 1988 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት።

<u>መልክአ ጉባኤ</u>፣ ብራና፣ ወሎ፣ ጀመዶ ማርያም ገዳም።

መልክአ ልደታ ለማርያም፣ ቀን አልተጠቀሰም፣ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት።

መልክአ ሥላሴ፣ 1972ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት።

<u>መልክአ ሐዲሳት ሠለስቱ፣ ንባቡና ትርጓሜው</u>፣ 1989ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

<u>መጻሕፍተ ሰሎሞን ወሲራክ፣ ንባቡና ትርጓሜው</u>፣ 1988ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

<u>መጽሐፍ ቅዱስ፣ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት</u>፣ 1980ዓ.ም አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ መ ጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት።

አያሌው ታምሩ /አለቃ/ ፣ መጋቢት 21 1992፣ ቃለመጠይቅ፣ አዲስ አበባ።

ኪዳነወልድ ክፍሌ /አለቃ/፣ 1948 ዓ.ም፣ መጽሐፈ ስዋሰው ወግሥ ወ መዝገብ ቃላት ሐዲስ፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ውዳሴ ማርያም ወቅዳሴማርያም፣ ንባቡና ተርጓሜው፣ 1983 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት።

Alemaychu Moges 1966E.C. "Ge'ez and Amaric study without Qene is incomplete " ***<u>Proceedings of the Third International Conference of Ethiopian Studies,</u>*** Vol. III, Addis Ababa, Haile Sillassie I University, pp. 99-116.

Ference, Alexander, 1985. "Writing and Literature in Classic Ethiopic (Giiz) " ***<u>Literature in African Languages: Theoretical Issues and Sample Surveys.</u>*** Andrzejwski, B. and etal (eds.) Cambridge: Cambridge University Press. Pp. 279 - 298

Harden, J.M. 1926. ***<u>An Introduction to Ethiopian Christian Literature</u>*** London: Luzac And comp.

Hyatt, H.m. 1928 ***<u>Church of Abyssinia.</u>*** London: Luzac and com.

Pedersen. Kristen. 1989. "The'Mälkë : An Ethiopian prayer form with Latin Origin?" ***Proceedings of the 8th International Conference of Ethiopian Studies.*** Taddesse **Beyene** (ed). Addis Ababa: Institute of Ethiopian Studies. Pp. 547 - 560.

Rundgren, Friethof. 1986. "Old Ethiopic Mälkë" ***Proceedings of the 7th International Conference of Ethiopian Studies.*** Addis Ababa: Institute of Ethiopian Studies. Pp 59-60

ማእዝ ትላንት፣ ዛሬና ነገ

ዲ/ን መርሻ አለሽኝ
ማኅበረ ቅዱሳን /የሐመር መጽሔት ዋና አዘጋጅ/
/ስ.ቁጥር 556328/
Email mershing@yahoo.com



ዲ/ን መርሻ አለሽኝ የጥናት መረቀታቸውን ሲያቀርቡ

1.መግቢያ

ሰኢትዮጵያ ታሪክ መልኳና ውበቷ ነው። ባሕሏ ሽልማቷና ጌጧ ነው። ጥንታዊ ሥልጣኔዋና ጥንታዊ ባሕሏ ከራሷ የመነጩ ናቸው። ይህንንም ታሪኳ ይመሰክራል። ሥርዓተ መንግሥትንና ሥርዓተ ከሰትን በዘመነ ብሉይ ጀምራ በሥጋዊና በመንፈሳዊ ሥልጣኔ የተጓዘችበት የታሪክ ጉዳና እጅግ ሰፊ ነው። ዘመር ብሉ በዐይነ ልቡና ለሚያስተውለው ወለል ብሎ ይታያል።

ከሥልጣኔዋ ብርታት የተነሣ ከትከሸዋ ሽማ ከእጇ ዶማ፣ ከአንደበቷ ዜማ ጠፍቶ አያውቅም። የዛሬን አያድርገውና ቆፍሮ፣ አርሶ፣ ዘርቶ፣ አምርቶ የልዩ ልዩ ሲሣይ ባለቤት መሆንና እንደልብ መቃምና መኰረስ፡ መርቅንና ብርን አንተሮ ማሬዋን ብረታ ብረትን ቀጥቅጦ ባለ መሣሪያ መሆንን ከራሷ ያገኘችው ፍልሰፍና ነው።

ሥዕሎችን፣ ቅርፆችንና ሐውልቶችን በራሷ ፈልስፋ አቆይታናለች። በአድናቆትም እንመለከታቸዋለን። ሌሎችም በአድናቆት ይመለከቷቸዋል። መንፈስን በደስታ ለሚያረኩና ለሚያድሉ ባሕላዊ ጨዋታዎች፣ ዘፈኖች፣ ውዝዋዜዎች፣ እሰክሰታዎች፣ ሜዳፈሪዎችና አንቅስቃሴዎች ሁሉ አሳማሪና አስተባባሪ እንጅ ተደናጋሪ፣ ተቸጋሪ አይደለችም።

ከዕውቀት ጣማቷ፣ ከመፍጠር ግሩም ክሂሏ የተነሣም የማንም እጅ የሌለበት ለጽሑፍ የተቃና ለጆሮ የማይጐረብጥ ፊደል ቀርጻ ከልጆቿ አልፎ ዓለምን ጉድ ያሰኘ ታሪክ፣ ትምህርት፣ ፍልስፍና፣ ሒሳብ ወዘተ. ጽፋለች። ከነዚህ የክታብ ዓለሞቿ በፈቃደኝነት ለገባባቸው ውጤ ውጤ

እንደማይሉ ገብተው በዚያው የቀሩት በአጽንኦት ሲናገሩ ይሰማሉ::

ታዲያ በዚህ ሁሉ ድንገል ኢትዮጵያዊ ሀብትና ሀብቱ የእሱ ሀብት ባልመሰለው ወይም እንዲሆን ባልፈለገው በዛሬው ትውልድ መካከል ሁሉም ተባብሮ ሊጠግነውና ሲያንጸው የሚገባ አንድ ድልድይ አለ:: ለመሆኑ ይህ ድልድይ ማነው? ውርስና መራሽ ይገናኙበት ዘንድ ሊታነጽ የሚገባው ድልድይ የግእዝ ቋንቋ ነው::

ጥናቱ የዚህን ቋንቋ የትሳንት ገጽታ በማተት ይጀምራል:: የትመጣውን /Origion/ በሚመለከት ሊቃውንት ከስነዘሯቸው አስተያየቶች ለንጽጽር ጥቂቱን በማቅረብ ቋንቋው ትሳንት ያዘረከታቸውን አስተዋጽኦዎች በመጠኑ በመመልከት የመጀመሪያው ክፍል ይጠናቀቃል::

የቋንቋውን የዛሬ ሁኔታ የሚያትተው ሁለተኛው የጥናቱ ክፍል ደግሞ የተለያዩ ለዎች ስለ ግእዝ ቋንቋ የዛሬ ሁኔታ የሚሰነዝሯቸውን አስተያየቶች እየዘረዘረ ያብራራል::

በጥናቱ የመጨረሻና ሦስተኛ ክፍልም የጥናቱ አቅራቢ የማሰብ ችሎታው በፈቀደለት መጠን ቋንቋው ያንሠራራ ዘንድ ነገ ምን መደረግ እንዳለበት ይጠቁማል::

የዚህ ጥናት አቅራቢ የግእዝ ቋንቋ ነገ ማንሠራራት አለበት ሲል ግእዝን በቋንቋነቱ ስለሚወደውና ብቻ ሳይሆን ቋንቋው ይዞት ጋደም ያለው ሀብት ብዙ፣ በጣምም ብዙ ከመሆኑ አንጻር የተሰወረው እንዲገለጥ ስማድረግ ነው::

2. ግእዝ ትሳንት ዛሬና ነገ

2.1. ትሳንት

2.1.1. የትመጣ?

የግእዝን ፊደል ቀጥረው፣ በግእዝ ቅኔ ከተቀኙት ከቤተ ክህነት ሊቃውንት ጀምሮ ግእዝና ዘመናዊ ትምህርት እስካጣጣሙት ሠይፍ ዘክልኤ እቱሀ የሆኑ ምሁራን ድረስ ስለ ግእዝ ቋንቋ ጥንታዊነትና ኢትዮጵያዊ መሠረታዊ ሀብትነት በብዕሮቻቸው ቃኝተዋል:: ምንም እንኳን ሁሉም ስለ ቋንቋው ጥንታዊነትና ታላቅ ሀብትነት የሚስማሙ ቢሆንም የቋንቋውን የትመጣ በሚመለከት በሚስጡት አስተያየት አልፎ አልፎ መለያየት ይታይባቸዋል:: የመጀመሪያ የስው ልጅ ቋንቋ እንደሆነ ገልጠው ስጠታኑንም ከእግዚአብሔር ጋር ከሚያያይዙት እንጀምር::

ለቋንቋውና ለባሕሉ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ የእርሱ ያልሆነውን ስመውሰድ ሲሻማ በሚውለው ቀላዋጭ ትውልድ እና በግእዝ እንዲሁም በእርሱም በኩል በገንዘብ በማይተመነው ኢትዮጵያዊ ሀብት መካከል ድልድይ በመፍጠር ቀላል የማይባል ሥራ የሠሩት አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ የግእዝን ቋንቋ «የመጀመሪያ የሰው ልጅ ቋንቋ ነው የተስጠውም ከእግዚአብሔር ነው» ይላሉ::

...ከአዳም ከሞኅ ከእባት ከናቷ
ለሴም የታጨች ስለ ውበቷ
ከንጉሡም ከእግዜር ከባስቤቷ
ስለተለጠች እቴጌነቷ
እንዲህ ብታይዋት ደሃ መስላችሁ
ባለጸጋ ናት ግእዝ ቋንቋችሁ

/አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ 1948፣184/

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ በዚህ ግጥማዊ ገለጻቸው የቋንቋውን አመጣጥ ከአግዚአብሔር ጋር ከማያያዛቸው አልፎ የቋንቋውን ባለጠግነት በማገለጽ ትውልዱ ያንን ተረድቶ እንዲማርና የሀብቱ ወራሽ እንዲሆን መክረዋል። አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ሰለ ቋንቋው የትመጣ ባላቸው አቋም አጋዥ ተባባሪ አግኝተዋል። ክነፈ ርግብ አታለል። እኒህ የቋንቋው ሊቅ ደግሞ «ግእዝ ማለት እንደኛ መጀመሪያ ማለት ነው» በማለት ከቃሉ ፍቺ በመነሣት የቋንቋውን አዳማዊነት ለማስረገጥ ሁለት የውጭ ሀገር ምሁራንን ጠቅሰዋል። «... ይህን መሠረት በማድረግ ሲዳ ጳውሎስና መልእክተ ዮሐንስ የተባሉ ሁለት ጀርመናውያን ሊቃውንት 'ልሳነ ግእዝ የአዳም ቋንቋ ነው' ብለውታል» ይላሉ። /ክነፈ ርግብ አታለል፣ አዲስ ዘመን፣ ታኅሣሥ 25፣ 1978፣3/

ይህንኑ ሐሳብ ዶ/ር ኢሳይያስ ዓለሜ እንግዳም ቀደም ሲል «ግእዝ ከአግዚአብሔር ሰለ መውረዱ አብደልመጅድ አቢድን የተባለ ዐረብ በካይሮ ዩኒቨርሰቲ የኢትዮጵያ ቋንቋ መምህር «በደነአል ሐበሻ-ወአል-ዐረብ፡ በሐበሻና በዐረቦች መካከል» በሚል መጽሐፉ «ግእዝ ከሰማይ የወረደ ቋንቋ በማለት ጽፏል» ሰሉ ገልጸው ነበር። /ኢሳይያስ ዓለሜ እንግዳ፣ አዲስ ዘመን፣ ሰኔ 14፣ 1977፣ 3/

በሁለተኛው ጉራ የሚታዩት አሰተያየት ሰጭዎች ደግሞ ምንም እንኳን አስተያየታቸው ቋንቋውን ከጊዜ በኋላ የመጣ ባያደርጉትም ከላይ ከተጠቀሱት ሊቃውንት ለየት የሚል አስተያየት የሚሰጡት ናቸው። ከእነዚህም ምሁራን ቋንቋውን ከሌሎች ቋንቋዎች ጋር በ ማነጻጸርና ከተናጋሪው ጉሣ ጋር በማገናኘት የሰጡትን እናቅርብ።

ደራሲ ማሞ ሙድነህ ቋንቋውን ጥንታውያት ከሆኑት የግሪክና የላቲን ቋንቋዎች ጋር በ ማነጻጸር እንዲህ ይላሉ። «... አስከ ዛሬ ድረስ በቤተ ክርስቲያን ሥራ የተያዘበት ሴማዊው የሆነው ጥንታዊ የግእዝ ቋንቋ እጅግ የተጣራ በመሆኑ ለግሪክና ለላቲን ቋንቋ ተወዳዳሪ ለመሆን ይቃጣዋል» ይበሉ እንጂ በቀረው ጽሑፋቸው ስለ ቋንቋው ጥንታዊነት በሰፊው አትተዋል። ሙሉውን ጽሑፍ ይመለከቷል።

የግእዝን ቋንቋ ከሀገር ውስጥ ቋንቋዎች ጋር በማነጻጸር በማንባር ፣ቀደምትነት የሚያበልፉት ሌሳው ሊቅ ደግሞ «አማርኛም ሆነ ትግርኛ እንዲሁም ሌሎች የአሁኑ ቋንቋዎቻችን ሪጅም ሰድሜ አንደሌላቸው ግልጽ ነው።... ኢትዮጵያ ከሠለጠኑ የድሮ ሕዝብ ውስጥ የሚያስቆጥራት አንደኛዋ ሀብቷ... ጥንታዊ ቋንቋዋ ግእዝ ነው።» ይላሉ። /አባ ተክስተ ብርሃን ግ/መድኅን፣ 1962፣3/

አሁን ደግሞ የቋንቋውን አመጣጥ ከተናጋሪዎቹ ሕዝቦች /ጉሣዎች/ ጋር በማያያዝ አስተያየታቸውን የሰጡትን ሊቅ እንጥቀስ።

ግእዝ ግእዛውያን አግአዝያን ወደ ብሔረ አግአዚ የተሻገሩበት ዘመን 700 ዓመት ተጌታችን በፊት ነው ይባላል ዘመኑ። ከነዚህ አግአዝያን ቀደም ብሰው የመጡም ሐበሻት የተባሉ አንድ የዓረብ ዘር ሰሐርታን ከተባለ ከባሕር ጠረፍ የሚገኝ ከየመን አውራጃ ተነሥተው ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ነበር። ሲሻገሩ በየትኛው ባር እንደመጡ አይታወቅም። ባብአል መንደብ /ኖኅተ ምንጻቤ/ የድንገት ደጃፍ ከተባለ ከኤርትራ ባሕር ከሕንድ አገር ውቅያኖስ በሚገኝበት ጠበብ ያለ ቦታ መሻገራቸው ወይም በምጽዋ ጠረፍ ብቻ አዱሊስ መርሶ በሚባለው

በር መምጣታቸው አይታወቅም፡ የሚመስለው ነገር በዚህ ብቻ መግባታቸው በተውት ስምና በጻፉት ድንጋይ በተከሉት ሐውልትና ባቋቋሙት መንግሥት ያስረዱናል። ... ከተባለው ዘመን ፊት ግእዝ ወደ ኢትዮጵያ ደረሱ። ለአገሩ የሚሆን ቋንቋ ይዘውም ገቡ። መምጣታቸው ሳባ ከሚባል ደቡባዊ ዐረብ አውራጃ ነው። ያመጡትንም ቋንቋ እንደ ባሕርያዊ አካሄድ ከአገሩ ቋንቋ ጋር በትንሽ ተሰማምቶ ተቀላቅሎ ግእዝን ወለደ።...»

/ገ/ኢየሱስ ኃይሉ /አሳ/፣ 1939፣ 30/

እንግዲህ ሰለ ግእዝ ቋንቋ የትመጣ ከሊቃውንቱ አስተያየት እነዚህን ከጠቀስን «የትኛው ትክክል ነው?» ለሚለው ጥያቄ ሁሉም የየራሱን መልስ ይሰጥ። ችሎታን ከመኑ ጋር አስተባብሮ የያዘ መዛግብትን በማገላበጥ ሌሎች ሊቃውንትን በማነጋገር ይመራመርና እውነታውን ይረዳ። የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ግን ወረቀቱን ሊጽፍ ሲነሣ ዓላማው ይሽ ስላልሆነ በአጭሩ እንዲህ ብሎ ያልፈዋል። ግእዝ ኢትዮጵያዊው ቋንቋችን ጥንታዊ ነው። በራሱ ዜጐች አማካኝነት በራሱ ፊደል የተቀመረ ኢትዮጵያውኛ።

2.1.2. አገልግሎት

ግእዝ ከአግዚአብሔር ለአዳም ይሰጥም ከነገር በኋላ የአዳም የብዙ ጊዜ ዘሮች ለመግባቢያነት ይፍጠሩት፣ ትነጋት በመግባቢያነትም ሆነ በጽሑፍ ቋንቋነት ከፍተኛ አገልግሎት ለዘመነኞቹ ሰጥቷል። ይህንን አገልግሎቱን ሃይማኖታዊ እና ብሔራዊ አገልግሎት በማለት ልንመለከተው እንችላለን።

ሀ. ሃይማኖታዊ አገልግሎት

የግእዝ ቋንቋ እንደ ጥንታዊ ቋንቋነቱ ጥንታዊትና ብሔራዊት በሆነችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ እገልግሎት ሰጥቷል። እየሰጠም ነው። ይህን አገልግሎቱን በሁለት ከፍለን እንየው። በመግባቢያ ቋንቋነትና በጽሑፍ ቋንቋነት በሚል።

ሀ.1. በመግባቢያ (በመነገሪያ) ቋንቋነት

የግእዝ ቋንቋ የቀደመ የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ ነው። ደራቢ ማሞ ውድነህ የቋንቋውን ቀዳሚ የሥነ ጽሑፍ ቋንቋነት ሲገልጹ «... ከክ.ል. በኋላ በ300ኛው ዘመን ሲጀምር ጽሕፈቱና ንግግሩ የተጣራ በግእዝ ቋንቋ ከሐውልት ላይ የተጻፈ መታሰቢያ አለ» ብለዋል። /ዝኒ ከማሁ/። ይህን የቋንቋውን ጥንታዊነት አባ ገ/ኢየሱስም በሚሰሯቸ በሚሰደገፍ ሲገልጹ «መጀመሪያ በአክሱም መንግሥት ጊዜ ከድንጋይ ላይ የተጻፈ የሐውልቱ ማሰሪጃ የሚሆን አለ።» ካሉ በኋላ ሰንዓፈ በተባለ አካባቢ በተገኘ ድንጋይ ላይ የተጻፈ ያሉትን ጽሑፍ አስቀምጠዋል። ይህ የድንጋይ ላይ ጽሑፍ «ዘሐወሰተ ዘአግበረ እገዘ ለአበውሁ ወሰሐበ ወሐዘተ አወፀ አሰፈነ ወደበለነ» ይላል። /1939፣31/።

የግእዝ ቋንቋ የራሱ የሆነ መነሻና የጽሕፈት ባሕል ያለው በዘሩ በርካታ ሃይማኖታዊ ታሪካዊና የፍልስፍና መጻሕፍት ተጽፈውበታል። ተተርጉመውበታል። ከሃይማኖታዊው ብሉያቱን፣ ሐዲሳቱን፣ ድርሳናቱን፣ ገድላቱን፣ ተአምራቱን፣ ቅዳሴያቱን፣ ውዳሴያቱን ወዘተ መግለጽ ይቻላል። ከታሪካዊው ደግሞ ከብረ ነገሥትን፣ ፍትሐ ነገሥትን ወዘተ መጥቀስ ይቻላል። ከፍልስፍናውም መጽሐፈ ፈላሰፉ ጠቢባን፣ አንጋረ ፈላሰፋ፣ አዙሻህር ወዘተ ይጠቀሳሉ።

የግእዝ ቋንቋ ቀዳሚ የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ በመሆኑ ያልዳሰሰው የዕውቀት ዘርፍ የለም። ይህንን ሐሳብ ከነፊ ርግብ አታለል የዲልማንን ምስክርነት በመጥቀስ ያስረዳሉ። «በዚህ ዓይነት አውገስት ዲልማን የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ሁሉንም አርእሰተ ጉዳዮች የዳሰሰና ያቀፈ መሆኑን ገልጾ ግእዝ ሰኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለአውሮፖውያን ሊቃውንት ሁሉ ተወዳጅና ተፈላጊ ቋንቋ መሆኑን አልደበቀም።» /ከነፊ ርግብ አታለል፣ አዲስ ዘመን፣ ታኅሣሥ 25፣ 1978፣4/

ይህንኑ የግእዝን ቋንቋ ባለሰፊ አድማስነት ኢትዮጵያዊው ምሁር ሊቀ ጠበብት አክሊለ ብርሃን ወ/ቂርቆስ ባሚረ ቋንቋቸው ሲገልጹ «ከእኔ የበለጠ ጥናት ያለው መኖሩን ሳልዘነጋ በቀድሞ ዘመን አባቶቻችን እንደምን ያለ የሥራ በዴ እንደነበራቸው በእምነትና በአስተዳደር፣ በሥነ ሥዕልና በሥነ ጽሑፍ፣ በሐረግና በቅርጸ ቅርጽ አኳኋን ከፍተኛውን ደረጃ ይዘው እንደነበሩ በየገዳማቱና በየአድባራቱ እየዞርሁ ስመለከት ብዙዎቹ የብራና መጻሕፍት ገበታቸው የወረቅ የሆነ የብዕራቸውን አጣጣልና የብራናቸውን ንጽሕና፣ የቀረጻቸውን ማማርና ውበት ሲ መለከቱት በውነት የእነርሱን መልክእና ቅርጽ የኑሮ ቤት አድርጉ መኖር እንጂ በዚህ ዓለም በሥጋዊ ኑሮ ታስሮ መኖርን አያስመኝም። ...በሀገራችን በኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም እግረ ጎሲና ያልደረሰበት፣ የእእምሮ ከንፍ ያልበረበረበት፣ ያሰተበረበረ፣ የተሸሸገ ጥበብና ያልተሞከረ ስውር ፍልሰፍና፣ ያላበሳ አዲስ ተግባርና ከዚህ በፊት ያልተከፈተ የዕውቀት ጉዳና፣ ሀይን ያላየው፣ ጆሮ ያልሰማው፣ በጥበበኞች ልብ ያልታሰበ ብልሃትና ሥነ ጽሑፍ እንዳለን መፈለግና መሻት ፈልጐም ማግኘትና አግኝቶም በፍሬውና በመልኩ መጠቀም ከአሁኑ ትውልድ የሚጠበቅ አዲስ ተስፋ፣ አዲስ የምሥራች መሆኑ እንዳይዘነጋ...» ብለዋል። /አክሊለ ብርሃን ወ/ቂርቆስ /ሊቀ ጠ በብት/ ፣28 /። እውነት ነው። በንባብ፣ በዜማ፣ በቅኔና በትርጓሜ መጻሕፍት ተማሪ ቤቶች ሲ ሰጥ የኖረው ትምህርት በዘመናቸው እጅግ ተፈላጊዎች የነበሩ ሊቃውንትን ከማፍራቱም በላይ ለትውልደ ትውልድ የሥነ ጽሑፍና የባሕል ቅርስ አውርሷልና።

ዛሬ በየትም ሀገ ይኑር በየትኛውም የ«እምነት ክፍል» ይኑር፣ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚመረምር ማንም ሰው የግእዝን ቅዱሳት መጻሕፍት ሊያይ ይገደዳል። ከላይ እንደተባለ የቋንቋው ሊቃውንት «ያልበረበሩት የተሸሸገ ጥበብ፣ ያልሞከሩት ስውር ፍልሰፍና፣ ያልከፈቱት የዕውቀት ጉዳና...» የለምና። አባ ተክሰተ ብርሃን እንዲህ ይላሉ።

> የቅዱሳት መጻሕፍት ሊቃውንት ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜና ታሪክ ሲመረምሩ የግእዝ ቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜን ሳይጠቅሱ አያልፉም። ምክንያቱም ለምስክርነት በቂ ከሆኑት የቅዱሳት መጻሕፍት ጥንታውያን ትርጓሜያ*ች አንዱ ግእዝ ስለሆነ ነው። /ዝኒ ከማሁ/

በቋንቋው የተጻፉና የተተረጉሙ ቅዱሳት መጻሕፍትን ቀደም ሲል የቋንቋውን ጠቃሚነት የተረዳው ተረድቶም የተወሰኑ ሥራዎችን ለመሥራት የሞከረው ዲልማን በመጽሐፉ ዘርዝሮ አስቀምጧል። እርሱ የዘረዘራቸውን በዚህች አጭር ጽሑፍ አካትቶ የማዘርዘር ማስታወሻ ከ ማድረግ የዚህ ጥናት አነባብያን መጽሐፉን እንደምንም ብለው በማግኘት እንዲያነቡ መጋበዙ ይበጃል። ይህ አርእስት ሲጠቃለል ግን የግእዝ ቋንቋ ዛሬ ጆሮ ያልሰማቸው፣ ዓይን ያላያቸው፣ በእጅ ያልተዳሰሱ፣ በኅሊና ያልተመረመሩ፣ በርካታ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ አንድም የደለበ ሀብት የያዘ ቋንቋ ነው በሚል ይዘናል።

ለ. ብሔራዊ አገልግሎት

የዛሬን አያድርገውና የግእዝ ቋንቋ ትሳንት «መንግሥት» ያጸደቀው ሕገቡ ናፍቆ የወደደው ብሔራዊ አንድም የአፍ መፍቻ ቋንቋ ነበር። ሊቃውንት የቋንቋውን የአፍ መፍቻነት አድማስ ሲገልጹ በተለያየ መንገድ ነው።

ከነፈ ርግብ አታለል ቋንቋው አፍ መፍቻነቱ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ ነበር ይላሉ። ግእዝ ቀደም ባሉት ዓመታት በኢትዮጵያ ከርሙ ምድር ለኢትዮጵያ ዜጐች ሁሉ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሆኖ የቆየ፣ በሥነ ጽሑፍ የበለጠገ ኢትዮጵያውያንን በዓለም የሥነ ጽሑፍ መድረክ ያስተዋወቀ፣ በስፋቱም ከሌሎች ጋር የሚመጣጠን ቋንቋ ነበር» /ከነፈ ርግብ አታለል፣ አዲስ ዘመን፣

ታኅሣሥ 25፣ 1978፣ 3/

አውግስት ዲልማን ደግሞ «የቀድሞው የአቢሲኒያ ብሔራዊ ቋንቋ የነበረው ልሳነ ግእዝ የሚለው ሰም ከቤተ ክርስቲያን ትምህርት ተወስዶ በሸዋ በጉንደርና በትግሬ ለሚገኙ ነዋሪዎች የመነጋገሪያ ቋንቋ ሆኖ እንደ ቆየ የታሪክ ትርሶች ይመሰክራሉ።... በዚሁም መሠረት መንግሥታቸውን ኢትዮጵያ ብለው ሲጠሩ ብሔራዊውን ልሳን ደግሞ «ልሳነ ኢትዮጵያ» ብለውታል። የሕዝቡ የመጀመሪያ የመነጋገሪያ ቋንቋ በዚያን ጊዜም ሆነ ቆይቶ ግእዝ ሆነ። ቀስ በቀስም የሕዝቡ ብሔራዊ መታወቂያ የአንድነቱ ምልክት ሆኖ የበላይነትን ሥልጣን ተረክቧል። /ዲልማን–በክነፈ ርግብ አታሰል ውስጥ፣ ዝኒ ከማሁ/

በዚህ ወረቀት እነዚህን የተሰያዩ ሐሳቦች ስማበታረቅ ያበቸግራል። የጥናቱም ዓላማ አይደለም። ነገር ግን በሁለቱም ጉራዎች ያሉትን ሐሳቦች ሰንመረምር አንድ የጋራ የሆነ ሐሳብ አናገኛለን። ይኸውም የግእዝ ቋንቋ በኢትዮጵያ በአፍ መፍቻ ቋንቋነት ማገልገሉን። ይህንን አንደ ብሔራዊ አገልግሎት በመቁጠር በዚሁ አንጻር ሌሎች ብሔራዊ አገልግሎቱን እንጥቀስ።

የግእዝ ቋንቋ በቤተ መንግሥቱ ፍቁድ የሆነ፣ በሕዝቡም የተወደደ ቋንቋ የነበረ በመሆኑ በባለሥልጣናቱ አጋዥነትና ትእዛዝ ዛሬም ድረስ ለመንግሥታዊው ሥራ የሚያገለግሉ መጻሕፍት በቋንቋው እንዲተረጐሙና እንዲጻፉ ሆነዋል።

ግእዝ በብሔራዊ ቋንቋነት የሰጠውን አገልግሎት ዲልማን ሲገልጽ «ግእዝ በሥነ ጽሑፍ ይዘቱ ለቤተ ክርስቲያንና ለሃይማኖት የሚሰጠው አገልግሎት በክፍተኛ ደረጃ አያደገ መጣ። በዚያን ጊዜ በተለይ በታሪክ፣ በሕግ፣ በዘመን አቆጣጠርና በሒሳብ ላይ የጻበረ የሥነ ጽሑፍ ክምችትን አላይቷል። የተለያየ ዓይነት ያላቸው የመጀመሪያዎቹ ሥራዎች የተስፋፉት ግን ጎብረተሰቡ በቋንቋው የመጠቀም ሁኔታ ዕድገት ባሳየበት ጊዜ ነው። ይህም ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከ14–17ኛው መ.ክ.ዘ ድረስ ሲሆን፣ ከእነዚህም መካከል የህገሪቱ ዜና መዋዕል የመጀመሪያውን ደረጃ ይዞ ይገኛል።» /ዝኒ ከማሁ/

ሐ. ቋንቋዎችን በመውሰድ

ይኸኛው ርዕስ ብሔራዊ አገልግሎት በሚሰው ህቢይ ርዕስ ሥር ሊካተ የሚችል ቢሆንም ከጉዳዩ ጥልቅነት አንጻር ራሱን ችሎ ቢታይ ይሻላል። በቋንቋ ጥናት ዘርፍ የተሠማሩ ሊቃውንት የኢትዮጵያን ቋንቋዎች በአራት መደብ ከፋፍለው ያበቀምጧቸዋል። ሴማዊ፣ ኩሻዊ፣ ኦሞእዊ እና ኒሎ ሰሃራ በሚል። ከእነዚህ ውስጥ ሴማዊ በሚለው መደብ የሚያበቀምጡዋቸው ግእዝ፣ ትግሬ፣ ትግርኛ፣ አማርኛ፣ ጉራጊኛ፣ ሐረሪኛ፣ አርጉባና ጋፋት የሚባሉትን ቋንቋዎች ነው። የእነዚህን ቋንቋዎች ታሪክ ስንመለከት ከላይ አንጻየነው ጥንታዊ የሆነውና አበከ ብሔራዊ ቋንቋነት ደርሶ የነበረው የግእዝ ቋንቋ ነው። ከዚህ አንጻር ከአንጋፋው የግእዝ ቋንቋ ጋር አብረው የተመደቡት ሌሎች ቋንቋዎች ከግእዝ የመጡ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል።

አባ ገ/ኢየሱስ ኃይሉ የሉም ተብለው ከተቀመጡት ቋንቋዎች ውስጥ ትግሬን፣ ትግርኛንና አማርኛን «በቀጥታ ከግእዝ የወረዱ» ሲሏቸው ጉራጌን፣ ሐረሪን፣ አርጉባንና ጋፋትን ደግሞ «በጉን ከግእዝ የመጡ» በማለት ያበቀምጧቸዋል። አባ ገ/ኢየሱስ «በጉን ከግእዝ የመጡ» ያሏቸው ቋንቋዎች አንዴት ከግእዝ ተወልደው ሊስፋፉ አንደቻሉ ሲያስረዱ «የመንግሥት ወታደሮች ባደሩበት ቦታ ከአገሩ ስዎች ተቀላቅለው ከዚያ ተተክለው ቋንቋቸውን ከሊዳማ ወይም ከሌሎች አስማምተው እኩሉ ግእዝ መሳይ አኩሉ ሌላ ቋንቋ ያላቸው ናቸው» ይላሉ። /ገ/ኢየሱስ /አሜ፣ 1936፣ 34/።

ከላይ ከተጠቀሱት ቋንቋዎች በዕድሜ ቀደምት የሆነው የግእዝ ቋንቋ መሆኑን በማሥረገግ የቀሩት ስድስት ቋንቋዎች እንዴት ከግእዝ እንደተወለዱ ሊያስረዱ የሚችሉ ቃላትን እናቅርብ፡

ግእዝ	ትግርኛ	ትግረ	ሐረር	አማርኛ	ጉራጌ
ሐማት	ሐማት	ሐማት	ሐማት	አማት	አማት
ዕዕ	ዕዘይቲ	ዕዳይ	ኢንዚ	ዕንጨት	እንተት
ሐሢር	ጎሢር	ጎሬጩር	ሐቲር	አጭር	አጭር

እንግዲህ በዚህ ዓይነት የግእዝ ቋንቋ ዛሬ በብሔራዊ ቋንቋነት ደረጃ እያገለገለ ያለውን አማርኛን ጨምሮ ሌሎች አምስት ቋንቋዎችን እንደወለደና ወልዶም እንዳሳደገ እንረዳለን።

2.2. ዛሬ

የግእዝ ቋንቋ ዛሬ ያለበትን ሁኔታ ሁላችንም እናውቃለን። የምናውቀው ግን በውቀን የምናምንበትን ብቻ ነው። ከዚያ የቀረ ዓለሙ እንደመሰለው የሚናገረውን አንቀበልም። ስንፍናችን ሆነና ዛሬን የምንኖር ትውልዶች የግእዝን ቋንቋ እናውቀውም። በብዛት እንዳሚታየው ለማወቅም ፈቃደኞች አይደለንም። ከዚህ የተነሣ ቋንቋውን ባለመላለሰ አእምሮአችን አስበን ግሱን ባልቆጠረ ምላሳችን ሰለ ግእዝ የምንናገረው ብዙ ብዙ ነው። ከሰ ግሁኣትው ምናልባትም እኔ ካልኳቸው ጥቂቱን እየጠቃቀስኩ የታየኝን ልበል። መወያያም ይሆኑናል።

ሀ. ግእዝ ዘመን ያሰፈሰበት ቋንቋ ነው

ምንም እንኳን ወደንና ፈቅደን እያደረግነው ቢሆንም ጥሎብን እኛ የዛሬዎቹ ከቋንቋችን ቋንቋቸውን፣ ከባሕሳችን ባሕሳቸውን፣ ከእምነታችን እምነታቸውን፣ በሠቅሉ ከማንነታችን ማንነታቸውን እንመርሳለን። የዚህ ሙድቀታችን አስተያየኒነት የበለጠ የሚገለጠው ገዝፎ መልቶ የሚታየው ዴግሞ ሰምን ወደነሱ እንደሄድን ሳንጠየቅ የሠናቀርበው ምክንያት ሲሰማ ነው። ባሕላችን ኋላ ቀርና ለዕድገት የማይመች፣ እምነታችን ኑታችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ መዘተ... እንላለን። ለምን ቋንቋችንን ትተን ወደ ሌሎቹ ቋንቋ እንደሄድን የምንሰጠው ምክንያት እንዲህ ያሙም ሳንጠየቅ በርዕሰነት እንደያዝነው ዓይነት ሰባራ ምክንያት ነው። «ዘመን ያለፈበት ቋንቋ ስለሆነ...»። ይህን ሐሳብ የሚሰጡ ሰዎች የእነሱ ተናጎጅነት ሳያንስ የቋንቋውን ጥቅም ሠሙቀው እያጠኑና እያሰጠኑ ያሉ አንዳንድ ሰዎችም አብረዋቸው እንዲነጉዱ ይቀሰቅሳሉ። ከመሬት ተነሥቶ ቋንቋውን ያጠገዘን እንድ ጽሑፍ እንጥቀስ።

> ...የግእዝ የንግግር ቋንቋ... ከብዙኃኑ ጆሮ ከራቀ ብዙ ትውልዶች በ ሚለፋቸው ነው አንዳንድ ቃላት በጽሑፍ ቀርበው ሲታዩ በብርቅየነት ሳይሆን በእሰልቺና ግራ አጋቢ እንግድነት የሚያደናግሩት።...ሰለዚህም ብዙኃኑ አንባቢ ዳንጉራ ዳንጉራ የሆኑ እሮጌ የግእዝ ቃላት ከማገለባበጥና ምሥጢራቸውም ተሠውሮት ከመፋጠጥ ይልቅ በቅርብ ከሚያገኛቸው ከየብሔረሰቡ ቋንቋዎች ቢሰማመድና ቢግራቸው ጠቃሚነቱ ለብሔራዊ ቋንቋው ዕድገት... ታላቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። /ተሸመ ከበደ፣ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፣ ታኅሣሥ 1977፣ 91/

እኒህ ጸሐፊ ለቋንቋው ካላቸው ጥላቻ ተነሥተው እንዲህ ይበሉ እንጅ በእውን እሳቸው ብሔራዊ በሚል ጥብቅና የቆሙለት ቋንቋ /አማርኛ/ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የተገነዘቡት አይመስልም። እንነግራቸዋለን። ልጅ አማርኛ «አከብር አባክ ወእማክ» የሚለውን ትእዛዝ

ያከበረ፣ «ወንድ ልጅ ተወልዶ» የሚለውን ኢትዮጵያዊ ብሂል በተረዳ ነገር ያወቀ በመሆኑ መቼም ቢሆን የአባቱን /የግእዝን/ ሀብትነት ዐውቆ መሠረሱንና አባቱን ሕያው ማድረጉን አይተውም። ለ.ቃውንቱም እንዲህ በማለት ይመሰክሩለታል።

ያማርኛም ቃል የግእዝ ሥጋ
እለ ማእዝ ነፍስ ሬሣ
ራሃውን ቃል የሚሸከሙ
በግእዝ ቋንቋ ሲፈታ ይስሙ /ዚዳነ ወልደ ክፍሉ፣ 1948፡ 248/

ለ. ግእዝ የሞተ ቋንቋ ነው

ይህ ሐሳብ በብዛት ሲሰነዘር የሚሰማው በቋንቋ ጥናት ተሠማርተዋል ከሚባሉ ሰዎች አካባቢ ነው። ምሁራኑ ግእዝን ሞቷል ሲሉ የሚያቀርቧቸውን ምክንያቶች በመዳቀስ እንጀምር።

በሥነ ልሳን ዙሪት የተለያዩ የቋንቋ ሞቶች አሉ ይላሉ። እነርሱም ቋንቋው ራሱን ሲ ገድልና በሌላ ባላንጣ ሲገደል ናቸው። /Aitchison. 1981,209/።

አንድ ቋንቋ ራሱን ገደለ የሚባለው ከሌላ ቋንቋ በብዛት ወይም በመጠን ባለፈ እየተዋሰ ሲጠቀም ነው። የዚህን ምክንያት ሲሰጡም ቋንቋው የአኔ የሚላቸው የቋንቋ ባሕሎችና ወጌች ጨርሰው ስለማይታዩ ነው። ዙሉም ነገሮች የአዋሺውን ቋንቋ መልክ ይይዛሉ። የውሰቱ ሂደት በቀጠለ ቁጥር መንትያ ቋንቋዎች የመሆን ደረጃ ይደርሳሉ። የዚህን ጊዜ አንድ ቋንቋ በሌላ ቋንቋ መ.ሉ በሙ.ሉ ይዋጣል ማለት ነው። ቋንቋው በራሱ የሞትን ጽዋ ይጠጣል። ይላሉ።

እስቲ በዚህ ሐሳባቸው ሚዛንነት እነሱ ያሉትን የግእዝን ቋንቋ እንየው። አንድ ቋንቋ ራ ሱን ገደለ የሚባለው ከሌላ ቋንቋ በብዛት ሲዋጽ ነው ይላሉ። ታዲያ የግእዝ ቋንቋ መዋሱ የታለ? የተዋሰውስ ከማን ነው? የምሁራኑን አንደበት ሆኖ መናገር ባይቻልም ስዚህ መልሱ «መልስ የለም» ነው። ግእዝ ባለበት ሆኖ በብዛት እየተዋሰ ሳይሆን በብዛት አያዋሰ ይገኛል። ማዋሱም ከድምጽ ጀምሮ እስከ ሰዋስዋዊ መዋቅር ነው። አማርኛ ዛሬ እየተጠቀመባቸው ካሉት 33 ፊደላት 27 ያህሉ ከግእዝ የተዋሳቸው ወይም የወረሳቸውን ራሱ ቋንቋው ይመቃቸው። ስለዚ ህ የግእዝ ቋንቋ በማዋሱ እንዴት ሞተ ሊባል ይችላል? በመዋስ በመዋዋሱ ረገድ ከሆነ የግእዝን ሳይጨምር ከሊሎች የአፍራንጅ ቋንቋዎች ሲዋስ የኖረው አማርኛ ከሞተ ሰንብቷል ማለት ነው።

ቋንቋን ቋንቋ የመግደሉ ሂደት ሌላው ነው። እንደ ምሁራኑ አባባል ይህ ሂደት ከመጀመሪያው ፈጠን ያለና ቅጽበታዊ ነው። ይህ የቋንቋ ሞት ከአንድ ቤተሰብ የማይመደቡ ሁለት የተለያዩ ቋንቋዎች በሚያደርጉት ተራክቦ የሚከሰት መሆኑን ይናገራሉ። ይኸውም በተለያየ ቤተሰብ የሚገኙ ሁለት ቋንቋዎች ዘአንድ ልሳነ ከልኤ /ሁለት ቋንቋ በሚናገር/ ማኅበረሰብ ውስጥ እኩል በሚያገለግሉበት ወቅት በቋንቋዎቹ መካከል በሚከሰት መዋዋጥ መሆኑ ነው። ታዲያ ግእዝ ከዚህ አንጻር መሞቱ የታለ? ብዙዎች እንደሚሉት ግእዝ ሞተ የሚባለው አ ማርኛ ሥጠት ነው። በዚያ እንኳ እንሂድ ከተባለ ሁለት ቋንቋዎች ሊዋዋሱና አንዱ ሌላውን ሊ ገድለው የሚችለው ቋንቋዎቹ በተላያየ መደብ ሲኖሩ ነው። ነገር ግን ግእዝና አማርኛ በአንድ የቋንቋ ቤተሰብ የሚመደቡ ቋንቋዎ ች ናቸው።

ምንም እንኳን ንድፈ ሐሳቦቹን የወሰድንለት ሰው በመጽሐፉ የጠቀሳቸው ባይመስልም

አንድ ቋንቋ ሞተ የሚባልበት ሌሎች ምክንያቶችን አንጥቀስ። አንድ ቋንቋ ሞተ የሚባለው ስለ ቋንቋው የሚያስረዳ ሲጠፋና ቋንቋው በአፍ መፍቻነት ማገልገሉን ሲያቆም ነው። ከእነዚህ ነጥቦች አንጻርም የታየኝን ልበል።

አንድ ቋንቋ ሞተ የሚባለው ስለዚያ ቋንቋ የሚያስረዳ ሲጠፋ ከሆነ ግእዝ ሕያው ቋንቋ ነው። በግእዝ አድገው በግእዝ ጉልምሰው አያሌተማሩትና እየተማሩበት ያሉ ሊቃውንት ዛሬም አሉና። ይህን እውነት የዕድሜያቸውን አብዛኛውን ክፍል በአብነት ትምህርት ጠዳሰለፉ ሊቃውንት እና በዕውቀታቸው በርካቶችን ወደሚወልዱባቸው ጉባኤያት ሄዶ ማረጋገጥ ይቻላል። ቋንቋውን ከሥነ ድምጽ ጀምሮ እስከ ሥነ ጽሕፈቱ ድረስ አሳምረው ያስረዳሉ ÷ ይተነትናሉ።

የግእዝ ቋንቋ ዛሬም አፍ መፍቻ ቋንቋ ነው። ይህ ሲባል ግን አንደ ትናንቱ ራሱን እንደቻለ ቋንቋ ሳይሆን አርሱ በወለዳቸው ቋንቋዎች አማካኝነት ነው። በአማርኛው፣ በትግርኛው፣ በትግሬው፣ በአርጉብኛው፣ በኩራማኛው፣ በሐረርኛው። አማርኛ ከፊደል ጀምሮ እስከ መዋቅር ድረስ የግእዙ ተጽእኖ እንዲህ ባያሌ በሚታይበት ሁኔቴ ግእዝ ሞቷል ማለት ተቀባይ አይሆንም። «ግእዝ በቋንቋነቱ በሰዎች ሲነገር ባይሰማም እንደ ጨው ለአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ጣዕም ሰጪ ሆኖ አለዙ ይላል» /ባጉር፣ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፣ ሚያዝያ 12፣ 1977፣ 9/

ጉዳዩን ተመራምረው እንደነገሩን ሰዎች ከሆነ ደንሞ ግእዝ አልሞተም። ከሕያዋን ቋንቋዎች እንደ አንዱ ሆኖ አለ እንጅ ብለን በሙሉ ልብ የምንናገርበት ድፍረት አናገኛለን። ይኸውም ግእዝ ራሱን አስመስሎ ራሱን አሳክሎ የወለደው ቋንቋ የመኖሩ ጉዳይ ነው። ትግረ ከላይ እንዳየነው ትግረ በሴማዊ የቋንቋ መደብ ሥር ከግእዝ ጋር ይመደባል። ይህ ቋንቋ ዛሬ ብዙዎች ሞተ ከሚሉት የግእዝ ቋንቋ ጋር በእጅጉ የሚመሳሰልና ሊቃውንት የግእዝን ግሥ ሲያመሠጥሩ እንደ መረጃ ይጠቀሙበት የነበረ ቋንቋ ነው። አባ ገ/አ.ያሱስ ይህንን ሲገልጹ «ትግሬ የሚባሉ ከሰሜናዊ ኢትዮጵያ ጽንፍና በዛሕር አጠገብ የሚቀመጡ ነገዶች ናቸው። ኑሮዋቸው እረኞችና ነጋዴዎች ናቸው። እርሻ ብዙ አያደርጉም። ቋንቋቸው በአብዛኛው ግእዝ በቁሙ ነው። የግእዝ ቋንቋ ጸንቶ የሚኖርበት ዐታ አግኝቷል። የኢትዮጵያ ሊቃውንት የቃሉቹን ምሥጢር በግሳቸው ሲጽፉ ጥርጥር ቢመጣባቸው ወደ ትግሬ እገር መሄዳቸው በታሪክ የታወቀ ነው» /1936፣ 34/። ታዲያ እንደዚህ ከመሰለ አልፎ ለግእዝ ቋንቋ አብነት፣ ግሥረጀ የሚሆን ቋንቋ ዛሬም ቢሆን እና እየተፈታበት ሥራ እየተሠራበት እያለ እንዴት ግእዝ ሞቷል ይባላል? የቋንቋ ምሁራን ከመናገራቸው በፊት ዝቅ ዝቅ ብለው እንዲያዩ ይጠየቃሉ።

ሐ. ግእዝ አማርኛን ሊያቀጨጨ ያለ ቋንቋ ነው፡

«አማርኛን ከሚች ግእዝ መቃብር በሚለቀሙ የቃሳት አጥንቶች ብቻ ሳይሆን አብሮ አደግ ጓደኞች ሕያው የብሔረሰብ ቋንቋዎችንም እየመጣብን እናሳድግ ነው ያልኩት።... ቋንቋነቱም ፊደሉም ያረጀ ያፈጀ ግእዝ ብቻ ሆኖ ለአዲስ ዘመን አኒጋገር ንባብ የሚያስከፋ ምሥጢር የሚያጠፋ እና የሚያስከፍት ነው።» /ተሾመ ከበደ፣ የዛሬይቱ ኢትየጵያ፣ ጥር 4፣ 1977፣ 8/

አቶ ተሾመ በዚህ ለአማርኛ ቋንቋ ያሰቡ ባስመሰላቸው ጽሑፋቸው የግእዝን ቋንቋ «ያረጀ ያፈጀ ለአዲስ ዘመን አኒጋገር የሚያስከፋ ምሥጢርንም የሚያጠፋ አፍን የሚያስከፍት» ብለውታል። በመሆኑም አማርኛ በቋንቋነቱ እንዲያድግ አንቅፋት እየሆነ በመሆኑ መዋሱን ያቁ ም ይላሉ። አቶ ተሾመ ይህን ሲሉ ሊያውቁት የሚገባ አንዱ ዐቢይ ጉዳይ ሊኖር በተገባ ነበር። የአማርኛ ሀልውና በግእዝ ላይ እንደሆነ። እንዴት የሚለውን አዚህም ላይ መመለሱ ነገር እንደመውቀጥ ስለሚቆጠር በዚሁ ይታለፋል። ሲታለፍ ግን አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌን በመጥቀስ ነው።

... እንደወጊኛ ገላ እንደሚያሸ
እንደ ሐኪምም እንደፈታሸ
ኑሰንተናዋን ቀምሰን
ዐይተን ስለጣንባት ነው እንክን
መስሰናኑል በጥሩ ሀይናማ
ከወጣቶች ልብ እንድትስማማ

... ሀይናን ስትነልጠው ከጥርሷ ጋራ
እስተያየድ በቀኝ በግራ
ስትናዝርም ከፊት ከኋላ
ካፍ ይፈላል የማር መሰላ
ልሳነ ጥሁም የወይን እሸት
እየተሻሙ የሚባሉት

... ግእዝ ግእዙ ወርቅ ቀለሟ
የግእዝ ቋንቋ ማይቱ ስሟ

/ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ 1948፣ 184/

መ የቤተ ክህነት ሰዎችም ትተውታል

ይኽኛው እባባል ደግሞ ብዙ ጊዜ ቋንቋው ይዞት ጋደም ያለውን ሀብት የተረዱ ነገር ግን ዕውቀቱን እንዲያውቁ የሚያደርግ እስተባባሪ ስላጡ በቁጭት የሚናገሩት ነው። እውነታው ምን ያህል እንደሆነ ፍርድ መስጠቱ የሁሉም መብት ቢሆንም እኔ የታዘብኁን ልስጥ። እውነት ነው። በሥራ እጋጣሚ ከእንድ የአገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት ከፍተኛ ባለሥልጣን ጋር ተገናኝቼ ስምን የግእዝን ቋንቋ እንደ እንድ የትምህርት ዓይነት መፈተን ስሚፈልጉ እንደ ማይሰጡ ስጠይቃቸው የመለሱልኝ ለዚህ ወረይ ማስረጃ ይሆናል። «ቤተ ክርስቲያን ሰላልፈቀደችላቸው ነው። ቤተ ክርስቲያን ብትፈቅድላቸው ኖሮማ የቋንቋውን ሥርዓተ ትምህርት አውጥታ ራሷ ባቋቋመቻቸውም ሆነ በመንግሥት ትምህርት ቤቶች እንዲሰጥ ማድረግ ትችል ነበር። እኛ እንደ ሕግ እንድ ተማሪ ከ9–12 ያንን ልፈተን ያለውን የትምህርት ዓይነት እንደተማረ የሚመስክር ማሥረጃ ካላቀረበ እንፈትንም።»

ባለሥልጣኑ እንዳሉትም ሆነ ሁላችንም እንደምንገነዘበው ቤተ ክርስቲያን ቋንቋውንም ሆነ በውስጡ የያዘውን የደለበ የኢትዮጵያውያን ሀብት ትውልዱ ጥቅሙን ተረድቶ የሌላውን በመሻ ማት ከሚላላጥ የራሱን ተቀብሎ እንዲሞቀውና እንዲደላው ጥረት ስታደርግ እትታይም። ወጣቱ እባቶቹ ያቆዩለትን ሀብት የሚወርስበት መድረክ እዘጋጅታለች። ስንበት ት/ቤቶች። ከወጣቱ ላይርቁ እብረውት እየዋሉና እያደሩ ማነህ ባለሳምንት ያስጠመድክ ባሥራ ስምንት ብለው የላይኛውን ስኦችኛው ላያስረከቡ በረሃብና በጥም እያለቁ ይገኛሉ። የከተማውን እያድርገሙና ወደገጠር መላ ብንል አይደለም ግእዝን የሚያስተምሩበት ቅዳሴ ቀድሰው ለተዘጋ ጁት ቅዱስ ሥጋውንና ከቡር ደሙን ስሚያቀብሉበት ደሞዝ እያጡ እየሞቱ ያልሞቱትም እየተስደዱ ይገኛሉ።

ከዚህ አንጻር ቤተ ክርስቲያን ባሏት መዋቅሮች አማካኝነት ወጣቱ ማእዘ ቋንቋውን ዐውቆ አባቶቹ በሚያስገርም ሁኔታ አስቀምጠውለት ያለፉትን ሀብቱን እንዲመረምርና እንዲጠቀም አሳደረገችም።

2.3. ነገ

በዚህ ክፍል ነገ ምን ይደረግ ወደሚለው ከመግባታችን በፊት የግእዝ ቋንቋ ሁለም ትኩረት ሰጥቶት ቢታወቅና ከእሁኑ በበለጠ ሁናቴ ቢያንሠራራ ምን ጥቅም አለው የሚለውን ነጥብ በነጥብ በአጭሩ እንመልከት።

ሀ. ለምርምርና ጥናት ይጠቅማል

የግእዝ ቋንቋ ከላይ ባየነው መንገድ ሁሉንም አርዕስተ ጉዳዮች የዳሰስና ያቀፌ ከመሆኑ አንጻር መጠናቱና መታወቁ በምርምርና ጥናት ዘርፍ ብዙ ነገሮች ሊመረመሩበት ይችላል። የሚከተሉትን ማየት ይቻላል።

ሀ.1. የሥነ ልሳን ጥናት

የግእዝ ቋንቋ በአባትነት ወልዶ ያሳደጋቸውንና ዛሬ በመግባቢያነት የሚያገለግሉ ቋንቋዎች መኖራቸው ከላይ በተደጋጋሚ ተገልጧል። ከዚህ አንጻር እነዚህን ቋንቋዎች በመረጠ ው የሥነ ልሳን ጥናት ዘርፍ ሳጥና ብሎ የሚነሣ ሰው በጥናቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ ወሳኝቸውን የግእዝን ቋንቋ በሚገባ ማወቅ ይጠበቅበታል። በዚህ ረገድ ጥቅሙ በገባቸው እና ቋንቋውን ባጠኑ የቋንቋ ምሁራን ተጠንተው ሀገር ውስጥ ባሉን አብያተ መጻሕፍት /በተለይ በኢትዮጵያ ጥናት ተቋም/ የተቀመጡትን ጥቂት ወረቀቶች ቆፍረ በአብዛኛው የተጠኑት በውጭ ሀገር ዜጐች ሆነው አናገኛቸዋለን። ይኽ በራሱ አሳፋሪ ቢሆንም ለወደፊቱ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ላይ የተሰማሩ የቋንቋ ምሁራን ሰራሳቸውም ለሀገርም የሚጠቅም ሥራ እንዲያቀርቡ የግእዝ ቋንቋ መጠናቱ በጣም ጠቃሚ ነው።

ሀ.2. በታሪክ ምርምር

ብዙ ጊዜ ከሚባለው አንድ እውነታ ስመነሳት የኢትዮጵያ ታሪክ ሲነሳ ብርዕ ቀርጸ ቀለም በተብጣ ብራና ጻምጣ በራሷ ፊደል በመመዝገብና በማቆየት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትነሣለች። ታዲያ የኢትዮጵያን ሁሉን አቀፍ /ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ/ ታሪክ ለ ማጥናት የታሪክ መዛግብቱ በግእዝ ከመጻፋቸው አንጻር ቋንቋው መረጃ በማቀበሉ ረገድ ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ሀ.3. በሥነ ሰብእ ጥናትና ምርምር

አንደርሰን የተባለው የቋንቋ ምሁር ለቋንቋ ጥናት የሥነ ሰብዕ ውጤትም ሆነ ሌሎች ሳይንሳዊ የጥናት መሰኮች ማስፈለጋቸውን ሲገልጽ «በሳይንሳዊ የቋንቋ ጥናት ስለ ቋንቋዎች ጥንተ ነገርም ሆነ ቋንቋዎች እርስ በርስ ስላላቸው ዝምድና ከሌሎች የሳይንስ መሰኮች ደጋፊ ማሥረጃ ያስፈልጋል። ከሥነ ሕይወት፣ ከሥነ ሰብዕ፣ ከባሕልና ከሌሎች መሰኮችና ሳይንሳዊ የጥናት ዘርፎች ጭምር» /Anthropology/ ጥናትም ጠቃሚ ነው። በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ላይ እንደተገለጸው በአንዳንድ ሊቃውንት የግእዝ ቋንቋ አዳማዊ ማለትም የመጀመሪያው የሰው ልጅ ቋንቋ ነው። ይህ ሥነ ልሳናዊ መላምት በሥነ ሰብዕ ጥናት ሳይደገፍ የሚቀር አይመስልም።

የስውን ልጅ ጥንተ ታሪክ ለማወቅ የሚደረገው የቁፋሮ ምርምር ረጅም ዕድሜ ያላት ቅሪት አካል /ሉሲ/ የተገኘችው በኢትዮጵያ ነው። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሥነ ሰብዕ ግኝት መረዳት እንደሚቻለው ማለት ነው። ከዚህ አንጻር በኢትዮጵያ ለሚደረግ የሥነ ሰብዕ ጥናት የማእዝ ቋንቋ መጠናቱ ጠቃሚ ነው።

ሀ.4. ለሥነ ጽሑፍ ጥናት

«... ግእዝ... ሐዲሳት፣ ብሉያት፣ ድርሳናት፣ ተአምራት፣ ገድላት፣ ቅዳሴያት፣ ውዳሴያት፣ ዜና መዋዕል፣ ቅኔያት... ሊሉችም መጻሕፍት ተተርጕመውበታል፣ ተጽፈውበታል» /ተክሉ ሚናስ፣ አዲስ ዘመን፣ ሐምሌ 11፣ 1978፣ 3/ አቶ ተክሉም ሆኑ ሌሎች የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ጥቂት ሊቃውንት እንደሚገልጹት የግእዝ ቋንቋ እጅግ የሚያስደንቅ ሥነ ጽሑፋዊ ዋጋ ያላቸው የጽሑፍ ይትበሃሎች የተመረቱበት ቋንቋ ነው። በግጥሙ፣ በወጋዊ ጽሑፉ፣ በየሕይወት ታሪኩ፣ በልቦለዱ ወዘተ.። ይኑን እንጂ ይህ ድንግል ይዞታው በብዙዎች የታወቀ አይመስልም። የሆነው ሆኖ ይህ ከእሳ አልፎ ሊላው ቢራከትበት የሚያልቀው የጥናት ዘርፍ ይታወቅ በሚገባ ይጠና ዘንድ ከመጀመሪያው ቋንቋው መታወቅ አለበት።

ለ. የግእዝ ቋንቋ የማንነታችን መገለጫ ነው

አንድ ሕዝብ ማንነቱ የሚታወቀው በሌሎች ፊት በኩራት ነፍ ነፍ የሚለው እምሮ የሚደምቀው የራሴ የሚለው ነገር ሲኖረው ነው። ኢትዮጵያ ሀገራችን በዓለም ሳይ ካሉ የራ ሳቸው የሆነ ፊደልና በእሱም በኩል የጽሕፈት ቋንቋ ካላቸው ጥቂት ሀገሮች አንዷ ናት። በዚህ ፊደሏ ታሪካን፣ ዕውቀቷንና ትምህርቷን ጽፋለች። የጻፈችውንም ለልጆቿ አስረክባለች፣ ለሌሎችም ስጥታለች። የእሷ ባያንሳትም ጠቃሚ የምትለውን ዕውቀት ከሌሎች የማምጣት እእምሮዋ ዝግ ባለመሆኑ በዚሁ በቋንቋዋ አማካኝነት ጠቃሚ ያለቸውን አስገብታለች። በዚህ ሁሉ ድርጊቷ በኩራት ደረጀ ይነፋል፣ ሆዷ ይሞላል፣ ጉንጯ ይቀላል። በዚህም የመቀበልና የ ማቀበል ሂደት የግእዝ ቋንቋ አንዱና ብቸኛው መሣሪያ ነው።

በቅርብ የምናውቃቸው ሕዝቦች /ስብረውያን/ ቋንቋችን የማንነታችን መለያ መከበሪያችን ነው ብለው ተማምለው እንደኛው የግእዝ ቋንቋ ሞተ ተቀበረ የተባለውን ቋንቋቸውን እንደገና እንዲያንሠራራ ያደረጉት ቋንቋቸው የማንነታቸው መገለጫ መለያ መከበሪያቸው መሆኑን በመረዳታቸው ነው። ስለዚህ እኛም ጥንታዊው ቋንቋችን ግእዝ መለያችንና የማንነታችን መገለጫ ነው።

ሐ. የግእዝ ቋንቋ ሃይማኖታዊ ጥቅም አለው

ከላይ እንዳየነው የግእዝ ቋንቋ ለኢትዮጵያውያን ከሰጣቸው አገልግሎቶች አንዱ ሃይ ማኖታዊ ዋጋው ነው። ይህ አገልግሎቱ ባራም ድረስ አለ። ዕለት ዕለት ከምናየው የዘመተ መቅደስ አገልግሎቱ ባሻገር በጎባኤ ቤት በመማሪያ ቋንቋነት፣ በሠዓደ ምሕረት በአጣቃሽ ቋንቋነት ያገለግላል። የጉባኤ ቤቱን ትተን የቤተ መቅደስና የሠዓደ ምሕረት አገልግሎቱን ብንመለከት ምእመናን ከሰኑቱ የሚያቀርቡትን ስብሐተ እግዚአብሔርና ቃለ እግዚአብሔር ሰምተውና ተረድተው ራሳቸውን ለሕገ እግዚአብሔር እንዲያስገዙ በእሱም በኩል ጥሩ ዜጋ እንዲሆኑ የእግዝ ቋንቋ ማወቃቸው በእጅጉ አስፈላጊ ነው።

ነገ ምን ይደረግ?

ከላይ እንዳየነው የግእዝ ቋንቋ አልሞተም፣ ሕያው ነው፣ ብንልም የዚህ ጽሑፍ አቅራቢም ሆነ ሌሎቻችን የማንክደው አንድ እውነታ አለ። የግእዝ ቋንቋ የነበረው የሕዝብ ፍትር፣ የሥነ ጽሑፍ መሣሪያነት መቀነሱን። ከዚህ እንጻር ነገ ቢሠሩ የምንላቸውንና ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ጥቂት የመፍትሔ ሐሳቦችን ልጠቀም።

ሀ. ቤተ ክርስቲያን ትኩረት ትስጥ

ለማለት ከፈለኩት ነገር ጋር ሙሉ በሙሉ የሚሄድ ባይሆንም በሀገራችን የተስመደን አንድ አባባል ልጥቀስ። «ባለቤት ካልሞሸ ጉረቤት አስሁ አይልም»። ምንም እንኳን የእግዝ ቋንቋ ባለቤት ኢትዮጵያውያን በመላ ቢሆኑም ሳያውቅም ሆነ አውቆ ይህን ትውልድ አስተምሮና ያልገባውን ምሥጢር ገልጦ ገፉ ያደረገውን ቋንቋውን ሳብ አድርጉ እንዲይዝ በ ግድረጉ ቤተ ክርስቲያን ከባድ ኃላፊነት አለባት። ያለፈውን ንዝህላልነት ሁሉ ስብስብ በዛሬው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ላይ መጫኑ የተገባ ባይሆንም በዚህ ረገድ በአርግጥ ዛሬ እየታዩ ያሉ ድክመቶችን መጠቋቆም ይገባል።

የመጀመሪያው ቤተ ክርስቲያን የራሷ የሆነውን ነገር ከልጆቿ ጀምሮ ሳላወቁት ስታስተዋውቅ እትታይም። ሲሆን አርሷ መደተኙት ሂዳ በመተስቀስ እንካ ይኸ የአንተ ነው፣ ለእንተኛው ይሽ ይጠቅምሀል ልትል በተገባ ነበር። ይቅር ምን ልሥራ ብሎ በተለያየ አቅጣጫ ከታዛዋ ሥር የከተመ ወጣት እያለ ለአርሱ እንኳን መጣህ ብሳ ጓዳዋን ከፍታ በእናቱ ጓዳ አንዲ ሆን ጉድጓዳ ማድረግ ነበረባት። ነገር ግን የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በቅርበት እንደሚያውቀው ሌሎችም እንደሚጋሩት በተግባር የሚታየው የተገላቢጦሹ ነው። ሲወርድ ሲወራረድ የቆየ ክፉ ልምድ ሆኖ ሊሆን ይችላል እባት ያወቀውን ስልጃ በደስታ ሲያስተላልፍ አይታይም። እንዳንድ የሚያበረታቱ አባቶች የመኖራቸውን ያህል ነስለት በሳስ ቅኔያዊ ሾተል እየሸስቱ ሠጣቱ በሀፍረት የጀመረውንም ትቶ እንዲሄድ የሚያደርጉ ሊቃውንት አሉ። በርከት ያሉ ገጠመኞች መጥቀስ ይቻላል። የሆነው ሆኖ ቤተ ክርስቲያን ትውልዱ የግእዝን ቋንቋ አውቆ በአርሱ በኩል ታግሎ የሚያሸንፍበት፣ ተነራክሮ የሚረታበት፣ ሮጦ የሚቀድምበት ለሙቀትን በሰጋ አለምሮው እንዲያካብት የሚነተሉትን የመፍትሔ ሐሳቦች ተግባራዊ ብታደርግ።

ሀ.1. ሥርዓተ ትምህርት ትቅረጽ

ይህ የመፍትሔ ሐሳብ በተከታታይ ለሚተርቡት ሌሎች የመፍትሔ ሐሳቦች አንደ ዋልታ እንደ ማገር ነው።

የጽሑፉ አቅራቢ በተለያዩ ደረጃዎች ካሉ አባቶች ጋር ሲወያይና ይህንን የመፍትሔ ሐ ሳብ ሲያቀርብ በተደጋጋሚ የበማው አንድ ወጥ የሆነ መልስ አለ። ብዙ አባቶች የግእዝ ቋንቋ ሥርዓተ ትምህርት የለም በሚለው አይስማሙም። ሥርዓተ ትምህርቱም አለ፣ ትምህርቱም እየተሰጠ ነው ይላሉ። ሥርዓተ ትምህርት ሲሉ በቅኔ ቤት የሚሰጥበትን፣ ትምህርት ሲሉ ደግሞ በየጉባኤ ቤቱ የሚሰጠውን የአብነት ትምህርት ነው። በዚህ ሐሳባቸው የምንስማማው በቅኔ ቤት ቋንቋው የሚሰጥበት ሥርዓተ ትምህርት በእንደኛና ሁለተኛ ደረጃ እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚማሩ ተማሪዎች፣ በዚያም አልፈው በሥራ ተሠማርተው ለሚገኙና ግእዝን ለማወቅ ለሚፈልጉ ሰዎች በተሳስ የሚዝ ሥርዓተ ትምህርት ሊሆን ነው። ነገር ግን ስላልሆነ ከሐሳባቸው ጋር አንስማማም። ስለዚህ ትውልዱን የዋጀና ሳይንሳዊ የሥርዓተ ትምህርት አወጣጥ ትውርን /theory/ መሠረት ያደረገ ቋሚ ሥርዓተ ትምህርት ማዕከላዊ በሆነ

ሁኔታ ማውጣት ይገባል።

ሀ.2. በሰንበት ት/ቤቶች በተጠናከረ መልኩ መሰጠት

አንድ በቅርብ የማውቃቸው አባት በገጠርም ሆነ በከተማ ባሉ አብያተ ክርስቲያናት ያለውን የወጣቱን መሰባሰብ ተመልከተው ባሉት ልጆምር። «ወይ አንተ እግዚአብሔር! ትላንት አንኳን አሱ ሊገባ ቀደም ብለው የገቡትን ካልወጣችሁ እያለ ሊያስገድድ የነበረ ወጣት ዛሬ በቤተ ክርስቲያን አጸድ ሥር ተሰባስቧል። ዛዴያ...»። ዛሬ በከተማም ሆነ በገጠር ያለውን የወጣቱን አንቅስቃሴ ያየ የእኒህን አባት አባባል አውነታ ያረጋግጣል። በመሆኑም በቤተ ክርስቲያን የሚመለከተው ክፍል ወጣቶቹ አሁን ከሚያደርጉት የመዝሙርና የመጠነኛ ስብከተ ወንጌል መርሐ ግብር በተጨማሪ የቤተ ክርስቲያናቸውን ልሳን ዐውቀው በተሰጣቸው ጸጋ /በስብከት፣ በምርምር፣ በዜማ ወዘተ./ ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲያገለግሉ ቢደረግ መልካም ነው።

ሀ.3. በከፍተኛ መንፈሳዊ የትምህርት ተቋማትም መሰጠት

ቤተ ክርስቲያን በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ብዙ ሊያውቋትና በእቅፏ ሊገቡ የሚገባቸው በርካታ ሕዝቦች ከመኖራቸው የተነሣ ያሏት ከፍተኛ መንፈሳዊ የትምህርት ተቋማት በቂ ባይሆኑም ባሏት ጥቂት ተቋማት መምህራንን እያሠለጠነች ለአገልግሎት ታሰማራለች። ከእነዚህ ተቋማት የሚወጡ ሊቃውንት ከሀገር አልፎ በዓለም ደረጃ የቤተ ክርስቲያንን በእርሷም በኩል የኢትዮጵያን ሁለንተና የሚመለከሩ ናቸው። ከዚህ አንጻር ሊቃውንቱ ቤተ ክርስቲያንን በራሷ ቋንቋ ሳለወቋት እንዲያስተምሩ በማስቻሉ ረገድ ችግር ያለ ይመስላል። ቡተቋማቱ የሚሰጡት ትምህርቶች በብዛት በኢትዮጵያዊው የግእዝ ቋንቋ አይደለም። በቤተ ክርስቲያን ዕውቀት ላይ ያተኮሩ አይደሉም። ከመማሪያ ቋንቋ ጀምሮ እስከ ትምህርት ዓ ይነቶቹ ድረስ ከውጭ የገቡ ይብዛኞቹ። ይህ ጉዳይ ራሱን የቻለ ይሽን መሰል ሌላ የጥናት ወረቀት የሚጠይቅ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ የትምህርት ተቋማቷ በግእዝ ተምረው በግእዝ የሚያስተምሩ፣ ለቋንቋው በእርሱም በኩል ይዞት ለተኛው የደለበ ዕውቀት ጠበቃ የሚሆኑ ሊቃውንት ቢፈሩበት የተሻለ ነው።

ለ. ዩኒቨርስቲው ትኩረት ይሰጥ

የጥናቱ አቅራቢ የሚፈቅድለት ካገኘ ይህን ርዕሰ ለዩኒቨርስቲው ማኅበረሰብ ለማቅረብ የሚያስብ ቢሆንም ይሽኛውን ወረቀት በመጠኑ ምሉዕ ለማድረግ ርዕሱን በአጭሩ ለመዳሰስ አስቧል።

ለግእዝ ቋንቋችን ቀና ማለት ኃላፊነት ያለበት ሌላው ተቋም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ነው። እንደሚታወቀው ዩኒቨርስቲው የተለያዩ የትምህርትና የምርምር ተቋማት አሉት። ከእነዚህ ተቋማት በዚህ ወረቀት የተያዘው ርዕስ በቀጥታ የሚመለከታቸው በቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ የአትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም እና የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ተቋማት ናቸው።

ዩኒቨርስቲው በእነዚህ ተቋማት ምን ያድርግ? ለሚለው ጥያቄ መልስ ወደ መሰጠት ከመሄዳችን በፊት አሁን በተቋማቱ በኩል ምን እያደረገ ነው? የሚለውን በአጭሩ ሰማየት እንሞክር።

የጥናቱ አቅራቢ ለውስጡ ቅርበት ያላቸውን ስዎች አነጋግሮ እንደተረዳው በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ከዛሬ 20 እና 30 ዓመታት በፊት የግእዝ ቋንቋ ከ12–16 «ክሬዲት አወር» ተሰጥቶት ለተማሪዎች ይሰጥ ነበር። ይህ ዋና የትምህርት ዓይነትነቱ ቆየት ሲ ል ዝቅ ብሎ በስድስት «ክሬዲት አወር» የትምህርት ዓይነትነት መስጠት ጀመረ። በዚህ ጊዜ የጥናቱ አቅራቢም ደርሶ ነበር። አሁን ደግሞ ያ ሁሉ ቀርቶ በሦስት «ክሬዲት አወር» ተወሰኖ ይገኛል። ከላይ ባየነው አካሄድ ከሦስትና አምስት ዓመት በኋላ ጭራሽ የሚሠረዝ ይመስላል።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ተቋም በመቋቋሩ በተለያዩ ክፍሎች ሲታቀፍ ይቆይ አንጂ ከተመሠረተ 50 ዓመታትን አስቆጥሯል። ዙተቋሙ ስም እንደምንረዳው የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በባለሞያዎች እንዲጠኑ ጥረት የሚያደርግ ተቋም ነው። ይህ ተቋም የግእዝን ቋንቋ በሚመለከት አጥጋቢ ሥራ አየሠራ ነው ብለው ራሳቸው የተቋሙ ባለሥልጣናትም አይመሰክሩም። ሠራን ቢሉ አንድ ሁለት የቅኔ መድብሎችን ማሳተማቸውን ነው። ያ ደግሞ የቋንቋ ጥናት አይደለም።

አነጋፋው የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም በአድማሱ ሰፋትና በአስተዳደራዊ መዋቅሩ ጐላ ብሎ የሚታይ ቢመስልም ግእዝን በቋንቋነቱ ከማሣጥናት አንጻር ብዙም የተሪመደ አይመስልም። በተቋሙ ቤተ መጻሕፍት ተሠርተው የተቀመጡ ጥቂት ሥራዎች ቢኖሩም አጥጋቢ ናቸው የሚባሉ አይደለም። አንድም ባሕር አቋርጠው መጥተው ግእዝን አጥንተናል በሚሉ ሰዎች የተ ሠሩ ከመሆናቸው አንጻር በሳል ሥራዎች ናቸው ለማለት አያስደፍሩም።

ከላይ በአጭሩ ለማየት እንደተሞከረው በዩኒቨርስቲው አካባቢም የግእዝ ቋንቋ የተረሳ ይመስላል። ለምን? ለሚለው በርካታ ምክንያቶች ማሰቀመጥ ቢቻልም ወደ መፍትሔ ሐሳቡ በመሄድ ጥቂት ነጥቦችን መዘርዘሩ ይበጃል።

ለ.1. የአመለካከት መስተካከል

የጥናቱ አቅራቢ ለዩኒቨርስቲው ካለው ውሱን ቅርበት ለመጣንዘብ እንደሞከረው የዩኒ ቨርስቲው ማኅበረሰብ ወደ ቋንቋው ጥናት ቀረብ ካሉት ሰዎች ብዙዎቹ የግእዝን ቋንቋ ጥቅም የተገነዘቡት አይመስልም። በዚህ የተነሣ እንደ «ሞቷል» ዓይነት የተዛቡ አስተያየቶች ሲሰጡ ይሰማሉ። በቋንቋው ላይ ብቻ ተመሥርቶ ሥነ ልሳናዊ ጥናት ላድርግ ብሎ አትሠራም የተባለ ባያጋጥመኝም በሥነ ጽሑፉ አካባቢ ልሥራ ብሎ ሐሳብ ያቀረበ ተማሪ ብዙም ሲሸረታታ አላየሁም። በዋና ከሚቀርበው «የአማካሪ የሰም» ምክንያት በተጨማሪ አኝተ /አንቺ አትችለውም /አትችይውም፣ ብዙም የሚያሰኪደህ/ሽ አይደለም ወዘተ. የሚሉት ሞራልን የሚገድሉ አስተያየቶች በተደጋጋሚ ሲሰጡ ይሰማሉ። ይህ የሆነው አንድም የቋንቋ ምሁራኑ ለቋንቋው ቅርበት ስለሌላቸው ሁለተኛ ደግሞ የሞተ ቋንቋ ነው ከሚል የተዛባ አመለካከታቸው ይመሰለኛል። ስለዚህ ልሥራ ብሎ ከሚፍጨረጨረው ተማሪ የበለጠ አነሱ በተማሪና ረጅም ጉዞን መጓዝ በለመደ አእምሮአቸው ቢመረምሩት የግእዝ ቋንቋና ጓዳው ሰፊ የደለበ ዕውቀት አለውና እነሱም ዘወር እንዲሉበት አመለካከታቸውን ሲያሰተካክሉ ይገባል።

ለ.2. ራሱን የቻለ ትምህርት ክፍል ቢከፈትለት

ከላይ ከተዘረዘሩት ምክንያቶችና ከሌሎች ከቀሩት ነጥቦች አንጻር የግእዝ ቋንቋ ጥቅሙ አያሌ በመሆኑ ዩኒቨርስቲው ባቋቋመው የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ሥር አንድ የትምህርት ክፍል ሆኖ ቢከፈት መልካም ነው የሚል «የደፋር አስተያየት» አለኝ።

የሚቋቋመው «የግእዝ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ክፍል» በዩኒቨርስቲው ለሚደረገው የሥነ ጽሑ

ፍ ጥናት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከመስጠቱ ባሻገር ለለሎች የትምህርት ዘርፎችም በቢያ መሠረት ይሆናል። ለምሳሌ በማኅበራዊ ሳይንስ ፋኩሊቲ ለታሪክ፣ ሥነ ማኅበረሰብ፣ የፖለቲካ ሳይንስ፣ የሕግና በሚዲካል ፋኩሊቲዎች ነባረ – ኢትዮጵያን አስመልክተው ለሚደረጉ ጥናቶችና ምርምሮች መረጃዎችን ከምንጩ ለማግኘት ቢቋቋም የተባለው ትምህርት ክፍል በቋርጣሚና አስተርኦሚነት እንዲሁም በአፋባይነት ከፍተኛ ጥቅም ይኖረዋል።

ለ.3. ልዩ ልዩ ዘውዴ ጥናቶችን በዘዕሰ ጉዳዩ ላይ ማድረግ

ሰሙ ዩኒቨርስቲ ቢሆንም በብዛት በተለያዩ ምሁራን ተጨምቀው በሚቀርቡ ቅንቶችና ግንቶች ሌሎች ምሁራን ተሰብስበው በመቅሠስ ዘውዴ ምክክሮች ሲደረጉ አይታዩም። የጥናቱ እቅራቢ ይህን እንደ አንድ የዩኒቨርስቲው ችግር በሚገባ የተረዳው ቢሆንም ከዓላማው እንጻር የመሰለውን ለማለት በመሞደዱ ነባረ ግእዝን በሚመለከት ራሳቸውን የቻሉ ዘውዴ ጥናቶች እያዘጋጀ ያሳወቁ ምሁራንም ሆኑ ትሙልዱ ወደግያልቀውና ወዳልተነካው የዕውቀት ዓለም እንዲገባ ቢደረግ መልካም ነው።

ለ.4. ልዩ ልዩ ኀትመቶችን ማዘጋጀት

ቀደም ሲል አስዘው ያደረጉት ምስጋና ይግባቸውና አዲስ አዘባ ዩኒቨርስቲ የእኔ የሚለውን እንዲያትምበት የተቋቋመ የራሱ የሆነ ማተሚያ ቤት አለው። ይህ ማተሚያ ቤት ምን ያህል ዩኒቨርስቲው የተለያዩ ምርምሮችንና የጽሑፍ ሥራዎችን በማሳተም ትውልዱ በሥራ ዎቹ እየተጠቀመ እንደሆነ ለታዛቢ ዘመተው እኔ ከያዝኩት ርዕሰ እንጻር ለማለት የወደድኩትን ልበል።

በተለይ ከአራትና አምስት ዓመት ወዲህ ነባረ ግእዝን በሚመለከት በጣም ጥቂት የጥናት ጽሑፎች በቅድመና ድኅረ ምረቃ ተማሪዎች እየቀረቡ እንደሆነ አስተውሳለሁ። ታዲያ እነዚህ የመመረቂያ ጽሑፎች እንኳን ግእዝን ቀብሮ ቁጭ ላሰው ለማእዝ የቀረበውም ስለመሠራታቸው በማያሙቅበት ሁኔታ በየአብያተ መጻሕፍቱ ተቆልፎባቸው ይገኛሉ። ከእነዚህ ሥራዎች ይሆናሉ ያሚባሉት ተመርጠው እየታተሙ ለንባብ ቢቀርቡ መልካም ነው።

ሐ. የምእመናን ተሳትፎ

ይኸኛው የመፍትሔ ሐሳብ በቋንቋው ተምረው ያደጉትን ጨምሮ በቤተ ክርስቲያን እገልግሉት ደፋ ቀና የሚሉትን ምእመናን የሚመለከት ነው። መቼም የትላንቶቹ አባቶች የቤተ ክርስቲያንን ሀብት በመላ በተጋድሎ ያቆዩን ለዛሬዎቹ ምእመናን ነው። በመሆኑም እኛም እንደ አባቶቻችን ቢያንስ እስከ አሁን ከእጃችን ያልወጡትን ጠብቀን ለእኛ ልጆች የማቆየት ከባድ ኃላፊነት ላይ እንገኛለን። ከዚህ አንጻር ግእዝ ቋንቋችንና በውስጡ የያዘው ሀብት ለልጆቻችን ወጥነቱን ጠብቆ እንዲደርስ የማድረግ ከፍተኛ ኃላፊነት አለብን። ስለዚህ ምን እናድርግ?

ሐ.1. ልጆቻችን ቋንቋውን እንዲማሩ እናድርግ

ዛሬ በከተማም ይሁን በገጠር ልጆቹን ከኡ.ቢ.ሲዲ በፊት ወይም ጉን አቡጊዳን እንዲማሩ የሚያደርግ ወላጅ የለም። ከሕጻን ልጇ አንደበት በሚወጣው የእንግሊዝኛ ቃል እንጅ በራሷ ጥረት ከእንደቡቱ በሚወጣው የግእዝ ቃል የተደሰተችና የሕጻን ልጇን እፍ ሳም ያደረገች እናት የለችም። ያደረገች አይደለም የፈለገች እናት የለችም። ስለዚህ ምእመናን ልጆቻቸውን እንግሊ

ዝኛውንና ፈረንሳይኛውን ለማበተማር የሚተጉትን ትጋት ግእዙንም ለማስተማር ቢተጉ መልካም ነው።

ሐ.2. ተቋማትን ማቋቋም

ዛሬ በየቦታው የትምህርት ተቋማት በባለሀብቶች ሲቋቋሙ እናያለን። ከአጠቃላይ ሕዝቧ ሰባ በመቶው ማይም ነው በሚባልባት ሀገር እንደዚህ የባለሀብቶች ማይምነትን ለመቀነስ መሰለፍ ይበል የሚባል ተግባር ነው። ይሁን እንጅ ግእዝ ለተራበው ግእዝን የሚያቀርቡ የትምህርትና የምርምር ተቋማት ማቋቋምም ይጠበቃል።

ሐ.3. ልዩ ልዩ ጎትመቶችን ማዘጋጀት

የግል ፕሬሱን በሚመለከትም ዛሬ ኢትዮጵያውያኑ ቀላል የሚባል ሥራ እየሠሩ እይደለም። የፕሬሶቹን ይዘት ትተን ቁጥራቸውን ብንመለከት ዛሬ ጥቂት የማይባሉ የፕሬስ ውጤቶች ገበያ ላይ አሉ። ወደፊትም ይውላሉ። ታዲያ በየጊዜው ብቅ ብቅ ከሚሉት የጎትመት ውጤቶች ነገረ – ግእዝ ላይ ያተኮረ አልታየም። ገበያ ላይ ያሉትም ቢሆኑ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ዓላማቸው ያደረጉትም ቢሆኑ ነገረ ግእዝን ቤት ለእንግዳ የሚሉባቸው ዓምዶች የሏቸውም። ስለዚህ ግእዝ ያንሠራራ ዘንድ ምእመናን በዚህም መንገድ ድጋፍ ማቀበል ይችላሉ።

ማጠቃለያ

በዚህ ጥናት የግእዝ ቋንቋ ትላንት እንዴት እንደ መጣና ምን አገልግሎት እንዳበረከተ፣ ዛሬ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፣ ነገ ደግሞ ምን ሊደረግ እንደሚገባ በወፍ በረር ለመዳሰስ ተሞክሯል። ነገረ ግእዝ በጣም ሰፊና በጥልቀት ሊታይ የሚገባው ከመሆኑ አንጻር ይህ ጥናት ለሙይይት ቢሆን ተብሎ የቀረበ ነው። በመሆኑም ደካማ መነሻ ሆኖ ይህ ከቀረበ ዘንድ ሁሉም ጠንካራ መድረሻ አንድም ተግባራዊ መፍትሔ እንዲገኝ መሪባሪብ አለበት። በድጋሚ ለመግለጽ የጥናቱ አቅራቢ ያለውን ሁሉ ያለው ለግእዝ በቋንቋነቱ የተለየ ፍቅር ይዞት ሳይሆን የግእዝ ውስጡ ብዙ በጣምም ብዙ በመሆኑ ነው። መስላሐት ለእግዚአብሔር።

መጽሐፍቱ

ገ/ኢየሱስ ኃይሉ /አባ/፣ 1936፣ ስለ ግእዝ ቋንቋ ታሪክ፣ መርሐ ጥበብ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ /አለቃ/፣ 1948፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ

[illegible]፣ 1962፣ የግእዝና ያማርኛ ቋንቋ መከፈቻ 2ኛ መጣፍ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ

ግሩም ታደለ፣ 1984፣ «ስለ ግእዝና አማርኛ የበላይነት – የበታችነት የተጻፉ መጣጥፎች ጥናት»፣ የኢትዮያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ አ.አ.ዩ.

ተከስተ ብርሃን ገ/መድኅን /አባ/፣ «ግእዝ አዲስ ቃላት ለመፍጠር ምንጭ»፣ አዲስ ዘመን፣ ጥቅምት 20/22፣ 1962

ባሳር፣ «ለእማርኛ ግእዝ ነው ዳኛ»፣ የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ፣ ጥር 18፣ 1977

ኢሳይያስ ዓለሜ፣ «ቅኔ በሴም መጻሕፍት»፣ አዲስ ዘመን፣ ሰኔ 21፣ 1977

ከነፈ ርግብ አታለለ፣ «ግእዝ በውጭ ሊቃውንት ዕይታ»፣ አዲስ ዘመን፣ 1978

ተከሉ ሚናስ፣ «ግእዝ ባማርኛ ቋንቋ ውስጥ»፣ አዲስ ዘመን፣ ሐምሌ 11፣ 1978

ተሾመ ከዘይ፣ «ለቋንቋችን መፋፋት» <u>የዛሬይቱ ኢትዮጵያ</u>፣ በጎሣሥ 6 1977

_____፣ «የማእዝ ጥብቅናቸው ትዝብት እንጅ ትምህርት አላፈራም»፣ <u>የዛሬይቱ ኢትዮጵያ</u>፣ ጥር 4፣ 1977

Aitchison, Jean. 1981, Language change; progress or Decay, Fontana Press.

Anderson, James M: 1973. <u>Structural prospects of Language Change</u>. New York: U.S.A. Inc.

በመጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ልዩ ትርጉሞች ላይ የሚታዩ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው

ዲ/ን ዳንኤል ክብረት
ማኅበረ ቅዱሳን
የኅትመት ዝግጅትና ማስተባበሪያ ክፍል ኃላፊ፣
የሰሞነ ጽድቅ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ
ስ.ቁጥር- 556328
Email: danail_kibret@yahoo.com



ዲ/ን ዳንኤል ክብረት ጥናታቸውን ሲያቀርቡ

መግቢያ

መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመርያ በሀገራቸው ቋንቋ ከተርጎሙ ሀገሮች መካከል እንዷ የሆነችው ኢትዮጵያ በትክክል የተተረጉመ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እላት ወይሕ ሰሚሰው ጥያቄ ልብ የሚያረካ ምላሽ የላትም። ላለፉት 300 ዓመታት/የመጀመርያው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ በእባ ሩሜ ከተተረጎመበት ዘመን ጀምሮ/ መጽሐፍ ቅዱስን በአማርኛ በሚገባ ተርጉሞ ማስቀመጥ ያልተቻለበት ምክንያትም ዕንቆቅልሽ ነው። ግእዙ ለጥንታውያን ቅጅዎች ካለው ቀረቤታ እንፃር የተሻለና ለሌሎች የእፍሪካ ሀገሮችም መረጃ የሚሆን የአማርኛ ትርጉም ለ ማቅረብ ቀርቶ እርስ በርሱ የሚጣጣም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ማቅረብ አልተቻለም።

በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች ላይ ያለውን ችግር በተመለከተ ከታሪክ፣ ከሰዋሰው፣ ከትርጉም ዘዴ (Style)፣ ከቃላት አመራረጥ፣ ወዘተ አንጻር በተናጠል ጥናት ተሠርቶባቸው በየራ ሳቸው ቢታዩ ምናልባት የተሻለ ግንዛቤ ይፈጥሩ ይመስለኛል። በዚህ ጥናት ግን የችግሩን መኖር ለማሳየት የሚያገለግል ፍንጭ ለመስጠት ታስቧል።

የጥናቱ ዓላማ

የዚህ መጠነኛ ጥናት ዓላማው በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች ላይ የሚታዩ የትርጉም ችግሮችንና ምእመናን ያጋጠማቸውን ፈተና ለማሳየትና መፍትሔውንም ለመጠቆም ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ታሪክ በዓለም አቀፍ ደረጃ

ለብዙ ዘመናት በብዙ ቋንቋዎች በመተርጐም መጽሐፍ ቅዱስን የሚስተካከለው የለም። ከ2500 ዓመታት በላይ ወደ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ሲተረጐም ኑሯል።

መጽሐፍ ቅዱስ በጠቅሳሳው /81ዱ/66ቱ/ ወደ 293 ቋንቋዎችና ዘየዎች ሲተረጐም ሐዲስ ኪዳን ለብቻ በ618፣ የተነጣጠሉ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ደግሞ በ918 ቋንቋዎችና ዘየዎች ተተርጉመዋል። /1/

ክጌታችን ልደት በፊት 900 ዓመት አካባቢ ከቀዳማዊ ምኒሊክ ጋር የመጡት የአይሁድ ሲቃውንት የብሉይ ኪዳንን የተወሰኑ ክፍሎች ይዘው በመምጣት ወደ ሳባ ቋንቋ ተርጉመውታል የሚሰው አባባል ርግጠኛ ከሆነ /2/ የዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ የተተረጐመበት የመጀመሪያ ቋንቋ የሳባ ቋንቋ መሆኑ ነው።

ከባቢሎን ምርኩ በኋላ/5ኛው መ/ክ/ዘ/ከክርስቶስ ልደት በፊት/ ተመላሽ አይሁድ በዕብራይስጥ የተጻፈውን ብሉይ ኪዳን በትክክል መረዳት የማይችሉበት ደረጃ ደርሰው ነበር። በአካባቢው የአራማይክ ቋንቋ የሠለጠነበት ጊዜ ነበርና። በዚህም ቦተኑ የወቅቱ ሊቃውንት የዕብራይስጥን ብሉይ ኪዳን ሐሳብ በአራማይክ ቋንቋ አሳጥረው /Paraphrase/ ይገልጹት ነበር። ይህም የአራማይክ ትርጉም ታርጉም /Targum/ በመባል ይጠራል። ከዚሉም የበለጠ ታዋቂ የሆነው ታርጉም የፍልስጤም ታርጉም /Palestinian Targum/ በመባል የሚጠራው ነው። /3/

በባቢሎን ምርኩ ጊዜም ሆነ ከምርኩው በኋላ በተፈጠሩ ችግሮች ወደ ግብጽ ተሰደው በዚያ ኑሯቸውን የመሠረቱት የእስክንድርያ አይሁድ ባደረጉት ግፊት በቶሊሞስ 2ኛ ፒላደልፎስ /285 247 ዓ.ፍ/ ትእዛዝ ሰባ ሊቃናት የዕብራይስጡን ብሉይ ኪዳን ወደ ግሪክ በ250 ዓ.ፍ ተረጐሙት /4/። ይህም «የሰባ ሊቃናት ትርጉም» (Septuagint or LXX) በመባል ይታወቃል።

ከዚህ የትርጉም ሥራ በኋላ የሰባ ሊቃናትን የግሪክ ትርጉም ለማሻሻል እነ አቂላ /130 ዓ.ም/፣ አርጌንስ /230–240 ዓ.ም/ አውሳብዮስ ዘቂሣርያ ፣ ሉቂያን ዘሰሞስታ እና ሄስኪየስ /4ኛው መ/ክ/ዘ/ ልዩ ልዩ ትርጉሞች ሠርተዋል። ይህ ግን ትርጉመ-ን ከማሻሻል ይልቅ አንዳንድ ጊዜ እርስ በርሳቸው የሚጋፉቱ ብዙ የትርጉም ሥራዎችን በማምጣቱ ትክክለኛው የቱ ነው? የሚል ጥያቄ በክርስቲያኖች ዘንድ ተፈጠረ /5/።

ይህንን ችግር ለመፍታት በግሰብ በ382 ዓ.ም የሮሙ ፓፕ ዳማሲስ 1ኛ አውሳብዮስ ሄሮኒመስን /ጀሮምን/ ለጉዳዩ ሰየሙት። ጀሮም ከ300–405 ዓ.ም ባለው ጊዜ ከጥንቱ ዕብራይስጥና ከሰባ ሊቃናት ትርጉም ጋር በማሰተያየት የመጀመርያውን የላቲን መጽሐፍ ቅዱስ አዘጋጀ። ይህ የጀሮም መጽሐፍ ቅዱስ «ቩልጌት» በመባል ይታወቃል።

እንደ ጀሮም ሁሉ የጥንቱን ዕብራይስጥና ግሪክ መጽሐፍ ቅዱሶችን መሠረት በማድረግ ወደየሀገራቸው ቋንቋ መጻሕፍትን የተረጐሙ እያሌ ሊቃውንት አሉ።

> አባ ሰላማ ከግዕዝ ብርሃንና ተስዓቱ ቅዱሳን /ከ350ጠ6ኛው ክ/ዘ/ የግብጽ ሊቃውንት /ከ2ኛው እስከ 4ኛው መ/ክ/ዘ/፣ የሮሐ ኤጲስ ቆጶስ ራቡላ /5ኛው መ/ክ/ዘ/፣ የመንበግ ኤጲስ ቆጶስ ፊልክሶስ /5ኛው መ/ክ/ዘ/፣ ቶማስ ዘሄራቅሊጠስ /7ኛው መ/ክ/ዘ/ የጥንቱን የሱርስት መጽሐፍ ቅዱስ አቃንተዋል።በአርማንያም ቅዱስ ሜስሮፕና ቅዱስ ሳሃክ /ከ3ኛው እስከ 4ኛው መ/ክ/ዘ / መጽሐፍ ቅዱስን ወደ አርመንያ ቋንቋ ተርጉመዋል። /6/

በአሁ ሮማንያና በዮንድ ጳኪያ (Dacia) ይኖሩ የነበሩት የጐቲኮች ወገን የሆነው ውልፊላ (Wulfila) /310 ዓ.ም ተወለደ/ መጽሐፍ ቅዱስን ከግሪክ ወደ ጐቲክ ቋንቋ ተርጉሞታል። /7/ ውልፊላ በ340 ዓ.ም ከአርዮሳዊው የቁስጥንጥንያ ጳጳስ ከአውሳብዮስ ዘኒቆሚ

ዲያ የጉቶች ጳጳስ ሆኖ ከተሾመ በኋላ ወደ ሀገሩ ቢመለስም ዘመዶቹ ስላልተቀበሉት በ350 ዓ.ም በቡልጋርያ ተቀምጦ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ሀገሩ ቋንቋ መልሶታል። /8/

በጠቅላላው እስከ ስድስተኛው መ/ክ/ዘ ድረስ መጽሐፍ ቅዱስ የተተረጐመባቸው ቋንቋዎች ግሪክ፣ ላቲን፣ ቅብጥ፣ ግእዝ፣ ሱርስት፣ አርሜንያ፣ ጆርጅያ እና ጐት ናቸው። /9/

በ8ኛው መ/ክ/ዘ አጋማሽ ቄርሎስ ዘሞራቪያ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ስሎቫክ ቋንቋ ተረጐመ፣ ከ9ኛው እስከ 10ኛው መ/ክ/ዘ የቄርሎስና የርሱ ደቀ መዝሙር የሜቶዲዮስ ተ ማሪዎች መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ራሺያ፣ ሰርቢያና ቡልጋርያ ቋንቋዎች ተርጉመዋል። /10/

ከ13ኛው እስከ 15ኛው መ/ክ/ዘ መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉና ልዩ ልዩ ክፍሎቹ ወደ አብዛኞቹ የአውሮፓ ቋንቋዎች ተተርጉመዋል። በተለይም ማርቲን ሉተር /1483 እስከ 1456/ ወደ ጀርመንኛ፣ ሄራሰመስ /1406 እስከ 1536/ ሐዲሰ ኪዳንን ወደ ላቲን፣ ቴንዴል /1494 እስከ 1536/ ወደ እንግሊዘኛ ተርጉመዋል/11/

የጎተንበት መሣርያ መፈልሰፍ /1443/ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉምን አበረታቷል። ብዙ ትርጉሞችም ከየአብያተ ክርስቲያናቱ ወደ ምእመኑ አጅ ታትመው ገብተዋል። ጀርመንኛ /1466/ ጣልያንኛ /1471/፣ ስፔንኛ /1478/፣ ፈረንሳይኛ /1487/ ታትመዋል። /12/

ከቴንዴል ቀጥሎ ኩቨርዳለ /1535/ ማቴያስ /1537/ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስን ለ ማዘጋጀት ተባዝተዋል። በ1604 በሐምፕተን በተጠራው የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ጉባኤ አዲ ስ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲዘጋጅ የቀረበውን ሀሳብ የእንግሊዙ ንጉሥ ጀምስ 1ኛ ተቀበለው። ከዚያም የተርጓሚዎች ቡድን በማደራጀት በ1611 እንዲጠናቀቅ አደረገ። ይህም ቦንጉሥ ጀምስ ትርጉም /King James version/ በመባል ይታወቃል። /13/

ዊሊያም ኬሪ የተባለ ሚሲዮናዊ በ1801 መጽሐፍ ቅዱስን /ከሌሎች ጓደኞቹ ጋር በመሆን/ ወደ 44 የሕንድ ቋንቋዎችና ዘዴዎች ተርጉሟል። አዶኒራም ጆድሰን /Adoniram Judson / በ1850 ወደ በርማ ቋንቋ፣ የስኩትላንድ ሚሲዮናዊ ሮበርት ሞሪሰን በ1823 ወደ ቻይንኛ፣ በ1837 ካርል ጉዝላፍ (Karl Gutzlaf) ዮሐንስ ወንጌልን ወደ ጃፓንኛ ተርጉመዋል። በጠቅላላው እስከ 1930 ድረስ በ13 የአስያ ቋንቋዎች መጽሐፍ ቅዱስ ተተርጉሞ ነበር። /14/

ወደ አፍሪካ መለስ ስንል የኢትዮጵያንና የግብጹን መጽሐፍ ቅዱሶች ትተን ስንም ከፋም መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ሌሎች አፍሪካ ቋንቋዎች የተመለሰው በ19ኛው መ/ክ/ዘ ነው ማለት ይቻላል። ዴቪድ ሊቪንግስተን በ1857 በደቡብ አፍሪካ ጽዋና (Tswana) ቋንቋ፣ በ1850ዎቹና 60ዎቹ ሳሙኤል ኤ ከሮውዘር ወደ ናይጄሪያ ዩሩባ ቋንቋ፣ በ1857 ጆን ዊልያም ቆሌንሶ ወንጌልን ወደ ዙሉ ቋንቋ ተርጉመዋል። /15/

የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ታሪክ በኢትዮጵያ

ምንም እንኳን የትርጉም ሥራው ዛሬ ባይገኝ የመጀመርያው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍ ቅዱስ ከፍል ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋ የተተረጐመው /ግእዝ/ ሳባ ያላልኩት በዚያ ዘመን የቱ ሠልጥኖ ነበር? በሚለው ነጥብ በሊቃውንቱ መካከል ከርከር ስላለ ነው/ ከጌታችን ልደት በፊት 900 ዓመት አካባቢ ነው። /16/

ከክርስትና መግባት በኋላ ደግሞ ብሉይን ከሰባ ሊቃናት ትርጉም ጋር በማዛመድና የሐ ዲስ ኪዳንን መጻሕፍት በመጨመር ወደ ግእዝ የተረጐሙት አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃንና ተስዐቱ ቅዱሳን ናቸው። /17/

ሰላማ መተርጉም /ሰላማ ዘእዜብ/ /ከ9-10ኛው መ/ክ/ዘ የቀድሞውን ትርጉም በማቃናት የነንቱን ግእዝ (Classical Geez) መጽሐፍ ቅዱስ በመካከለኛው ግእዝ (Medieval Geez)

ተርጉመውታል። /18/

መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ በነጠላ ትርጉም ወደ አማርኛ የመለሰው አባ ሮሜ የተባለ የጐንደር ተወላጅ መነኩሴ ነው /18ኛው መ/ክ/ዘ/። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ በ1816 አርባዕቱ ወንጌላት፣ በ1821 ሐዲስ ኪዳን፣ በ1832 ደግሞ ፴ሱው መጽሐፍ ቅዱስ ታትሞ ወጥቷል። /19/

እነ ማርቲን ፍላድ ከኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ጋር በመሆን ትርጉሙን ካሻሻሉት በኋላ በ1878 እንደገና ታትሞ ነበር። ዛሬ በብዛት በየሰው እጅ የሚገኘው 66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ የታተመው በ1953 ዓ.ም ነው። አለቃ ወልደ መድኅን ገብሩ ወደ ትግርኛ፣ አናሲሞስ ነሲቡ ደግሞ ወደ ሰሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስን ተርጉመዋል። /20/

የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐም
በኢትዮጵያ

ወደ ግእዝ

ከጌታችን ልደት በፊት 900ዓመት ወደ ኢትዮጵያ የገቡት የአይሁድ ካህናት መጽሐፍ ቅዱስን የተረጐሙት ወደ ግእዝ ነው የሚለው ሀሳብ ፴ሉ በ፴ሉ ስምምነት ላይ ባይደርስበትም እንኳን አመነጫጫቸው በነብረት በመሆኑ የተከተሉት የትርጉም መንገድ ሣዕከላዊ ሲሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል። በዚያ ዘመን የነበረውን የአሪት ቤተ ከህነት የሚመሩት ካህናትና ሊቃውንት በትርጉሙ ሥራ፣ ከትትልና ማረጋገጥ (Approval) ከአንድ እምነት ላይ መድረሳቸው ይገመታል።

በከሣቴ ብርሃን ሰላማ ጊዜም ሆነ በተሰዓቱ ቅዱሳን የትርጉም ሥራው የተለያዩ ሊቃውንት አንድ የግእዝ መጽሐፍ ቅዱስ ለማውጣት የደከሙበት ነው። በተስይም ተሰዓቱ ቅዱሳን ሥራውን ተከፋፍለው መሥራታቸው ይገመታል። ይሁን እንጂ በዘመኑ የቤተ ከህነቱ ሰዎች፣ በእንዲት ቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር፣ ሰተመሳሳይ ዓላማ የተፈጸመ በመሆኑ አሠራሩ ማዕከላዊ መሆኑ ይታመናል።

በለሳማ መቶርጉም /ሰላማ ዘአዜብ/ሁሰተኛውን የትርጉም ሥራ ለመሥራት፣ ተነሣሺነቱን ቢመሰክም የቤተ ክህነቱ ሰዎች በትርጉም ሥራው ተካፍለዋል/ምክንያቱም ሰላማ መቶርጉም እንደ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ከልጅነታቸው ጀምሮ ወይም ደግሞ ለብዙ ዘመናት በኢትዮጵያ ባለመኖራቸው ሰትርጉም ሥራ የሚበቃ ግእዝ ይችሉ ነበር ብሎ መገመት ይከብዳል/። ያም ሥራ ነባሩን ትርጉም የማቃናት ሥራ የተሠራበት እንጂ ከሌላ ምንጭ የመጣ አዲስ ትርጉም የተፈጠረበት አልነበረም። ሥራውም የተከናወነው በቤተ ከህነቱ በማዕከል ነው።

እስከዚህ ዘመን የተሠሩትን የግእዝ የትርጉም ሥራዎች ሰንመረምር ተመሳሳይ የሆኑ ባሕርያትን እናይባቸዋለን። እነርሱም፡-

1. ማዕከላዊነት፡- የትርጉም ሥራው የተከናወነው በቤተ ክህነቱ መሪነትና ተከታታይነት በመሆኑ ባለቤቱ አንድ ብቻ ነበር።

2. ሥልጣን፡- ተርጓሚዎቹ የአሪት ካህናት /ምሁራን ወይም የቤተ ክርስቲያን እባቶች የሃይማኖት መሪዎች በመሆናቸው የትርጉሙን ሥራ የመሥራት ወይም

የትርጉም ሥራዎችን ትክክለኛነቱን አረጋግጠ የመቀበል ሥልጣን አላቸው/የብሉይንም ሆነ የሐዲስን መጻሕፍት ትክክለኛነት አረጋግጠው በቀኖና የተቀበሉት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ናቸውና/::

3. አብነት:- ተርጓሚዎቹ /እስተርጓሚዎቹ በቤተ መቅደስ/ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ያሉ፣ የአሪት/ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርት የተማሩ፣ ሕይወታቸው ቤተ መቅደስን/ ቤተ ክርስቲያንን ማገልገል ብቻ የሆነ ለቤተ ክርስቲያን ትምህርትም ሆነ አምነት አብነቶች ናቸው እንጂ ሌጣ ምሁራ ን/secular scholars/ ::

ወደ አማርኛ

መጽሐፍ ቅዱስ ወደ አማርኛ ሲተረጐም ሦስት ዓይነት መንገዶችን ተከትሏል:: የመጀመሪያው በግለሰቦች የተተረጉሙት ሲሆኑ እነ አባሮሜ /አባ አብርሃም/ እነ ማርቲን ፋሳድና ሊሉቹም ያዘጋጁት ትርጉም በዚህ መልክ የተሠራ ነው:: ሁለተኛው ደግሞ በድርጅቶች የተፈጸመ ሲሆን የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበርንና የመሳሰሉት የሚሠሩት የትርጉም ሥራ ለዚህ ተጠ ቃሽ ነው:: ሦስተኛው ደግሞ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተተረጉመት የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶችን የሚያጠቃልለው ነው::

በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች አተረጓጐም ላይ የሚታዩ ችግሮች

በአማርኛ የቀረቡ መጽሐፍ ቅዱሶች ሕዝቡ ከማእዝ ቋንቋ እየራቀ ዘመምጸቱ በምእመናንና በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል የተፈጠረውን ክፍተት ለመሙላት ሞክረዋል:: ይኑን እንጅ እተረጓጎማቸው ከብለያየ ምንጭ፣ በተለያዩ እካላት፣ ለተለያየ ዓላማ በመሆኑ የአተረጓጎም ችግሮች አሉብቸው:: የተመሰኑትን ቀጥለን እንመለከታለን::

1. <u>የባለቤትነት ችግር</u>

መጽሐፍ ቅዱስ የአማርኛው ትርጉም የሚተረጉመው የሚከታተለውና ትክክለኛነቱን የሚያረጋግጠው ባለቤት የለውም:: የመተርጉም ፍላጐት ያለው ሁሉ ተርጉሞ ያሠራጨዋል:: ለምሳሌ በሰንበት ት/ቤቶቻችን

– የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር

-የሲታውንት ጉባኤ

–የጌዲዎን ዓለም ዐቀፍ ያሰተሚቸው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች ይገኛሉ:: ከነዚህም በተጨማሪ ደግሞ ከ12 ዓይነት በላይ የመጽሐፍ ቅዱስ የአማርኛ ትርጉሞች በምእመናን እጅ ይገኛሉ:: እነዚህን መጽሐፍ ቅዱሶች ትክክለኝነት ያረጋገጠው፣ ለምእመነቷን እንዲዳረሱ የፈቀደው፣ ስሕተት ካለባቸውም የሚያርመው ማን እንደሆነ አይታወቅም:: በየጊ ዜው ምእመናን በየሠርክ ጉባኤውና በየሰንበት ት/ቤቱ ጥያቄ ሲያነሡ ችግራቸውን ለማን ማቅረብ እንዳለባቸው ግልጽ አይደለም:: ቤተ ክርስቲያናችንም መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ ሀብቷ መሆኑን ተገንዝባ ባለቤትነቷን ስታስጠብቅና ትክክለኛውን ስታሠራጅ ስሕተቱንም ስታመጣዝ

አይታይም::

2. የመደበኛ ትርጉም ያለመኖር (Luck of Standardization)

ኪንግ ጄምስ 1ኛ የእንግሊዝ ሊቃውንትን ሰብስቦ መደበኛ ትርጉም እንዳሠሩት ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት የተዘጋጀ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ የለም:: ለምሳሌ ለሥርዓተ ቅዳሴ የምንጠቀምባቸው አራት ዓይነት የተለመዱ መጽሐፍ ቅዱሶች አሉ::

1. በ1947 ዓ.ም የታተመው ትልቁ መጽሐፍ ቅዱስ
2. በ1975 ዓ.ም በሊቃውንት ጉባኤ ተዘጋጅቶ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት የታተመው ሐዲስ ኪዳን
3. በ1970 ዓ.ም በማኅበረ ሐዋርያት የታተመው መጽሐፍ ቅዱስ /በልዩ ልዩ ጥራዝ/
4. በ1980 ዓ.ም በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ለኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የታተመው ትልቁ መጽሐፍ ቅዱስ

እነዚህ የቤተ ክርስቲያን የትርጉም ሥራዎች ናቸው በመባል የሚጠሩት ትርጉሞች በራ ሳቸው ልዩነት አሳቸው::

ለምሳሌ:-

በዘሌ. 11÷5- ሽኮኮ ያመሰኳል፣ ነገር ግን ሰኰናው ስላልተሰነጠቀ በእናንተ ዘንድ ርኩስ ነው:: / 1980 መ.ቅ. /

- ይህ ወንቀጽ በማኅበረ ሐዋርያት የ1970 መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም::

በዘሌ. 11÷14- ንሥር፣ ገዲ፣ ዐሣ አውጭ፣ ጭላት፣ ጭልፊት በየወገኑ /1980 መ.ቅ. /

- /ጊጸ/ አገዳ ስበር አሞራ፣ /ገላውቃ/ ጨት /አራት ራስ/ አሞራ፣ /ሆባይ/ አንጭት አሞራ ይህን የመሰለው ሁሉ/የ1970ዓም የ ማኅበረ ሐዋርያት መቅ/

ራእይ 1÷10- ፍጥሞ በምትባል ደሴት ውስጥ ሳለሁ አሑድ ቀን መንፈስ በእኔ ላይ መጣ:: /የሊቃውንት ጉባኤ ትርጉም/

- ፍጥሞ በምትባል ደሴት ነበርሁ:: በጌታ ቀን በመንፈስ ነበርሁ:: /የ1980 መ.ቅ./

ራእይ 1÷15- እግሮቹ በእሳት እንደ አጋሉት እንደ ሊባኖስ ነሐስ ናቸው:: ድምፁም እንደ መጣያ ውኃ ድምፅ ይመስላል /የሊቃውንት ጉባኤ ትርጉም/

– እግሮቹ በእቶን የነሐሪ የጋለ ናስ ይመስሉ ነበር፣ ድምፁም እንደ ብዙ ውኃዎች ድምፅ ነበር /የ1980 መ.ቅ/

በአንዲት ቤተ ክርስቲያን በብዛት ተቀባይነት ያገኙትን/የተተረጐሙትን እንኳን ስንመለከት ይህን ያህል የቅርጉም ልዩነት ካመጡ በልዩ ልዩ ተቋማት የተተረጐሙት ምን ያህል ሊሰዩ እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም። በመሆኑም በአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥያቄ ላይ የመጨረሻ የአማርኛ ትርጉም ማመሳከርያ (Last Reference)ሊሆን የሚችል መደበኛ ትርጉም የቱ እንደሆነ በርግጥ የሚታወቅ ነገር የለም።

3. <u>የትርጉሞች መብዛት የማያስከትለው መደናገር</u>

አንድን መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ቋንቋ በብዙ ዓይነት መንገድ መተርጐም አንባብያንን ያደናግራል። የሚነበበውን የመጽሐፍ ክፍል፣ ኃይለ ቃልና ሰም በአጃቸው በሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ካሳገኙት እውነትኛነቱን ይጠራጠራሉ። በአውሮፓ ቡተሊይ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ዓይነቶች በፈጠሩት የትርጉም ልዩነት «የእግዚአብሔር ቃል የቱ ነው?» በማለት እነ አህመድ ዲዳት አስከ መሳለቅ ደርሰዋል።

የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶችም /ቡኮለይ በቀላል አማርኛ ተተርጉመዋል እየተባሉ የሚወጡ ት/ በአገላለጥ፣ በቃላት አመራረጥ፣ በመሠረተ ሀሳብና በሰያሜ ያመጡት መለያየት ሕዝብ ክርስቲያኑን ትክክለኛው መጽሐፍ ቅዱስ የቱ ነው? እንዲል አድርገውታል። እስካሁን ድረስ እኔ እንዳየሁት ከ12 ዓይነት በላይ በአማርኛ የተተረጐሙ መጽሐፍ ቅዱሶች አሉ። እነዚህም ከመ ሠረታዊ የነገረ ሃይማኖት ልዩነት እስከ ቃላት ልዩነት የሚራራቁ ናቸው።

4. <u>ግድፈት</u>

በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች የሚታየው ሊላው ችግር ደግሞ ግድፈት ነው። በጥንታውያን የግእዝ፣ የሰብራይስጥና የግሪክ መጽሐፍ ቅዱሶች የሚገኙ ነጥቦች ተገድፈው ይታያሉ። ለምሳሌ. ከጥንቱ የግእዝ መጽሐፍ ቅዱስ የሚገኝና በአማርኛው የተገደፉ አንዳንድ ነገሮች እናንሣ።

– ዘፍ. 32፡43- ይትፈሣሕ ኩሉን ሰማያተ ጎቡረ ወይሰግዱ ሎቱ ኩሉሙ መላእክተ እግዚአብሔር

ይህ ሐረግ በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ተገድፏል። ነገር ግን ሐ ዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራ.1÷6 ጠቅሶት ይገኛል።

በዮሐ 3÷14– ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ የሚለው በጥንቱ የግእዝ መጽሐፍ ቅዱስ «የናሱን እባብ» በሚል የተገለጠ ነው። ይህም ከዘኍ.21÷8 ጋር ይዛመዳል።

– በሉቃ.2÷7 ወወለደት ወልደ ዘበኩራ፣ ወአሠረት መንኰቢያቲሁ ወጠ ብለለት በአጽርትት /ግእዝ. መ.ቅ/

በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ– የበኩር ልጇን ወለደችው፣ በመጠ ቅለያም ጠቀለለችው የሚል እንጂ –አሠራ፡ ጣቱን እሠረችው /ወአ ሠረት መንኰቢያቲሁ/ የሚለው ተገድፏል። በኩር ሲወለድ አሠራ-

ጣቱን ማሠር በእሥራኤል ልማድ ለመሆኑ በዘዳ.38÷26-30 ባለው ታሪክ የትዕማር አዋላጅ የፈጸመችው ምሥክር ነው።

- ዮሐ.20÷15- ንግረኒ ጎበ መሰድኩ ከመ እሑር አነ መእንሥእ ኀቤየ መአቀብየ ዕፍረተ

  - ወዴት እንዳኖርኸው ንገረኝ እኔም እወስደዋለሁ አለችው /በብዙ የአማርኛ መጽ የሚገኝ/ «ሽቱ እንድቀባው» የሚለው ሐረግ ተጎድፏል።

- ዮሐ.21÷6- ሠራሕነ ኩሳ ለሊት መአልዘ ዘረከብነ መአምነትኒ ወበቃልከሰ ናወርድ/ሴሊቱን ሁሉ ደክምን አንዳች ግን አላገኘንም። ነገር ግን ስለቃልህ አንጥለዋለን/

  - በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች /ከ1980 ዓ.ም በፊት/ አይገኝም።አርሱም ቢሆን ከሉቃስ የተወሰደ ነው ይላል።

5. <u>ሙላቴ</u>

ሊላው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ችግር የቃላት ወይም የስሞች መለዋወጥ ነው። ለምሳሌ፦

ሉቃ.2÷24 «ዋኖስ» የሚለው በአማርኛው «ዋልያ» ተብሏል።

ማቴ.1÷19 ወዮሴፍስ ፈጻሪሃ እስመ ጸድቅ ወእቱ ኢፈቀደ ይክሥታ፡ አላ መኪረ ጽሚተ ይኅድጋ

- «ሊገልጣት አልወደደም» የሚለው በአዲሱ የአማርኛ ትርጉም ሊ ያጋልጣት አልወደደም / የኢትዮጵያ መጽ ማኅበር በ1980 ተለል ባለ አማርኛ ያተመው መጽ/ ተብሎ ተቀምጧል።

- መዝ.44÷16 ኀቡኦ አዘውኒ ተወልዱ ለኪ ደቂቅ ወትሰይሚየ መላእክተ በኩሉ ምድር ወይዘክሩ ስምኪ በኩሉ ትውልደ ትውልድ

  የሚለው ትንሣኤ አሳታሚ ድርጅት በ1984 ዓ.ም ባሳተመው ጸዊትና በአዲሱ የ1993 መደበኛ ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ በመንድ አንቀጽ

  « በአባቶችህ ፋንታ ልጆች ተወለዱልህ በምድርም ሳይ አለቆች አድርገህ ትሾማቸዋለህ ለልጅ ልጅም ስምህን ያሳስባሉ ተብሎ ተተርጉሟል።

- ሮሜ.8÷34. ወይትዋቀሳ በእንተአነ ስለሣ ይካሰሳል የሚለው

  ስለሣ ይግልጻል ተብሎ ተተርጉሟል።

- ሮሜ. 8÷26 ወባሕቱ መንፈስ ለሊሁ ይትዋቀስ ለነ- መንፈስ ቅዱስ ግን ራሱ ስለኛ ይካሰስራል /ይፈርድልናል/

– ነገር ግን መንፈስ ራሱ በግልጥነገር መቃተት ይገልጽልናል። ተብሏል።

- 1ዮሐ. 2÷1. መአመኒዩ ዘአበሰ ጸራቅሊጦስ ብነ ኀበ አብ ኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቅ ውእቱ ይኅድግ ለነ /የበደለም ቢኖር ጸራቅሊጦስ አለን፣ዘአባት ዘኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ጥሩ ነው።ንጠቢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ።/

  – ማንም ኃጢአት ቢያደርግ ዘአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም የኃጢአታችን ማስተሥረያ ነው።/አብዛኞቹ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች/

- ዘሌዋ. 11÷22 ዝንቱ ዘትበልዑ መዝንቱ ዘኢትበልዑ እምኔሁ ደጉብያ መዘአምሳሊሁ፣ ወአቃጣን መዘአምሳሊሁ፣ ወአፍዮግክን መዘ አምሳሊሁ፣ ወአንበጣ መዘአምሳሊሁ። –«ከነ የምትብሉትም ይህ ነው፣ የማትበሉትም ይህ ነው። ደጉብያና የሚመስለው ሁሉ፣ አቃጣንና የሚመስለው ሁሉ፣ አፍዮግክንና የሚመስለው ሁሉ፣ አንበጣና የሚመስለው ሁሉ»

  – ከእነርሱም እንዚህን ትበላላችሁ። አፉቱን ዓይነት አንበጣዎች በየመነናቸው /የ1980 ዓ.ም መ/ቅ /

  The locust after his kind, and the bald locust after his kind, and the beetle after his kind and the grasshopper after his Kind (KJV-1611)

- 1ዮሐ.5÷7 እስመ ሠለስቱ እሙንቱ አለ ይነውኑ ስምዐ በሰማያት አብ ወወልደ ወመንፈስ ቅዱስ

  / የቡራና መጽሐፍ ሠለስቱ ሐዲሳት፣ ከጉንደር አደባባይ ኢየሱስ የተገኘ/

  – የሚመሰክሩት መንፈሱና ውኃው ደሙም ሦስት ናቸውና። ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ /የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ/

  For these are three that bear witness in heaven: the Father The Word and the Holy Spirit: and these three are one. (KJV 1611, The Orthodox study Bible-1993)

- ዮሐ 2÷4 ወይቤላ አግዚእ ኢየሱስ ምንት ብየ ምስሌኪ ኦ ብእሲቶ

  - Woman, what have I do with thee (KJV. 1611)

  – 'Woman' የሚለው አጠራር በጥንቱ ዘመን የክብርና የልዕልና ማዕረግ ነው። /21/

  – በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች– «አንቺ ሴት» በሚል ተራ ንግግር ተተርጉሟል።

- «መዝሙረ ዳዊት» በመባል የሚጠራው የዳዊት መዝሙር በቅርቡ በሚወጡት የአማርኛ

መጽሐፍ ቅዱሳች «መጽሐፈ መዝሙር» እየተባለ ቀርቧል።መጽሐፉ ከዚህ በፊት በቤተ ክርስቲያን ላለፉት 2000 ዓመታት ከሚታወቅበት ስያሜ በተለየ ስም የተጠራበት ምክንያትና ጥቅሙም ግልጽ አይደለም።ምናልባት ዳዊት ደጋግሞ የሚባለውን ነገር ለ ማስቀረት ካልሆነ በቀር።

6. ሞገሬ

መጽሐፍ ቅዱስን የሚተረጉም ሁሉ የመጽሐፉን ትክክለኛ መልእክት በመተርጉሚያው ቋንቋ ማስተላለፍ ብቻኛው ዓላማው መሆን አለበት። ከዚህ ሠጭ የራሱን እምነት ወይም ደግሞ አመለካከት በልዩ ልዩ መንገድ የሚጨምርበት ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑ ቀርቶ ግላዊ አመለካከት መጽሐፍ ይሆናል።

እነዚህ ፍጭግሪዎች በሰፊው የሚታዩት በግርጌ ማስታወሻዎች ላይ ነው። ለምሳሌ

በ1993 ዓ.ም የዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር መደበኛ ትርጉም ብሎ ያሳተመው አዲስ መጽሐፍ ቅዱስ ለዘፍ. ዘፍ.18÷1–3 በሰጠው የግርጌ ማስታወሻ «ሦስት ሰዎች» የሚለውን ሲ ተረጉም «ሁለቱ መላእክት ከእግዚአብሔር ጋር» የሚል አስቀምጧል። ይህ ግን ስህተትም አሳስፈላጊም ማስታወሻ ነው።

ለዕብራ. 13÷2– አንዳንዶች ሳያውቁ መላእክትን እንግድነት ተቀብለዋል ለሚለው የተሰጠው የግርጌ ማመሳከሪያ ዘፍ.18÷1–3 ያለው ነው። ይህ ግን ስሕተት ነው። አብርሃም ሥላሴን ተቀበለ መላእክትም ከሥላሴ ስለማይለዩ መጥተዋል ብሎን ካለጠንን በቀር አብርሃም መላእክትን ተቀበለ የሚል ትምህርት የለም/እግዚአብሔር በሙሃራ አድባር ተገለጠለት–አለ እንጅ አግዚአብሔር ከመላእክት ጋር ተገለጠለት አላለም/።

- በዘፍ.11÷17 ኦ እንሙራድ በግለት እግዚአብሔር በአንድነት በሦስትነት የተናገረውን የ1993 ዓም የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር መደበኛ ትርጉም / መቅግጠት/ በግርጌ ማስታወሻው«ኦ እንሙራድ የሚለው ከሰማይ የወጣው የእግዚአብሔር ቃል ኦ እንሥራ ለሚለው ከምድር ለመጣው ቃል አጸፋ ነው። »ይላል። ይህን መሰል ትምህርት የያዘውን መጽሐፍ የቤተ ክርስቲያን ነው ብሎ መቀበል እንዴት እንደተቻለ አጠያያቂ ነው።

- ለ ይሁዳ.9 የተሰጠው «የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ግን ስለ ሙሴ ሥጋ ከዲ ያብሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ...»የሚለውን ኃይለ ቃል በግርጌ ማስታወሻው ሲ ተረጉም«እነዚህ ጥቅሶች የተወሰዱበት መጽሐፍ የእግዚአብሔር አስትንፋሳዊ ቃል ነው እንድንል አያደርገንም» ይላል/ መቅግጠት/

- ለይሁዳ.14 በተሰጠው የግርጌ ማብራርያ የሄኖክን መጽሐፍ «አዋልድ መጽሐፍ» ይለዋል/መቅግጠት/

- ያዕ.2÷2፡ «አብራችን አብርሃም ልጁ ይስሐቅን በመሠዊያው ላይ ባቀረበ ጊዜ በሥራ የጸደቀ አልነበረምን?»የሚለውን ሲተረጉም«ክፍሉን ከዘመዱ ንጥልን ከተመለከትነው ሰው ድኅነት የሚያገኘው በእምነት እንጂ በሥራ አይደለም ከሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የሚቃረን ይመስላል። ያዕቆብ የሚለው ግን የጽድቅ ሥራ የእውነተኛ እምነት መገለጫ እንጅ ለድኅነት የሚያበቃ አይደለም...» /መቅግጠት/

በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች ላይ የሚታዩት ችግሮችና የችግሮቹም ዓይነቶች እነዚህ ብቻ አይደሉም።ሰፊና ዋልቅ ጥናት ቢደረግ ብዙ ነገሮችን መመልከት ይቻል ነበር።ዋናው ነገር

ግን ችግሮች መኖራቸውንና የችግሮቹን ዘርፈ ብዙነት ተገንዝበ ጥንቃቄ ለመውሰድ መነሣቱ በመሆኑ ለአብነት የቀረቡት ምሳሌዎች የሚጠቁሙት ዐቢይ ነገር አለ። አተረጓጎማችን ችግር እየገጠመው መሆኑን ::

<u>መፍትሔ</u>

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደመሆኑ መጠን ወደ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ሲ መለስ ጥንቃቄ ያሻዋል። የራስን አመለካከት ለማንጸባረቅ ወይም ደግሞ ኑፋቄን ለማሥረጽም ሊ ውል ይችላል። ስለዚህም በተለይ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ አየታዩ ላሉት ችግሮች አስቸኳይ መፍትሔ የመስጠቱ ተግባር ይሞል ይደር እይባልምና የዚህ ጥናት አቅራቢ የሚከተሉትን መፍትሔዎች ሊጠቁም ይወዳል።

1. <u>መደበኛ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ማዘጋጀት፡-</u> ክግእዝ፣ ዕብራይስጥ፣ ግሪክና ቅብጥ ጥንታዊ መጽሐፍ ቅዱሶች ጋር የተገናዘበ መደበኛና ለአማርኛ የመጨረሻ ምሥክር እና ለሥርዓተ ጸሎትና ለትምህርት የሚሆን መጽሐፍ ቅዱስ ማዘጋጀት

2. <u>ማዕከላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ምርምር ማዕከል ማቋቋም፡-</u>የመጽሐፍ ቅዱስ ጥንታዊ ቅጅዎች የሚቀመጡበት፣ ነጠላና አንድምታ ትርጉሞችን የሚሠሩበት፣ በትርጉም ሥራዎች ላይ ምርምር የሚካሄድበትና መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ ለጠየቅ የሚችል ማዕከል ማቋቋም ያስፈልጋል። ይህ ማዕከልም ሳንጠቀምባቸው እያለፉ፣ በየቦታው ተበታትነው እየተቸገሩ ያሉትን ሊቃውንት ለማሰባሰብና ዕ ውቀታቸውንም በተገቢው መንገድ ለመጠቀም ያስችላል።

3. <u>በየጊዜው ትምህርት መስጠት፡-</u> በውስጣቸው የጉሳ ስሕተት ያለባቸው አያሌ የአ ማርኛ መጽሐፍ ቅዱሶች በየአብያተ ክርስቲያናቱና በየሰንበት ት/ቤቱ ተሠራጭተው በጥቅም ላይ እየዋሉ ነው። አነዚህ ትርጉሞች ስሕተትን ከማካመታቸውም በላይ በምእመናን መካከል የክርክርና የመለያየት ምክንያት እየሆኑ ነው። በመሆኑም ስሕ ተቱን ስሕተት ትክክሉን ትክክል ብሎ ለመለየት የሚያስችል ትምህርት በየጊዜው መስጠት ያስፈልጋል።

4. <u>ቤተ ክርስቲያናችን ከመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ጋር ያላትን ግንኙነት እንደገና ብትመረምረው፡-</u> ከቤተ ክርስቲያንም መሠረተ እምነት ጋር የሚጋጨ፣ የትክክለኛውን የመጽሐ ፍ ቅዱስ ቃል የሚያዛቡ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ሰም ይታተማሉ። ያንን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ያዘጋጁት «አብያተ ክርስቲያናት» ስም ዝርዝር ውስጥ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ተጠቅሳለች። ይህ ደግሞ ምእመናን አባቶቻቸውን እንዲጠራጠሩና ለስሕተት እንዲጋለጡ ያደርጋልና ቤተ ክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ውስጥ ያላትን ሚና ብትመረምረው መልካም ነው።

<u>ማጠቃለያ</u>

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ለሕዝቡ ሁሉ አስፈላጊ ምግብ ነው። ይህ ምግብ ግን ጤናማ ሕይወት የሚሰጠው ሳይበረዝ የተሪበ እንደሆነ ነው። ስለሆነም አቡን እየወጡ ያሉት የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ሊታሰብባቸው፣ ሊመረመሩና ሰንዴውን ከእንክርዳዱ የመለየት ተግባር በአስቸኳይ ሊከናወን ይገባል። ወለእግዚአብሐር ስብሐት

የግርጌ ማስታወሻ

1. Tkent C. Butler(ed). Holman Bible Dictionary. USA. 1991. P 188
2. ትንሣኤ ዘጉባኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣ መጽሐፍተ ሰሎሞን መሰረታዊ ጉባዬና ትርጓሜው፣ አዲስ አበባ፣ 1989 ዓ.ም /መግቢያ/
3. Allen C. myers(ed). **The Eerdmans Bible Dictionary**.WM. Eerdmans pub. company 1987. P. 154
4. Ibid; Holman p. 188
5. Eerdmans ,p154
6. የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ ኤፈስ አበባ፣ 1972 ዓ.ም ገጽ 82
7. Readers Digest. The Bible Through the Ages. Readers Digest Ass. New york. 1996. p. 224
8. Ibid
9. Holman. p. 189
10. The Bible Through the Ages. p. 235
11. የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ ገጽ 83
12. Holman, p. 188
13. The Bible Through the Ages, p. 316
14. Ibid
15. Ibid. p. 325
16. ዓባይነህ ካሤ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ኀይ መጽሐፍ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ ሚዜጋ ማተሚያ ቤት፣ 1992 ዓ.ም ገጽ. 33
17. ዝኒ, ከምዙ ገጽ 35
18. Belayinesh Michael and others, The Dictionary of Ethiopian Biography. V1.1. IES. Addis Ababa University. 1975. P. 143፣ ስንክሳር ኀሙሴ 20
19. የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ገጽ 83
20. ዝኒ, ከምዙ
21. Fr. peter E. Gillquist and Others, The Orthodox Study Bible. Thomas Nelson pub. 1997. p. 215

የአብነት ትምህርት ቤቶች

ንጉት ከበደ
ማኅበረ ቅዱሳን
ኔዘሚትና አደባራት እና የአብነት ት/ቤቶች
መረጃና ማቋቋሚያ ንዑስ ክፍል
ስ.ቁጥር 5651159



ንጉት ከበደ የተናት መረቀታቸውን ሲያተርቡ

1. *መግቢያ*

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ክብረከተቸው የእምነት እና የሥራ ውጤት እንዱ ዛሬ በዓለማችን ሳይ የራሳቸው ፊደላት ካላቸው ጥቂት ሀገሮች ሙስጥ ብቸኛዋ የአፍሪካ ሀገር እንድትሆን ማድረጓ ነው። በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሙስጥ በእነዚህ ቁጥር እና ፊደላት የመጀመሪያ ተጠቀሚዎቹ ደግሞ የቆሎ /የአብነት/ ትምህርት ቤቶች ናቸው።

ቀለም ቢበጠበጥ፣ ብራና ቢፋቅ፣ መጽሐፍ ቢጻፍ፣ ዜማርቅ ቢለበጥ፣ በእንጭት ዝቡን ሳይ ቅዱሳ ቢሳሉ፣ ካህኑ መሪጌታው፣ የኤታ ሊቅ ጳጳሱ፣ ፓትርያርኩ ሁሉም በአጠቃላይ ከቆሎ /በአብነት/ ትምህርት ቤት ውጤት ናቸው።

የዘመናዊ ትምህርት ወደ ሀገራችን ከመግባቱ በፊት ቀደምትነት እንዲሁም ሰዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት መሠረትነት ያላቸው እነዚህ የላሬምቹ የአብነት ትምህርት ቤቶች መሆናቸው የማይካድ ሀቅ ነው። የቆሎ ተማሪ ከተባለ ብዙምቶችን በአእምሮአችን ሙስጥ የተሳሉ ነገሮች አሉን። ይኸውም የቆሎ ተማሪ ማለት ቦር ለምኖ ካልበላ፣ ውኛ ካልነከሰው፣ እከክ ካልያዘው ብቻ በደፈናው ካልተቸገረ ትምህርት እንደማይገባው እንደሆነ ነው። ይህንንም ለረጅም ጊዜ የቆሎ ተማሪ ሪምችም፣ ጎብረተሰቡም አምኖበት የማሠራበት ነበር። ዛሬስ? ይህን አባባል ተማሪውም

ጎብረተሰቡም ይተበለሞል? እንኳህ የአብነት ትምህርት ቤቶች ዛሬ በምን ደረጃ ላይ ይገኛሉ?

ዛሬ እየመነመኑ እና እየተዘጉ ስመጡት የአብነት /የቆሎ/ ትምህርት ቤቶች ዋና መንስኤዎች ምንድናቸው የሚለውንም ማየት አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም የዛሬ የአብነት ትምህርት ቤቶቻችን የነገው ተተኪ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት አባቶች ማፍሪያ መድረክቻችን ናቸውና።

1.1 የጥናቱ ዓላማ

በአሁኑ ወቅት እየተዳከሙ የመጡትን የአብነት ትምህርት ቤቶች ምክንያታቸው ምን እንደሆነ በማጥናት ጠቃሚ መፍትሔዎችን ከመሰንዘር፣ ከዚህ በተጨማሪ ሰሌሎች ጥናቶች መነሻ እንዲሆን እና በርዕሱ ዙሪያ ላለው ችግር ተግባራዊ ሊሆን የሚችል መፍትሔ ስመፈለግ ነው።

1.2 መላምት

የአብነት ት/ቤቶች ጥናት በነበሩበት ሁኔታ ስላሉ ወይንም አሁን ካለው ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ጋር አብረው ስላልሄዱ እየመነመኑ እና እየተዘጉ ይገኛሉ።

1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት

የአብነት ት/ቤቶች ያሉባቸውን ችግሮች ለማየት እና መፍትሔ ለማፈላለግ

1.4 የጥናቱ ዘዴ

ይህን ጥናት በስድስት ገዳማት በሚገኙ 15 የአብነት ት/ቤቶች ሙስዋ በመማር ላይ ላሉ 166 ተማሪዎች የቡድን ውይይት /focus group discussion/ በማድረግ ለ15 መምህራን እና ከገዳ ማቱ አስተዳዳሪዎች ጋር መጠይቆችን በመጠየቅ እና የመስክ ምልከታ በማድረግ እንዲሁም የተለያዩ ጽሑፎችን በማንበብ መረጃዎችን ስመሰብሰብ ተሞክሯል።

2. በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች እና የሚመስድባቸው ዘመን

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የለውቀት ምንጭ ናት። ዘመናዊ ትምህርት ወደ ሀገራችን ሳይገባ ቤተክርስቲያን የአብነት /የቆሎ/ ትምህርትን በሥርዓቱ ከፋፍሳ ስተማሪዎችም ደረጃ አውጥታ ስታስተምር ኖራለች፣ አሁንም በማስተማር ላይ ትገኛለች። በዚህ የትምህርት ሕ ይወት ሙስዋ የቤተክርስቲያን አባቶች ብቻ ላይሆኑ በኅብርናውም፣ በንግድም አንዲሁም በዘመናዊ ትምህርት ውስዋ የገቡ ሁሉ የሚያልፉበት፣ ያለፉበት ነበር። ዛሬም እያለፉበት ይገኛል። ስለዚህ ለዚህች ሀገር ይህች ቤተክርስቲያን እጅግ ብዙ ነገሮችን አበርክታለች። ከነዚህም ሙስዋ፣

ሀ. ሙሉ ትምህርት
ለ. ፍፁም ቋንቋ ከነፊደሉ
ሐ. ሥነ ጽሑፍ ከነለባዩ፣ ከነሙያው
መ. ኪነ ጥበብ በየዓይነቱ
ሠ. ሥነ ጥበብ በየመልኩ
ረ. ታሪካዊና ጥንታዊ ቅርስ
ሰ. እምነት ከሰፍልስፍናው
ሸ. ነፃነት ከክብሩ
ቀ. አንድነት ከነጀግንነቱ
በ. አገር ከነድንበሩ
ተ. ስም ከነምልክቱ ከትርጉሙ /አባ ጎርጎርዮስ፣ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፣ 1974 ፣ ገጽ 9/

አሁንም ቢሆን ትውልዱ ጀግንነትን፣ አገር ወዳድነትን ለታሪክ፣ ለባሕልና ለሃይማኖት ተቆርቋሪነትን ይዞ እንዲያድግ በማስተማርና በማበረታታት ቤተክርስቲያን የበኩሏ ድርሻ አላት። ጥንታዊት፣ ታሪካዊት እና ብሔራዊት የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርቱን በሦስት ታላላቅ ክፍሎች ከፍላ እያስተማረች ትገኛለች። እነርሱም፣

1. ለጀማሪዎች /የመጣንያን/
2. ለማስነሳዊያን /መለስተኛ ዕውቀት ላላቸው/
3. ለምሁራን

2.1 ለጀማሪዎች /ለመጣኒያን/

ለጀማሪዎች ወይንም ለመጣንያን የሚሰጠው ትምህርት ንባብ ቤት በመባል ይታወቃል። በዚህ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጠው በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች ሲሆኑ አብዛኛውን ጊዜ ልጆች አራት ዓመት ከሞላቸው በኋላ የሚጀምሩት ነው። ይህ ለጀማሪዎች የሚሰጠው የትምህርት ዓይነት ሦስት ክፍሎች አሉት።

ሀ. ፊደል ት/ቤት

ለ. ፊደል ሐዋርያ

ሐ. ንባብ ሐዋርያ /ዝቡኦ ሐዋርያ/

ሀ. ፊደል ት/ቤት /የፊደል ሥርዓተ ትምህርት/

በዚህ የመዋዕለ ሕፃናት ት/ቤት ለቋንቋው መሠረት የሆኑ ፊደላት በጥንቃቄ ይሰጣሉ። እያንዳንዱ ፊደል ሰባት የተለያዩ ቅርፆች /አኒጋጋሪ ቅጥያዎች/ ያሉት ሲሆን ይህ ክፍል እነዚህን ለይቶ ስማወቅ ያስችላል። ከዚሁ ጋር የአቡጊዳ ፊደላትን የአኃዝን /የሒሣብን/ ትምህርት ከፊደሉ ጋር አብረው በመገበለት የቁጥርን መልክና ቅርጽ እንዲሁም የግእዝ አቆጣጠርን ያጠናሉ።

ለ. ፊደል ሐዋርያ

በዚህ ክፍል ውስጥ የሚማሩት /ሕሣሩቱ/ የፊደልን ትምህርት በሚገባ አጠናቀው የመጡ ሲሆን እዚህ የሚማሩት «መልእክተ ዮሐንስ ሐዋርያ ወልደ ዘብዴዎስ» ብለው ስለሃይማኖት ጥልቅ ምሥጢር የያዘውን የሐዋርያው የቅዱስ ዮሐንስን መልእክት /ምዕ1+1/ ፊደላቱን በሚገባ ካወቁ በኋላ በአንደኛው ደረጃ ማእዙን ያግባሉ። ይህም ማለት ከቁጥር ለቀቅ ባለ መልኩ ሁለቱን ፊደላት አንድ ላይ አድርገው ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከቀኝ ወደ ግራ፣ ከላይ ወደታች፣ ከታች ወደ ላይ፣ በመስቀልያ ይመሳልሱታል። በሁለተኛ ደረጃ ውርድ /ንዑስ/ ንባቡን በዕለተ ስቅለት ግብረ ሕማማት በሚነበብበት የንሀን መልእክ ባለው ቤዛ ያነባሉ፣ በሶስተኛ ደረጃ ቁም /ዓቢይ/ ንባቡን ያለ ችግር በተዋሂዶ ያነባሉ። ከዚህ በኋላ ተማሪዎች ከፊደል ቆጠራ እንደወጡ ተደርገው ይቆጠራሉ።

ሐ. ንባብ ሐዋርያ /ዝቡኦ ሐዋርያ/

በዚህ የትምህርት ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች ሳይቆጠቡና ሳያግዙ ያገኙትን መጽሐፍ እንደተረዘላቸው በቀጥታ ተነሺውንና ወዳቂውን ሩቅና ቅርቡን ወንዱንና ሴቱን ነጠላውንና ብዙውን ስይጥሙ ዘርፍና ባሕሌቱን ያነባሉ። በቤተ ክርስቲያን የተመሰኑትን ለንባብ አስቸጋሪ መስለው የትባመቱት መጻሕፍት መጽሐፈ ግንዘት፣ አርጋኖን፣ መቅድምና ተአምረ ማርያም፣ ተአምረ ኢየሱስ፣ ውዳሴ እምላክና ሠዓታሐፈ አርድእት የመሳሰሉት ናቸው። በቅዳሴ ጊዜም በቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ሃይማኖተ አበው ከቅዳሴ በኋላም ሰንክሳርን በአትሮኑስ ላይ ዘርግተው ያነብ ባሉ።

ከዚህም ሌላ በጥንቱ ሥርዓተ ትምህርት ላይ ለልጆች የግብረ ገብ ትምህርት ከፍተኛ ቦታ ነበረው። ልጆች በግብረ ገብ ታንፀው እንዲያድጉና ትህትና እንዲሠሩ፣ ታላላቆችን እንዲያከብሩ የተሰየ ትምህርት ይሰጣቸዋል። በተጨማሪ መጠንም ልጆች መጻሕፍተ ሰሎሞንን እንዲያነቡና

በውስጡም ያለውን ምሥጢር እንዲያውቁ ያደርጓቸዋል። ከሕግጋትም ውስጥ የግብረ ገብነትን እና የእምነት አንቀጽ ያለበትን ያስጠኑአቸዋል።

2.2 ለማዕከላውያን /መለስተኛ አውቀት ላላቸው/

ለማዕከላውያን ወይንም መለስተኛ ዕውቀት ላላቸው የሚሰጠው ትምህርት በክፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መከናወን የሚገባቸው የትምህርት ዓይነቶች ናቸው። እነዚህም

2.2.1 ዜማ

2.2.2 የቅኔ ትምህርት ናቸው

2.2.1 ዜማ ቤት

ዜማ ማለት የምስጋና መዝሙር ስልት ያለው ጨኸት፣ የንዋየ ማኅሌት፣ የደስታ ድምጽ ማለት ነው። ደራሲው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እንዚራ ቅዱስ ያሬድ ነው። የዜማው ስልት በሦስት መሠረታውያን መደቦች ይጠቃለላል። እነሱም ግእዝ፣ እዝል እና አራራይ በመባል ይታወቃሉ። በዜማው ሥርዓት ውስጥም ዋና ዋና ምልክቶቹ ድፋት፣ ይዘት፣ ሂደት፣ ሙሪት፣ ቅናት፣ ቁርጥ፣ ርክርክ፣ ደረት፣ ድርስ፣ አንብር ናቸው።

የዜማ ቤት ጸዋትዎ ዜማን /ቅዳሴን፣ ጸመ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬ እና መዋስዕት/ የቅዱስ ያሬድን ድርሰት ሁሉንም ያጠቃልላል። እነዚህ ትምህርቶች ብዙ ጊዜ የፈጁት ትምህርት በመባልም ይታወቃሉ። የቅዱስ ያሬድ የዜማ መጻሕፍት በቁጥር አምስት ሲሆኑ እነርሱም፡- ድጓ፣ ጸመ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ዝማሬና መዋሥዕት ይባላሉ።

ሀ. ድጓ

በትርጉሙ ዜማ መዝሙረ ኃዘን፣ ሙሾ፣ ረቂቅ ማለት ሲሆን በታላላቅ በዓላትና በሰንበተ ክርስቲያን የሚደርሱትን የዓመቱን መዝሙራት አጠቃልሎ የያዘ የዜማ መድብል /ምንጭ/ ነው። ስለዚህ ሌሎች የዜማ መጻሕፍት ሁሉ ከዋናው ምንጭ ከድጓ የተቀዱ ናቸው።

ድርሰቱ በጥራቱ ብቻ ሳይሆን በኃይለ ቃሉ ታላቅ አንደመሆኑ ለዝማሬ ይመች ዘንድ በአራት ወንጌላት ምሳሌ በአራት አርእስት ተከፍሏል። አነርሱም ዮሐንስ፣ አስተምህሮ፣ ጸመ ድጓና ፋሲካ ይባላሉ። እንድም በአራቱ እንሰሳት ኪሩቤል አምሳል ቁም ዜማ ፣ ዝማሜ፣ ድፋትና መረግድ የተባሉ የዜማ ስልቶች አሉት።

የታወቀው የድጓ ማድረሻ ጊዜ አራት ዓመት ሲሆን አንዳንድ ፈጣን ተማሪዎች ግን ከዚህም በፊት ፈጽመው ይሄዳሉ። አስከ ሰባት ዓመትና ከዚያም በላይ የሚቆዩ አሉ። የዜማ ምልክቶችን ከጠረፍ እስከ ጠረፍ በቃል አጥንቶ ጽሮ አመልክቶ ጥሩ የድጓ መምህር ለመሆን ከ10-15 ዓመታት ሊወስድ ይችላል። ስለድጓ ሲነሳ የማይታለፈው ድጓ ዘሩ አንድ ዓይነት ሆኖ የዜማው ስልት /ቃና/ በአምስት ይትበሃል ይነገራል። እነርሱም፣

1. የዜተልሔም የዜማ ልክ
2. የአጫብር የዜማ ልክ
3. የቆሚ /ዋድሴ/ የዜማ ልክ
4. የተጉለቴ የዜማ ልክ
5. የወንጪራ የዜማ ልክ ናቸው።

ለ. ጸመ ድጓ

ከድጓው አንደኛው ክፍል ነው። ይህን ስያሜ ያገኘበት ምክንያትም በዐቢይ ጾም የሚዘመር ለጾም ጊዜ አገልግሎት የተቀመረ በመሆኑ ነው። ጸመ ድጓ ለብቻው ወንበር ባይኖረውም ከምዕራፍ ጋር ለጀማሪዎች ይሰጣል። ጸመ ድጓን ደህና አድርጎ ለማጠናቀቅ ከአንድ ዓመት ያ ላነሰ ጊዜ ይወስዳል።

ሐ. ምዕራፍ

በመርሃ ጸም የሚደርስ በስንበትና በክብረ በዓላትም ከዋዜማው ጀምሮ የጸሎት የምስጋናና የዜማ ሥርዓት የሚከናወንበት ነው። ምዕራፍ በቀጥተኛ ትርጉሙ "ማረፊያ ማሳረፊያ" ማለት ሲሆን በዜማ ቤት ደግሞ በመላ ስላም ለኪ ብሉ ጀምሮ የጸም ምዕራፍ እስኪፈጸም ድረስ ያለው ትምህርት ኡሉ ምዕራፍ በመባል በኡለት ይከፈላል። የምዕራፍ ትምህርት ሁለት ዓመት ይወስዳል። ይኸውም ተማሪው ትጉህ የሆነ እንደሆነ ነው። ምዕራፍንና ጸመ ድጓን የሚያስተምር መምህር መጋቤ ስብሐት ይባላል።

መ. ዝማሬ መዋሥዕት

ዝማሬ ማለት ምስጋና ሲሆን የሥጋ ወደሙ ሥነ ሥርዓት ከተከናወነ በኋላ በምሥጢረ ቁርባን ክብር የሚዘመር ጎብስት፣ ድምፅ፣ መንፈስ፣ አኩቴትና ምሥጢር የተባሉ አምስት ክፍሎችን የያዘ ድርሰት ነው።

መዋስዕት ማለት ደግሞ እንደ ጸሎተ ግንዘትና ፍትሐት የሚጸለይ ሲሆን በነግህ በሥርዓተ አርያም ይቀርባል ። አንድ ተማሪ አስቀድሞ በዜማ የገፋ/ዘረ ደፋር/ ከሆነ በሁለት ዓመት ዝማሬ መዋሥዕት አሞቆ በሶስተኛ ዓመት አስመስክሮ መምህር ሲሆን ይችላል።

ሠ. አቋቋም

የጠቆም ሥነ ሥርዓት ወይንም ማኅሌት በሚቆምበት ጊዜ የአገልግሎቱን ልክና መልክ የዜማውን ስልትና ሥነ ሥርዓት የሚገልጥ ነው። ቅዱስ ያሬድ ከጽናጽል ከበሮ ና ከመቋሚያ አነሳሥና አዋድዶ አንደ ጀመረው የሚነገር ሲሆን በአሁኑ ወቅት የሚታወቁት የአቋቋም ቤቶች አራት ናቸው። እነዚህም ሠዝ በመስዑርና አንዳንድ ይትበሃል በማሻሻል የመጡ ናቸው። እነርሱም

1 ዐላይ ቤት- ጎንደር ከጃን ተከል ዋርካ በላይ የሚገኙ አዚያተ ክርስቲያናት የሚከተሉት ሊሆኑ መንገድ አውጥቶ በለቀቃ የሚሄድ ነው።
2 ዮታት ቤት- ጎንደር ከጃን ተከል ዋርካ በታች የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የሚከተሉት ሲሆኑ ጥንታውያን ማለትም ምልክቱን ተከትለው የሚሄዱ ናቸው።
3 ዖሳኒ- የጎጃም ሳንኒ ጊዮርጊስ ደግሞ በቁም የሚዘመር ነው።
4 የተክሌ አቋቋም- አለቅ ገብረሃና ገብረማርያም ለልጃቸው ለአለቃ ተክሌ ገ/ሃና ያስተማሩትና ምስክሩ በደብረ ታቦር አየሱስ/ በደቡብ ጎንደር ደብረ ታቦር ከተማ/የሚገኙት ናቸው። የተክሌ አቋቋም ስዝማሜ /ለዘንግ/ የጎንደር አቋቋም ደግሞ ለጸናጽል የሚፈለግ ነው።

የቅዳሴ ትምህርት

ከአምስቱ የቅዱስ ያሬድ ድርሰት በተጨማሪ የቅዳሴ ትምህርት በዜማ ቤት ውስጥ የሚገኝ ነው። ግብረ ዲቁናን፣ ሰዓታቱን፣ መዝገብ ቅዳሴውን /የ14ቱን ቅዳሴያት ዜማ/ እና አንቀፀ ቅዳሴን የሚያካትት የቅዳሴ ትምህርት ነው። መዘግበ ቅዳሴ የተባለበት ምክንያት በዚያ የተጻፉ ቀለሞች /በንባብ ከሚባሉት ጥቂት ክፍሎች በቀር/ በሙሉ ስለሚዜሙ ነው። አንቀጸ ቅዳሴ ከመዝገበ ቅዳሴ አስበ ቢዳን ተወጣጥቶ የተጻፈ ርክርክና ስረዩ የበዛበት አንዲሁም ድርብ ዜማ ያለበት ስተሜሪ አሰቸጋሪ መስሉ የሚታይ ነው። ይህን የተማረና ጽፎ የያዘ ቅዳሴ ዘወቶ ይባላል። መምህርም ሆኖ ሊያስተምር ይችላል።

የ14ቱ ቅዳሴያት መጻሕፍት ደራሲያን ልዩ ልዩ ሲታውንት ሲሆኑ ዜማውን ያቀናበረው

ቅዱስ ያሬድ ነው። የቅዳሴ ትምህርት በጥንት ዘመን ከጠማሪ መዋሥዕት ጋር በቡር አምላ ጽርሐ አርያም ገዳም ያስተምሩት ያስመሰክሩትም ነበር። እየቆየ ግን የቅዳሴ ምስክር ተብሎ ይነገርለት የነበረው እስከ አሁንም ድረስ የሚታወቀው በሰሜን ሠሌ ዋድላ ወረዳ የሚገኘው የስሌ ኩላ ቅዱስ ሚካኤል ገዳም ነው። ቅዱስ ያሬድ በዚሁ ገዳም ለሦስት ወር እንዳስተማረበት ይነገራል።

በትግራይ ክልል ደቡባዊ ዞን በሽሬ ወረዳ የሚገኘው የደብረ ዓባይ ሳሙኤል ገዳም የቅዳሴ ማስመስከረያ ሲሆን የስሌልኩላ ዜማ አጠር ያለና የድጓውን ዜማ ተከትሎ የሚሄድ ሲሆን የደብረ ዓባይ ግን ጠማምና ረዘም ያለ ነው። አንድ ደቀ መዝሙር በጸዋትወ ዜማ የበሰለ እንደሆነ መዝገበ ቅዳሴን ተምሮ አንቀጽ ጽፎ በሁለት ዓመታት አስመስክሮ ይወጣል። በዜማ ትምህርት ያልገፋ ከሆነ ግን ከ3-4 ዓመታት ይወስድበታል። ዲያቆናትንና ቀሳውስትን ቅዳሴና ሰዓታት የሚያስጠና መምህር መጋቤ ጎፍያን ይባላል።

አንድ ደቀመዝሙር በቁም ዜማ እና በአቋቋም ት/ቤት የሚያሳልፈው ዘመን አስቀድሞ እንደተገለጠው ከአስር ዓመት በላይ ሰመሆኑ እነዚህን ጊዜያት የሚጠቀምባቸው ማማሹን ወደ ቅኔ ት/ቤት ከመሄዱ በፊት ሲሆን ግማሹን ደግሞ ከቅኔ ት/ቤት ከተመለሰ በኋላ ነው። አስካሁን የተማሪ ረቾው የንባብና የዜማ መጻሕፍት ሁሉ በማእዝ ቋንቋ ሆደደሉ ሰመሆናቸው እና ትርጓሜ ያላቸውን ባለማወቁ ቅሬታ አይለየውም። ስለዚህ ብዙውን ጊዜ ጸመ ድጓ ብቻ ተምሮ ወደቅኔ ት/ቤት ይዛወራል።

2.2.2 የቅኔ ትምህርት

የቅኔ ትምህርት እንደ ዜማ ትምህርት ለማዕከላውያን /መስስተኛ ዕውቀት ላላቸው/ የሚሰጥ ትምህርት ነው። የቅኔ ትምህርት ቤት የግጥም ፍልስፍና ከነአገባቡ የሚጠናበት ትምህርት ቤት ነው። ይህ ከፍል የግእዝን ቋንቋ በስፋት የሚጠናበትና ልጆች በግእዝ ትምህርት /ዘይቤ/ የሚራቀቁበት የላቀ የትምህርት ደረጃ ነው። የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርት መመረት በተሰይም በክህነት ሥራ ላይ ለመሰማራት ለሚፈልጉ የቤተክርስቲያን ልጆች ጥንትም ሆነ ዛሬ ግእዝ ማወቅ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ግእዝ ያልተማረ ካህን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን አይጠነቅቅም። የወንጌልንም ትምህርት የረቀቀውን አጉልቶ በልሳነ ግእዝ የተሰወረውን ሀሳብ ተርጉሞ ስምእመናን ሊያስረዱ አይችልምና ግእዝ ማወቅ ተገቢ/ማዴታ/ ነው።

የቅኔ መንገዱ ብዙ ነው። ትምህርት ቤቶችም የተለያዩ ናቸው። የምዕራብ ጎጃም ዞን ይል ማና ዲንሳ ወረዳ በደብረ ጽላሎ አማኑኤል የሚገኘው የጎንጅ ቅኔ፣ በሰሜን ሠሌ ዞን ዋድላ ወረዳ /ዞን/ የሚገኘው የዋድላ መንገድና የጎንደር መንገድ ቀደምት ተጠቃሽ ናቸው። የልዩነቱ መንስኤ የዘመን ብዛት የተተኪ ምእመናን መኳህልም የተፈጠሩ ጠርነቶች መሆኑ ይታመናል። በዮሐንስ ንብላዊ የተመደበ የዋድሌች የቅኔ መንገድ 650 ፡ የዋሽሮች 250፣ የጎንጅች መንገድ ደግሞ 350፣ ነው። ዋሸራና ጎንጅ ይበልጥ የሚያተኩሩት በቅኔ መንገድ ሲሆን ዋድሌች ያቆዩን ደግሞ አገዛዙን /ሕጉንና ደንቡን/ ነው።

ተማሪው ግሥና ኑባር ካጠና በኋላ ጉባኤ ቃና የተባለችውን የቅኔ ትምህርት መግቢያ እያጋጠመ ወደ መምህሩ ፊት ቀርቦ ለመንገር ይሞክራል። መምህሩም እያረመና እያስተካከለ ይረዳዋል፣ ያበረታታዋል። ከእነዚህም አያይዞ ቀስ በቀስ ከጉባኤ ቃና እስከ መወድስ እያስበቆጥር ሊመናገር ይችላል። አንዳንድ ከብረ በዓል በሆነበትም ቀን በየቤተ ክርስቲያኑ እየሄዱ ብዙ ሊቃውንት በተሰበሰቡበት ይበል መልካም አጽብ እያሰኝ ዋዜማ፣ ሥላሴና እማኑ ሞገር የተባሉትን ሰምና ወርቅ ቅኔዎች/ታሪክና ምሳሌ/ ይቀኛል።

አንድ ደቀ መዘሙር ብልህ ከሆነ በቀላል ሰምና ወርቅ መንገድ በአንድ ዓመት ቅኔ ይቀኛል። ከ2 - 3 ዓመት ቅኔ ያውቃል። ከ4 - 8 ዓመት ስመ ጥር የቅኔ መምህር ቅኔ ዘራፊና ምስክር ሊሆን ይችላል። የቅኔና የአገባብ መምህር መጋቤ ምሥጢር ይባላል።

3. <u>ሰምሁራን</u>

በሦስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መከናወን የሚገባቸው የትምህርት ዓይነቶች ሰምሁራን የሚሰ ሲሆን ትምህርት ቤቱም መጻሕፍት ቤት ወይንም የንባብና ትርጓሜ ቤት በመባል ይታወቃል። በመጻሕፍት ቤት የሚሠራበትና ንባብ ለማቃናት ምሥጢር ለማደላደል የሚያመችው ደሂው የአንድምታ ትርጓሜ ስልት ነው። በዚህም አገባብን ወይንም ዘይቤን ብቻ በመጠበቅ አለያም ምሥጢሩን በመከተል ወዲያውም ደግሞ ታሪክ በመተረክ፣ ምሳሌ በመመስል፣ ሐተታ በማተት ለእያንዳንዱ ኃይለ ቃል ሞያ ሰጥተው ይተረጉማሉ፣ የተሰወረውን ገልጠው ያሰረዳሉ።

ይህ ጉባኤ ቤት መጻሕፍትን አስተካክሉ ማንበብና መተርጉም መሰረተ ሐይማኖትን የክርስትናን ታሪክ የመሰሰሉትን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንና የክርስትናን እምነት ጠንቅቆ ለ ማወቅ የሚያስችል ከፍተኛ የምርምር ተቋም ነው። በተጨማሪም ምሁራኑ ሌሉችንም የትምህርት ዓይነቶች ማለትም ዜማ፣ ቅኔ..... የመሰሰሉትን በሦስተኛው የትምህርት ተቋም ተምረው በሊቅነት በማዕረግ አሰመስከረው ይወጣሉ። ለምሳሌ መዝሙረ ዳዊትን ወጣንያን በንባብ፣ መለስተኛ ዕውቀት ያላቸው በዜማ፣ ምሁራን በትርጓሜ ይማሩታል።

አንድ ተማሪ ከቅኔ ትምህርት ቤት ወጥቶ ወደ ከፍተኛ የመጻሕፍት ትርጓሜ ት/ቤት ሲገባ በዕድሜው የበሰለ በአእምሮ የተደላደለ የግእዝን ቋንቋ ጠንቅቆ ያወቀ መሆን ይገባዋል። ምክንያተ ም የትርጓሜው አንድምታና ሐተታ ረዥምና ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ እርሰ በእርስ ማገናዘብ፣ የተዛባውን ንባብ ማቃናትና ማስተካከል አድካሚ በመሆኑ አስተዋይ ጭንቅላት ሰለሚጠይቅ ነው። የመጻሕፍት ቤት ተማሪ በጠባዩ ግብረ ገብነት ያለው የመናንነት መልክ የሚታይበት፣ ትምህርቱን በሚገባ አጠናቅቆ በመምህርነት የሚገለጠው በእርጅና ዘመኑ ሰለሆነ መጻሕፍት ቤት ሲገባ አንደ ሎጥ ሚስት ዞሮ ለማየት አይደለም የሚሉት ለዚህ ነው።

ምንጊዜም ቋንቋቸው እንዳይለወጥ ምሥጢር እንዳይፋለስ ዓይናቸው መጽሐፍ ከመመልከት አለምርአቸው ምሥጢር ከማሸራሸር አይለይም። ሌሉች ሲቃውንት ምንም ውሉን ሲያውቁት ትንሽም ትልቅም ከርከር በመካከላቸው ኩተነሳ ከመጽሐፍ መምህር እንሂድ በማለት ነገሩ ያልቅ ከርከሩም ይበርድ ነበር። ይህም ያላቸውን የላቀ አስተያየትና ጥበብ እንዲሁም ክብር ያሳያል። ይሁንና በዋና ዋና ከተሞች ስመጥር በሆኑ አድባራትና ገዳማት ካልሆነ በቀር በየደብሩና በየገጠሩ በብዛት ከሚገኙት የቤማና የቅኔ መምህራን አንዣር የመጻሕፍት መተርጉም ቁጥር አናሳ ነው።

ይህ የመጻሕፍት ቤት ከብሉይ ኪዳን ዘመን ጀምሮ በአይሁድ ዘንድ የነበሩት ት/ቤቶች ሲሠ ሪበት የኖረ ሲሆን ከሕገ ኦሪት ጋር ሲቃውንተ ኦሪት ከቀዳማዊ ሚኒልክ ጋር አብረው ወደ ሀገራ ቸው ከገቡ በኋላ ይዘዋቸው የመጡትን መጻሕፍተ ኦሪት/ሰምንቱ ብሔረ ኦሪት፣ መጽሐፈ ኩፋሌ፣ መጽሐፈ ሔናን፣ መጽሐፈ ኢዮብና እስከ ሰሎሞን ዘመን ድረስ የሚተረከውን መጽሐፈ ነገሥት ከእብራይስጥ ወደ ግእዝ በአንድምታ በመተርጉም ሲያስተምሩት ሰለሚኖሩ ትርጓሜ መጻሕፍት ከዚያን ዘመን አንሰቶ በኢትዮጵያ አንደተጀመረ ይታመናል። ከጊዜ በኋላም በእነ አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን፣ በእነ ቅዱስ ያሬድና በመሳሰሉት አባቶች ትጋት ተሰፋፍቷል።

የትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርት በንግግር መልክ አንድ ጊዜ ብቻ ተሰምቶ በቃል የሚጮህ ወይንም የሚነገር ትምህርት አይደለም። የመምህሩ የንግግር መልክ ማሄድ ይባላል። የጉባኤውም ዓ ይነት በመጽሐፍ ክፍል ብቻ ሳይሆን በሰዎች ልክ ይወሰናል። ሁልጊዜ በሚተ የማይታጉሉ ጉባኤዎች አሉ። እኒህንም አልፎ አልፎ በትምህርት መልክ ይከታተሏቸዋል። ተማሪዎቹ የተማሩ ት በቃል አንዳይቀር በጽሑፍም ያሰቀሯቸዋል።

የትርጓሜ ትምህርት ቤት አራት ጉባኤያት ሲኖሩት አነሱም፣

ሀ. ብሉይ ኪዳን
ለ. ሐዲስ ኪዳን
ሐ መጻሕፍተ ሊቃውንት

መ.መጻሕፍተ መነኮሳት ናቸው። እኒህን ሙያዎች አጠናቀው የሚያውቁት ሊቃውንት የአራት ጉባኤ መምህር እገሌ፣ አራት ዓይና የሚል የሊቅነት ሰም ይሰጣቸዋል።

ሀ. ብሉይ ኪዳን

ይህን ትምህርት ለመማር በመጀመሪያ የግእዙን ቋንቋ እና ቅኔ ማወቅ ይጠቅማል። ይህ ከሆነ የብሉይ ኪዳንን ማለትም የሕግ፣ የታሪክ፣ የመዝሙር/የጥበብ ወይም የቅኔ እና የትንቢት መጻሕፍትን አንድ ብለህ ደቀመዝሙር በ6 ዓመታት በሚገባ ሊያጠናቅቅ እና ለመምህርነት ሊበቃ ይችላል። እነኝህን በአራት ክፍል የተከፈሉት የብሉይ መጻሕፍት ቁጥራቸው 46 ነው። እነዚህን አጠናቆ ያወቀ ምሁር መጋቤ ብሉይ ተብሎ ይጠራል።

ለ. ሐዲስ ኪዳን

ሐዲስ ኪዳን በቁጥር 35 ሲሆን በጉባኤ ደረጃ ግን በሦስት ተከፍለዋል እነሱም፣

* አርባእቱ ወንጌል
* 14ቱ መልእክታት ¡ጳውሎስ
* ግብረ ሐዋርያት
* ሰባቱ መልእክታትና የዮሐንስ ራዕይ ናቸው። እነዚህን እያንዳንዳቸውን በዓመት ሁሰት ጊዜ ያህል ይዘልቃሉ።

ሐ. መጻሕፍተ ሊቃውንት

መጻሕፍተ ሊቃውንት ብዛትና ጥልቀት ያላቸው ከመሆናቸውም ባሻገር ንባባቸው ጠንከር ያለ በመሆኑ ይህን ትምህርት በሚገባ ለማጠናቀቅ ከ6 - 8 ዓመታት ይወስዳል። እነዚህ መጻሕፍት እንደ ፍትሐ ነገሥት፣ መጻሕፍተ ቄርሎስ ፣ መጻሕፍተ ዮሐንስ እፈወርቅ፣ ሃይማኖተ አበው፣ 14ቱ መጻሕፍተ ቅዳሴያት የመሳሰሉት ናቸው።

የውዳሴ ማርያምንና የቅዳሴ ማርያምን፣ የኪዳንን፣ የትምሕርተ ሐቡአትን፣ የጹሎተ ሃይ ማኖትን ትርጓሜ ግን ማንኛውም ¡የመጽሐፍ ተረጓሚ ማወቅ ይኖርበታል። የቁጥር መጻሕፍት /አዙሻህር፣ ባህረ ሐሳብ ወይም መረሐ እውር/ ከፍተኛ ትምህርት ቢሆኑም ከአንዳንድ ሊቃውንት በቀር ሁሉም እያጠኗቸውም።

መ. መጻሕፍተ መነኮሳት

መጻሕፍተ መነኮሳት ሦስት ዓይነት ናቸው እነርሱም፣

⇒ ግሪ ይስሐቅ
⇒ ፊልክሲስዩስ
⇒ አረጋዊ መንፈሳዊ ሲሆኑ እያንዳንዳቸውን በአንድ ዓመት መፈፀም ስለሚቻል በጠቅሳላው በሦስት ዓመታት ማከናወን ይቻላል። እነዚህንም ጠንቅቆ ወውቆ ለማሰተማር የሚችል መምህር መጋቤ ምክር ይባላል።

የአብነት ት/ቤቶች ያጋጠሟቸው ችግሮች

የአብነት ት/ቤቶቻችን የሚገኙት በየገዳማቱ እና አድባራቱ ነው። እነዚህን ገዳማትና አድባራ ት ደግሞ ትናንት ነብሮን በሰፈው ይኖሩት የነበሩ ናቸው። ምክንያቱም ነገሥታት ለገዳማቱ እና አድባራቱ ሰፊ የእርሻ መሬት ሰጥተው እንዲኖም አንደነገሥታቱ የሚገብሩ ቀርዎችን ወስነውላቸው ይኖሩ ነበር። ገዳማትና አድባራት በነገሥታቱ ዘንድ ልዩ ቦታ ተሰጥቷቸው ነበር። የሐሳብ ድጋፍ፣ ምክር፣ ጸሎት፣ ሲፈልጉ ሄደው የሚያማክሩት እነዚህን ገዳማትና አድባራት ነበር። ሕዝቡም ፈረሰ

እግዚአብሔር ያሰው ሰገዳማቱ፣ አድባራቱ ሰቆሱ ተማረው ቦሚያሰቡ በአንተ ሰማ ሰማርያዎ የሚላቸውን የተሜን ድምጽ የሚናፍቁ ተሜ ሳይመጣ ቢቀር ቅር የሚላቸው፣ መሽቶበት የመሸበት የእግዚአብሔር አንግዳ የሚሰውን ቃላት የሚናፍቃቸው ነበሩ።

ሰስዚህ ተማሪዎች ከትምህርት ትምህርት ክቦታ ቦታ አያማረጡ ይማሩ ነበር። በየገዳማቱ ና አድባራቱ የትምህርት ጉባኤ ተሟልቶ እንዲሁም እንዱ የትምህርት ዓይነት ሁሰት፣ ሦስትና ከዚ ያም በላይ አየሆነ ጉባኤዎች ተዘጋጅተው ይሰጥባቸው ነበር።

ዛሬ እንደጥንቱ ትምህርት ቤቶች ተሟልተው ጥንድ ጥንድ መሆናቸው ቀርቶ ያሱትን ትምህርት ቤቶች አንኳን ሰሚሟላት አጠያያቂ የሆነበት ጊዜ ነው። እንደ ትርጓሜ ያሱ ትምህርት ቤቶች በጣት የሚቆጠሩ ገዳማት ውስጥ ክመጣጎታቸውም በተጨማሪ የሚማሯቸው ተማሪዎችም ያጡ አና አየተዘጉ የመጡ ትምህርት ቤቶች ናቸው። በአንዳራዊ ሁኔታ ስናያቸው ከሌሱች ት/ቤቶች አሁን ብዙ ተማሪዎች አየወሰጿቸው ያሱት ቅኔ፣ ዜማ ፣ አቋቋም እና ቅዳሴ ትምህርት ቤቶች ምንም እንኳ ከመዘጋት ቢድኑም አሁን ባሰብት ሁኔታ እንኳ ነባ ሰለመጣጎታቸው አጠያያቂ አየሆነ ነው። ለዚሁም ዋና ዋና ምክንያቶች፣

ሀ. በ1967 ዓ.ም በወጣው መሬት ላራሹ አዋጅ አና በ1968 በወጣው የከተማ ቦታ አዋጅ በከተማ የነበራቸው የኪራይ ቤት መወረስ፣ ደርግ የቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ የነበረውን መሬት በመውረሱ ገዳማት አና አድባራትን ያሰመተዳደሪያ አስቀርቷል። ይህ ደግሞ መነሳት አና መሥህራን ይተዳደሩበት የነበረውን መሬት በማጣታቸው ገዳማት አንዲፈቱ፣ የአብነት ት/ቤቶች እንዲ ቀንሱ ብሎም እንዲበተኑ አስተዋጽኦ አድርጓል።

ለ. ለአብነት መምህራን የሚደረገው ዝቅተኛ እንክብካቤ ለአብነት ት/ቤቶች ማሽቆልቆል ሌላው ምክንያት ነው። የአብነት ት/ቤቶች በሚገኙባቸው ቦታዎች በሙሱ ይዘ ችግር ጉልቶ ይታያል። እንደሚታወቀው የአብነት መምህራን ለዜተ ክርስቲያን ተተኪ ሲቃውንትን በማፍራት በኩል ታላቅ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ አባቶች ናቸው። ነገር ግን ለእነዚህ ሲቃውንት የሚደረገው እንክብካቤ እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ ለረሀብና ለበሽታ፣ ለአርዛት ብሎም ሰስደት የተጻረጉ ጥቂት አይደሉም። የአብነት መምህራን አስቸጋሪውን የአብነት ት/ቤት ኑሮ ተቋቁመው አስመስክረው ክመጡ በኋላ የሚከፈላቸው ክፍያ እጅግ አነስተኛ ነው። እንኳን ቢተሰባቸውን ሲያስተዳድር አናርሱንም ወር ማድረሱ ያጠራጥራል። አንዳንድ ቦታ ላይ ደግሞ ያለክፍያ በተሰፋ ብቻ የሚያስተምሩ መምህራን አለ። ይህ ሁኔታ የአብነት መምህራኑን ብቻ ሳይሆን የአብነት ተማሪዎችንም ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው።

ሐ. የአብነት ተማሪዎች መሰረታዊ ፍላጉታቸውን ማሟላት አለመቻል ሌላው ችግር ነው። እንደሚታወቀው የአብነት ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎች ከአካባቢያቸው ራቅ ብለው ሄደው የሚ ማሩ ስለሆነና ከዜተሰባቻቸው ስለሚለዩ በትምህርት ላይ ያሱት የሚተዳደሩት በልመና ነው። ገዳ ማቱና አብረተሰቡ በጥሩ ሁኔታ ላይ በነበሩበት ዘመን የአካባቢው አዝብ ሰተማሪዎቹ የሚያስፈልጋቸውን በመለገስ ሲተባበር ቆይቷል። በአሁኑ ወቅት ግን በተለያዩ ምክንያቶች የምአመኑ መንፈሳዊ ጥንካሬ በመላላቱና ኢኮኖሚያዊ ዐቅሙ በመድከሙ ተማሪዎቹ እንደቀድሞው በልመና መሰረታዊ ፍላጉቶቻቸውን ሲያሟሱ አልቻሱም። ይህ ተማሪዎቹን ሰስደት ሰለዳረጋቸው በታላላቅ ከተሞች ውስጥ የአብነት ተማሪዎችን ሲቸገሩ ማየት የተለመደ ሆኗል። እንዲሁም ተማሪዎች መኖሪያ ቤታቸው ብዙ ጊዜ ትንንሽ ጉጆ ቢበዛ ሁሰት አርምጃ ስፋት ያላት ስትሆን በውስጧም አስከ ሰድሰት ተማሪዎች ይኖሩባታል። ይህ ደግሞ ተማሪዎችን ሰልዩ ልዩ ተላላፊ በሽታዎች ያጋልጣቸዋል። ሰምሳሌ እከክ፣ የሳንባ በሽታና የመሳሰሰሉት የአብነት ት/ቤቶችን መጋለጥ አድክሟል።

ሠ. የዘመናዊ ትምህርት ቤቶች መስፋፋት የአብነት ት/ቤቶችን አዳክሟል። ይህም ሲባል የአብነት ት/ቤቶችን ከዘመናዊው ትምህርት ቤቶች ጉን ሰጉን ማሳደግ ሲቻል ተረስተዋል። በዘመናዊ ትምህርት ቤት ተምረው ጥሩ ክፍያና ጥሩ ኑሮ ስለሚኖራቸው ወላጆቸ ልጆቻቸውን ወደ አብነት ት/ቤት ከመላክ ወደ ዘመናዊ ት/ቤት መሳኩን እየመረጡ ነው። ሰለዚህ የአብነት ትምህርቱን የሚ ማገር ተማሪ ማግኘት አስቸጋሪ እየሆነ ነው።

ሠ. የማኅበረሰቡ አስተሳሰብ መቀየር ዛሬ በገዳማት እና አድባራት ሰም የሚያታልሉ ሰዎች እየበዙ በመምጣታቸውና መገናኛ ብዙኋንም ይህንን አጉልተው ስለሚያሳዩት ሕብረተሰቡ ስገዳማትና እድባ ራት መርዳት ማለት ገንዘቡን እንደመስረቅ እየቆጠረውና ለገዳማዊያን የነበረው በጉ አመለካከት እየተቀየረ በመምጣቱ ገዳማት አድባራት እና የአብነት ተማሪዎችን የመርዳቱ ሂደት እየቀዘቀዘ ነው። አንዲሁም በኑሮ ውድነት ምክንያት ትሩንት የነበሩንን ጥሩ ጥሩ ባሕሌች አጥንተናል። ተ ማሪዎች እንደጥንቱ በእንተ ሰማ ለማርያም ብለው ለምነው ቁራሽ የሚከለክሉ አጅግ ብዙ ወቀት ያለኝን ማንሳቱ አስፈሳጊ ነው። ናቸው። ዛሬ አንደ ድሮው ተሜ አይናፈቅም። በእንተ ስማ ለ ማርያም ቢል ሠርተህ አትበላም ይባላል። አሁን በአነሱ ዘንድ ተሜ ዘዘኔ ነው። ዲማ ቅዱስ ጊ ዮርጊስ ላይ አንድ ተማሪ ባንጋገርኩበት «... ቀኑን ሙሉ ስትሰምኝ ውለሽ ለምሳ የምትሆን አንኪ ላታገኝ ትችያለሽ» አዘር ያለኝ። ሌላው ስሜን ሽዋ ያገኘሁት ተማሪ ደግሞ ጀርባውን እያሳየኝ «በአንተ ስማ ስማርያም ብዬ ብለምን ደበደቡኝ፣ የታለ መታወቂያህ? ውሸቱን ነው፣ ይህ ማነው? ከዦት የመጣ ነው? እያሉ እጣደቆኝ። ወትሮስ ተማሪ በሀገሩ አይማር» አለኝ። የኑሮ መወደድ ሰውን አጨካክኖታል።

ረ. በስማኑ የአገራችን ክፍል በተደጋጋሚ የተከሰተው ድርቅ በገዳማቱና እድባራቱ ሕልውና ሳይ ያስከተሰው አሉታዊ ተጽእኖ የአብነት ት/ቤቶችን አዳክሟል። ምክንያቱም በሰፊራ ሁሉም ቀዬውን እየለቀቀ ሲሄድ ገዳማቱና አድባራቱ እንዲፈቱ መነሳሳት እና ተማሪዎች እንዲበተኑ አድርጓል።

ሰ. በቤተክርስቲያን ውስጥ ማዕከላዊነትን የጠበቀ የአብነት ት/ቤት አሠራር አለመኖር፣ ሰምሳሌ ከተ ማ ውሰጥ የሚገኙ አንድ የቅኔ መምህርና በገጠር ገዳም የሚኖሩ የቅኔ መምህር ከፍያቸው እንድ አይደለም። ይህ ደግሞ ጥሩ ክፍያ ለማግኘት ሲባል መምህራኑ ወደ ከተማ እየተሰደዱ ነው። በገጠ ር በየገዳማቱ የሚገኙት መምህራን ወደ ከተማ ለተሻለ ክፍያ መሰደድ ደግሞ እግራቸው ሥር ቁጭ ብለው ይማሩ የነበሩትን በርካታ ተማሪዎችን እንዲበተኑ ያደርጋቸዋል።

ሸ. የምእመኑ መንፈሳዊ ሕይወት መሳሳቱ ሌላው ችግር ነው። ይህም ሲባል እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ምእመኑ ከልጆቹ ቢያንሰ አንዱ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግል ለቤተክርስቲያን በኩራቱን ይስጥ ነበር። ተማሪዎቹም ሲማሩ፣ መምህራኑም ሲያስተምሩ የሚያስበት በቆሎ ት/ቤት ተምረው የሚያገኙትን ፀጋ ፡ በረከት፣ የአገዚአብሔርን ቸርነት... ነበር። ተምረውም ሲጨርሱ አለያም አስተምረው የሚያገኙትን ክፍያ አስበው አልነበረም የሚማሩት። ስዚህ ነው እብዛኞቹ የቆሱ ተ ማሪዎች ተምረው ወደ ምነናው የሚገቡት። ዛሬ ግን አንዲህ አይደለም። ተማሪዎቹ እዚህ የአብነት ት/ቤት የገቡበትን ቀን የሚያማርሩ በመላጆቻቸው የሚያዝኑ ናቸው። አንዳንዱም እንደምንም ጥርሱን ነክሶ ጨርሶ ወደ ከተማ መማበት የሚፈልግ ነው። ይህ ደግሞ ለአብነት ት/ቤቱ ብቻ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን ሕልውና አስጊ ነው።

ቀ. ሌላው ችግር የገዳማቱ አስተዳዳሪዎች በገዳማቸው ውሰጥ በሚገኙት ት/ቤቶች ላይ የእኔነት ስሜት የላቸውም። ዐትምህርት ቤቱ ጨመረ መነመነ ለአነሱ ምንም ማለት አይደለም። ተማሪዎች በበሽታ ቢሰቃዩ፣ ቤቶቻቸው ብጎርፍ ቢወሰዱ፣ ቢፈርሱ ተማሪዎቻቸው መጽሐፍት ቢያጡ አነሱ ካላቸው ክፍሰው መርዳት ያለባቸው አደመስላቸውም። በገዳሙ ውሰጥ አንኪን ምን ያህል ተማሪ

አንዳሏቸው አያውቁም::

ከላይ የተዘረዘሩትን እና ሌሎች ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለገጽማት መፈታትና ለተማሪዎች ቁጥር መቀነስ ምክንያቶች ናቸው:: ስለዚህ ከላይ አንደ-ተመሰከተው በኢትዮጵያ የሚገኙ ገዳማት፣ አድባራትና የአብነት ት/ቤቶች ችግር በሀገሩቱ ሲከሰት የኖረው የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ገጽታ አለመረጋጋት ውጤት ነው::

የአብነት ት/ቤቶች ለነገው የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ማፍሪያ መሆናቸው የማይካድ ሀቅ ነው:: የአብነት ት/ቤቶቻችን ጉዳይ አነሳን ማለት የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ጉዳይ አነሳን ማለት ነው:: ምክንያቱም የቤተክርስቲያኑ መሪዎች፣ አስተባባሪዎችም ሆኑ አገልጋዮች የአብነት መምህራንና ተማሪዎች የነበሩ በመሆናቸው ነው::

ዛሬ ግን የአብነት ት/ቤቶች አንዲህ እንደ ድሮው ይቀጥሉ / እከክ ይያዛቸው፣ ውሻ ይንከሳቸው ፣ በእንተ ስማ ለማርያም ብለው ይለምኑ/ ብሉ መተው ለነገው ትውልድና ለቤተክርስቲያን ሊቃውንት አባቶችን ማጣት ነው:: ዛሬ ያለው የተማሪዎችና የመምህራን በተለያዩ በሽታዎች መሰቃየት ፣ ተማሪዎች በእለት ጉርስ ማጣትና ከመናፍቃን አዳራሽ ቁጭ ብለው መለመን፣ ልብስና መማሪያ መጻሕፍትን የሚረዳቸው በማጣት ከትምህርታቸው መስተጓጎል የ ማደሪያ ቤት እጥረት በማኅበረሰቡ ዘንድ ተማሪዎችን እንደ ሥራ ፈት መመልከትና በሌሎችም ችግሮች ምክንያት የአብነት ት/ቤቶች እየተዘጉና አየመነመኑ ነው:: በተለይ ሰመምህራኑ የሚደረገው እንክብካቤ መቅረትና ከእጅ ወደ አፍ የማይሆን ክፍያ ተማሪዎችን ተስፋ አያሰቆረጠ ትምህርቱን እንዲተውት ያደርጋቸዋል:: አናም የምናስበውን የነገ ተተኪ ሊቃውንት አባቶችን ማግኘት እጠያያቂ ነው:: ይህ ከመሆኑ በፊት ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ በተለይ ምእመናን ትኩረት መስጠት አለባቸው::

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ብራና ፍቃ፣ ቀለም በጥብጣ ፣ ብርዕ ቀርጻ ከፈደል ጀምሮ አጅግ ብርቅና ድንቅ የሆኑ የሃይማኖት፣ የታሪክ፣ የፍልስፍና ወዘተ መጻሕፍትን በመጻፍ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለክርስትናው ዓለም ያበረከተችው አስተዋጽኦ ወደር የማይገኝለት ነው:: ስለዚህ መንግስትም የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያበረከተችውን በማገናዘብ ለቤተክርስቲያኗ ተገቢውን ድጋፍና እንክብካቤ ትኩረት መስጠት መቻል አለበት:: ሌላው ቢቀር ይህች ጥንታዊት ፣ ሐዋርያዊት እና ታሪካዊት ቤተ ክርስቲያን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የትምህርት ሚኒስቴርነቱን ኃላፊነት ይዛ ስለመናት ኢትዮጵያን በትምህርትና በሃይ ማኖት ስትመራ መኖሯ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው::

የመፍትሔ ሐሳቦች

1. የአብነት ት/ቤቶችን ማጠናከር የሚቻለው ት/ቤቱ የሚገኝባቸውን ገዳማቱንና አድባራቱን በማጠ ናከር ነው:: ይህ ሲባል ገዳማውያኑን ከተማሪዎቹ ጋር በማቀናጀት ገዳማትና አድባራትን ማል ማት ነው:: ከዚያም የአብነት ተማሪዎችን ቋሚ ድጐማ እንዲያገኙ ማድረግ፣ የማደሪያ ቤቶችንና ቤተ መጻሕፍትን በማዘጋጀት እና ለተማሪ ያሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮችን ማሟላት:: ተማሪዎች ድጐማ ከገዳሙ ማግኘታቸው ለልመና ውተው የሚያጠፉትን ጊዜ በመቆጠብ በአብነት ት/ቤት የሚኖራቸውን ቆይታ ማሳጠር ይቻላል:: ስለዚህ ገዳማትና አድባራት በማኖራቸው የልማት ሥራ ከራሳቸው አልፈው ለአካባቢው ሕብረተሰብ የሚተርፍ ገቢ ይኖራቸዋል:: በዚህም የዛሬ የአብነት ትምህርት ቤቶቻችንን እንደ ዘመናዊው ኮሌጆች በጉጉት የሚገባባቸው ማድረግ እንችላለን:: ይህን ሁሉ ማድረግ የሚቻለው ግን ገዳማቱ እና አድባራቱ ቋሚ የልማት አንቅስቃሴን በተለይ ባላቸው የሰው ኃይልና የተፈጥሮ ሀብት ጥምረት በጋራ በመስራት ነው::

2. ገዳማት አድባራት እና የአብነት ት/ቤቶች ማዕከላዊ በሆነ አስተዳደር የመተዳደሪያ በጀት ቢኖ ራቸው

3. የአብነት ትምህርትን ለአንድ ለተወሰነ ክፍል /በገጠሪቱ የአገራችን ክፍል /ብቻ እንዳይተው ማድረግ። ይህም የአብነት ትምህርት መማርን እንደ ኋላቀርነት እንዳይታይ ይረዳዋል። ስለዚህ ቤተክርስቲያኗ ስሏት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከኮርስ ትምህርት ጐን ለጐን የአብነት ትምህርትን መስጠት፣ ለንቡት ተማሪዎች የአብነት ትምህርትን እንዲማሩ ማድረግ፣ ሠራተኛ ጉባኤያት የአብነት ትምህርት እንዲመቻችላቸው ማድረግ፣ በመረጃ መረብ የአብነት ትምህርት ቢስጥ፣ የአብነት ትምህርት ሰቪዲዮና በቴፕ ካሴት በመጻሕፍት ስመሳስሉት ቢ ሠጋጅ።

ከላይ የተጠቀሱት ከተመቻቹ ማንኛውም ምእመን የትም ሆኖ የአብነት ትምህርትን በማግኘት ሊማር ይችላል። ስለዚህ ነገም እንደትላንቱ ተተኪ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት የሆኑ አባቶችን ማፍ ራት ቀላል ይሆናል።

ዋቢ መጻሕፍት

1. አባ ጎርጎሪዎስ ካልዕ /ሊቀ ጳጳስ/ ፣ <u>የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን</u> 1974 ዓ.ም
2. ክፍያለው መርሐዊ /ቀሲስ/ <u>የቤተክርስቲያን አስተዋጽኦ ለቤተክርስቲያን ሥልጣኔ</u>፣ አዲስ አበባ፣ 1986 ዓ.ም
3. ኪዳነማርያም ጌታሁን /መምህር/፣ <u>ጥንታዊ የቆሎ ተማሪ</u> ፣ አዲስ አበባ፣ 1980 ዓ.ም
4. <u>ሐመር</u>፣ 9ኛ ዓመት ቁጥር 3፣4 እና 5 1994 ዓ.ም

ማኅበረ ቅዱሳን

ታሪክ፡- ማኅበሩ በ1987 ዓ.ም. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በነበሩ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ተመሠረተ። ከዚያም በተጠናከረ መልኩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው የሰንበት ትምህርት ተማሪዎች እንዲሆኑ፣ የሩቅ ተመልካች የነበረውን ትውልድ ቀርቦ ማንቃቱን እንዲያጠቅና እናት ቤተ ክርስቲያኒን ለማገልገል እንዲችል በማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያበረክት ቆይቷል። አሁንም በማበርከት ላይ ይገኛል።በ1984 ዓ.ም. በአባቶች ቡራኬ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን የሚለውን ስያሜ አግኝቶ በተጠናከረ መልኩ አገልግሎቱን እንዲያበረክት ተደረገ።አበረ አሁን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አባላት የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ሥርዓትና ትውፊት በሰንበት ትምህርቱ እንዲማሩ በማድረግ በአባቶች በቡራኬ አስመርቋል።

ስያሜ፡- ክቢያት የተነበየላት፣ ቅዱሳን ሐዋርያት ያስተማሩላትን፣ ቅዱሳን ሰማዕታት የተጋደሉላትን፣ ሥጋዊውን ዓለም ያሸነፉባትን ተጥተኛ ሃይማት የሚታመንባትና የቅዱሳንን አማላጅነትና አዘር የሚከበርበት በመሆኑ ማኅበረ ቅዱሳን ተብሏል።

ዓላማ፡- ከሚመሰከቱቸው የቤተ ክርስቲያን አባላት ጋር በመተባበር ትምህርቱ መንፈሳዊ በተሰያዩ በደ ምት ለመጽሔት፣ በጋዜጣ፣ በመጽሔትና በበራሪ ጽሑፎች፣ ማስፋፋት፣ የተማረው የትበራተሰበ ክፍል አርቶ ዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያኒን በጸሎቱ፣ በገንዘቡና በጉልበቱ እንዲያገለግል ትድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና አባላቱ ባለቸው ሙያ፣ ዕውቀትና ገንዘብ ነዳና ሰብአዊ የሆኑ ማኅበራዊ አገልግሎቶችን እንዲያበረክቱ ማድረግ የሚሉት የማኅበሩ ዓላማዎች ናቸው።

አስፈላጊነት፡-

- የተለያዩ የእምነት ድርጅቶች በየከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ እየገቡ ልዩ ልዩ በደ በመጠቀም የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች በአርባና በስሚያ ቁጥራው ያገኙትን የመንፈስ ቅዱስ ልጅነታቸውን በማሳጣት የራሳቸው ወገኖች ለማድረግ ስለሚራረጡ ይህንኑ የሚከላ ክፍል በየተቋማቱ መገኘ ት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣
- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲን እምነትና ሥርዓት እንዲማሩና ከአባቶቻቸው ያገኙትን ትውፊት ለትውልድ ለማስተላለፍ እንዲችሉ አመቺ መንገድ ለመቀየስ፣
- በየከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በልዩ ልዩ ሞያ ተመርቀው በተሰያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በልዩ ልዩ የሥራ መስክ የተሰማሩ የቤተ ክርስቲያን ልጆች በየጌዜበት ዐቃ በማገኖማቸው ማኅበራዊ ችግሮች ተወጠው ከቤተ ክርስቲያን እንዲይለዩና ቤተ ክርስቲያናቸውን በጉልበታቸው፣ በገንዘባቸውና በየተማሩበት የዕዉቀት በርዳ የቤተ ክርስቲያንን ደንብና ሥርዓት ተከትለው እንዲያገለግሉ ለማድረግ፣
- ከጭቱ ተምሮ ለሥራ ሲሰማራ እምነቱንና ሥርዓቱን ሰመማር እንዲሁም በአኅጉረው ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትቤትና ሰበካ ጉባኤ መሳተፍ እንደሚገባው አውቆ በተግባር መተርጎመን ለመከታተል።

አቋም፡- በማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጉዳይም ሆነ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ሦንም ዓይነት ጣልቃ ገብነት የለውም።

አባላት፡-

- ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ባሏት ማሠልጠኛዎች ሠልጥነው የወጡ በትምህርተ መንፈል እ ንፈግሎት ላይ የተሠማሩ አባቶችና ወንደሞች ደቀመዛሙርት፣
- በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አኅጉረ ባሉት የሰንበት ትቤቶች መርሐ ግብር የሚማሩ ተማሪ ዎች፣
- በየአጥቢያ ሰንበት ትቤቶቻቸው መርሐ ግብር ሲከታተሉ ቆይተው ከየተቋማቱ ተመርቀው ከወጡ በኃላ የሰንበት ትምህርት ቤት አገለገይም የሰበካ ጉባኤ አባል ሆነው መንፈሳዊ አገልግሎት የሚፈጽሙ እና
- ለማኅበሩ ዓላማ ተግባራዊነት በገንዘባቸው በዕውቀታቸውና በጉልበታቸው የሚረዱ ምእመናን ናቸው።

አባልነት፡- ከላይ አባላት በሚለው ሥር የተዘረዘሩትን ማማሟላታቸው በማኅበሩ መመሪያ መሠረት የተ ረጋገጠላቸው።

መዋቅር፡- በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት በሰንበት ትቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሥር ሆኖ መንፈሳዊ አገልግሎቱን ሲፈጽም በሀገሪ ስብከቱም ንዑሳን ማዕከላት አሉት።

የአገልግሎት ክፍሎች፡- የትምህርት ክፍል፣ የመዝሙርና ሥነጥበባት ክፍል፣ የሥልጠና ክፍል፣ የሞያ አገልግሎትና ተራድኦ ክፍል፣ የግንኙነት ክፍል፣ የሒሳብ ክፍል፣ ሠረጃና መሠባሰብ ማዕከል፣ የጥናትና ዕቅድ ክፍል፣ የኅትመት ዝግጅት ማስተባበሪያ ክፍል ፡ የልማት ተቋማት አስተዳደር ቦርድ ናቸው።